# 90 ደቂቃ
# በመንግሥተ ሰማይ ደጅ

ሞቶ የተመለሰ ሰው እውነተኛ
የሕይወት ታሪክ

ዶን ፒፐር
ከሲሰል ሙርፊ ጋር በመተባበር

ተርጓሚ ደረጀ በቀለ

ራዕይ አሳታሚ
አዲስ አበባ 2001 ዓ.ም.

# 90 ደቂቃ
# በመንግሥተ ሰማይ ደጅ

ይህ መጽሐፍ የተተረጎመው
90 Minutes in Heaven
ከሚለው መጽሐፍ ነው፡፡
Don Piper with Cecil Murphey

ይህንን መጽሐፍ ያለ አሳታሚው ፈቃድ ማባዛት ወይም
እንደገና ማሳተም በሕግ የተከለከለ ነው፡፡

ራዕይ አሳታሚ
የፖ. ሳ. ቁ 2332
አዲስ አበባ

RPTR-29 3M

“እኩለ ሌሊት አካባቢ ጓደኛዬ ይህንን መጽሃፍ ሰጠኝ፤ እናም ከማለዳው ወደ ሁለትና ሦስት ሰዓት አካባቢ ተመልሶ መጣ፤ በዚያ ጊዜም እያነበብኩት ነበር። በአመለካከትዎ ላይ ብርሃን የሚፈነጥቅ፣ ደህንነትዎን የሚያረጋግጥልዎት ግልጽነትና ሞቅ ያለ ስሜት እንዲሰማዎ የሚያደርግ አስደናቂና በመገለጥ የተሞላ መጽሐፍ ነው።”

ዶናልድ ሚለር

የብሉ ሌክ ጃዝ

ደራሲ

“የዶን ፒፐር ዘጠና ደቂቃ በመንግሥተ ሰማይ የሚለው ይህ መጽሐፍ ሕይወቱንና አመለካከቱን ለውጦታል። ይህንን መጽሐፍ ማንበብዎ እግዚአብሔር እጅግ ዘግናኝ ከሆነ ሁኔታዎ ውስጥ እንኳን አሳልፎ ሊያወጣዎ ታማኝ እንደሆነ እንዲተማመኑ ያስችልዎታል። የዚህ ሰው የአይን ምስክርነት ዘገባ በፊትዎ ስላለው ተስፋና ስለዚህም ሕይወት ያለዎትን አመለካከት ይቀይረው!”

ሚካኤል ካርተር

የሲ.ቢ.ኤን የፋይናንስ ቢሮ ኃላፊ

“ማራኪነት ያለውና በወጉ የተጻፈው ይህ መጽሐፍ ቀልብዎን ብዙውን ጊዜም ልብዎን ገዝቶ ይይዛል። ዶን ታሪኩንና ክርስቲያኖች ሁሉ ሊሰሙት የሚናፍቁትን የሕይወት ልምዱን ያጫውተናል። የሕይወት ልምምዱ መንፈስዎን ያነቃቃል የውስጥዎንም ስቃይ ያስረሳል። ”

ሮን ሂል

የሳን አንቶኒዮ ፌሎሽፕ ፓስተር

ለፀሎት ጦረኞች ...

እናንተ በመጸለያችሁ እኔ በዚህ አለሁ!



# ማውጫ

ገጽ

ምስጋና 7

መቅድም 12

1. አደጋው ........13
2. የመንግሥተ ሰማይ ቆይታዬ........22
3. ሰማያዊ ዝማሬ........34
4. ከመንግሥተ ሰማይ ወደ ምድር ........45
5. በምድር ሆስፒታል ውስጥ ........56
6. እየተሻለኝ መጣ........71
7. ውሣኔና ተግዳሮቶች ........86
8. የሕመም ስቃይና ማስተካከያዎቹ ........101
9. ማለቂያ የሌለው ማስተካከያ ........125
10. ተጨማሪ ተዓምራት........139
11. ወደ ቤተክርስቲያን መመለስ........152
12. መንገዱ ተከፈተ ........174
13. አጥብቆ የያዘኝ እጅ........188
14. አዲሱ ሕይወት........193

15. ነፍሳትን መድረስ..........224
16. ዓላማን ማወቅ..........258
17. ወደ ቤቴ እናፍቃለሁ..........277
18. ለምን? ..........284



# ምስጋና

ይህንን መጽሐፍ የጻፍኩት ራሴን የሚገባውን ያህል ለመግለጽ ኋው:: ከ1989 ጀምሮ የሕይወት ልምምዴን እንደገና በመናገር ፈጣን ወይም የተብራራ መልስ በመስጠት ብዙዎችን ማርካት እንዳልቻልኩ ተገንዝቤአለሁ:: በሬዲዮ፣ በቴሌቪዥን፣ በጋዜጦች፣ ቁጥር ስፍር የሌላቸው መድረኮችና ንግግር እንዳደርግ በተጋበዝኩባቸው ሥፍራዎች ሁሉ፤ አመርቂ የሆነ ምላሽ ከመስጠት ይልቅ በጥቅሉ ሲታይ በርካታ ጥያቄዎችን ሳልመልስ ቀርቻለሁ:: ሰዎች ያለማቋረጥ ተጨማሪ ነገሮችን ማወቅ ይፈልጋሉ . . . ሁልጊዜም ተጨማሪ:: በጥያቄ የተሞሉ የሰዎችን አዕምሮዎች ለማርካት ይህን ተሞክሮየን አስመልክቼ ሦስት ያህል ጽሑፎችን ጽፌአለሁ:: ሁሉም እርካታን አልሰጡኝም:: በዚያ ጊዜ ነበር እጅግ አጠያያቂ ለሆነው የሞቴና የሕይወቴ ጉዳይ ምላሽ ለመስጠት፤ በአሜሪካ ታዋቂ ከሆኑት የመጽሐፍ ደራሲ ጋር በመተባበር እንድ መጽሐፍ ለመጻፍ የተነሣሣሁት:: ስሲል ሙርፊ፤ የፍራንክሊን ግራሃማን፣ ትሩት ካቲን፣ የቢ.ጄ ቶማስን፣ የዲኖ ካርስ አንካስንና የዶ/ር ቢን ካርስንን የሕይወት ታሪክ በመጻፍ ኮከብ የሆኑ ሰው ናቸው:: እኚህ ሰው ናቸው አሁን በእጅዎ የያዙትን መጽሐፍ ልጽፍ በፈለግኩበት መንገድ እጽፍ ዘንድ አቅጣጫን ያመላከቱኝ::

ስሲል ታማኝ፣ ልብ የሚጣልባቸውና መልካም ምክር የሚለግሱ ጓደኛዬ ሆነው አግኝቻቸዋለሁ:: በርግጥም ይህንን መጽሐፍ በማዘጋጀት ካገኘኋቸው በረከቶች አንዱ ከስሲል ሙርፊ ጋር መተዋወቅ መቻሌ ነው:: በመጽሐፍ ዝግጅቱ ሂደት ውስጥ በእያንዳንዱ ገጽ ላይ ብርቱ ጥረታቸው ታክሎበታል:: አመሰግናለሁ ሲስ! በጥልቀት ሊመሰገኑ የሚገባዎ ነዎት:: እንደዚሁ ደግሞ ከናይት ኤጃንሲ የሆኑት ዴድር

ናይት በመጽሐፍ ዝግጅት ላይ የነበራቸው ታላቅ እምነት በእጅጉ የሚመሰገን ነው። በተጨማሪም ከባከር አታሚዎች ሕብረት ለሆኑት ዶ/ር ቪ.ከ. ክሩሞፐቶን አድናቆቴ እየጨመረ የሚሄድ ነው። ታሪኩ ታትሞ ለማየት በነበራት ፍላጎት ያደረገችው ጥረት ታላቅ ዋጋ የሚሰጠው ነው።

የኸርማነን መታሰቢያ የህክምና ማዕከል የጉዳተኞች ክፍልንና በሆስተን የሚገኘው የቅዱስ ሉቃስ መታሰቢያ ሆስፒታል ውስጥ የነበሩ የህክምና ባለሞያዎች ለሰውነቴ መዳን ስላደረጉት ትልቅ ጥረት ላመስግናቸው እወዳለሁ። ይልቁንም ደግሞ ከዚያች ከጥር 18፤ 1989 አስጨናቂ ሌሊት ጀምሮ የኦርቶፔዲክ ቀዶ ጥገና ህክምና ሲያደርጉልኝ ለቆዮት ለዶ/ር ቶማስ ገራደር የተለየ ምሥጋና አቀርባለሁ።

እጅግ በርካታ በሆኑ አብያተ ክርስቲያናት የሚገኙ የተወደዱ የእግዚአብሔር ህዝቦች እንዳገለግላቸው ፈቅደውልኛል። በሕይወት ለመኖሬ የሚያደርጉልኝ ጸሎት ወሳኝ ነበር፤ ይልቁን ደግሞ በአካል ተገኝተው ማጽናናታቸው ለአገልግሎቴ ታላቅ በረከት ሆኗል። በአልቪን፣ በቴክሳስ ለሚገኙ የደቡብ ፓርክ መጥምቃውያን ቤተክርስቲያን የእግዚአብሔር ታላላቅ የፀሎት ጦረኞት የጠለቀ ምስጋናዬን እነሆ እላለሁ። የተለየ አስተዋጽኦዋቸውን ላደረጉልኝ ለመጀመሪያው የመጥምቃውያን ቤተክርስቲያን፣ የኤርላይን መጥምቃውያን ቤተክርስቲያንና የባርክስዳል መጥምቃውያን ቤተክርስቲያን፣ በሉሲያን ለምትገኘው ለመላዋ የቦስሲር ከተማም ምስጋናዬን አቀርባለሁ። የእኚህ የሁለቱ አብያተ ክርስቲናት የቀድሞ እረኛ የነበሩት አባቴ ዶ/ር ዳሞን ቪ ፒሁገን የጣሉብኝ ውለታ እጅግ ታላቅ ነው።



አደጋው ከደረሰብኝ ጊዜ አንስቶ በታማኝነት አጠገቤ ለቆሙት በሮሻሮን፣ በቴክሳስ ለሚገኙት የመጀመሪያዋ የመጥምቃውያን ቤተክርስቲያን፣ በቴክሳስ ፕሌኖ ውስጥ ለሚገኙ የሃንተርስ ግሊንና በሙርፊ ጎዳና የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት የአገልግሎት መስማሪያዎቼ ነበሩና ህያው የሆነ ፍቅሬን ለመግለጽ እፈልጋለሁ። ይህ የመጽሐፍ ዝግጅት እንዲጠናቀቅ ያደረጋችሁልኝ ድጋፍ መልካምና ያልተቋረጠ ነበር።

ለእኒታ ዋንሪከርና ለሚቹ ባለቤትዋ ጂክ እግዚአብሔር በዚህ ሥራ ላይ አስደናቂ በሆነ መንገድ እንዲጠቀምባችሁ ፈቅዳችኋልና አመሰግናለሁ። በክርስቶስ ላላችሁ ወንድሞቼና እህቶቼ ጓደኞቼም ሁሉ፤ ከልባችሁ በሆነ ፍቅር ለጸለያችሁልኝ ሁሉ ምስጋናዬ ይድረሳችሁ። የከፈላችሁትን መስዋእትነትና የፍቅራችሁን ልክ የሚያውቀው እግዚአብሔር ብቻ ነው። ከሁሉም በላይ ደግሞ ከእግዚአብሔር ዘንድ የተሰጡ እውነተኛ ስጦታዎች የሆኑልኝን የረዥም ዓመታት ጓደኞቼን ክሊፍ ማክአርድልንና ዴቪድ ጀንቷልስን አመስግናቸዋለሁ። በቀንም ይሁን በሌሊት፣ በተመቸም ባልተመቸም ጊዜ፣ ቀናም ይሁን ዋጋ መክፈል በሚያስፈልግበት ሁኔታ ውስጥ ሁልጊዜም ታማኝ ሆናችሁልኛል። ይህ መጽሐፍ እንዲጠናቀቅ ላደረጋችሁልኝ ማበረታታት ሁሉ አመሰግናለሁ።

በመጨረሻም፤ የባለቤቴ ወላጆች የሆኑት ኢልደንና ኢቴል ፔኒኮስት እንዲሁም የራሴ ወላጆች የሆኑት ራልፍና ቢሊ ፒፐር ለከፈሉት በዋጋ ለማይተመን መስዋእትነትና የታመነ ድጋፋቸው ወሰን የሌለው አክብሮቴን እገልጻለሁ። ለሦስቱ ልጆቼ ለኒኮል፣ ለክሪስና ለጆይ ... ማግኘት ከሚገባኝ በላይ እግዚአብሔር የሰጠኝ መልካም ልጆች ለማለት


እደፍራለሁ:: በእናንተ እጅጉን ተባርኬአለሁ:: ለእኔ እጅግ ዋጋ ላላችሁ ለእናንተ ይልቁን ደግሞ ከዚያች የቆየች ረቡዕ ሌሊት ወዲህ ስላሉት ጊዜያት አመሰግናለሁ ማለት ብቻ በቂ ይሆን? እንደገናም ደግሞ ለሠላሣ አመታት ያህል የትዳር ጓደኛዬ የሆንሽው ኢቫ፣ አንቺ ለእኔ ያደረግሽውን ያህል የትኛውም ሰው እንዳላደረገልኝ ልገልጽልሽ እወዳለሁ:: አንቺ ነገሮችን ሁሉ ያደረግሽልኝ በታማኝነት፣ በርህራሄና ያለምንም ማመንታት ነበር:: ከጓደኞቼና ከቤተሰቦቼ ሁሉ ይልቅ በእያንዳንዱ እለት ባለው ጉዞዬ ስቃዮ ምን ያህል ታላቅ እንደነበር በእውነት የምታውቀው ኢቫ ብቻ ነች፤ ምክንያቱም በቅርቤ ሆና ሁኔታዎችን በጽናት ተጋፍጣቸዋለችና ነው:: ኢቫ! አንቺ እኮ ከእግዚአብሔር የተሰጠሽኝ ስጦታ ነሽ::

ጌታ ሆይ፤ እኔ ሁልጊዜም የሆኑት ነገሮች በምን መንገድ እንደሆኑ እንደማላውቅ አንተ ታውቃለህ፤ ቢሆንም በአንተ መታመኔን አላቋርጥም:: አብ አባት ሆይ! በፍጹም የልብ ትህትና የምተርከው ታሪክ አንተን ደስ እንዲያሰኝህ ለብዙዎችም ባርኮት ይሆን ዘንድ እጸልያለሁ:: አሜን::

ዶን ፒፐር

የካቲት 2004





በ1982፣ ዶን ከመንትያ ልጆቹ ከክሪስ እና ከጆይ ጋር

## መቅድም

ጥር 18 1989 ከዚህ ዓለም በሞት ተለየሁ:: የህክምና ባለሙያዎች የአደጋው ውጤት ምን እንደሆነ ለመናገር የፈጀባቸው የደቂቃዎች ጊዜ ብቻ ነው:: የልብ ምቴ ፈጽሞ ቆሞ ስለነበር እንደሞትኩ ተናገሩ:: በአንሶላ ሸፍነውኝ ስለነበር ሌሎች ቁስለኞችን ለመንብኘት የሚመጡ ሁሉ አፍጥጠው ሊመለከቱኝ እድል አልነበራቸውም:: በአጠገቤ ሃኪምም ይሁን ማንም ሰው እንዳለ ፈጽሞ አላውቅም ነበር::

· ከሞትኩ በኋላ ወዲያውኑ በቀጥታ ወደ መንግስተ ሰማይ አመራሁ::

በመንግስተ ሰማይ በነበርኩበት ጊዜ፤ አንድ የመጥምቃውያን ሰባኪ አደጋው የፈጠረበት ሃዘን ውስጥ ሆኖ ወደ እኔ መጣ:: እንደሞትኩ ያወቀ ቢሆንም እንኳን ወደ ሙት አካሌ በፍጥነት መጥቶ ይጸልይልኝ ጀመር:: የድንገተኛ አደጋ የህክምና ባለሙያዎች በዙሪያው ሆነው ቢያላግጡበትም እርሱ ግን መጸለዩን ለማቆም አልፈለገም::

የህክምና ባለሙያዎቹ መሞቴን ከተናገሩ ቢያንስ ቢያንስ ከዘጠና ደቂቃ በኋላ እግዚአብሔር የዚያን ሰው ጸሎት መለሰ::

እንደገና ወደ ምድር ተመለስኩ::

እናም ታሪኬ እንዲህ ነው::



# 1 አደጋው

ስለዚህ በድፍረት "እግዚአብሔር ይረዳኛልና አልፈራም ሰው ምን ያደርገኛል?" ዕብ 13፥6

ብለን መናገር የምንችልበት ምክንያት ያ ነው::

በቴክሳስ የሚገኘው የመጥምቃውያን አጠቃላይ ጉባኤ፤ ዓመታዊ የሆነ አገር አቀፋዊ ስብሰባውን ለማካሄድ በዝግጅት ላይ ነበር:: ጥር ወር 1989 በታላቁ ሀውስተን አካባቢ የሚገኙ ከሁሉም የመጥምቃውያን አብያተ ክርስስቲያናት የተውጣጡ የመጥምቀውያን ጉባኤ ህብረት አባላት፤ ጉባኤው ከሊቪንግስተን ሃይቅ ዳርቻ በስተሰሜን በሚገኘው ትሪኒቲ ፒንስ በተባለው ታላቅ የጉባኤ አዳራሽ እንዲሆን መረጡ:: ጉባኤው ያተኮረው የቤተክርስቲያንን እድገት በሚመለከት ጉዳይ ላይ ነበር:: እኔም በዚያ የተገኘሁበት ምክንያት በወቅቱ አዲስ ቤተክርስቲያን ለመመስረት ብርቱ ጥረት በማድረግ ላይ የምገኝ በመሆኔ ነበር::

ጉባኤው የተጀመረው ሰኞ ዕለት ሲሆን እስከ ረቡዕ ድረስ እንዲቀጥል የታቀደለትም ነበር:: ማክሰኞ ምሽት የህብረቱ መሪና ወዳጆም ከሆኑት ጄ.ቪ. ቶማስ ጋር በመሆን ረዘም ያለ የእግር መንገድ አደረግን:: እርሳቸው የልብ ድካም ህመም ከያዛቸው ወዲህ የእግር ጉዞ

የሚያዘውትሩ ሆነው ነበር። ለዚህም ነበር የጉባኤውን የመጨረሻ ምሽት በእግር ጉዞ ለማሳለፍ የወሰንነው።

ከወራት በፊት፤ አዲስ ቤተክርስቲያን መመሥረት እንደሚገባኝ ማሰብ ጀምሬ ነበር። ወደዚህ ታላቅ ሥራ ከመግባቴ በፊት ግን ማግኘት የሚገባኝን መረጃ ሁሉ ማግኘት ያስፈልገኝ ነበር። የጉባኤው ህብረት መሪዎች ሁሉ ጂ.ቪ. ቶማስ ስለ አዲስ ቤተክርስቲያን ምሥረታና እድገት የላቀ ተሞክሮና እውቀት እንዳላቸው እናውቃለን። በግዛታችን ውስጥ ስኬታማ የሆኑ በርካታ አብያተክርስቲናትን መስርተው ስለነበር ሕብዛኞቻችን በዚህ ጉዳይ ላይ የተለየ ባለሙያ አድርገን እንቆጥራቸዋለን። በዚያ ምሽት አብረን በመጓዝ ላይ ሳለን እኔ ስለምመሠርታት አዲስ ቤተክርስቲያን እንጫወት ነበር። መቼ እንደምጀምራት፣ የት እንደምመሠርታት ሁሉ አወራን። ያለውን ውጣ ውረድና ሊደርስ የሚችለውን ችግር እንዴት ማስወገድ እንደሚቻል ለማወቅ እፈልግ ነበር። እርሳቸውም ማለቂያ የሌላቸው የሚመስሉ ጥያቄዎቼን ይመልሱና ፈጽሞ አስቤአቸው የማላውቅ ጉዳዮችን እያነሱ በዝርዝር ያጫውቱኝ ነበር።

ለአንድ ሰዓት ያህል እየተጓዝን ብዙ ነገሮች አወራን። ምንም እንኳን ዝናባማና ብርዳማ ምሽት ቢሆንም የነበረን የአንድነት ጊዜ ድንቅ ነበር። ጂ.ቪም ያንን ጊዜ ደህና አድርገው ያስታውሱታል።

እኔም ያችን ምሽት በፍጹም አልረሣትም፤ ይሁን እንጂ በተለየ ምክንያት ነው። ምናልባትም ያች ምሽት በትክክል መራመድ የቻልኩባት የመጨረሻዋ ምሽት ነበረች።



በቀጣዩ ቀን ማለት ረቡዕ የአየሩ ሁኔታ እየባሰበት ሄደ። የማያቋርጥ ዝናብ መዝነብ ቀጠለ። የነበረው ቅዝቃዜ ከዚያ በላይ ጥቂት እንኳን ቢጨምር ፈጽሞ መጓዝ አንችልም ነበር፤ ምክንያቱም ሁሉም ነገር ወደ በረዶነት ይለወጥ ነበር።

የማለዳው ስብሰባ በሰዓቱ ተጀመረ። የመጨረሻውን ንግግር አቅራቢ የመጥምቃውያን ቤተክርስቲያን ሰባኪ፣ አድርጎት የማያውቀውን እንግዳ ነገር አደረገ ንግግሩን በአጭር ቋጨው። በትሪኒቲ ፒንስ የሚገኙ ሠራተኞች ከምሣ ሰዓት በፊት በአራት ሰዓት ተኩል አካባቢ የምንቀማምሰውን ነገር አቀረቡልን። እናም ምሽቱ ከመቃረቡ በፊት ጓዜን ሁሉ የ1986 ሞዴል በሆነችው ቀይ ፎርድ መኪናዬ መጫኛ ላይ ቀረቀብኩ።

ምግብ መመገባችንን እንዳበቃን ወዲያውኑ ወዳጆቼን ሁሉ ተሰናብቼ ወደ መኪናዬ ገባሁ። ጉዞዬም ወደመጣሁበት በአልቪን ወደሚገኘው ወደወከልኩት የሳውዝፓርክ መጥምቃውያን ቤተክርስቲያን በመጓዝ ከሁሰተን ማህበረሰብ ጋር ለመቀላቀል ነበር።

በመኪናው ውስጥ ገብቼ ገና ሞተሩን እንደቀሰቀስኩ አንድ ነገር ትዝ አለኝ። ከሦስት ሣምንት በፊት መኪናዬን በማሽከርከር ላይ ሳለሁ የአደጋ መከላከያ ቀበቶዬን ባለማጥለቁ የትራፊክ ቅጣት ደረሰኝ ተቆርጦ ተሰጥቶኛል። በዚያ ጊዜ የጉሮሮ ቀዶ ህክምና ሊደረግለት በዝግጅት ላይ ለነበረ አንድ መጋቢ ጓደኛዬ ቃል ላካፍለው እየሄድኩ ነበር። የቴክሳስ ትራፊክ ያዘኝ። ደረሰኙ አጠገቤ ካለው ወንበር ላይ ተቀምጦ ስለነበር ወደአልቪን እንደተመለስኩ ቅጣቱን ወዲያውኑ መክፈል እንዳለብኝ አሳሰበኝ። የቅጣት ደረሰኙን ከመቀበሌ በፊት የአደጋ መጠበቂያ

ቀበቶውን የማጥለቅ ልምድ አልነበረኝም፤ ከዚያ በኋላ ግን መንገዴን በመቀየር ህጉን ማክበር ጀምሬአለሁ።

ያንን ደረሰኝ ባየሁት ጊዜ፤ "ዳግመኛ ትራፊክ እንዲያስቆመኝ አልፈልግም፤" ስል አሰብኩ። በመሆኑም ቀበቶውን አጠላኩና ደህና አድርጌ አሰርኩት። ይች ትንሽ ተግባር ታላቅ ውሳኔ ልትሆን ችላለች።

ወደ ሀውስተንና ወደ አልቪን ለመሄድ ሁለት አማራጭ መንገዶች አሉ። የትሪኒቲ ፒንስን የጉባኤ አዳራሽ ዋንኛ በር አልፌ እንደወጣሁ፤ በሊቪንግስተን አቆራርጬ ቁልቁል ወደ ሃይዌይ 59 ወይም ደግሞ ብዙ ጊዜ ገልፍ ፍሪዌይ ተብሎ ወደሚጠራው ሁንትስቪል እና አይ - 45 በምሥራቅ አቅጣጫ መንዝ እንደነበረብኝ መምረጥ ነበረብኝ። ሁለቱም ምርጫዎች ምናልባትም ርቀታቸው እኩል ይሆናል። ወደ ትሪኒቲ ፒንስ በመጣሁባቸውና በተመለስኩባቸው ጊዜዎች ሁሉ ምርጫዬ በሃይዌይ 59 አቅጣጫ ማሽከርከር ነበር። በዚያ ጠዋት ግን በገልፍ ፍሪዌይ አቅጣጫ ለመንዝ ወሰንኩ።

በጠዋት መንዝ እንድንችል አስቀድመው ስላለቀቁን እፎይታ ተሰምቶኝ ነበር። አምስት ሰዓት ሊሆን የቀሩት ጥቂት ደቂቃዎች ነበሩ፤ በመሆኑም በስምንት ሰዓት አካባቢ ወደ ቤተክርስቲያኔ ተመልሼ መድረስ እችላለሁ ማለት ነው። የቤተክርስቲያናችን ዋንኛው አገልጋይ አንድ ህብረት ለመምራት ወደ ቅድስቲቱ ከተማ ተጉዞ ነበር። በመሆኑም በሳምንቱ አጋማሽ ላይ በሳውዝ ፓርክ ቤተክርስቲያን የነበረውን የአገልግሎት ሃላፊነት የጣለው በእኔ ላይ ነበር። በቀጣዮቹ ሁለት ሣምንታትም በቤተክርስቲያን የስብከቱን አገልግሎት እንዳገለግል ጠይቆኛል። በዚያ ማክሰኞ ምሽት ጥቂት ዝግጅት የሚጠይቅ የፀሎት



አገልግሎት ነበረን፤ እኔ ግን ለቀጣዩ ሰንበት የማሆነውን ስብከት ማዘጋጀት ያስፈልገኝ ነበር።

አልቪንን ለቅቄ ከመውጣቴ በፊት ለመጀመሪያው ሳምንት የሚሆነኝን ስብከት ረቂቅ አዘጋጅቼ ነበር፤ የሰጠሁትም ርዕስ በታላቁ እግዚአብሔር አምናለሁ! የሚል ነው። መኪናዬን በማሽከርከር ላይ እያለሁ ይህንኑ የስብከት ረቂቅ ጽሑፌን በጨረፍታ እየተመለከትኩ እስከ አሁን የሠራሁትን ለመገምገም አቀድኩ።

ከዚያ በኋላ ባለው ጊዜ በገልፍ ፍሪዌይ አቅጣጫ ለመንዝ የወሰንኩትን ውሳኔ ደጋግሜ ማሰላሰል ጀመርኩ። አንዳንድ ጥቃቅን ውሣኔዎችን ስንወስን ምንም ያህል ትኩረት ሳንሰጥ የመሆኑ እውነት ያስደንቃል። ያም ቢሆን እጅግ ትንሽ የሆነች ውሳኔአችን በቀጣዩ ሕይወታችን ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ የሚያስከትሉ ውጤቶችን ያቀፈች እንደሆነች ራሴን ማሳሰቤን አልተውኩም።

ከትሪኒቲ ፒንስ ቅጥር ግቢ እንደወጣሁ በስተቀኝ በመታጠፍ በቴክሳስ ሃይዌ 19 አቅጣጫ ቁልቁል ተፈተለኩ። በዚህ መንገድ ወደ ሁንትስቪል እነዳለሁ፤ ቀጥሎም አይ - 45ን አቋርጣለሁ፤ ከዚያም ወደ ሃውስተን ገባሁ ማለት ነው። ሰው ሰራሽ ወደሆነው የትሪኒቲ ወንዝ ግድብ ለመድረስ ብዙ ማሽከርከር አልነበረብኝም። አንድ ጊዜ የወንዝ ውሃ ይተኛበት የነበረው ያ ስፍራ እጅግ የሚያምር ሰፊ ሃይቅ ሆኗል። ከውሃው ከፍታ በላይ የሊቪንግስተንን ሃይቅ አቋርጦ የሚያልፍ ባለ ሁለት አቅጣጫ መንገድ ተዘርግቷል። መንገዱ በግራና በቀኝ የመጠበቂያ ደርዝ ያልነበረው ከመሆኑም በላይ እጅግ ጠባብ ነው። ወደሚቀጥለው የመንገድ ጫፍ እስክደርስ ድረስ በውሃው ላይ በተሠራው ጠባብ ጎዳና ላይ የግድ መንዝ ነበረብኝ። በዚያ መንገድ ላይ ለማሽከርከር ፈቃድ

አልነበረኝም፤ ያም ቢሆን መንገዱ የግራና ቀኝ ደርዝ እንደሌሰው አውቄአለሁ።

በሃይቁ ላይ የተዘረጋው መንገድ ሲያበቃ፤ በትሪኒቲ ወንዝ ላይ የተሠራው የቀድሞው ድልድይ ይገኛል። ከድልድዩ ቀጥሎ ደግሞ መንገድ እየጠበበ ይሄድና ሽቅብ የትሪኒቲን ወንዝ አሳብሮ ያልፋል። ጠባብ የሆኑት የመታጠፊያ ስላቾች ከሁለቱም አቅጣጫዎች የሚመጡ አሽከርካሪዎች አደጋ ሊያጋጥማቸው እንደሚችል ግልጽ አድርገው ያሣያሉ።

ያንን ድልድይ ስመለከት የመጀመሪያ ጊዜዬ ነበር፤ በሚያስገርም ሁኔታ ያለስፍራው የተቀመጠ ነበር። ስለተሠራበት ዘመን የማውቀው ነገር የለም ይሁን እንጂ ድልድዩ እጅግ ረዥም ነው። አሮጌ ከመሆኑም በላይ በግዙፍ የዛጉ ብረቶች የተገጣጠመ ነበር። ከፊት ለፊቱ ካለው - አውራ ጎዳናና ከጥቂት ተሽከርካሪዎች በስተቀር ሌሎች መኪናዎችን ማየት አልቻልኩም። በጣም አደገኛ ድልድይ ነበር፤ በኋላ እንደሰማሁት በዚያ ድልድይ ላይ በርካታ አደጋዎች ተከስተዋል (በአሁኑ ጊዜ በጥቅም ላይ ባይውልም ድልድዩ በነበረበት ስፍራ አለ። መንግስት ከአጠገቡ ሌላ ተለዋጭ ድልድይ ሠርቷል)።

እንዝ የነበረበት ፍጥነት በሰዓት ሃምሣ ማይል ነበር፤ ምክንያቱም ያ ስፍራ ለእኔ አዲስ ነው። በመኪናው ውስጥ ከነበረው ቅዝቃዜ የተነሣ ትካሻዎቼ ተቆራምደዋል። በዚያ ላይ ንፋሱ ደግሞ የጠዋቱን ቅዝቃዜ ይበልጥ እንዲጨምር ያደረገው ይመስላል። ሣያቋርጥ ይዘንብ የነበረው ዝናብ ወደ ውሽንፍርነት ተቀይሯል። ተመልሼ ወደ አልቪን የምደርስበትን ጊዜ እጅግ ናፈቅሁ። ድልድዮን አቋርጬ ከመውጣቴ በፊት አምስት ሰዓት ከአርባ አምስት አካባቢ፤



የቴክሣስ ጠባይ ማረሚያ እስረኛ በሆነ ከእስር ቤቱ ውጭ መኪና ለመንዳት በጎ ፈቃደኛ ሆኖ በተገኘ እስረኛ ሰው ይሽከረከር የነበረ፣ ባለ 18 ጎማ ከባድ መኪና በአውራ ጎዳናው መካከል እየተጠማዘዘ መጥቶ መኪናዬን ፊት ለፊት ገጫት። መኪናዬም በድልድዩና በከባድ መኪናው መካከል እንደ ሳንድዊች ሆነች። እነኛ ሁሉ ጐማዎች በመኪናዬ ላይ ተከመሩና ጨፈላለቋት። የማስታወሰው የአደጋውን ከፊል ሁኔታ ብቻ ነው፤ አብዛኛውን መረጃ ያገኘሁት ግን በኋላ ከአደጋው ዘገባና በስፍራው ከነበሩ ሰዎች ነው።

የአይን ምስክር ከሆኑ ሰዎች እንደደረሰኝ ገለጻ፤ ያ ከባድ መኪና ወደ ሌላው የጎዳናው አቅጣጫ ተጠማዞ ወደ ጠባቡ የድልድዩ ወገን በማምራት ሁለት መኪናዎችን ጠርጎ ከድልድዮ ላይ አፈናጥሮ ጥሏቸዋል። እነዚህ መኪናዎች ከከባድ መኪናው ፊት ፊት ይጓዙ የነበሩና በተቃራኒ አቅጣጫ እኔን አልፈውኝ የሄዱ መኪናዎች ነበሩ። የፖሊስ ዘገባ እንደገለጸው ከሆነ ከባድ መኪናው መኪናዬን በገጨበት ጊዜ ቢያንስ ቢያንስ ስድሣ ማይል በሰዓት በመጓዝ በፍጥነት የሚሽከረከር ነበር። ልምድ ያልነበረው አሽከርካሪ በመጨረሻው በድልድዩ ማብቂያ አካባቢ መኪናውን ሊያቆመው ችሏል።

ግጭት ከደረሰባቸው ሁለት መኪናዎች በአንደኛው ውስጥ አንድ ወጣት ቬትናማዊ የነበረ ሊሆን በሁለተኛው መኪና ውስጥ ደግሞ አንድ እድሜ የጠገቡ የካሁሳ ተወላጅ ነበሩበት። ምንም እንኳን በግጭቱ ታላቅ ድንጋጤ የደረሰባቸው ቢሆንም ያገኛቸው መጠነኛ የሆነ የመቁሰልና የሰውነት መላጥ ጉዳት ብቻ ነበር። እርዳታ ማግኘት ባለመፈለጋቸው የህክምና ሰዎች ሁለቱንም ወደ ሆስፒታል አልወሰዷቸውም።

በከባድ መኪናው ፍጥነት ምክንያት የአደጋው ውጤት እንደ መቶ አስር ማይል በሰዓት እንደነበር የአደጋው ሪፖርት ይዘግባል:: ይህም ከባድ መኪናው መኪናዋን ሲገጭ ይሽከረከርበት የነበረው የስድሣ ማይል በሰዓት ፍጥነት፤ እኔ በዝግታ አሽከረክርበት ከነበረው የሃምሳ ማይልስ ፍጥነት በሰዓት ተደምሮ ነው:: እስረኛው መኪናውንና የመኪናውን ፍጥነት መቆጣጠር ባለመቻል ክስ ተመሠረተበት:: በኋላ ላይ የተገኙ መረጃዎች እንደጠቆሙት እሥረኛው ያንን ከባድ መኪና ለማሽከርከር የመንጃ ፈቃድ አልነበረውም:: በእስር ቤቱ ውስጥ ተቆጣጣሪው በዚያ ከባድ መኪና ምግብ ወደ እሥር ቤቱ ለማምጣት ፈቃደኞች እንዳሉ ጠይቆ ነበር:: የተገኘው ብቸኛ ፈቃደኛ እርሱ በመሆኑ ያንን መኪና እንዲነዳው ይፈቅዱለታል:: ሌሎች ሁለት ዘቦች ደግሞ የመንግስት በሆነች አንድ ፒክ አፕ መኪና በቅርብ ርቀት ይከተሉት ነበር::

ከአደጋው በኋላ፤ የከባድ መኪናው አሽከርካሪ አንድም ጭረት እንኳን በሰውነቱ ላይ አልተገኘም:: የወህኒ ቤቱ ከባድ መኪና ብቻ ጥቂት ጉዳት አጋጥሞታል:: ይሁን እንጂ ያ ግዙፍ መኪና የኔን ፎርድ ጨፈላልቆ ከጠባቡ መንገድ ገፍቶ አውጥቷታል:: ወደ ሃይቁ ከመወርወር ያዳናት የድልድዮ ድጋፍ ብቻ ነበር::

በስፍራው የነበሩ የዐይን እማኞች እንደተናገሩት ከሆነ፤ በፒካፕ መኪናዋ ውስጥ የነበሩ ዘቦች ወደ እስር ቤቱ በመደወል የህክምና እርዳታ በመጠየቃቸው ባለሙያዎቹ ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ደረሱ:: አንድ ሰው ምርመራውን አደረገልኝ፤ የልብ ምቴ ፈጽሞ ቆሟል፤ በመሆኑም አደጋው በተፈጸመበት ቅጽበት እንደተገደልኩ አስታወቀ::



ከዚያ በኋላ ስለተፈጸመው ነገርም ይሁን ስለአደጋው ውጤት የማስታውሰው ነገር አልነበረም::

እጅግ ሃያል በሆነች በአንዲት ሰከንድ ሞትኩ::

# 2

# የመንግስተ ሰማይ ቆይታዬ

ፈራ እንዲህም አለ፤ "ይህ ስፍራ እንዴት ያስፈራል፤ ይህ ሥፍራ የእግዚአብሔር ቤት ነው እንጂ ሌላ አይደለም፤ ይህም የእግዚአብሔር ደጅ ነው::" ዘፍ 28፥17

በሞትኩ ጊዜ፤ እረጅምና ጥቁር በሆነ ዋሻ ውስጥ እየተንሳፈፍኩ አልሄድኩም:: የመነጠቅም ይሁን ወደ ምድር የመመለስ ስሜት አልተሰማኝም:: አካሌ ወደ ብርሃንነት እየተለወጠ እንዳለም አልተሰማኝም:: እኔን የሚጠራ ወይም ሌላ ድምጽ በጭራሽ አልሰማሁም:: የመጨረሻው ትውስታዬ ከሆነው ከድልድዩና ከዝናቡ እይታዬ በኋላ ወዲያውኑ፤ ከቶውን ምድራዊ ቃል ሊገልጸው በማይችል አንጸባራቂ ብርሃን ውስጥ ተጠቀለልኩ:: የማውቀው ያንን ብቻ ነው::

ቀጥሎ ያወቅኩት ነገር ቢኖር፤ በመንግስተ ሰማይ ውስጥ መቆሜን ነበር::

ዙሪያዬን ስመለከት ደስታ በውስጤ መፍሰስ ጀመረ፤ በዚያው ቅጽበት ደግሞ በአካባቢዬ እጅግ በርካታ ሰዎች እንደነበሩ ተረዳሁ:: አንጸባራቂና ድንቀኛ ውበት ባለው መግቢያ በር ላይ ቆመዋል:: ከእኔ ምን ያህል ርቀት እንደነበራቸው አላውቅም፤ በዚያ ርቀትን የመሳሰሉ



ነገሮች ዋጋ ያላቸው አይደሉም:: ሰዎቹ ወደአለሁበት ሥፍራ እየተመሙ በመጡ ጊዜ፤ ኢየሱስን አላየሁትም ነበር:: ነገር ግን የማውቃቸውን ሰዎች አይቻለሁ:: በዚያው ቅጽበት አንድ ነገር ተገነዘብኩ፤ እነዚያ ሁሉ ሰዎች የሞቱት እኔ በኖርኩባቸው የሕይወት ዓመታት ውስጥ ነው:: ሁኔታቸው ሁሉ ልክ ፍጹም ፍጥረታዊ ሰዎችን ይመስላል::

ወደ እኔ እየፈጠኑ መጡ፤ እያንዳንዳቸው ፈገግ ይሉ፤ ይጮኹና እግዚአብሔርን ያመሰግኑ ነበር:: ማንም ሰው እንዲህ ነው ብሎ ባይነግረኝም እንኳን እኔን በክብር ለመቀበል የመጡ የእንግዳ ተቀባይ ቡድኖች መሆናቸውን ተረዳሁ:: ነገሩ ሁሉ ሁሉም ከመንግስተ ሰማይ ደጃፍ ላይ ሆነው እኔን እየተጠባበቁኝ እንደነበር ይመስላል::

በደንብ ያስታወስኩት የመጀመሪያው ሰው አያቴ ጆ ኩልቢዝን ነበር:: ልክ ያን ጊዜ የማውቀውን ነው የሚመስለው፤ ሽበቶ ፀጉሩና "ትልቅ ሙዝ ይመስላል እለው የነበረ" አፍንጫው ሁሉ እንዳለ ነው:: ለቅጽበት ያህል ቆም አለና በአፍታ ደግሞ በፊት ለፊቴ ቆመ:: ፊቱ በፈገግታ ተሞልቷል:: ስሙን የጠራሁት ይመስለኛል፤ እርግጠኛ ግን አይደለሁም::

"ዶኒ!" አለና ጮኸ (አያቴ ሁልጊዜም የሚጠራኝ እንዲህ ነበር):: አይኖቹ መብራት ጀመሩ፤ አጠገቤ በደረሰባት የመጨረሻ እርምጃውም እጆቹን ወደ እኔ ዘረጋ:: በእቅፉ ውስጥ አስገብቶ ጀርባዬን በእጆቹ እየጠበጠበ ያጽናናኝ ጀመር:: ልክ በልጅነቴ ዓመታት እንደማውቀው ግዙፍና ጠንካራ አያቴ አሁን ደግሞ እንደቀድሞው ሆኖ አየዋለሁ::

በቤታችን ውስጥ በልብ ድካም ህመም በመሰቃየት ላይ ባለበት ሰዓት ከእርሱ ጋር ነበርኩ፤ በአምቡላንስ ውስጥ ሆኜ አብሬው ሄጃለሁ:: ዶክተሩ ወደ እኔ እየተራመደ መጥቶ ከፊት ለፊቴ ሲቆም በድንገተኛ አደጋ የህክምና ክፍል በር ላይ ቆሜ ነበር:: ራሱን በሃዘኔታ እያወዛወዘ፤ ማድረግ የምንችለውን ነገር ሁሉ አድርገን ነበር አለ ልስልስ ባለ ድምጽ::

አያቴ ለቀቀኝ፤ አሻቅቤ ፊቱን ስመለከት ወሰን በሌለው ደስታ ተሞላሁ:: ስለ ልብ ድካም በሽታውም ይሁን ስለ ሞቱ አላሰብኩም፤ ምክንያቱም እንደገና የመገናኘታችንን ደስታ ገና አልጠገብኩትም ነበር:: ሁለታችንም በገነት የመገኘታችንም ጉዳይ ትኩረት የሰጠነው ነገር አልነበረም::

በመጀመሪያ ያየሁት ሰው ለምን አያቴ ሲሆን እንደ ቻለ ምክንያቱን አላውቅም:: ምናልባትም እርሱ በሞተበት ጊዜ አጠገቡ የነበርኩት ሰው እኔ ስለነበርኩ ይሆናል:: እርሱ ምንም እንኳን ሕይወቴ በቀና መንገድ እንዲመራ አስተዋጽኦ የነበረው ሰው ቢሆንም፤ ሕይወቴን በመንፈሳዊ አቅጣጫ ከመሩት ትልቅ ሚና ከነበራቸው መካከል አንዱ አይደለም::

በአያቴ እቅፍ ውስጥ ከተጽናናሁ በኋላ ቀጣዩ ሁለተኛው ወይም ሦስተኛ ሰው ማን እንደነበረ አላስታውስም:: ህዝቡ በዙሪያዬ ከበቡኝ:: አንዳንዶቹ ያቅፉኛል፣ ሌሎች ደግሞ ጉንጬን ይስሙኛል፤ እጆቼን ይጨብጣሉ:: ከዚያ ጊዜ በፊት እንደዚያ የመወደድ ስሜት ተሰምቶኝ አያውቅም::

እኔን ለመቀበል ከመጡት ሰዎች መካከል አንዱ፤ የልጅነት ጓደኛዬ የነበረው ሚክውድ ነበር:: ሚክ ለእኔ የተለየ ሰው ነበር፤



ምክንያቱም ወደ ሰንበት ትምህርት ቤት የጋበዘኝና ክርስቲያን እንድሆን ትልቁን አስተዋፅኦ ያደረገው እርሱ ነው:: ከማውቃቸው ክርስቲያኖች ሁሉ ሚክ ለእምነቱ ፈጽሞ የተሰጠ ወጣት ክርስቲያን ነበር:: ዝነኛና በእግር ኳስ፣ በቅርጫት ኳስ፣ በሩጫና በሜዳ ላይ በሚደረጉ ውድድሮችም ለአራት ዓመታት ኮከብ የነበረ ልጅ ነው:: በተጨማሪም ለእኔ እንደ ሞዴል የሆነልኝም ልጅ ነበር፤ ምክንያቱም የሚናገረውን ቃክርስትና ሕይወት ሲኖረው ተመልክቻለሁ:: የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን ካጠናቀቀ በኋላ ሚክ በሉሲያና ግዛት ዩኒቨርስቲ ውስጥ የሙሉ ነፃ ትምህርት ዕድል አገኘ:: ዕድሜው አስራ ዘጠኝ በደረሰ ጊዜም ሚክ በመኪና አደጋ ተገደለ:: የሞቱን ዜና በሰማሁ ጊዜ ልቤ በሀዘን ተሰብሮ ነበር፤ ያንን ሃዘን ለመርሳትም የወሰደብኝ ብዙ ጊዜ ነበር:: በሕይወቴ ውስጥ እስከዚያን ጊዜ ድረስ ከደረሰብኝ ሃዘን ሁሉ የእርሱ ሞት እጅግ አስደንጋጩና የመረረው ሃዘኔ ነበር::

በቀብሩ ሥነ ሥርዓት ላይ በተገኘሁበት ጊዜ ማልቀስ አቁሜ ከሆነ ይገርመኛል:: እግዚአብሔር እንደዚያ ያለውን ደቀመዝሙር ለምን እንደወሰደው አልገባኝም:: ከዚያ በኋላ ባሉት ዓመታት መሪር ሃዘኑንና መለያየታችንን ለመርሳት አልቻልኩም ነበር:: ሁልጊዜም አስታውሰዋለሁ ማለት አይደለም፤ ባስታወስኩት ጊዜ ግን ንዴቴ ይመጣል::

አሁን ሚክን በመንግስተሰማይ አየሁት:: በክንዶቹ አቅፎ ጀርባዬን በእጆቹ ሲጠበጥብ ስቃዮና ሃዘኔ ጥሎኝ ሄደ:: እንደዚያ ባለ ብሩህ ፈገግታ ውስጥ ሚኪን አይቼው አላውቅም:: እስካሁንም ምክንያቱ ባይገባኝም እንኳን በአካባቢው የተፈጠረው ደስታ ጥያቄን ሁሉ የሚያስረሳ ነው:: ሁሉም ነገር የተባረከና ፍጹም ነው::

ብዙ ሰዎች ወደ እኔ እየመጡ በስሜ ይጠሩኝ ጀመር:: በመንግስተ ሰማይ ሊቀበሉኝ በመጡ ሰዎች ብዛት ትልቅ ደስታ ተሰማኝ:: ቁጥራቸው ብዙ ነበር፤ በፊታቸው ላይ የማየውን ደስታ ያህል ማንም ሰው ተደስቶ እንደሚያውቅ አልገምትም:: ሁሉም ሕይወት የሞላባቸውና ፍልቅ ደስታ የሚነበብባቸው ነበሩ::

በዚያ ጊዜ ትርጉም አልነበረውም:: ይሁን እንጂ ነገሩን ግልጽ ለማድረግ ይህንን የመንግስተ ሰማይ ልምምዴን ከጊዜ ጋር እንዲገናዘብ አድርጌዋለሁ::

እንደገናም ቅድመ አያቴን አየሁት፤ ድምጹንም ሰማሁ:: እነርሱን ለመቀላቀል በዚያ በመገኘቴም የተሰማውን ደስታ ገለጸልኝ:: በትምህርት ቤት የክፍል ጓደኛዬ የነበረውንና በኋላም በሃይቅ ውስጥ ሰጥሞ የሞተውን ቤሪ ዊልሰንን አየሁት:: ቤሪ አቀፈኝ፤ በፊቱ ላይ በማየው ፈገግታ ውስጥ የሚንጸባረቀው ደስታ መገመት ከምችለው በላይ ነበር:: እርሱና ሌሎቹም እግዚአብሔርን እያመሰገኑ የሚከተሉኝ ሁሉ እኔን በማየታቸውና በመንግስተ ሰማይ ሊቃበሉኝ በመምጣታቸውና አብረን ሕብረት በማድረጋችንም የተሰማቸውን ደስታ ሁሉ ገለጹልኝ::

ከዚያ በኋላ ደግሞ፤ ይወዱኝ የነበሩና ብዙ ጊዜ ስለ ኢየሱስ ያጫወቱኝ የነበሩ አስተማሪዎቼን አየኋቸው:: በመካከላቸው በማለፍ ላይ ሳለሁ በእድሜያቸው መካከል የነበረውን ሰፊ ልዩነት አስተዋልኩ:: በእድሜ የሸመገሉና ወጣቶች፤ በእነርሱም መካከል ያሉ በሁሉም ዕድሜ ውስጥ የሚገኙ ሰዎች ነበሩ:: አብዛኞቹ በምድር በኖሩበት ዘመን አይተዋወቁም፤ ይሁን እንጂ ሁሉም ቢሆን በአንድ ወይም በሌላ መንገድ በሕይወቴ ላይ በጎ ተጽእኖ የነበራቸው ሰዎች ናቸው:: ምንም እንኳን



በምድር ላይ እርስ በእርሳቸው የማይተዋወቁ ቢሆኑም፤ አሁን በዚያ የሚተዋወቁ ይመስላሉ::

ይህንን ለመግለጽ ስሞክር፤ ቃላቶቼ የደከሙና ብቃት የሌላቸው ይሆኑብኛል፤ ምክንያቱም ትርጉም ሊሰጠው የማይችል ደስታን፣ ሃሴትን፣ መጽናናትንና ሙሉ ፍስሃን ለመግለጽ ምድራዊ ቋንቋ መጠቀም ግድ ስለሚሆንብን ነው:: ሁሉም ያለማቋረጥ ያጽናኑኝ፣ ይደባብሱኝ፣ ያናግሩኝ ያሳስቁኝና እግዚአብሔርን ያመሰግኑ ነበር:: ይህ ለረዥም ጊዜ የቀጠለ የሚመስል ነበር፤ ይሁን እንጂ በፍጹም አልደከመኝም ነበር::

አባቴ፤ ወላጆቹ ከወለዷቸው አሥራ አንድ ልጆች መካከል አንዱ ነበር:: አንዳንዶቹ ወንድሞቹና እህቶቹ አሥራ ሦስት የሚደርስ ቁጥር ያላቸው ልጆችን ወልደዋል:: ገና ልጅ በነበርኩበት ጊዜ ቤተሰቡ በአንድነት ለመሰብሰብ ብዛት ያሰው ከመሆኑ የተነሣ በአርካንሰስ ሞንትሴሎ ከተማ የሚገኘውን ሙሉውን የመዝናኛ ሥፍራ እኛው እንከራየው ነበር:: እኛ የፒፐርስ ቤተሰቦች እርስ በእርስ የምንዋደድ ስለነበርን በተገናኘን ጊዜ ሁሉ እንተቃቀፋለን፤ እንሳሳማለን:: ይሁን እንጂ በምድር ላይ የነበረው ያ የቤተሰብ የአንድነት ጊዜ በዚህ በመንግስተ ሰማይ ደጃፍ ላይ ካጋጠመኝ የቅዱሳን ጉባኤ ጋር ፈጽሞ ሊመሳሰል የሚችል አልነበረም::

በዚያ በሞንትሴሎ ይሰበሰቡ ከነበሩ ሰዎች መካከል አንዳንዶቹ አሁን ደግሞ በዚህ በመንግስተ ሰማይ ደጃፍ ላይ ሲጠብቁኝ አገኘኋቸዋለሁ:: መንግስተሰማይ ብዙ ነገር ናት፤ ይሁን እንጂ ያለጥርጥር ከሁሉም ይልቅ የቤተሰቦች እንደገና የመገናኛ ሥፍራ ናት::

እዚያ እየሆነ ያሰው ሁኔታ ሁሉ በአዕምሮ ውስጥ ትልቅ ትውስታን የሚያሠርጽ ነው። እንደዚያ ያሰ ታላቅ መጽናናት ተሰምቶኝም ይሁን በእንደዚያ ያሰ ውበት አይኖቼ ተስበው የሚያውቁበት ጊዜ የሰም። የመንግስተ ሰማያዊ ብርሃንና ውበት ምድራዊ እይታንም ይሁን ገሰጻን አልፎ የሚሄድ ነው። ሙቀትና አንጸባራቂ ብርሃን ከቦኛል። አካባቢዬን ስቃኝ አንጸባራቂውንና እጅግ የተዋቡ ቀሰማት ያሉትን የደመና ቁልል ማየት ውበቱ መገመት ከምችሰው በላይ ነው። የማየው የቀሰማት አይነትና የነገሮች ውበት ከዚያ በፊት ያየኋቸውን ማናቸውንም ነገሮች ሁሉ የሚያስንቅ ነበር።

የስሜት ህዋሳቶቼ ሁሉ ንቁና የተጉ ቢሆኑም ቅሉ፣ ከዚህ በፊት ማንኛውም ነገር እንዲህ ፍጹም ወደ እውነት ቀርቦ አይቼም ሆነ ሰምቼ እንደማላውቅ ተሰማኝ። ምንም ነገር መቅመሴን አላስታውስም፣ ይሁን እንጂ ብቀምስ ኖሮ እርሱም በምድር ላይ ከተመገብኳቸው ወይም ከጠጣኋቸው ነገሮች ሁሉ የበሰጠ ሞገስ ያሰው ሲሆን እንደሚችል እውቃሰሁ። ይህንን ነገር መግሰጽ የምችልበት በጣም የተሻሰው መንገድ፣ በተሰየ ሁኔታና አቅጣጫ ውስጥ እንደሆንኩ ይሰማኛል፣ ብሎ መናገር ይመስሰኛል። በምድር ላይ እጅግ ደስተኛ በሆንኩበት ሁኔታ ውስጥ እንኳን እንዲህ ሙሉ የሆነ ሕይወት በጭራሽ ተሰምቶኝ አያውቅም። በእነዚያ በተወደዱ ሰዎች ፊት ሰፊት በዝምታ ቆሜአሰሁ፣ አሁንም ሁሉንም ነገር ሰመረዳት እየሞከርኩ ነበር። አሁንም አሁንም ደጋግሜ የምሰማው ነገር እኔን በማየታቸው ምን ያህል እንደተደሰቱና በመካከላቸውም በመሆኔ የተሰማቸውን ሃሴት የሚገልጹበትን ቃላት ነበር። ቃላቶቹን ይናገሯቸው ወይም አይናገሯቸው እርግጠኛ አይደሰሁም፣ ይሁን እንጂ መምጣቴን ተዘጋጅተው ይጠብቁ እንደነበር



አውቄአሰሁ። በተጨማሪም ደግሞ በመንግስተ ሰማይ ጊዜ እያሰፈ የማይሄድ መሆኑን አውቄአሰሁ።

የሰዎቹን ፊት ትክ ብዬ እንደገና ስመለከት፣ በምድር ላይ ክርስቲያን እንድሆን አስተዋጽኦ አድርገው የነበሩ ወይም እንደ አማኝ በመንፈሳዊ ሕይወቴ እንዳድግ ያበረታቱኝ ሰዎች መሆናቸውን ተገነዘብኩ። እያንዳንዳቸው አዎንታዊ በሆነ መልኩ በሕይወቴ ላይ ተጽእኖ ነበራቸው። እያንዳንዳቸው በሆነ መንገድ የተሻለ ደቀመዝሙር እንድሆን መንፈሳዊ አስተዋጽኦዋቸውን አበርክተዋል። ያንን መረጃ እንዴት እንዳገኘሁት ባልገነዘበውም እንኳን፣ እንደገና ደግሞ አንድ ነገር አውቄአሰሁ፣ ከእርሱ ጋር በመንግስተ ሰማይ እሆን ዘንድ የቻልኩት በእነርሱ ምክንያት ነው።

ለእኔ አድርገውት ስለነበረው ነገር አልተጨዋወትንም። ነገራችን ሁሉ ያጠነጠነው የእኔ በዚያ መገኘት የፈጠረው ደስታና እኔን በማየታቸው ስለተሰማቸው ሃሴት ነው።

በዚያው የተሟሟቀ ሁኔታ ውስጥ እንደነበርን ላቀረቡልኝ የአቀባበል መልካም ቃላት እንዴት መልስ እንደምሰጥ አላወቅኩም ነበር። ከእናንተ ጋር መሆን በመቻሌ በጣም ደስተኛ ነኝ አልኳቸው። እነኝህም ቃላት ቢሆኑ በምወዳቸው በእነዚያ ሰዎች መካከል መሆኔና በመጽናናቴ በውስጤ የሚፈሰውን ደስታ የሚገልጡ አልነበሩም።

ወደ ኋላዬ ትቼው ስለመጣሁት ነገር ሁሉ ምንም አላስታውስም፣ ቤተሰቦቼንም ይሁን የነበረኝን ንብረት ትቼ በመምጣቴ አንዳች ቅሬታ አልተሰማኝም። እግዚአብሔር አስጨናቂ የሆኑና አሉታዊ ነገሮችን ሁሉ ከአዕምሮዬ ውስጥ የጠረጋቸው ይመስላል፣ ማድረግ የቻልኩት አንድ

ነገር ከእነዚህ አስደሳች ሰዎች ጋር በአንድ ላይ በመሆኑ ወሰን የሌለው ደስታ መፌንጠዝ ነበር።

አንድ ጊዜ እንደማውቃቸው እንደነበሩ ሆነው ነው አሁን ያሉት። ልዩነቱ በምድር ላይ ከነበሩበት ከማናቸውም ጊዜ ይልቅ አሁን የሚያንጸባርቁና በደስታ የተሞሉ መሆናቸው ነው።

ቅድመ አያቴ የሆነችው ሃቲ ማነን ዘሯ ከአሜሪካ ጥንታዊ ነዋሪዎች መካከል ነው። በልጅነቴ እርሷን የያኋት በአጥንት ህመም በሽታ ከተያዘች በኋላ ነበር። ጭንቅላቷና ትከሻዋ ወደ ፊት አዘንብለው ነበር። ይህም ክብ ሊሆን ምንም ያህል ያልቀረው የጎበጠ እይታ ሰጥቷት ነበር። በጣም የማስታውሳት ደግሞ ፊቷ በጣም የተጨማደደ በመሆኗ ነው። ስለ እርሷ በነበረኝ ትውስታዬ ሌላው የማልረሳው ነገር ጥርሶቿ አርቴፊሻል መሆናቸውን ነው። ብዙ ጊዜ ግን አታደርጋቸውም ነበር። በመንግስተ ሰማይ በተገናኘን ጊዜ ግን ፈገግታዋን ስትለግሰኝ ጥርሶቿ ያንጸባርቁ ነበር። እነኚህ ጥርሶች አርቴፊሻል ሳይሆኑ የራሷ ጥርሶች እንደሆኑ አውቄአለሁ፤ ፈገግ ስትል ካየኋቸው ፈገግታዎች ሁሉ ውበት ያለው ፈገግታ ነው።

እንደገና ደግሞ አንድ ነገር አስተዋልኩ አሁን እንደ ጥንቱ ጎባጣ አልነበረችም። ጠንካራና ቀጥ ብላ የቆመች ነች፤ ፊቷን ያጨማደዱት እነዚያ የሕይወት መስመሮች ሁሉ ሙልጭ ብለው ጠፍተዋል። በምን ያህል ዕድሜ ላይ እንደሆነች አላውቅም፤ ስለዚህ ነገር ለማሰብም እንኳን አልፈልግም። የሚያንጸባርቅ ፊቷን ትክ ብዬ ስመለከት በመንግስተ ሰማይ የዕድሜ ጉዳይ ዋጋ ያለው ነገር እንዳልሆነ ተገነዘብኩ።

ዕድሜ የሚገልጸው የጊዜን እያለፈ መሄድ ነው፤ በዚያ ደግሞ ጊዜ የሚባል ነገር የለም። በዚያ ያገኘኋቸው ሰዎች ሁሉ ልክ ለመጨረሻ



ጊዜ ባየኋቸው ዕድሜ ላይ ነው የሚገኙት-ልዩነቱ በምድር ላይ ያሳለፉት ሕይወት ያሳደረባቸው ክፉ የሕይወት ጠባሳ ፈጽሞ ተጠርጎ መወሰዱ ነው። በምድር ላይ ምንም እንኳን አንዳንዶቹ የለውነት ገጽታቸው ውበት ያልነበረው ቢሆንም በመንግስተ ሰማይ ግን ሁሉም ነገር አትኩረው ሲመለከቱት የሚያጓጓ ፍጹም የሆነ፣ ውበትን የተጎናጸፈና አስደናቂ ነው።

እነሆ ብዙ ዓመት ካለፈ በኋላ አሁን እንኳን፤ አንዳንድ ጊዜ አይኖቼን ጨፍኜ፤ ከአየኋቸው የለው የፊት ገጽታዎች ሁሉ ፍጹምነት ባለው አቻ በማይገኝለት ፈገግታ ወንድማዊ የፍቅር ግለት ተሞልተው ያስደነቁኝን እነኛን ፊቶች ለማየት እችላለሁ። ከእነርሱ ጋር አብሮ መሆን በራሱ የተቀደሰ ጊዜና ታላቅ ግምት በሚሰጠው ተስፋ ውስጥ እንደመቆየት ማለት ነው።

ለመጀመሪያ ጊዜ መንግስተ ሰማይን ስረግጥ፣ አስቀድሞም ከፊት ለፊቴ ነበሩ፤ ደግሞም እየፈጠኑ ወደ እኔ ይመጡ ነበር። ሁሉም የማጽናናትን ቃል ይናገሩኛል፤ በየትኛውም አቅጣጫ ልመልከት አንድ ጊዜ ይወደኝና እኔም እወደው የነበረውን ሰው እመለከታለሁ። በዙሪያዬ ከበውኝ ይዞሩ ስለነበሩ እያንዳንዳቸው ወደ መንግስተ ሰማይ እንኳን ደህና መጣህ ሊሉኝ ሰፊ እድል ነበራቸው።

የተወደድሁ እንደሆንኩ ተሰማኝ በኖርኩባቸው ዘመናት ከተወደድኩት በላይ እንደተወደድኩ ተሰማኝ። ይናገሩኝ የነበሩትን ቃላት አሁን አላስታውስም። ወደ እኔ አተኩረው ሲመለከቱ፤ መጽሐፍ ቅዱስ፤ ፍጹም ፍቅር ሲል ምን ማለቱ እንደሆነ አወቅሁ። እኔን ከከበቡኝ ሰዎች ሁሉ ፊት ላይ የሚንጸባረቀው ይሄው ነበር።

ወደ እነርሱ አተኩሬ ተመለከትኩ፤ እንዲህ ባደረኩ ጊዜ ደግሞ በእነርሱ ውስጥ የነበረ ፍቅር ወደ እኔ የሚሰርጽ ይመስለኝ ነበር:: ቀና ብዬ በዙሪያዬ ያለውን ሁሉ ቃኘሁት፤ ባየሁት ነገር ሁሉ ፈጽሞ ተማረኩ:: በዚያ ያለው እያንዳንዱ ነገር ብሩህ ገጽታ ነበረው:: ከመግቢያው በር ወጥተው ጥቂት እልፍ እንዳሉ፤ አሁን ከቦን ካለው ብርሃን ይልቅ የደመቀ ንጻት ያለው ውብ ብርሃን ሙሉ በሙሉ ይንጸባረቃል:: የሰዎቹን ፊት አተኩሬ መመልከቴን ባቆምኩ ጊዜ፤ በአካባቢዬ ያለው ሁሉ አስገራሚ በሆነ ደማቅ ብርሃን የሚንቆጠቆጥ እንደሆነ ተገነዘብኩ:: በዚያ የነበረውን ሁኔታ ለመዘገብ፤ ቃላት ፈጽሞ አቅም የላቸውም፤ ምክንያቱም ሰውኛ የሆኑ ቃላት የነበርኩበት ሁኔታ የፈጠረብኝን የአግራሞትና የመደነቅ ስሜት ሊገልጹት አይቻላቸውም::

እመለከተው የነበረ ማንኛውም ነገር አንጸባራቂ የሆነ ብርሃን ያመነጫል:: ደህና አድርጌ ልገልጸው የምችለው ነገር ወደዚያ ብርሃን እየቀረብን መሄዳችንን ነው:: ማንም ሰው እንደዚያ ለማድረግ ጊዜው እንደሆነ አልተናገረንም፤ ይሁን እንጂ ሁላችንም በአንድ ጊዜ ወደፊት መሄድ ጀመርን የእያንዳንዱ ነገር አንጸባራቂነት እየጨመረ ይሄዳል:: ነገሩ ሁሉ ልክ ወደ አንድ ተራራ እየቀረብን በሄድን መጠን ግዝፈቱ እየጨመረ እየጨመረ እንደሚሄደው አይነት ነው:: በሩን አልፈን በገባን ጊዜ የሆነ ጨለማ ነገር እያለሁ ብዬ ገምቼ ነበር፤ ነገር ግን ማየት የምችለውን ያህል አርቄ በተመለከትኩ ጊዜ ሌላ ነገር አልተመለከትኩም ነገር ግን ያየሁት ነገር ቢኖር ብሩህና አንጸባራቂ ብርሃን ብቻ ነው::

በንጽጽር ሲታይ፤ ከመግቢያው በር ላይ ወዳጆቼንና ጓደኞቼን ባገኘሁበት ሥፍራ ያየሁት ታላቅ ብርሃን፤ ከፊት ለፊቴ ካለው እየጨመረ ከሚሄደው አንጸባራቂ ብርሃን ጋር ሲነጻጸር እንደ ጨለማ



የሚቆጠር ነው:: የምራመደው እያንዳንዱ እርምጃዬ የብርሃኑን ነጸብራቅ እየጨመረ እንዲሄድ የሚያደርገው ይመስላል:: ብርሃኑ እንዴት እየጨመረ እንደሚሄድ አላውቅም ነበር፤ የሆነው ግን እንደዚያ ነው:: ነገሩ ሁሉ የጨለማውን ክፍል በር ሰብሮ በመውጣት በእኩለ ቀን ብርሃን ውስጥ እንደመራመድ ይቆጠራል:: በሩ ተበርግዶ በተከፈተ ጊዜ፤ እንደባረቂ በሆነ የፀሐይ ብርሃን ሙላት እንከበባለን፤ ለቅጽበት ያህልም ማየት አንችልም::

በርግጥ ማየት የማልችል አልሆንኩም፤ የብርሃኑ ድምቀትና ውበት እየጨመረ በመሄዱ ግን አገረም ነበር:: ሁሉም ነገር እንግዳ ነገር ይመስላል፤ የሚታየው ነገር ሁሉም ያንጸባርቃል፤ ወደፊት በተራመድኩበት በእያንዳንዱ ቅጽበት አስገራሚው ውበት እየጨመረ ይሄዳል:: ርቄ በሄድኩ መጠን ብርሃኑ ይደምቃል:: ብርሃኑም አጥለቅልቆኛል፤ ወደ እግዚአብሔር መገኛ እየቀረብኩ እንደመጣሁ ይሰማኝ ጀመር:: ምንም እንኳን ምድራዊ አይናችን ከብርሃን ወይም ከጨለማ ጋር የሚላመደው ቀስ በቀስ ቢሆንም፤ ሰማያዊ አይኖቼ ግን ያለምንም ችግር ሙሉ ለሙሉ ይመለከቱ ነበር:: በመንግስተ ሰማይ እያንዳንዱ የስሜት ህዋሳቶቻችን ሙሉ ለሙሉ ለመሥራት መጠነ ሰፊ በሆነ ሁኔታ ብቃታቸው ይጨምራል:: አ! ለስሜት ህዋሶቻችን ይህ እንዴት ያለ ድንቅ ነገር ነው!

ወደፊት እየተራመድኩ በሄድኩ ቁጥር በተቀደሰ አግራሞት እየተሞላሁ መጣሁ:: ከፊት ለፊቴ ሲሆን ስላለው ነገር ምንም እውቀት የለኝም፤ ይሁን እንጂ በማደርጋት በእያንዳንዷ እርምጃዬ መደነቁ እየጨመረ እንደሚሄድ ገምቻለሁ::

እናም ዝማሬ ሰማሁ::

# 3

# ሰማያዊ ዝማሬ

"ኣየሁም፤ በዙፋኑም፣ በእንስሶቹም፣ በሽማግሌዎቹም ዙሪያ የብዙ መላእክትን ድምፅ ሰማሁ፤ ቁጥራቸውም እእላፋት ጊዜ እእላፋትና ሺህ ጊዜ ሺህ ነበረ።" ራዕ 5፥11

ልጅ በነበርኩበት ጊዜ በገጠርና ጥቅጥቅ ባለ ደን ውስጥ ረዘም ያለ ጊዜ አሳልፍ ነበር። በደረቀው ሣር ላይ በምረማመድበት ጊዜ፣ ብዛት ያላቸው ወፎች ከጉጆቻቸው ውስጥ እየወጡ በመሬቱ ላይ ሲያርፉ እደነቅ ነበር። በሚበሩበት ጊዜ የንፋሱ ድምጽ የሚርገበገቡትን ክንፎቻቸውን ያጅበዋል።

በመንግስተ ሰማይ ቆይታዬ ጥርት ያለ ትውስታ ያለኝ ለሰማሁት ነገር ነው። ጥሩ አድርጌ እገልጽበታለሁ የምለው ቃል የክንፎችን የተቀደሰ እርግብግቦሽ ብቻ ነው።

ይሁን እንጂ በመንግስተ ሰማይ ያለው ድምጽ የሚፈጥረውን ሁኔታ በአግባቡ ለመግለጽ ይህንን አባባሌን ሽህ ጊዜ አጎላው ዘንድ ያስፈልገኛል።

ከሰማኋቸው ድምጾች ሁሉ ውበት ያለውና አስደሳች ድምጽ ነበር፤ ደግሞ እኮ ፈጽሞ የሚቆም ድምጽ አልነበረም። ልክ ከዘላለም እስከ ዘላለም እየቀጠለ እንደሚሄድ ዝማሬ ነበር። በመገረም ከመሞላቴ የተነሳ፤ የምፈልገው ነገር ማድመጥን ብቻ ነበር። ዝማሬን ብቻ አልነበረም የምሰማው። እኔ ራሴ የዝማሬው አካል የሆንኩኝ ይመስል



ነበር እናም ዝማሬው ወደ እኔ ውስጥ ይገባል በውስጤም ይመላለሳል። ቀጥ ብዬ ቆሜአለሁ፤ ይሁን እንጂ በዝማሬው ድምጽ እየተጽናናሁ ነበር።

አየሩን ከሞላው አስደሳች ድምጽና ዜማ ጋር መዋሃዴን ተገነዘብኩ፤ ፈጽሞ የሚጠገብ አልነበረም። ሰማያዊያኑ ዘማሪዎች የማንነቴ ሁለንተና ሁሉ በዝማሬው እንዲሳተፍ የፈቀዱልኝ ይመስላል። በዚያው ጊዜ ውስጥ ደግሞ በዙሪያዬ ስለሚሆነው ነገር ሁሉ ለማወቅ አትኩሮቴን ከአካባቢው ላይ አድርጌአለሁ።

የድምጹ ምንጭ ከወዴት እንደሆነ ያየሁት ነገር የለም። እኔ እንደገመትኩት ዝማሬውን ማንም ያመነጨው ድምጽ የሚመጣው ግን ከእኔ በላይ ካለ ስፍራ ነው። ነገር ግን ቀና ብዬ አላየሁም። ለምን እንደሆነ እርግጠኛ አይደለሁም። ምናልባትም ዙሪያዬን በብዙ ሰዎች ስለተከበብኩ ወይም በአንድ ጊዜ በሁሉም ነገር ላይ ትኩረት በማድረጌ ስሜቶቼ በብርቱ ሥራ ስለተጠመዱም ሊሆን ይችላል። አንዳችም ጥያቄ አልጠየኩም፤ ስለምንም ነገር አልተደነቅኩም። ሁሉም ነገር ፍጹም ነበር። ልክ ሁሉንም ነገር እንደማውቀውና የምጠይቀው ነገር እንዳልነበር ይሰማኝ ነበር።

የሚኘርኅደጉዱ ድምጾች አዕምሮዬንና ልቤን ጭምር ሞልተውት ነበር፤ እነኝህን ድምጾች መግለጽ አስቸጋሪ ነው። ይሁን እንጂ እጅግ አስደናቂ የነበረው የመላእክቱ ክንፎች ናቸው። በእርግጥ አላየኋቸውም፤ ይሁን እንጂ የሚያሰሙት ድምጽ ግን ውበት ነበረው፤ በጭራሽ የማያቋርጥ ስልቱን የጠበቀ የተቀደሰ ዜማ። በአየሩ ላይ የሰፈፈው የሚያስተጋባ ድምጽ ማለቂያና ማብቂያ ከሌለው የዘላለም ምስጋና

ምንጭ የሚፈልቅ ይመስላል:: ባደመጥኩት ቁጥር ምን እንደሆነ እረዳው ነበር::

ሁለተኛው ድምጽ ዛሬም ድረስ በውስጤ ቀርቷል፤ ከመንግስተ ሰማይ ቆይታ ልምምዶቼ መካከል ጥርት ያለ ትውስታ ለዚህ አንድ ድምጽ አለኝ:: እኔ ሙዚቃ ብዬ ነው የምጠራው፤ ይሁን እንጂ በምድር በኖርኩበት ዘመን ከሰማሁት ሙዚቃ ሁሉ የተለየ ነው፤ ወደፊትም በምድር ላይ እሰማዋለሁ ብዬ አልገምትም:: የምስጋናው ዜማ እየሩን ሁሉ ሞልቶታል:: የማያቋርጠው አንጸባራቂ ብርሃንና ማለቂያ የሌለው ተሰዋዋጭነቱ በአግራሞት ሞላኝ::

ምስጋናው ፈጽሞ የሚያቋርጥ አልነበረም፤ ይሁን እንጂ እኔ በጣም የማስታውሰው ነገር በአንድ ጊዜ በመቶዎች የሚቆጠሩ መዝሙሮች የመዘመራቸው ነገር ነው ሁሉም እግዚአብሔርን የሚያመልኩ ነበሩ:: ወደ ታላቁ አንጸባራቂ የመግቢያ በር ስቃረብ ዝማሬዎቹን ከተለያዩ አቅጣጫዎች መስማት ቻልኩ፤ እናም እያንዳንዱ ድምጽ እግዚአብሔርን የሚያከብር እንደ ነበር ተገነዘብኩ:: እኔ ዜማ መቀመር እችላለሁ፤ ይሄ ግን ከዚያ የላቀ ነበር:: አንዳንዱ ዝማሬ በሙዚቃ መሣሪያ የታጀበ ይመስላል፤ ነገር ግን እርግጠኛ አይደለሁም ስለ እርሱም ብዙ ትኩረት አልሰጠሁትም:: በየትም ቦታ የምሰማው የምስጋና ድምጽ ነበር፤ ሁሉም ደግሞ በሙዚቃ የተቀነባበረ ነበር፤ ይሁን እንጂ በውስጣቸው ያዘሉት ዜማና ድምጽ ግን ከዚህ በፊት አድምጬው የማውቀው አልነበረም::

"ሃሌ ሉያ!" "ምስጋና!" ክብር ለእግዚአብሔር! "ክብር ለንጉሱ!" የሚሉ ቃላት በሙዚቃው ጣልቃ ገልተው ይደመጣሉ:: እነኝህን ዝማሬዎች መላእክቱ ይዘምሯቸው ወይም ከሰዎች ይውጡ ያወቅኩት



ነገር አልነበረም:: በመንግስተ ሰማይ ሁኔታ እጅግ ተገርሜ ስለነበር ዙሪያዬን አልቃኘሁም:: ልቤ ከዚህ በፊት ቀምሳው በማታውቅ ታላቅ ደስታ ተሞልታ ነበር:: በአምልኮው አብሬ አልተሳተፍኩም፤ ይሁን እንጂ ልቤ በዚያው አይነት ደስታና መንፈሳዊ ልቀት ውስጥ ትፈስ ነበር::

ሦስት የምስጋና ሲዲዎችን በአንድ ጊዜ ከፍተን ብንሰቃቸው ድብልቅልቁና ምስቅልቅሉ የወጣ ድምጽ አዕምሯችንን ይረብሸዋል:: ይህ የምላችሁ ግን ፈጽሞ የተለየ ነው:: እያንዳንዱ ድምጽ ኅብር ባለው ሁኔታ የተዋሃደ ነው፤ እያንዳንዱ ድምጽ ወይም የሙዚቃ መሣሪያ ለሌላው ውበትን የሚጨምር ነው::

ምናልባትም እንግዳ ነገር ሊመስል ይችል ይሆናል፤ ይሁን እንጂ እያንዳንዱን ዝማሬ ጥርት አድርጌ እሰየው ነበር:: የመግቢያ በሩን አልፌ በሄድኩ መጠን የእያንዳንዱን ዜማ ቅኔ እየተረዳሁት የምሄድ ይመስላል::

በሕይወት ዘመኔ በተለያዩ ዓመታት የዘመርኳቸው የቆዩ ቅኔዎችና ዝማሬዎች፤ ከዚህ በፊት ስምቻቸው ከማላውቅ በመቶዎች ከሚቆጠሩ ዝማሬዎች ጋር ተደምረው የሙዚቃው አካል ነበሩ:: የምስጋና ቅኔዎች፣ ዘመናዊ ድምጸት ያላቸው ዝማሬዎችና የቆዩ አጫጭር አዝማቾች ጆሮዎቼን ሞሉት:: በውስጤ የፈጠሩትም ጥልቅ ሰላምን ብቻ ሳይሆን አይቼው የማላውቀውን ደስታ ጭምር ነበር::

ከመግቢያው ፊት ለፊት እንደቆምኩ፤ በዚያ ጊዜ ልብ ባልለውም በኋላ ላይ እንደተገነዘብኩት ግን፤ "እሮጌውና ግዙፉ መስቀል" ወይም፤ "በሚስማር ተቸንክረው የተዘረጉ እጆች" የሚሉ ዝማሬዎችን

አልሰማሁም:: አየሩን የሞሉት የትኞቹም ዝማሬዎች ኢየሱስ በምድር ላይ ስለከፈለው መስዋእትነት ወይም ሞት የሚያወሱ አልነበሩም:: አሳዛኝ ዝማሬዎችን አላዳመጥኩም፤ እንዲሁ በደመ ነፍስ አንድ ነገር ተረዳሁ:: በመንግስተ ሰማይ አሳዛኝ ዝማሬዎች የሉም:: ለምን እንዲዚህ ሆነ? ሁሉም ዝማሬዎች ኢየሱስ የነገሥታት ንጉሥ በመሆኑ የሚያመሰግኑ ነበሩ፤ በዚያ የነበረ በደስታ የተሞላ አምልኮ ለእኛ ስላደረገልን ታላቅ ነገርና ኢየሱስ ምንኛ ድንቅ እንደሆነ የሚያበስሩ ዝማሬዎች ነበሩ::

ሰማያዊ ዝማሬዎች ከሰማኋቸው ሁሉ የላቁ ነበሩ:: የዝማሬዎቹን ቁጥር ማስላት አልችልም:: ምናልባትም በሺህ የሚቆጠሩ ይሆናሉ፤ በአንድነት ያለማቋረጥ ይንቆረቆራሉ፤ ይሁን እንጂ አይዘበራረቁም፤ ይህን እንድል ያስቻለኝ እያንዳንዱን ዝማሬ ለማዳመጥና ግጥማቸውንና ዜማቸውንም አጣርቼ ለመለየት ችሎታው የነበረኝ በመሆኑ ነው::

ሞገስ በጠገበው በዚያ ዝማሬ ተገርሜ ነበር:: በሕይወት ሳለሁ ጥሩ የተባለ የዝማሬ ድምጽ ባይኖረኝም፤ አሁን ግን ብዘምር ድምጼ በትክክለኛው ቅኝት ውስጥ እንደሚገባና፤ በጆሮዬ እየተንቆረቆረ ካለው አየሩን ከሞላው በሺህ የሚቆጠሩ ሌሎች ድምጾችና የመዚቃ መሣሪያዎች ጋር ህብር ባለው ሁኔታ ተዋህዶ መዘመር እንደምችል አውቄአለሁ::

አሁን ወደ ምድር ከተመለስኩ በኋላ እንኳን፤ አንዳንድ ጊዜ እነኛ ዝማሬዎች እንደ ገደለ ማሚቶ ድምጽ እያስተጋቡ በዝግታ ሲመጡ አደምጣቸዋለሁ:: በተለይ ደግሞ ድክምክም ብዬ በአልጋዬ ላይ ጋደም ባልኩና አይኖቼን በጨፈንኩ ጊዜ፤ አልፎ አልፎ በእንቅልፍ የምወሰደው



በነዚያ ልቤንና አዕምሮዬን በሚሞሉ ሰማያዊ ድምጾች እየሰማሁ ነው:: ቀኑ ለእኔ ምንም ያህል አስቸጋሪ ሆኖ ይዋል፤ ወዲያውኑ እያንዳንዱ ህልውናዬ ጥልቅ በሆነ ሰላም ይሞላል:: ዛሬም ቢሆን ትውስታዎቼ አልጠፉም፣ እርግጥ ነው እነኝህ ትውስታዎች እኛ ትውስታ ከምንላቸው ነገሮች የተለዩ ናቸው:: የእኔው ትውስታ ከእይታ ይልቅ አጅጉን በድምጽ ላይ የተመሠረተ ነው::

ስለ ዝማሬዎቹ ያለኝን ትውስታ በጥልቀት ስመለከተው፤ ሁኔታዎቹ ያልተለመዱ ናቸው:: በመንግስተ ሰማይ ላየሁት አንድ ነገር ወይም የተወደዱት ሰዎች ላደረጉልኝ ማጽናናት ጥልቅ የሆነ ትውስታ እንዲኖረኝ እፈልጋለሁ:: ከዚያ ይልቅ ደግሞ እነዚያን የሰማሁዋቸውን ድምጾች እጅግ ወድጃቸዋለሁ፤ አንዳንድ ጊዜም፤ እንደገና በግል እሰማቸው ዘንድ በጣም እናፍቃለሁ እላለሁ:: ወደፊት ይሆናል ብዬ የምጠብቀውም ይህንኑ ነው:: በዚያ ያሉትን ሁሉ ማየት እፈልጋለሁ፤ አንድ ነገር ደግሞ አውቃለሁ ከእነርሱ ጋር ለዘላለም እሆናለሁ:: በመንግስተ ሰማይ በተዘጋጀው ነገር ሁሉ ላይ መሣተፍ እፈልጋለሁ፤ ከሁሉም ይልቅ የምናፍቀው ግን እነዚያን ማብቂያ የሌላቸውን ዝማሬዎች መስማት ነው::

እውነቱን ለመናገር እግዚአብሔር ምን እንደሚሰማው አላውቅም፤ በማያቋርጠው የምስጋና ድምጽ እንደሚደሰትና እንደሚባረክ ባሰብኩ ጊዜ ግን ደስታና መጽናናት ይሰማኛል::

በእነኛ ደቂቃዎች ውስጥ-እርግጥ ነው ለእኔ የጊዜ ጉዳይ ግምት የሚሰጠው አልነበረም-ሌሎች ይነኩኝ ነበር፤ ፍቅር የተሞላው ሞቅ ያለ

የማበረታታት መንካታቸው ፍጹም እውነታዊ ነበር:: በዚያ ከዚህ ቀደም አይቻቸው የማላውቃቸውን ቀለማትም ተመልክቻለሁ:: በዚያ ከነበርኩበት ጊዜ ይህ ሕይወቴ ሙሉ እንደሆነ ተሰምቶኝ የሚያውቅበት ጊዜ የለም::

በቤቴ ውስጥ ነበርኩ፤ ለእኔ ሊሆን በተፈጠረና እኔም የእርሱ በሆንኩ ቤቴ ውስጥ! በምድር ላይ በየትኛውም ስፍራ ከተገኘሁበት ጊዜ ይልቅ በዚያ ብዙ ጊዜ ለመቆየት እፈልግ ነበር:: ጊዜው እያለፈ ሄዷል፤ እኔ ግን አሁንም በመንግስተ ሰማይ ውስጥ ነኝ:: የትኞቹም ጭንቀቶቼ፣ መረበሾቼና ስጋቶቼ ሁሉ ከእኔ ተጠርገው ተወስደዋል፤ ምንም አይነት ፍላጎቶች የሉኝም:: ሁሉም ነገር ፍጹም እንደሆነ ተሰማኝ::

መንግስተ ሰማይ ምን እንደሚመስል ለመግለጽ ፍርሃት ይሰማኛል፤ ምክንያቱም የመንግስተ ሰማይ እይታ ምን እንደሚመስል፣ ሁኔታው ምን እንደሚመስልና ምን ስሜት እንደሚሰማ በቃላት ልገልጸው ስለማልችል ነው:: በርግጥ ሁሉም ነገር ፍጹም ነው፤ ምንም ተጨማሪ ፍላጎት እንደሌለኝና ወደፊትም እንደማይኖረኝ አውቃለሁ:: ሌላው ይቅርና ስለምድር ወይም ወደ ኋላ ትቼው ስለመጣሁት ነገር በፍጹም አላሰብኩም::

እግዚአብሔርን አላየሁትም:: ምንም እንኳን እግዚአብሔር በዚያ እንዳለ ባውቅም፤ መለኮታዊ መገኘቱን የሚጠቁም ምስል ወይም የሚያንጸባርቅ ብርሃን አልተመለከትኩም:: አንዳንድ ሰዎች ወደ ውስጥኛው በር ገብተው እንደገና ስለመመለሳቸው ሲናገሩ ሰምቻለሁ:: ያ በእኔ ልምምድ ውስጥ አልተፈጸመም::



ያየሁት ነገር ቢኖር እጅግ አንጸባራቂ የሆነ የቀስተ ዳመና ከፊል ክበብ ነው:: በበሩ አቅጣጫ አሻግሬ ተመለከትኩ፣ በዚያ ያለውን ለማየት እጅግ ጓጉቼ ነበር:: ጭንቀት የተሞላበት ጉጉት አልነበረም፤ ይልቁንም የመንግስተ ሰማይን ፀጋና ደስታ ለመለማመድ ከነበረኝ ሰላም ካለው ግልጽነት የመነጨ ጉጉት ነበር::

ያንን ሁኔታ በሚመለከት ለእኔ ትርጉም የሚሰጠኝ አስተሳሰብ አንድ ብቻ ነው፤ በእርግጥ እግዚአብሔርን አይቼው ቢሆን ኖሮ ወደ ምድር ለመመለስ በጭራሽ አልፈልግም ነበር:: አንድ ጊዜ በእርግጥ በእግዚአብሔር ህልውና ፊት ከሆንን፤ በጭራሽ ወደ ምድር ዳግመኛ እንመለስም፤ ምክንያቱም በንጽጽር ሲታይ ሁሉም ነገር ባዶና ትርጉም የሌለው እንደሆነ አስባለሁ::

እንደ እኔ ከሆነ፤ ከመንግስተ ሰማይ ደጃፍ ላይ መድረሱ በራሱ አስደናቂ ነገር ነው:: ከመታወቅ ያለፈም መለኮታዊ ደስታ ነው:: የሆነውን ነገር ለመግለጽ ቃላት እጅጉን ብቃት ያላቸው አይደሉም::

እንደ ቤተክርስቲያን መጋቢነቴ፤ በመካነ መቃብር ሥፍራ በበርካታ የአስከሬን ሳጥኖች ፊት ቆሜ፤ "ጌታን ለሚያውቁትና ለሚወዱት፤ ከሥጋ መለየት ማለት ከእርሱ ጋር መሆን ማለት ነው" እያልኩ ሰብኬአለሁ::

እነዚያን ቃላት አምናቸው ነበር:: አሁን ግን አብዝቼ አምንባቸዋለሁ::

ጥቂት ቆይቶ፤ በአንድነት ሆነን ወደ መግቢያው በር መጓዝ ጀመርን:: ማንም ሰው ባይናገርም እንኳን እግዚአብሔር እነዚህን ሰዎች ሁሉ እንዲቀበሉኝና ወደ መግቢያው በር እንዲሸኙኝ የላካቸው መሆኑን አወቅሁ::

አቀባበል ባደረጉልኝ ሰዎች አናት ላይ አሻግሬ ስመለከት፤ በሁለት አቅጣጫዎች ለአይን እየራቁ በሚደበዝዙ አጥሮች ጋር የተያያዘ አስደናቂ የመግቢያ ደጅ ቆሟል:: ከዚህ ከታላቁ የመግቢያ በር ጋር ሲነጻጸር አስቀድሞ ያለው በር በጣም ትንሽ ነው:: አፍጥጬ ተመለከትኩ፤ ከበሩ በሁለት አቅጣጫዎች የተዘረጉትን አጥሮች መጨረሻ ስማየት ግን አልቻልኩም:: ወደ ላይ ቀና ብዬ ስመለከት የከፍታቸውን መጨረሻ ማየትም አልቻልኩም::

አንድ ነገር እጅግ አስደነቀኝ:: በምድር ላይ ሆኜ ስለመንግስተ ሰማይ ባሰብኩ ቁጥር፤ አንድ ቀን በከበሩ ድንጋዮች የተሠራ አምድ እንደምመለከት እገምት ነበር፤ ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስም በከበሩ ድንጋዮች ስለተገነባ የመግቢያ ደጅ ይናገራል:: ደጁ የተሠራው በከበሩ ድንጋዮች አልነበረም፤ ይልቁን በብርሃን በተንቆጠቆጡ አምዶች የተገነባ ነበር:: ምናልባትም በተለያየ አቅጣጫ ሲመለከቷቸው የተለያየ ቀለማት በሚፈነጥቁ ፈርጦች የተገነባ ቢባል፤ ምናልባት በተሻለ ሁኔታ ይገልጸው ይሆናል:: እኔ የመሰለኝ፤ ልክ አንድ ሰው በተጋገረ ድፎ ኬክ ላይ አንጸባራቂ ማጣፈጫዎችን እንደሚረጭባቸው አይነት ሆኖ ነው የተሰማኝ:: ደጁ ያበራል ደግሞም ያንጸባርቃል::

ባገኘኋት ትንሽ ፋታ አንጸባራቂ ወደሆኑ በቀለማት የተዋቡ የብርሃን አመልማሎችና ወደ ነፀብራቃቸውም ተመለከትኩ:: የቀለማቱ ህብርና ውበት እጅግ አስገረመኝ፤ ለተወሰነ ጊዜም በእርሱ ላይ



እንዳተኩር አደረገኝ:: ይሁን እንጂ ወደፊት መራመዴን ቀጠልኩ፤ ሁኔታው ሁሉ ወደ እግዚአብሔር መገኛ ሥፍራ በክብር እየተሸኘሁ ይመስላል::

ከደጁ ውጭ ቆም አልኩ፤ ወደ ውስጥም መመልከት ቻልኩ:: በተጠረቡ ድንጋዮች የተሰሩ አውራ ጎዳናዎች እንዳሏት ከተማ ትመስላለች:: እጅግ የተደነቅኩት ደግሞ እነኝህ ጎዳናዎች የተሠሩት እውነተኛ በሆነ የወርቅ ጥርቦች ነው:: ምናልባት ከወርቅ ጡቦች የተሠሩ መንገዶችን በአይነ ልቡናችሁ መሣል የምትችሉ ከሆነ፤ ከደጁ ዘልቆ የተመለከትኩትን ሊገልጸው የታቃረበ ገጽታ እንደሆነ አስባለሁ::

ያየሁት ነገር ሁሉ የሚያበራ ነው:: አይኖቼ ካዩዋቸው አንጸባራቂ ቀለማት ሁሉ ድምቀት ነበራቸው በመሆኑም ከኃይሉ የተነሣ እንዲህ ያለውን ብሩህ ድምቀት ምድራዊ ሰው ሊቋቋመው አይቻለውም::

እንዲህ ባለው ታላቅ አግራሞት ውስጥ ሆኜ ወደ በሩ እየተራመድኩ ተጠጋሁ፤ ወደ ውስጥ እየገባሁ እንዳለም ገመትኩ:: ጓደኞቼና ዘመዶቼ ሁሉ ከፊት ለፊቴ ናቸው፤ ይጠሩኛል፣ ያበረታቱኛል፣ እንድከተላቸውም ይጋብዙኛል::

ድንገት ሁኔታዎች ተቀየሩ:: ይህን መግለጽ የምችለው በዚህ መንገድ ብቻ ነው፤ ከፊት ለፊት የነበሩት ከበስተጀላዬ ሆነው አገኘ ኋቸው:: በዚያ ታላቅ ደጅ ውስጥ በማልፍበት ጊዜ ከጎኔ መሆን እንደፈለጉ ገመትኩ::

አንዳንድ ጊዜ ሰዎች፤ “እንዴት ነበር የምትንቀሳቀሰው? ትራመድ ነበር? ትንሳፈፍስ ነበር?” እያሉ ይጠይቁኛል:: እንዴት እንደሆነ እኔ አላውቅም:: እኔ የማውቀው ሊቀበሉኝ ከመጡት ሰዎች

ጋር ሆኜ ዝም ብዬ እሄዳለሁ፡፡ ከደጃፉ ዘንድ በተቃረብን ጊዜ የዝማሬው ድምጽ እየጨመረ ውበቱም እያየለ ሄደ፡፡ ነገሩ ሁሉ በጥቂቱ የስሙትን በጣም ከርቀት የዩትን አስደናቂ ሁኔታ በቅርበትና በዝርዝር ለመረዳት እየቀረቡ እየቀረቡ እንደመምጣት ያለ ነው፡፡ በተጠጋን መጠን ሁሉም ነገሮች ውበት ያላቸው፣ ሕይወት ያላቸውና አስገራሚዎች እየሆኑ ይሄዳሉ፡፡ ልክ ወደ ደጁ እንደቀረብኩ ስሜቴ ይልቁን እየተነቃቃ ሄደ፤ እናም ወሰን በሌለው ደስታ ተሞላሁ፡፡

ልክ በደጃፉ ላይ ቆም አልኩ፤ ለምን እንደሆነ ግን አላውቅም፡፡ እይታዬን በገዛው ነገር ሁሉ ተደስቻለሁ፤ እናም ወደ ውስጥ ለመግባት ፈለግኩ፡፡ እስከ አሁን ካየሁትና ከሰማሁት ነገር ሁሉ የላቀና አስደሳች ነገር አውቄአለሁ፡፡ ልክ በዚያው ቅጽበት የሰው ልጆች ሁሉ ናፍቆት ምን እንደሆነ ተገነዘብኩ፡፡ በዚያ ጊዜ በመንግስተ ሰማይ ደጅ ቆሜ ነበር፤ በሚያንጸባርቁ የብርሃን አምዶች አቋርጬ ወደ ውስጥ ለመዝለቅ ተዘጋጅቻለሁ፡፡

ቅጽበታዊ በሆነች የእረፍት ጊዜ ውስጥ፤ አንድ ሌላ ነገር ደግሞ ተቀይሮ ነበር፡፡ እግዚአብሔርን የሚያመሰግኑ በሽዎች የሚቆጠሩ ድምጾችንና ዝማሬዎችን ከመስማት አልፌ፤ አሁን እኔ ራሴ የዝማሬው ተሣታፊ ሆኜአለሁ፡፡ ከሁሉም ጋር አንድ ሆኜአለሁ፤ በመካከላቸውም አስገብተውኛል፡፡ ለረዥም ዓመታት ልጎበኘው እናፍቀው በነበረው ሥፍራ ላይ ተገኝቻለሁ፡፡ ወደ ፊት ከመቀጠሌ በፊት በዝግታ ዙሪያዬን ሁሉ ቃኘሁ፡፡

ከዚያ በኋላ፤ በድንገት በመንግስተ ሰማይ ደጆች ላይ እንደ ተገኘሁ ሁሉ፤ ድንገት ትቻቸው ሄድኩ፡፡



# 4

# ከመንግሥተ ሰማይ ወደ ምድር

"በሞት ጥላ መካከል እንኳን ብሄድ አንተ ከእኔ ጋር ነህና ክፉን አልፈራም በትርህና ምርኩዝህ እነርሱ ያጽናኑኛል፡፡" መዝ (23)፥4

የህክምና ባለሙያዎቹ አደጋው በደረሰበት ሥፍራ እንደተገኙ ወዲያው የመሞቴን ዜና ተናገሩ፡፡ አደጋው በተፈጠረበት ቅጽበት እንደሞትኩም ገለጹ፡፡ እንደተዘገበው ከሆነ ግጭቱ የተፈጠረው ከቀኑ 5:45 ነበር፡፡ የህክምና ባለሙያዎቹ በአደጋው የተጎዱትን ሌሎች ሰዎች ሲረዱ ቆይተው ወደ እኔ እንደገና የተመለሱት በ7:15 ላይ ነው፡፡ የልብ ምቴን አንድ ጊዜ እንደገና ተመለከቱ፡፡

እንደሞትኩ ነበርኩ፡፡

የመንግስቱ ህግ፤ አስከሬኑን ከአደጋው ስፍራ ከማንሳታቸው በፊት መሞቴን በይፋ ማረጋገጥ እንደሚገባቸው ይደነግጋል፡፡ "ሞቷል" ብለው የማያረጋግጡ ከሆነ አምቡላንስ ወደ ስፍራው መጥቶ አስከሬኑን በማንሣት ወደ ሆስፒታል መውሰድ ይጠበቅበታል፡፡ አደጋው የተፈጠረበት አካባቢ መንግስት በአደጋ የሞቱ ሰዎችን ጉዳይ የሚመረምር የተለየ ቢሮ አልነበረውም፤ ይሁን እንጂ በኋላ ልረዳ እንደቻልኩት፤ የፍትህ ቢሮው የጸጥታ ክፍል ሞቴን ሲያረጋግጥላቸውና ሙት አካሌን ማንሣት እንዲችሉ ማድረግ ይችል ነበር፡፡

ከእስር ቤቱ አምቡላንሶች መጡ፤ ንብረትነታቸው የመንግስትና የሀንትስ ቢላ ነበር፡፡ ከአንዱ በስተቀር ሌሎቹ አምቡላንሶች ምንም



ከወደላይ: የዶን ፎርድ መኪና ከአደጋው በኋላ የነበረበት ሁኔታ ነው::
ከወደታች: አደጋው የተፈፀመበት ሥፍራ





ተጎጂዎችን ሳይጭኑ በመጡበት ተመለሱ:: የመጨረሻውም ሊሄድ ተዘጋጀ:: በኋላ ላይ ከሰበሰብኩት መረጃ እንደተረዳሁት፤ አንድ ሰው በአደጋ የሞቱ ሰዎች ከመቀበራቸው በፊት አስከሬናቸው ወደሚያርፍበት ሥፍራ ሊያስወስደኝ የሆነ መኪና አዘጋጅቶ ነበር::

ከተጨረማመተችው መኪና ውስጥ አካሌን ለማውጣት የሚረዳ መሣሪያ አስመጡ:: የሞትኩ በመሆኑ ነገሮቹን ፈጠን ማድረግ ያን ያህል አስፈላጊ አልነበረም:: ትልቁ ትኩረታቸው መኪናዋን ከድልድዮ ላይ በማንሣት የትራፊክ ፍሰቱ እንደገና ሂደቱን እንዲቀጥል ማድረግ ነው::

ያ ከባድ መኪና ተጠምዝዞ በመምጣት በላዩ ላይ በወጣበት ጊዜ፤ የመኪናዬን የላይኛውን ክፈን ሙሉ ለሙሉ ጨፈላልቆት ነበር:: በዚህ ጊዜም ዳሽ ቦርድ ወደ እግሬ መጥቶ የቀኝ እግሬን አደቀቀው:: የግራ እግሬ ደግሞ ለሁለት ተጎምዶ በዳሽ ቦርድና በመቀመጫው መካከል ተበታትኗል:: የቀኝ እጄ ከጭንቅላቴ በላይ አልፎ በመቀመጫዎቹ ላይ ተጋድሟል:: ገናም ሙሉ ለሙሉ ከሰውነቴ አልተላቀቀም፤ የሆነ ነገር አጣብቆ በጥቂቱ ተንጠልጥሏል::

ያ የግራ እጄ በሾፌሩ በኩል ባለው በር ላይ የተደገፈ ነበር፤ መኪናውን አሽከረክር የነበረው በቀኝ እጄ ነው:: በኋላ ላይ እንደተረዳሁት ዋና ዋናዎቹ አጥንቶቹ ጠፍተዋል፤ በዚህም ምክንያት የታችኛው የግራ እጄ ክፍል ከቀሪው ሰውነቴ ጋር የተያያዘው በትንሽ ሥጋ መሰል ነገር ብቻ ነው:: በግራ እግሬ ላይ የሆነውም ተመሳሳይ ነገር ነው:: ከጉልበቴ በላይ የነበረ አንድ የደም ሥር ገናም ደም ከጉልበቴ በታች ባለው እግሬ ላይና በእግሬ ጫማ ላይ በማፍሰስ ላይ

ነበር። የህክምና ዶክተሮች መላው ደሜ ከሰውነቴ ፈሶ ለምን እንዳላለቀ ለመግለጽ የህክምና ቋንቋ የላቸውም።

የመስተዋት ስብርባሪና ደም በስፍራው ሁሉ ተረጭቷል። በአደጋው ጊዜ የመኪናው መስተዋት ሲደቅቅ በፊቴ ላይ የፈሰሰ በመሆኑ በርካታ ጥቃቅን ጉድጓዶች በፊቴ ላይ ተፈጥረዋል። የካባድ መኪናው በፊት ጎማ በደረቴ ላይ ቆሞ ስለነበር፣ ከአይኔ፣ ከጆሮዬና ከአፍንጫዬ ደም ይጎርፍ ነበር።

በአደጋው ወቅት የተዘገበውን የህክምና ሪፖርት በማየት እንደተረዳሁት፣ ሃኪሙ ጭንቅላቴ እንደተጠፈጠፈና የውስጥ ብልቶቼ ሁሉ ስፍራቸውን እንደለቀቁ አውቋል። ገና ከመጀመሪያው የልብ ምቴ መቆሙን ካረጋገጠ በኋላ፣ አንድ የህክምና ባለሞያ ውሃ የማያሳልፍ ጨርቅ ሸፈነኝ፣ ይህም የመኪናዋን አካል ሁሉ የከደነ ነበር። እኔን ከስፍራው ለማንቀሳቀስ ወይም ወዲያውኑ ካለሁበት ሁኔታ ውስጥ ለማውጣት ምንም ሙከራ አላደረጉም። ምክንያቱም አካሌን ከመኪናው ውስጥ ጎትቶ ወይም ወደ ላይ አንጠልጥሎ ለማውጣት ከቶውን የማይታሰብ ነገር ነበር የግድ ያ አካልን ከተጨፈላለቀ መኪና ውስጥ ማውጣት የሚችል መሣሪያ ያስፈልጋል።

አደጋው በደረሰ ጊዜ እርዳታ ፈጥኖ መገኘት እንዲቻል ያደረጉት፣ ከከባድ መኪናው ኋላ ኋላ በመከተል ላይ የነበሩት ፖሊሶች ወደ እስር ቤቱ በመደወል የድንገተኛ አደጋ እርዳታ ሰጭ ሠራተኞች እንዲደርሱ በማድረጋቸው ነው። እንደዚያ ባይሆን ኖሮ የእርዳታ ሰጭ ተሽከርካሪዎች ከሚገኙበት ሥፍራ በጣም የራቅን ነበርን።

በሌሎቹ ሁለት መኪናዎች ውስጥ የነበሩትን አሽከርካሪዎች መረመሯቸው፣ ሁለቱም አልቆሰሉም፣ በመሆኑም ቀጣይ የህክምና



ዕርዳታ እንዲደረግላቸው ወደ ሆስፒታል ለመሄድ ፈቃደኞች አልሆኑም። ከባድ መኪናውን ያሽከረክር የነበረው እስረኛም ምንም አይነት የመቁሰል አደጋ አልደረሰበትም። የህክምና ባለሙያዎቹ ጤነኛ እንደሆነ ባረጋገጡበት ቅጽበት ይዘው ወደ እስር ቤቱ መለሱት። ፖሊስ በድልድዩ ላይ የነበረውን ሁሉንም የትራፊክ እንቅስቃሴ በመግታት የአምቡላንሱን መምጣት በመጠባበቅ ላይ ነበር። አምቡላንሱን እየተጠባበቁም በሁለቱም አቅጣጫዎች በተለይም እኔ በመጣሁበት አቅጣጫ ረዥም ርቀት መኪና ተሰልፎ መቆም ቀጠለ። ከሁለት አቅጣጫ መኪና ማስተላለፍ የሚችል ጠባብ መንገዶች ያሉት ድልድይ ነበር፣ መኪኖችን በቀላሉ መታጠፍ የሚያስችል አልነበረም። መጠራቀም የጀመረው ተሽከርካሪዎች መታጠፍ ቢችሉ እንኳን ወደ አቅጣጫቸው በሚያስገባቸው መንገድ ውስጥ ለመግባት ተጨማሪ አርባና ሃምሣ ማይሎችን መጓዝ ይጠበቅባቸዋል።

ከተለዋጩ መንገድ ቢያንስ ቢያንስ ግማሽ ማይል በመጓዝ፣ ዲክና አኒታ ዋንሪክር በእግራቸው በመጓዝ ወደ አደጋው ሥፍራ ደረሱ። ዲክና አኒታ በሰሜን ሃውስተን በሚገኘው ካሊን ውስጥ ቤተክርስቲያን መሥርተዋል። ተካፍዬው በተመለስኩት ጉባኤ ላይ ሁለቱም ንግግር አቅርበዋል። በትሪኒቲ ፒንስ የጉባኤ አዳራሽ በግል ስለመገናኘታችን እርግጠኛ አይደለሁም። ለብዙ ዓመታት የዲክ ዋንሪክርን መልዕክቶች አዳምጫለሁ፣ በአካል እርሱን ያየሁበት ጊዜ ግን ያ ጉባኤ ነበር።

ረቡዕ ዕለት ጠዋት ባልና ሚስቱ ከእኔ ጥቂት ደቂቃዎች ቀደም ብለው የትሪኒቲ ፒንስን የጉባኤ አዳራሽ ለቀው ወጡ። ከሀውስተን አማካይ የሙቀት መጠን አኳያ የጥር ወር ጠዋት በጣም ቀዝቃዛ ነው።

በጉዟቸው ላይ ሳሉ፤ አኒታ እንዲህ አለች፤ "በብርድ እየተንቀጠቀጥኩ ነው፤ አንድ ጊዜ ቆም ብለን ቡናመጠጣት እንችላለን? ምናልባት ሙቀት ሲሰጠን እንዲችል አስባለሁ" አለች::

ዲክ፣ በሊቪንግስተን ሃይቅ አቅራቢያ አንድ ምግብ ቤት በማየቱ ወደዚያው አመሩ:: እነርሱ ቡና በመግዛት ላይ ሳሉ ነበር እኔ በመኪናዬ አልፌአቸው የሄድኩት::

ከዚያ በኋላ ዲክ ብዙ ጊዜ ፊቱን በእጁ መዳፎች ውስጥ እየቀበረ፤ "በቀላሉ ምን ይደርስብን እንደነበር ታውቃለህ? አደጋው የሚደርሰው በእኛ ላይ ሊሆን ይችል ነበር፤ አንተ እኮ የተጋጨኸው እኛ መኪናችንን በማቆማችንና አንተ አልፈኸን በመሄድህ ነው" ሲል ተናግሯል::

ባልና ሚስቱ ወደ ድልድዩ ከመድረሳቸው በፊት አደጋው ተፈጠረ፤ የመኪና እንቅስቃሴም ቆሞ መኪናዎች መጠራቀም ጀመሩ:: ሰዎች ከመኪናዎቻቸው እየመጡ በአካባቢያቸው እየተንቀሳቀሱ ከፊታቸው ስለተፈጠረው ነገር ጥያቄ መጠያየቅ፣ ያላቸውንም ጥቂት መረጃ ይወያዩበት ነበር::

ዲክና አኒታ ከመኪናቸው ውስጥ እንደወጡ አንዱን አሽከርካሪ፤ "በዚያ የተፈጠረው ነገር ምንድን ነው?" ሲሉ ጠየቁት::

"አንድ ከባድ መኪና አንዷን መኪና ጨፍልቋታል" የሚል ወሬ እየተላለፈ መጣ::

ዲክና አኒታ ጥቂት ደቂቃዎች በዚያ ቆዩ፤ የተፈጠረ ነገር ግን አልነበረም፤ ጭራሽ ከእነርሱ መኪና በኋላ ሌሎች መኪናዎች እየመጡ ይደረደሩ ጀመር:: በ6:30 እና 6:45 መካከል ባለ ጊዜ ውስጥ አደጋው



ወደተፈጠረበት ሥፍራ ለመሄድ ወሰኑ:: አንድ ፖሊስ ባገኙ ጊዜም ዲክ፤ "እኔ የቤተክርስቲያን አገልጋይ ነኝ፤ እኔ ልረዳው የምችል ሰው ይኖር ይሆን? ማለትም ልጸልይለት የምችል ሰው ይኖር ይሆን?" ሲል ጠየቀው::

ፖሊሱ ራሱን በመነቅነቅ፤ "በእነዚያ ሁለት መኪናዎች ውስጥ ያሉ ሰዎች ..." አለ፣ ወደ መኪናዎቹ በጣቱ እየጠቆመ፤ "የደረሰባቸው ግጭት አነስተኛ ቢሆንም በጥሩ ሁኔታ ላይ ነው የሚገኙት:: ከፈለጋችሁ ልታነጋግሯቸው ትችላላችሁ::"

"ሌላውስ መኪና? ከባድ መኪናው በላዩ ላይ የቆመበት?"

"በቀይዋ መኪና ውስጥ ያለው ሰው ሞቷል::" ዲክ ከፖሊሱ ጋር በመነጋገር ላይ እንዳለ አኒታ ወደ ሌሎቹ መኪናዎች አመራች:: ገና በጥቂቱ ጎንጨት ያደረገችለትን ቡና ለሽማግሌው ሰጠችው::

በኋላ ላይ ዲክ ሁኔታውን የገለጸው እንዲህ ሲል ነበር፤ "እግዚአብሔር እንዲህ ሲል ተናገረኝ፤ በቀይዋ መኪና ውስጥ ላለው ሰው መጸለይ ያስፈልግሃል":: ዲክ እጅግ ታዋቂ የሆነ የመጥምቃውያን ቤተክርስቲያን ሰባኪ ነው:: ለሞተ ሰው ጸሎት ማድረግ እርሱ ከሚያምንበት ትምህርተ መለኮት ያለፈ ነገር ነው:: "ይህን ማድረግ አልችልም፤" ሲል አሰበ:: "እዚያ ሄጄ የምጸልየው በምን መንገድ ነው? ሰውየው እኮ ሞቷል::"

ዝናቡ ጥቅጥቅ አድርጎ ካፊያውን እየለቀቀው ነበር፤ ይሁን እንጂ ዲክ በዙሪያው ያለውን አጥርቶ መመልከት ችሏል:: ወደ ፖሊሱ አፍጥጦ ተመለከተ፤ ሊናገረው ያለው ነገር ትርጉም ሊሰጠው

እንደማይችል አውቋል። ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ጥርት አድርጎ ስለተናገረው ሊያደርግ ስላሰው ነገር አንዳች ጥርጥር አልነበረውም። ለሞተው ሰው ይጸልይለት ዘንድ እግዚአብሔር ተናግሮት ነበር። ነገሩ ሁሉ እንግዳና ያልተለመደ ቢሆንበትም ዲክ መንፈስ ቅዱስ ወደ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ውስጥ እንዲገባ ውስጡን እያነሳሳው ነበር።

"በቀይዋ መኪና ውስጥ ላለው ሰው መጸለይ እፈልጋለሁ" አለው ዲክ በመጨረሻው።

"እንደነገርኩህ ሰውየው ሞቷል። "

"ነገሩ እንግዳ እንደሚሆንብህ አውቃለሁ፤ ይሁን እንጂ በማንኛ ውም መንገድ ልጸልይለት እፈልጋለሁ።"

ፖሊሱ አንዳች ቃል ከመናገሩ በፊት ትኩር ብሎ ሲመለከተው ቆየና በመጨረሻው፤ "ደህና ማድረግ የምትፈልገው ያንን ከሆነ ቀጥል፤ ነገር ግን እንደነገርኩህ በዚያ የሚታየው ነገር ሁሉ ዘግናኝ ነው። ሰውየው ሞቷል፤ ከዚያ መኪናውን ከሸፈነው ጨርቅ በታች የምትመለከተው ነገር ቢኖር የተበጣጠሰ የሰው አካል ነው። ስፍራውን የሞላው ነገር ደምና ስብርባሪ ጠርሙስ ነው። አካሉ ደግሞ እንዳይሆን ነገር ሆኗል። "

ዕድሜው በአርባዎቹ ውስጥ የነበረው ዲክ እንዲህ አለው፤ "በሼትናሙ ጦርነት ጊዜ ህክምና በመስጠት አገልግያለሁ፤ እናም የደሙ ጉዳይ የሚያስቸግረኝ አይደለም።"



"ላስጠነቅቅህ ግድ ነው" አለ ሰውየው ቆም አለና፤ ትከሻውንም ሰበቅ አድርጎ "ማድረግ የምትፈልገውን አድርግ፤ ነገር ግን ከዚህ ቀደም እንደዚህ አደጋ የደረሰበት አካል አይተህ እንደማታውቅ እነግርሃለሁ።"

"አመሰግናለሁ" አለና ዲክ ወደተሸፈነችው መኪና አመራ። በፎቶግራፉ ላይ እንደምትመለከቱት፣ ለማመን እጅግ አስቸጋሪ ነው፤ ይሁን እንጂ ዲክ በደረቱ እየተሳበ በመኪናዪ ኮፈን ላይ ወጣ። መኪናዋ ከኋላዋ የሚከፈት በር ነበራት፤ ደግነቱ ያ የመኪናዋ አካል አልተጎዳም። መኪናዋ በጨርቅ ተሸፍናለች፤ ያንን ከላዪ ላይ ማንሣት አልቻለም፤ በመሆኑም የመኪናዋ ውስጥ ሙሉ ለሙሉ ጨልሟል። ዲክ በጥንቃቄ እየተሳበ ከኋላዪ ወደ እኔ ተጠጋ፤ በጀርባው መቀመጫ ላይ በደረቱ ተኛ ና እጁን በቀኝ ትከሻዪ ላይ አሣረፈ።

እናም ይጸልይልኝ ጀመረ። በኋላ ላይ "እንድጸልይ አንዳች ነገር እያስገደደኝ እንዳለ ተሰማኝ። ሰውዬው ማን እንደሆነ፤ አማኝ ይሁን አይሁን አላውቅም። የማውቀው ነገር ለዚያ ሰው እንድጸልይለት እግዚአብሔር እንደተናገረኝ ብቻ ነው" ሲል ተናግሯል።

ዲክ በመጸለይ ላይ ሳለ፤ ስሜቱ ይቀስቀስና ደጋግሞ ማልቀስ ይጀምራል። ቀጥሎ ደግሞ መዘመር ጀመረ። ዲክ ድምፀ መልካምና በአደባባይም የሚዘምር ሰው ነው። ዝማሬን ለመዘመር ሲል ደጋግሞ ጸሎቱን ቆም ያደርግ ነበር።

ዲክ እግዚአብሔር ለእኔ እንዲጸልይልኝ እንደጠራው ብቻ አልነበረም ያመነው፤ ይልቁንም የማይታየው በሽታ ማለትም ህሊናየና ውስጣዊ አካሌ ህመም ሁሉ እንዲፈውስ ነበር በእምነት ይጸልይልኝ የነበረው።

ይህ ምናልባት ግራ የሚያጋባ ይሆናል፤ ምክንያቱም ዲክ መሞቴን ያውቅ ነበር፡፡ ፖሊሱ በነገረው ብቻ ሳይሆን እርሱ ራሱ ንዝረቴን ተመልክቶ አረጋግጧል፡፡ በዚያ ሁኔታ ለምን ይጸልይ እንደነበረ አልተረዳውም፤ የሚያውቀው አንድ ነገር እግዚአብሔር እንደተናገረው ብቻ ነው፡፡ ይፀልይ የነበረው ለሚመለከተው ውጫዊ አካሌ ጉዳት አልነበረም፤ ውስጣዊ ለሆነው ጉዳቴ ብቻ መጸለዩን ቀጠለ፡፡ እርሱ እንደተናገረው ይፀልይ የነበረው ከዚህ በፊት ጸልዮ በማያውቀው ሁኔታ በከፍተኛ ፍቅር፤ ጽናትና ስሜት ውስጥ ሆኖ ነበር፡፡ በኋላ ልረዳው እንደቻልኩት ዲክ በከፍተኛ ስሜት የሚቀጣጠል ሰው እንደሆነ ነው፡፡

እናም እንደገና መዘመር ጀመረ እንዲህ እያለ፤ "ከውድቀት ሥጋት የተነሳ ለምን ሰላምን አጣን? አላስፈላጊ የሆነ ስቃይስ ስለምን ተሸከምን? ምክንያቱ ነገሮችን ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት በጸሎት ማቅረብ ባለመቻላችን ነው!" እየሆነ ስለነበረው ነገር ሁሉ በግሌ እርግጠኛ ሆኜ የማውቀው ነገር ቢኖር፤ ዲክ "በክርስቶስ ወንድሞች ነን" የተሰኘውን ቆየት ያለ የተባረከ መዝሙር መዘመር በጀመረበት ጊዜ አብሬው መዘመር መጀመሬን ነው፡፡

ወደ አዕምሮዬ በተመለስኩበት ቅጽበት፤ ሁለት ነገሮችን ተገነዘብኩ፡፡ የመጀመሪያው ነገር እየዘመርኩ ነበር፤ በመንግስተ ሰማይ ከነበረው የዝማሬ ዜማ የተለየ ዝማሬ፡፡ አስቀድሞ የራሴን ድምጽ ነበር የሰማሁት፤ ቆይቶ ደግሞ ሌላም ሰው ይዘምር እንደነበር ተገነዘብኩ፡፡

የተገነዘብኩት ሁለተኛው ነገር፤ አንድ ሰው እጄን ግጥም አድርጎ እንደያዘኝ ነበር፡፡ ያ አያያዝ ጠንካራና ኃይለኛ ነበር፤ ወደ ምድራዊው ሕይወት በተመለስኩ ጊዜ በአካሌ ላይ በመጀመሪያ የተሰማኝ ስሜት ያ ነበር፡፡



እጄን አጥብቆ የያዘኝን የእዚያን እጅ ታላቅነት ለመረዳት ከዓመት በላይ ወስዶብኛል፡፡

# 5
# በምድር ሆስፒታል ውስጥ

"አሁን ግን የሚበልጠውን እርሱም ሰማያዊ አገር ይናፍቃሉ። ስለዚህ እግዚአብሔር አምላካቸው ተብሎ ሲጠራ በእነርሱ አያፍርም፤ ከተማን አዘጋጅቶላቸዋልና"

ዕብ 11፥16

ስለዚያች ብትንትኗ ወጥቶ ስለቆመች መኪና ዓለም ምን እንደዘገበች አላውቅም፤ በዚያ ረቡዕ ከሰዓት በኋላ ግን ዲክ ዋንሪከር መናገር እስኪሳነው ድረስ ይንተባተብ እንደነበር እርግጠኛ ነኝ። የሞተ ሰው አብሮት መዘመር በጀመረ ጊዜ፤ ከዚያች ጭርምትምቷ ከወጣ መኪና ውስጥ እየደኸ ወጥቶ በቅርቡ ወደሚገኝ የህክምና ባለሙያ እየሮጠ ሄደ።

"ሰውዬው በሕይወት አለ! አልሞተም! በሕይወት አለ! " ማን ሊያምነው ይችላል? ሰባኪው፣ ከሞተ አንድ ሰዓት ተኩል ላለፈው ሰው መፀለይ መጀመሩ በራሱ አስገራሚ ነው።

መንገዱን በፈጣን ሩጫ እያቋረጠ፤ "ሰውየው ወደ ሕይወት ተመልሷል! " እያለ ይጮህ ጀመር።

የህክምና ባለሙያው ትኩረት ሰጥቶ ይመለከተው ገባ። "በሕይወት አለ! የሞተው ሰውዬ አብሮኝ መዘመር ጀምሯል"



በኋላ ላይ ከሁኔታቸው ሊረዳው እንደቻለው የሚናገራቸው ቃላት ትርጉም የሰጣቸው አልነበረም። እርሱ ግን፤ "እየዘመረ ነው! በሕይወት አለ" እያለ መጮሁን ቀጠለ።

"ኧረባክህ ... እውነትህን ነው?" ሲል ሃኪሙ በፌዝ ጠየቀ።

"ከምሬ ነው የምናገረው፤ ይህ ሰው በሕይወት አለ! "

"እኛ የህክምና ባለሙያዎች ነን። የሞተን ሰው በእይታ ብቻ ለይተን እናውቃለን። ያ ሰው ፈጽሞ ሞቷል። "

"የምነግራችሁን አድምጡ፤ ሰውየው ከእኔ ጋር እየዘመረ ነበር በሕይወት አለ! "

"ለማንኛውም የፍትህ ቢሮው የፀጥታ ሠራተኛ ወደዚህ እየመጣ ነው።" ካለ በኋላ እኔ መሞቴን እነርሱ ቢያውቁም እንኳን በጉዳዩ ላይ ስልጣን ያለው ሰው በስፍራው ተገኝቶ መሞቴን እስካላረጋገጠ ድረስ አካሌን ማንሣት ባለመቻላቸው ምክንያት መዘግየታቸውን ገለጸለት። በመቀጠልም፤ "ነገር ግን ፍጹም እርግጠኛ ሆኜ እነግርሃለሁ ሰውዬው ሞቷል" አለው። ወደ መኪናው ተጠግቶ ሁኔታዬን ማየት ስላልፈለገ ሰውዬው ፊቱን አዙሮ ከዲክ ፊት ፈቀቅ አለ።

በርካታ አምቡላንሶች መጥተው በመጡበት ሁኔታ ተመልሰው ሄደዋል።

ዲክ በዚያ ቀርቶ ወደነበረው አንድ አምቡላንስ በፍጥነት ሄዶ ሹፌሩን፤ "ያ ሰው በሕይወት አለ። ብትፈልግ ሂድና ተመልከተው" ሲል ተማጸነው።

የህክምና ባለሙያው የአዕምሮ ጤና የጎደለበትን ሰው እንደሚያነጋግር እርግጠኛ ሆኖ፤ "እባክህ፤ ሥራችንን ጠንቀቅን እናውቃለን:: ሰውየው ፈጽሞ . . ."

"አንድ ጊዜ አድምጠኝ! በዚህ ድልድይ ላይ ተጋድሜ እተኛለሁ፤ ወደዚህ መጥተህ የማትመለከት ከሆነ፤ ረግጠኸኝ ብቻ ነው ማለፍ የምትችለው!"

"ሰውዬው ሞቷል:: "

"እንደዚያ ከሆነ በእኔ ላይ ማላገጥ ትችላለህ:: አንድ ጊዜ ሄደህ የደም ንዝረቱን እጣራ" ዲክ ልመናውን ቀጠለ::

"ይሁን ለአንተ ስንል ሄደን እናጣራለን" ሲል አጉተመተመ ሰውዬው:: ወደ መኪናው ሄደ፣ የተሸፈነውን ጨርቅ ገለጠ፣ ወደ ውስጥ ገባና የቀኝ እጄን ጨበጠ:: የደም ንዝረት እንዳለኝ አየ::

አሁን ሰው ሁሉ በፍጥነት መንቀሳቀስ ጀመረ:: ከመኪናው ውስጥ እንዴት እንደሚያወጡኝ መነጋገር ቀጠሉ:: በአንደኛው የመኪናዋ ጎን ሊያወጡኝ ይችሉ ነበር፤ እንደዚያ አድርገው ቢያወጡኝ የግራ እግሬ እዚያው ይቀር ነበር:: በዳሽቦርዱ፣ በእግሬና በመቀመጫው መካከል እንዳችም ክፍተት አልነበረም:: ስለሆነም የግድ እግሬን መቁረጥ ነበረባቸው:: ለነገሩ እግሬ ከቀረው ሰውነቴ ጋር የተያያዘው ላመል ያህል ነው:: ቀኝ እግሬንም ማውጣት ስለመቻላቸውም እንኳን እርግጠኛ አልነበርኩም:: በተጨፈለቀ መኪና ውስጥ የሰውን አካል የሚያወጣውን ጃውስ ኦፍ ላይፍ የተባለውን መሣሪያ ሳይጠቀሙ እኔን ለማውጣት ቢሞክሩ የተወሰነው አካሌ መኪናው ውስጥ መቅረቱ የግድ ነበር:: አስፈላጊው መሣሪያ እስኪመጣ መቆየቱን መረጡ:: መሣሪያው



ከሁንትስቪላ በፍጥነት እንዲመጣ ስልክ መደወል ጀመሩ፤ ያ ስፍራ ደግሞ ቢያንስ ቢያንስ ሰላሣ ማይሎች ያህል ርቀት ነበረው:: እርግጠኛ ነኝ ማድረግ የሚችሉትን ሁሉ አድርገውልኛል፤ እኔ ግን የማውቀው ነገር አልነበረም:: ብዥታ በሞላበት ትውስታ ውስጥ ሆኜ ሰዎች በዙሪያዬ ሲንቀሳቀሱ፣ ሲዳስሱኝና ሲነጋገሩ ይታወቀኛል:: ድምጽ ይሰማኛል፤ ነገር ግን የሚነጋገሩት ምን እንደሆነ በውል መረዳት አልችልም:: ዲክ ትቶኝ ለመሄድ አልፈቀደም:: እንደገና ወደ መኪናው ውስጥ ገባና በአጠገቤ ተንበርክኮ መሳሪያው እስኪመጣ ድረስ መጸለዩን ቀጠለ:: ከአጠገቤ የተለየው ከመኪናው ውስጥ አውጥተው አምቡላንስ ውስጥ ካስገቡኝ በኋላ ነበር:: የህክምና ባለሙያዎቹ ከመኪናዋ ውስጥ ሲያወጡኝ ብዙ ሰዎች መሆናቸውን ማስታወስ ጀምሬአለሁ ቢያንስ ስድስት ወይም ሰባት ያህል ነበሩ:: እያንቀሳቀሱኝ ሳለ ስለ እግሬ ሲነጋገሩ ሰማሁ:: እንዲያውም አንደኛው ሰው፤ የግራ እግሬ ተጎምዶ እንዳይወድቅ ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚገባቸው ይናገር ነበር::

መላው የሰውነት ሥርአቴ ተናግቶ ስለነበር ምንም የህመም ስሜት አይሰማኝም ነበር በዚያ ጊዜ በምንም አይነት ሁኔታ ህመም አልተሰማኝም:: የህመም ስሜት ይሰማኝ የጀመረው በኋላ ላይ ነው::

በቃሬዛው ላይ አስተኝተው ወደ አምቡላንሱ እየገፉ ወሰዱኝ:: የሆነ የብርሃን ጨረር በፊቴ ላይ አረፈ:: ከበላዬ የነበረው ድልድይ ከተሠራበት የብረት ፍርግርጎች ሌላ የታየኝ ነገር አልነበረም:: ጭንቅላቴን ማንቀሳቀስ አልቻልኩም:: ሰዎች ሲንቀሳቀሱና በእግራቸውም የጠርሙስ ስብርባሪዎችን ከመሬቱ ጋር እያሹ ሲያደቅቁ ይሰማኛል:: ድምጻቸውን ዝቅ አድርገው ነበር የሚናገሩት:: በመሆኑም የሚናገሩት ምን እንደነበር ለማወቅ ተቸግሬ ነበር::

"አንድ አስቃቂ ነገር በዚህ አካባቢ ተከስቷል:: ይህ አስቃቂ ነገር የደረሰው ደግሞ በእኔ ላይ ይመስለኛል" የሚል ዐይነት ሃሣብ ያሰብኩ ይመስለኛል:: ምንም እንኳን ወደ አምቡላንሱ እየወሰዱኝ እንደነበር ባውቅም፤ ያለክብደት እንደሆንኩ ይታወቀኛል::

አምቡላንሱ ወዴት ወዴት እንደተጓዘ የማውቀው ነገር የለም፤ በኋላ ግን ወደ ሁለት ሆስፒታሎች መሄዳችንንና የእነዚህ ሆስፒታሎች ደረጃም ከገጠር ክሊንኮች ትንሽ ከፍ የሚል እንደነበር ተረድቻለሁ::

"ልናደርግለት የምንችለው ነገር የለም" ሲል ሰማሁት አንድ ዶክተር ከመረመረኝ በኋላ:: "በሕይወት መቆየት የሚችል አይደለም:: ምንም እንኳን ከመኪናው ውስጥ በሕይወት ብታወጡትም፤ የሚተርፍ ነገር አይደለም:: ተስፋ የለውም"

እንደገና በአምቡላንሱ ውስጥ አስገብተው ይዘውኝ ሄዱ:: ከአምቡላንሱ ውስጥ አውጥተው በመጠኑ ሰፋ ወዳለው የክልሉ የህክምና ማዕከል ወደሆነው ሁንትስቪላ ወደተባለው ሆስፒታል ሲያስገቡኝ እንደሰመመን በሆነ ትውስታ ትዝ ይለኛል:: ከቀኑ 8:30 ላይ ነበር::

በዚያ ጊዜ ባለስልጣኖቹ ጉዳዩን ለባለቤቴ ለኢቫ አሳውቀዋት ነበር:: በትምህርት ቤት ውስጥ እያስተማረች ነበር፤ አንድ ሰው ወደ ትምህርት ቤት ደውሎ ስለ አደጋው እንዲነገራት አደረገ:: ሌላ ሰው ደግሞ ሦስቱ ልጆቻችን ወደሚማሩበት ት/ቤት ደወለ:: የቤተክርስቲያን አባላት የሆኑ ሰዎች ከኢቫ አንዳች ቃል እስኪያገኙ ድረስ ልጆቹን ወደ ቤታቸው ወሰዷቸው::

ከሰዓታት በላይ ሞቼ እንደነበር ማንም አላወቀም:: ወደ ምድር በተመለስኩበት የመጀመሪያዎቹ ሰዓታት የጉዳቱ መጠን ምን ያህል



ታላቅ እንደነበር ምንም ዐይነት ግንዛቤ አልነበራቸውም:: ስለአደጋው ዝርዝር ሁኔታ በትክክል ባይረዱትም እንኳን፤ የቤተክርስቲያን አባሎች ስለ መፈወሴ ይጸልዩልኝ ነበር:: ሌሎችም በጸሎት እንዲተባበሯቸው መደዋወል ጀምረዋል::

ኢቫ ሞቼ እንደነበር ያወቀችው አደጋው ከደረሰ ከሁለት ሣምንት በኋላ ዲክ ዋንሪከር ሲጠይቀኝ ወደ ሆስፒታል በመጣባቸው ቀኖች በአንዱ ነበር:: ከዚያ በኋላ ብቻ ነበር ነገሩ ምን ያህል ከባድ እንደነበረ የተረዳቻው:: በተጨማሪም በዚያው ጊዜ የኢንሹራንስ ወኪላችንና የሳውዝ ፓርክ ቤተክርስቲያን አባል የሆነችው አንዲልማን በአደጋው የተጨፈላለቀችው መኪና ከድልድዩ ላይ ከተነሳች በኋላ የተወሰደውን ፎቶ ግራፍ ይዛ መጣች:: ኢቫ የአደጋውን ከባድነት ማወቅ የነበረባት ቀደም ብሎ መሆን እንደነበረበት ተናገረች:: ጨምራም፤ በወቅቱ ትሠራው በነበረው ነገር ላይ ትኩረት ስጥታ ስለነበር ስለአደጋው በሰማች ጊዜ ቀላል ይሆናል ብላ በመገመት ያን ያህል ትኩረት ሳትሰጠው ልትቀር ትችል እንደነበር ተናግራለች::

ከዚያ በኋላ ልጆቻችን፣ ቤተሰቦቻችንና ወዳጆቻችን ሁሉ አደጋው ምን ያህል ከባድ እንደነበርና በሕይወት መኖር ወደማልችልበት ሁኔታ ተቃርቤ እንደነበር ተገነዘቡ::

ከህክምና ባለሙያዎቹ አንዱ፤ "አሁን እዚህ ደርሰናል:: አሁን ደህና ትሆናለህ" አለ::

ወደ ሆስፒታል ውስጥ እንደገባሁ አውቄአለሁ:: እኔን ለተሸከመው ባለተሽከርካሪ ጎማ ቃሬዛ መንገድ ለመልቀቅ ሰዎች

በፍጥነት ወደ ኋላቸው ሲያፈገፍጉ ድንግዝግዝ ባለ ብዥታ ውስጥ ማየት ቻልኩ:: ፊቶች ወደ እኔ አጎንብሰው ይመለከታሉ፤ ቃሬዛው እየተሽከረከረ ባለበት ሁኔታ ለቅጽበት አይኖቻችን ይጋጫሉ::

እኔን ይጠባበቅ የነበረ ዶክተር ወዳለበት ክፍል ወሰዱኝ:: ሁሉም ነገር እንግዳ ነው፤ ይመረምረኝ ስለነበረው ዶክተር የማስታውሰው አንድ ነገር፣ ሰውየው መላጣ እንደነበረ ነው:: ለተወሰነ ጊዜ ስመረምረኝ ቆየ:: በኋላም፤ "ሚስተር ፒፐር፤ አንተን ለማዳን ማድረግ የምንችለውን ነገር ሁሉ አድርገናል" አለ:: ሦስት ጊዜ ያህል እንደተናገረ እርግጠኛ ነኝ:: "ክፉኛ ነው የተጎዳኸው፤ በጽኑ ተጎድተሃል፤ ይሁን እንጂ ማድረግ የምንችለውን ሁሉ አድርገናል::" በኋላ ላይ እንደተረዳሁት፤ ምንም እንኳን ለእፉ ይህንን ቢናገርም ይተርፋል ብሎ በፍጹም ተስፋ አላደረገም:: ይሁን እንጂ ተስፋ እንዲኖረኝና በሕይወት ለመኖር እንድፍጨረጨር ማድረግ የሚችለውን ነገር ሁሉ አድርጓል:: በርካታ ሰዎች በዙሪያዬ ይሽከረከሩ ነበር:: በእርግጥ እኔ በሕይወት እንድቆይ ጥረት እያደረጉ ነበር፤ እኔ ግን ምንም ዐይነት የህመም ስሜት አይሰማኝም:: ነፍሴ በሰለለች ቀጭን የብርሃን አመልማሎ ላይ የተንጠለጠለች አይነት ሁኔታ ውስጥ ነበርኩ:: ምንም ስሜት አይሰማኝም፤ ይሁን እንጂ ድንግዝግዝ ባለ ሰመመን ውስጥ በዙሪያዬ እየሆነ ስላለው ነገር በጥቂቱም ቢሆን ግንዛቤ ነበረኝ::

"ባለቤትህን በስልኩ ውስጥ አቅርበንልሃል" ሲል አንድ ሰው ተናገረ:: በቴሌፎን ወደ ድንገተኛው ክፍል አመጧት፣ ነርሷ የቴሌፎኑን ቀፎ ወደ ጆሮዬ አቀረበችው፤ እናም ከኢቫ ጋር መነጋገራችን ትዝ ይለኛል፤ ይሁን እንጂ ስለተነጋገርነው ነገር አንዲት ቃል አላስታውስም::



ኢቫ የተለዋወጥነውን ንግግር ሁሉ ታስታውሰዋለች:: እርሷ እንደተናገረችው ከሆነ የተናገርኩት፤ "ይህ ስለተፈጠረ በጣም አዝናለሁ" የሚሉትን ቃላት ብቻ ነበር::

"አይዞህ ዶን፤ ያንተ ስህተት አይደለም"

እኔ እየደጋገምኩ፤ "በጣም አዝናለሁ:: ወደ ቤቴ መምጣት ነበር የፈለኩት፤ እባክሽ ወደ ቤቴ ውሰጂኝ" ማለቴን ቀጠልኩ:: ልክ ህፃናት እንደሚያደርጉት ዐይነት ባለ ሁኔታ፤ በሰማያዊው ቤቴ መቆየት የማልችል ከሆነ ምድራዊ ወደሆነው ቤቴ መመለስ እንደምፈልግ እገልጽ ነበር::

በሀውስተን ወደሚገኘው ሂርማነን ሆስፒታል የአካል ጉዳተኞች ማዕከል፤ በሕይወት እድን ሂሊኮፕተር ሊያጓጉዙኝ እንደሆነ ደጋግመው አሳውቀውኛል:: ይሁን እንጂ የአየሩ ጠባይ ጥሩ ያልነበረና ደመናውም በጣም ወርዶ ሰማዮን ጋርዶ ስለነበር ሂሊኮፕተሯ እንዳትንቀሳቀስ ወሰኑ::

የጤንነቴ ሁኔታ በፍጥነት እያሽቆለቆለ በመውረዱ፤ ነፍሴ ያንን ከሰዓት በኋላ እንኳን ማለፍ እንደምትችል እርግጠኞች አልነበሩም:: በዚህ ምክንያት የህክምና ቡድኑ ከበድ ያለ ውሳኔ ወሰነ:: ወደ አምቡላንሱ መልሰው በማስገባት ሰማንያ ማይልስ ያህል ርቆ ወደሚገኘው ወደ ሀውስተን ሊወስዱኝ ተስማሙ:: እኔን ሊንከባከቡ የሚችሉበት የተሟላ ነገር አልነበራቸውም:: ዳግመኛ በሕይወት የመኖር እድል ያለኝ ከሆነ፤ መድረስ ያለብኝ ብቸኛው ስፍራ የሂርማነን ሆስፒታል ብቻ ነበር::

ሌላ አዲስ አምቡላንስ አቀረቡ:: እንደዚያ በቆሰልኩበት ሁኔታ ውስጥ በየትኛውም ሰኮንድ ልሞት እንደምችል ያስቡ ነበር:: አንዳንድ ጥቃቅን ነገሮች ማገናዘብ ጀመርኩ፤ ለምሳሌም የአዲስን መኪና አዲስ መአዛ በተለይም ደግሞ የቀለሙን ሽታ መለየት ቻልኩ::

መኪናው መንቀሳቀስ እንደጀመረ "አንተ የመጀመሪያው ህመምተኛችን ነህ" አለ የህክምና እርዳታ የሚሰጠኝ ሰው::::

"ምን አልክ?"

"በዚህ አምቡላንስ ለመጓጓዝ አንተ የመጀመሪያው ሰው ነህ አለ":: ወደ ሀውስተን ልንወስድህ ነው:: በምንችለው ፍጥነት ሁሉ ወደዚያ እናደርስሃለን::"

"በምን ያህል ፍጥነት ልንጓዝ?" ሾፌሩ በአጠገቤ የተቀመጠውን ረዳቱን ጠየቀው::

"መብረር በምትችልበት ፍጥነት ሩጥ"::

"ያ ማለት ፍጥነቱ ምን ያህል ይሁን ማለት ነው?" ሾፌሩ ደግሞ ጠየቀ::

የነዳጅ መስጫውን እስከመጨረሻው እርገጠው! አሁኑኑ ከዚያ መድረስ አለብን!

ጉዞውን ከመጀመራችን አስቀድሞ ምንም አይነት የህመም ስሜት አይሰማኝም ነበር:: በውጪ ነፍስ ግቢ ነፍስ ሁኔታ ውስጥ ነበርኩ:: ክብደት አልባ እንደሆንኩ ይሰማኛል ማለትም አዕምሮዬ መላውን አካሌን መቆጣጠር አይችልም:: ይሁን እንጂ እስር ደቂቃ ያህል ቁልቁለቱን እንደተጓዝን ቀለል ያለ የህመም ስሜት ይሰማኝ ጀመር:: በመጀመሪያ



የተሰማኝ በግራ ክንዴ አካባቢ ነበር:: ቀጥሎ ደግሞ የግራ እግሬ ህመም ተሰማኝ:: ራስ ምታቱ ቀጠለ:: በደቂቃዎች ውስጥ የመላው አካሌ ስቃይ ተሰማኝ፤ በተለይ የትኛው ስፍራ ላይ እንደሚያመኝ ለይቼ ማወቅ እስከማልችል ድረስ አካሌ ሁሉ በህመም ይሠቃይ ጀመር:: በመሆኑም ከስቃዩ ለማምለጥ ስል መጮህ ቀጠልኩ:: ጥልቅ የሆነ የህመም ስቃይ ሁለንተናዬን አዳረሰው:: ሰውነቴ ሙሉ በሙሉ የቆሰለ፣ የተቆነጠጠ ወይም እንደተነከሰ ዐይነት ነበር የሚሰማኝ:: ከሰውነቴ አካል በስቃይ የማይጮህ እንዳልነበረ አስባለሁ:: እጮህ እንደነበር እገምታለሁ፤ እርግጠኛ ግን አይደለሁም:: በእያንዳንዱ የልቤ ምት ፍጥነት መላው አካሌ አንዳች በሚያህል መራጃ እንደተፈለጠ ያህል ይሰማኛል::

"እባካችሁ አንድ ነገር ማድረግ አለባችሁ" ስል ልመናዬን አቀረብኩ፣ በመጨረሻው "መድሃኒት ... ወይም የሆነ ... " እስከዚያ የነበረውን ነገር አስታውሣለሁ::

"መስጠት የምችለውን ሁሉ ሰጥቼሃለሁ"

"መስጠት የምትችሉትን ሁሉ ሰጥታችሁኛል?" የተናገረው ቃል ትርጉም የሚሰጥ አልነበረም:: መድሃኒት ሰጥተውኝ ከሆነ ያን ያህል ስቃይ እየተቀበልኩ የነበረው ለምንድን ነበር?

"እባካችሁ ..."

"አዕምሮህን እንድትስት ማድረግ አልችልም" አለ ሃኪሙ::

"አዕምሮህ ንቁ እንደሆነ መቆየት አለበት"

"እባክህ ... አንድ ነገር ..."

በአዕምሮዬ ነቅቼ መቆየት ለምን እንዳስፈለገ ሊገባኝ አልቻለም:: አውጥተው ቢወረውሩኝ እንኳን ህመሙ ለቆኝ ይሄድ ነበር:: "እባክህ ... " ስል እንደገና ለመንኩት::

"አዝናለሁ:: ባደርግልህ ደስ ይለኝ ነበር፤ ነገር ግን ከዚህ በላይ ተጨማሪ ልሰጥህ አልችልም:: አንተ የወሰድከውን ያህል መድሃኒት ሰዎች ቢወስዱ ብዙዎቹ ሩሃቸውን ይስታሉ:: በአመዛኙ ሲታይ ግዙፍ የምትባል ዐይነት ሰው ነህ፤ ይሁን እንጂ ህሊናህን እንድትስት አልፈልግም::"

በቀረው የጉዟችን ወቅት በስቃይ እንዳጓራሁ፣ እንዳጣጣርኩ ወይም ብዙ ጊዜ እንደጮኩ እርግጠኛ ነኝ:: መኪናው በሌሎች ተሽከርካሪዎች መካከል እየተሽሎከለከ ወደፊት ወደኋላ እያለና እየተንገጫገጨ ጉዞውን ቀጠለ፤ የሳይረኑ ድምጽ ያለማቋረጥ ይጮሃል:: በሕይወቴ ካደረኳቸው ጉዞዎች ሁሉ ስቃይ የተሞላበትና አስጨናቂው ጉዞ ነበር::

አሁን እንኳን አይኖቼን ጨፈን አድርጌ አንቡላንሱ በዚያ ፍጥነት እየበረረ በኩርባ መንገዶች ላይ ሲተጣጠፍ የነበረውን መንገራገጭ ማስታወስ እችላለሁ:: ከሃኪሞቹ አንደኛው የተጨናነቀ የትራፊክ ሰዓት ሲናገር ሰማሁ፤ በመሆኑም ሰዓቱ 11:00 አካባቢ እንደሆነ ገመትኩ:: በዚያው ቅጽበት ቀኑ እንዴት እየተንቀረፈፈ ይሄድ እንደ ነበር ገረመኝ::

ጉዞው ፈጽሞ ማለቂያ የሌለው ይመስል ነበር፤ ይሁን እንጂ በህመሙ ምክንያት ብዙ ጊዜ ነፍሴ እየወጣች እንደገና እየተመለሰች እንደነበር አስባለሁ:: በመጨረሻው በህውስተን ውስጥ በሚገኘው



ሄርማንን ሆስፒታል የድንገተኛ አደጋ እርዳታ መስጫ ክፍል ውስጥ ተገኘን::

ሰዓቱ ከምሽቱ 12:20 ደርሶ ነበር:: አደጋው ከደረሰ አሁን ስድስት ሰዓት ተኩል ሆኗል ማለት ነው::

በህውስተን በሚገኘው ሆስፒታል በደረስን ጊዜ በሽህ የሚቆጠሩ ሰዎች በፀሎት ላይ ነበሩ:: መልዕክቶች በፍጥነት በመቶዎች ለሚቆጠሩ አብያተ ክርስቲያናት ተላልፈው ስለነበር ሰዎች ስለ መዳኔ ይጸልዩ ነበር:: ለቀጣዩቹ ጥቂት ቀናት፤ ስለደረሰብኝ የአካል ጉዳት መነገር ስለቀጠለ ብዙ ሰዎች በፀሎት መተባበራቸውን ቀጠሉ:: በዓመታት ውስጥ በዚያ ጊዜ እግዚአብሔር ነፍሴን እንዲታደጋት ሲጸልዩ ከነበሩ ብዙ ሰዎች ጋር ተገናኝቻለሁ:: ምናልባትም ይህንን መጽሐፍ በማንበብ ላይ ያላችሁ አንዳንዶቻችሁ በሕይወት ስለመቆየቴና ስለመዳኔ ፀልያችሁ ይሆናል:: ፀሎቱ ውጤታማ እንደነበር ጨምሬ መናገር እፈልጋለሁ:: በሕይወት ተርፌአለሁ፤ አሁንም እየኖርኩ ነው::

ሀኪሙ የተኛሁበትን ቃሬዛ ከአምቡላንሱ ውስጥ ሲያወጣው፤ የኢቫን ፊት አየሁት:: ከአጠገቧ ደግሞ የቤተክርስቲያናችን አንድ ዲያቆን ቆሟል:: በታላቅ አግራሞትና ድንጋጤ ውስጥ ነበሩ፤ አንዳች ቃል ግን አልተነፈሱም::

ኢቫ ወደ እኔ አፍጥጣ ትመለከታለች:: እስከዚያ ሰዓት ድረስ በሰውነቴ ላይ ስለደረሰው ጉዳት የማውቀው በጥቅሉ ብቻ ነበር:: የህመም ስሜቱ አልቀነሰም፤ ያም ቢሆን በእንደዚያ ዐይነት አደጋ ውስጥ መሆኔን ራሴን ለማሳመን አልቻልኩም:: እኔን ለመግደል የመጣ አደጋ ሊሆን አይችልም::

ፊቷን ትኩር ብዬ ስመለከታት በአይኗ ውስጥ የነበረውን ስጋትና ሀዘን አስተዋልኩ:: ምናልባትም ልታጽናናኝ የሆነ ነገር ተናግራ ሊሆን ይችላል፤ አላውቅም:: ትዝ የሚለኝ ነገር በሕይወት ይኖራል ብላ ባለማሰቧ በፊቷ ላይ ይነበብ የነበረው የስቃይ ስሜት ነበር::

በዚያ ጊዜ ነበር በሰውነቴ ላይ የደረሰው ጉዳት ከባድ እንደነበረና አካሌም ትክክለኛ ቅርጽን እንዳልያዘ ማወቅ የጀመርኩት ደረቴ ወደ ግራጫነት ተለውጧል፤ ሃኪሞቹ አብዛኛውን የሰውነቴን ክፍል በፋሻ ጠቅልለውታል:: ደቃቅ የጠርሙስ ስብርባሪዎች በፊቴ በደረቴና በጭንቅላቴ ውስጥ ዘልቀው ገብተዋል:: እነኝህ ደቃቅ የጠርሙስ ስብርባሪዎች ከቆዳዬ ላይ እየተራገፉ በቃሬዛው ላይ ከጭንቅላቴ አጠገብ ሲበታተኑ አወቅኩ::

በአስቀያሚ ሁኔታ ውስጥ እንደነበርኩ የነገረኝ ሰው አልነበረም:: ያውቀኝ የነበረው ሰው በዚያ ሁኔታ ውስጥ ሆኜ እኔ እንደሆንኩ ሊለየኝ አይችልም:: ኢቫ ራሷ እኔ እንደሆንኩ እንዴት እንዳወቀችኝ ይገርመኛል::

የስቃይ ስሜቱ ወሰኑን ያለፈ ነበር:: በድንገተኛ አደጋ ህሙማን ክፍል ውስጥ ነርሷ አንድ ጊዜ ሞርፊን የተባለ መድሃኒት ወጋችኝ፤ ከዚያ በኋላ ደግሞ በተከታታይ መድሃኒቶችን ተወጋሁ:: የረዳኝ ነገር አልነበረም:: ስቃዩን ሊያስዝበው የሚችል ነገር አልነበረም::

በሂርማንን ሆስፒታል በገባሁ በጥቂት ጊዜ ውስጥ ወደ ቀዶ ጥገና ህክምናው ክፍል በአጣዳፊ ተላኩ፤ በዚያ ክፍል ውስጥ ለአሥራ አንድ ሰዓታት ቆይቻለሁ::



የተወዳደው ጓደኛችን ክሊፍ ማክአርድል ቀሪውን ምሽት ከኢቫ ጋር በሆስፒታሉ ቆየ:: ክሊፍ፣ የቅርብ ጓደኛዬ ዴቪድ ጀንቲልስና እኔ ከመጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጅ ከተመረቅን በኋላ የቅርብ የአገልግሎት አጋሮች ሆነን እስከ አሁን ድረስ አለን::

እንደገና ወደ አዕምሮዬ በተመለስኩ ጊዜ፣ ሐሙስ ጠዋት ሆኗል:: አይኖቼን ስገልጽ በዚያ አዲስ የህክምና ክፍል ውስጥ ስመታከም የመጀመሪያው ህመምተኛ እኔ መሆኔን አወቅኩ:: አንደኛዋ ነርስ ቁስሌን እያጸዳች ነበር፤ ሌላዋ ደግሞ ሰውነቴ እንዲፈታታ እያደረገች ነበር:: የሆነ ረዥም ብረት በቁርጭምጭሚቴና በክንዴ መካከል ስትከት አስታውሳለሁ:: ስጮህ ራሴን አዳመጥኩት::

"የቀዶ ጥገና ህክምናውን አከናውነናል" አለ ዶክተሩ:: እስከተናገረበት ጊዜ በክፍሉ ውስጥ መኖሩን አላስተዋልኩም:: በጣም ከባድ ጉዳት ነበር የደረሰብህ፣ አስደሳቹ ዜና ግን በጭንቅላትህም ይሁን በመተንፈሻ አካልህ ላይ የደረሰ ጉዳት የለም::

በዚያ ጊዜ ጉዳቱ በየትኛው አካሌ ላይ መድረሱ ግድ የሚሰጠኝ አልነበረም:: አስጨናቂው ህመም በሁሉ አካላቴ ሁሉ ላይ ተሰራጭቷል:: ሰው ሊቋቋመው ከሚችለው በላይ የሆነውን ስቃይ እየተቀበልኩ እንደሆነ አሰባለሁ::

ከዚህ ሥቃይ መገላገልን ፈለግኩ::

ከአደጋው በኋላ ሁለት ሳምንት ቆይቶ፤ ዲክ ዋንሪከር ሊጎበኘን ወደ እኔ በመጣ ጊዜ፤ ከቀዶ ጥገናው ክፍል ገና ወደ ሆስፒታሉ መኝታ

ክፍል እየተዘዋወርኩ ነበር:: እግዚአብሔር፣ እንዲጸልይልኝ እንደተናገረውና ይህንንም ደጋግሞ እንዳደረገው ነገረኝ::

"እጅግ አስደሳቹ ዜና የአንጎልም ይሁን የሌሎች ውስጣዊ አካላት ጉዳት በፍጹም አልደረሰብኝም" አልኩት::

ዲክ ትከሻውን ሰበቀና፤ "በእርግጥ ሊደርስብህ አይችልም፤ እግዚአብሔር እንድጸልይልህ ይናገረኝ የነበረው ለውስጥ አካልህ ክፍሎች ነበር፤ እናም እግዚአብሔር ያንን ጸሎት መልሷል" አለ::

"ያንን አምነህ ነበር? እግዚአብሔር ያንን ጸሎት እንደሚመልስ አምነህ ነበር?"

"አዎን አምኜ ነበር" አለ:: "ያጋጠሙህን እነኛን ጉዳቶች ሁሉ ለማስተካከል፤ እግዚአብሔር ጸሎቴን እንደሚመልስ አውቅ ነበር::"

እየተናገረ ያለውን ነገር በአግባቡ ለመገንዘብ ጥቂት ሰከንዶች ወሰዶብኝ ነበር:: በአደጋው ጊዜ ከተፈጠረው ሃይልና ሃይሉም ከፈጠረው ግፊት አኳያ፤ ውስጣዊ የአካል ክፍሎቼ ጉዳት ሊደርስባቸው ይገባ ነበር:: ዶክተሩ እንኳን በመደነቅ የጭንቅላትም ይሁን የመተንፈሻ አካላት ጉዳት እንዳልደረሰብኝ ተናግሯል::

"ይህንን ልነግርህ እፈልጋለሁ" አልኩት:: "የውስጥ አካል ጉዳት እንደነበረኝ አውቃለሁ፤ ይሁን እንጂ ከድልድዩ አንስቶ እስከዚህ ሆስፒታል መካከል ባለ በአንድ ስፍራ ላይ ያ ጉዳት ከእኔ ተወግዷል:: "

በዲክ ፊት ላይ እንባ ዘለላዎች መውረድ ጀመሩ፤ "አውቃለሁ:: በአደጋው ጊዜ እንደጸለይኩበት ባለ ሁኔታ ሁሉ ጊዜም ለመጸለይ እመኛለሁ" አለኝ::



# 6 እየተሻለኝ መጣ

"በእርሱ ዘንድ ያለን ድፍረት ይሄ ነው፤ እንደፈቃዱ አንዳች ብንለምን ይሰማናል:: የምንለምነውንም ሁሉ እንዲሰማልን ብናውቅ ከእርሱ የለመንነውን ልመና እንደተቀበልን እናውቃለን:: "

1ዮሐ 5፥14-15

የህመም ስሜት የማይለየኝ ጓደኛ ሆነኝ:: ለረዥም ጊዜ ምን እንደሆነ አላውቀውም ነበር፤ እንዲህ ሰውነቴ ሁሉ በስቃይ ይጠቃል ብዬ አስቤውም አላውቅም::

ከዚህም ሁሉ ጋር፤ አደጋው በደረሰ በጥቂት ቀናት ውስጥ፣ ምን ያህል ተአምራቶች እንደተከናወኑ መገንዘብ ጀመርኩ:: አንዳንዶች እንደ እድል አጋጣሚዎች ቢቆጥሯቸውም፤ እኔ ግን ተዓምራት ነው የምላቸው:: ምክንያቱም በእግዚአብሔር ዘንድ አጋጣሚም ይሁን ድንገት የሚሆኑ ነገሮች እንደሌሉ አምናለሁ::

በመጀመሪያ ደረጃ፤ የአደጋ ጊዜ መከላከያ ቀበቶዬን አጥልቄአለሁ:: ትራፊክ የመቀጫ ደረሰኝ እስከቆረጠልኝ ቀን ድረስ፤ ያንን ቀበቶ ለማጥለቅ እጅግም የማልጨነቅ እንደነበር ከሃፍረት ጋር ስህተቴን እቀበላለሁ:: በዚያ ቀን ጠዋት ሆን ብዬ በቀበቶው ራሴን አስሬአለሁ::

በሁለተኛ ደረጃ፤ አደጋው የተከሰተው በድልድዩ ላይ ነው። ወደ ድልድዩ ስንገዛ በሃይቁ መካከል ባለው መንገድ ላይ ደርሶ ቢሆን ኖሮስ? መኪናዋ እየተንከባለለች ቢያንስ ቢያንስ ሰላሳ ጫማ ያህል ተወርውራ ወደ ሃይቁ ትገባለች፤ እንደዚያ ከሆነ ደግሞ መስጠሟ አይቀሬ ነበር።

ሦስተኛ፤ በጭንቅላቴ ላይ ጉዳት አልደረሰም። እኔን የተመለከተና የህክምና ሪፖርቱን ያነበበ ማንም ሰው፤ የአዕምሮ ጉዳት ሳይደርስብኝ ይቀራል ብሎ በጭራሽ አይገምትም። (ኢቫ አሁን ድረስ፤ ይህ አይነቱ ጉዳት አልደረሰብህም ብዬ ያስብኩበት ጊዜ የለም እያለች ትቀልዳለች) ምንም እንኳን ጉዳዩ ለህክምናው ዓለም ሰዎች ግራ የሚያገባ ቢሆንም፤ አደጋው አንዳችም የውስጥ አካል ጉዳት አላደረሰብኝም። ይህ እውነት በህክምናው ዓለም ምክንያት የሚሰጥበት አልነበረም።

በአራተኛ ደረጃ፤ በአደጋው ዕለት ሂርማንን ሆስፒታል ውስጥ ተረኛ የነበሩት የአጥንት ህክምና ባለሞያ ዶ/ር ቶም ግሪደር ነበሩ እግሬ እንዲተርፍ ያደረጉት። እኚህ ሰው በአሜሪካ ምድር ካሉ እንዲህ ያለውን ጥልቅና ውስብስብ ጉዳት ለማከም ብቃቱ ካላቸው ባለሙያዎች ጎራ እየተቀላቀሉ ያሉ ሰው ናቸው። በጊዜው አዲስ የሆነውን ኤልዛሮቭ ፍሬም የተሰኘውን አዲስ የህክምና ዘዴ ለመጠቀም ነበር የመረጡት። የቀዶ ጥገናውን ህክምና የጀመሩት ከአደጋው አንድ ሳምንት በኋላ ነበር። በስጋዬ ውስጥ የተቀበረው ኤልዛሮቭ የተሰኘው ቁስ እግሬን እንዲድን ብቻ አልነበረም የረዳው፤ ይልቁንም በአደጋው ጊዜ አራት ኢንች ያህል ተጎርዶ የጠፋው የግራ እግሬ ፊምዮር የተሰኘ አጥንት አካል እንዲረዝምና ስፍራውን እንዲይዝ አድርጎታል። ፊምዮር በሰውነታችን ውስጥ ከሚገኙ አጥንቶች ሁሉ ትልቁና ለመስበርም በጣም አስቸጋሪ የሆነው ነው።



ዶ/ር ግሪደር በመረመሩኝ ጊዜ፤ ምርጫ ነበራቸው። አንድም ኤልዛሮቭ ፍሬም የተሰኘውን ህክምና ጥበብ መጠቀም፤ ካልሆነም እግሬን ቆርጦ ማስወገድ። ምንም እንኳን የመጀመሪያውን አማራጭ ቢጠቀሙም እግሬን ላለማጣቴ ግን አስተማማኝ ሁኔታ አልነበረም። እንደእውነቱ ከሆነ በዚያ ሁኔታ ውስጥ እንኳን ልተርፍ እንደምችል እርግጠኛ አልነበሩም። እጅግም ልምድ የሌለውና ትጋት አልባ የሆነ ዶ/ር ቢሆን ኖሮ እግሬን ቆርጦ ያስወግደው ነበር። ምክንያቱም ፈጥኖም ሆኖ ዘግይቶ መሞቱ አይቀርም ብሎ ስለሚገምት ለእርሱ ብዙ ልዩነት አያመጣም።

በአምስተኛ ደረጃ፤ ሰዎች ለእኔ ይጸልዩ ነበር። አደጋው በደረሰ ጊዜ ወሬውን የሰሙ በርካታ ሰዎች በወቅቱ ይደልዩልኝ እንደ ነበር የሚገልጹ በሺህ የሚቆጠሩ ካርዶችንና ደብዳቤዎችን ልከውልኛል፤ አብዛኞቹን ሰዎች አላውቃቸውም። የመኖሪያ ስፍራዎቻቸውንም ረግጬው አላውቅም። ብዙ ሰዎችም ይህ ተግባራቸው የፀሎት ሕይወታቸውንና በጸሎት ኃይል ያላቸውን እምነት እንደለወጠው ነግረውኛል።

ወደ ሂርማንን የድንገተኛ አደጋ ማዕከል ውስጥ በገባሁበት ምሽት አሥራ አንድ ሰዓት የፈጀ የቀዶ ጥገና ህክምና ተደርጎልኛል። በዚያ ህክምና ወቅት፤ በቀኝ እግሬ ላይ የተሰበረ አጥንት ነበር። የግራ እጄ የመጀመሪያው አንጓ እንደገና መስተካከል ያስፈልገው ነበር፤ ምክንያቱም ከሁለቱም አጥንቶቼ ላይ ሁለት ኢንች የሚያህሉ አጥንቶች ተጎምደው ጠፍተዋል። የግራ እግሬ አጥንቴ መወጠር ያስፈልገው ነበር፤ ምክንያቱም ፊምዮር ከተባለው የአጥንት ክፍል አራት ተኩል ኢንች ተጎርዶ ጠፍቷል። በቀዶ ጥገና ጊዜም አንድ የአየር መስጫ የላስቲክ ቱቦ

በስህተት ወደ ሆድ እቃዬ ውስጥ ተጨምሮ ነበር። ይሄ ደግሞ ሆዴ ውስጥ አየር እንዲጠራቀም፣ እንዲነፋ፣ ሳንባዬ ደግሞ አየር ቶሎ ቶሎ እንዲተነፍስ አደረገው። የሆዴ ማበጥ ምክንያቱ ይህ መሆኑን ለመገንዘብ በርካታ ቀኖች ፈጅተውባቸዋል። ከዚህም የከፋው ነገር ደግሞ ተከስቶ ነበር፤ ይህም በአተነፋፈሴ ላይ የተፈጠረ ችግር ሲሆን አየር መሳብ አልቻልኩም፤ በመሆኑም ኒሞኒያ በተሰኘ የሳንባ በሽታ ተለከፍኩ፤ ለሁለተኛ ጊዜ ከመሞት ያመለጥኩት ለጥቂት ነው።

ከቅጥቅጡና በግልጽ ከሚታየው ቁስል ብዛት የተነሣ ዶክተሮቼ ሥራቸውን ከየት እንደሚጀምሩ እንኳን በውል አላወቁም ነበር። እጅግም ጉዳት የሚያስከትሉ ችግሮች የታወቁት ከሳምንታት በኋላ ነበር። በመጀመሪያ ላይ ያላገኙትን በብራኳዬ ላይ ያለ ስንጥቅ ያገኙት ከብዙ ዓመታት በኋላ ነበር።

መላው አካሌ ከጥቅም ውጭ ሆኖ በአልጋ ላይ ተጋደምኩ፤ መንቀሳቀስ አልችልም፤ የሰውነትን አካል ሰብስቦና ደግፎ በሚይዝ መሣሪያ ብርታት ነው ያለሁት። ካጠለቅኩት የኦክስጅን ጭንብል በስቲያ አሻግሬ የማየው በመጠኑ ነበር። በቀዶ ጥገና ክፍሉ ውስጥ በነበርኩባቸው በእነዚያ ቀናት ህሊናዬን አሁንም አሁንም እስት ነበር። አንዳንድ ጊዜ ስነቃ ሰዎች ከፊት ለፊቴ ቆመው እመለከትና እገረማለሁ፤ እስከ አሁንም እዚሁ ነኝ ወይስ ዝም ብዬ በሃሣቤ የምፈጥረው ቅዠት ነው?

የህክምና ተቆጣጣሪዎች አዘውትረው ከበውኝ ይቆማሉ? በጣቴ ላይ የተሰካው የደም ግፊት መለኪያ መሣሪያ የኦክስጅኑን መጠን ያመላክታል። በቂ ኦክስጅን የማላገኝ ስለነበር፤ ብዙውን ጊዜ



የማስጠንቀቂያው ድምጽ ይጮህ ነበር፤ በመሆኑም ነርሶቹ እየሮጡ ወደ ክፍሌ ይመጣሉ።

የሂርማነን ሆስፒታል ከሄሊኮፕተር አየር ጣቢያ አቅራቢያ የተሠራ በመሆኑ ሄሊኮፕተሮች ቀኑን ሙሉ ሲነሱና ሲያርፉ ይውላሉ። ከስመመኔ ነቅቼ ይህንን ድምጽ ስሰማ የቬየትናምን ጦርነት ፊልም እየተመለከትኩ እንደሆነ ይሰማኛል። በክፍሉ ውስጥ ሰዓት አልነበረም፤ እናም ስለ ጊዜ ምንም አይነት ግንዛቤ አልነበረንም።

አጠገቤ ባሉ አልጋዎች ላይ ሌሎች ሰዎች ተኝተዋል፤ አልጋዎቻችን የተከለሉት ከመጋረጃ ባልወፈረ ነገር ነው። ከአንድ ጊዜ በላይ ነቅቼ የህክምና ሰዎች ነጭ አንሶላ የተሸፈነ አካል በቃሬዛው ላይ አስተኝተው ሲያወጡ ተመልክቻለሁ። እንደ ቤተክርስቲያን መጋቢነቴ ከአደጋ የቀዶ ጥገና ክፍል ውስጥ ብዙዎች በሕይወት አይወጡም።

ቀጣዩ ሰው እኔ እሆን? እያልኩ ራሴን እጠይቃለሁ። ምንም እንኳን ጥያቄውን ብጠይቅም፤ የህመም ስቃዩ ከሃሳቤ ያናጥበኛል። ጉዳቱን አልፈለግኩትም፤ እናም ቀላሉና ፈጣኑ መልስ መሞት ነበር።

መንግስተ ሰማይን ተመልክቻለሁ፤ ወደ ምድር ተመልሻለሁ እናም ፈጽሜ በማልፈልገው የምድር ገሃነም በሆነ ስቃይ ውስጥ ገብቻለሁ። የነበርኩበት ሁኔታና የነበረኝ አመለካከት ሊለወጥ ረዥም ጊዜ ወስዷል።

የቅዠት ድምጾች ቀናትንና ሌሊቱን ሙሉ ሳያቋርጡ ይሰሙኛል። የጣር፣ የለቅቃና የጭንቀት ጩኸት ያለማቋረጥ ከእረፍቴ ይቀሰቅሱኛል፤ ወደ አዕምሮዬም መልሰው ያመጡኛል። ነርሷ ወደ አልጋዬ ትቀርብና፤ “ልረዳህ እችላለሁ?” ትላለች።

“ስለ ምን ጉዳይ ነው የምታወሪው?” ብዬ እጠይቃታለሁ:: አንዳንድ ጊዜ ዝም ብዬ አተኩሬ እመለከታታለሁ፤ ለምን እንደምትጠይቀኝ ሊገባኝ ከቶ አይችልም::

“የምታሰማው ድምጽ ታላቅ ስቃይ ውስጥ እንዳለህ ያስረዳል”::

“አዎን ነኝ፤ ይመስለኛልም፤” ከዚያ በኋላ እንዲህ ስል እጠይቃለሁ፤ “ይህንን ግን እንዴት ልታውቂ ቻልሽ?”

“ትጮህ ነበር”

በዚህ ጊዜ ነበር አንዳንድ ጊዜ የምሰማው የጩኸት ድምጽ ከራሴ የሚወጣ እንደነበር የተረዳሁት::

እነኝህ የጣርና የጭንቀት ድምጾች እየተፈተለኩ የሚወጡት፤ ቀላል የሆኑ እንቅስቃሴዎች ሳደርግ ለምሳሌም እጆቼንና እግሮቼን ማንቃነቅ በጀመርኩት ጊዜ ነበር:: በቀዶ ጥገና ክፍሉ ውስጥ መኖር እጅግ ዘግናኝ ነው:: ማድረግ የሚችሉትን ነገር ሁሉ ያደርጉልሃል፤ ይሁን እንጂ የህመም ስሜቱ ፈጽሞ አይቆምም::

“እግዚአብሔር ሆይ ለዚህ ነው ተመልሼ የመጣሁት?” እያልኩ ብዙ ጊዜ ጮኬአለሁ:: “ወደ ምድር መልሰህ ያመጣኸኝ ለዚህ ነው?”

ሁኔታዬ ሁሉ ተስፋ አስቆራጭ ወደሆነ አዘቅት እየወረደ መጣ:: ከግራ እግሬ ላይ በጎደለው አጥንት ምክንያት በአልጋው ላይ በጀርባዬ ለጥ ብዬ መተኛት ነበረብኝ:: (አጥንቱን ፈልገው አላገኙትም:: በአደጋው ወቅት እግሬ በመቀመጫውና በዳሽ ቦርዱ መካከል ገብቶ በተጨፈለቀ ጊዜ ከመኪናው ውስጥ ተፈናጥሮ በሃይቁ ውስጥ ለመግባቱ ጥርጥር የለውም):: በጀርባዬ ለጥ ብዬ በመተኛቴ ሳንባዎቼ በፈሳሽ ይሞሉ



ጀመር:: አሁንም እንኳን ሳንባዎቼ ሥራ አቁመው እንደነበር አልተገነዘብኩም፤ ነርሶቹና የመተንፈሻ አካል ሃኪሞቹ አተነፋፈሴን ለማስተካከል ስፖይሮ ሜትር የተሰኘ ትልቅ መሣሪያ በመጠቀም በኃይል እንድተነፍስ ይረዱኝ ነበር::

በስድስተኛው ቀኔ ላይ፤ ፈጽሞ ለሞት እየታቀረብኩ ስለመጣሁ፤ ሆስፒታሉ ቤተሰቦቼ መጥተው እንዲያዩኝ ጥሪ አደረጉላቸው:: የሳንባ ምች በሽታ በእጥፍ እየጨመረ ሄደ:: ሀኪሞቹ ያችን ሌሊት በሕይወት ኖሬ የማድር አልመሰላቸውም::

በአደጋው ምክንያት ከደረሰብኝ ጉዳት ከሞት ተርፌአለሁ፤ አሁን ደግሞ በሳንባ ምቹ ምክንያት ልሞት ነው::

ዶክተሬ ኢቫን አነጋገራት::

“አንድ ነገር የግድ ማድረግ አለብን” አላት ዶክተሩ:: “አንድም እግሩን ቆርጠን ማስወገድ አለዚያም አንድ ታላቅ ጥረት”

“እንዴት ያለ ታላቅ ጥረት?”

“አንድ ነገር ካላደረግን፤ ማለዳ ላይ ባልሽ በሕይወት የለም”:: በዚያ ሰዓት ነበር የጸሎት ተአምራት በእውነት መሥራት የጀመረው:: አደጋውን ከሰሙበት ጊዜ ጀምሮ በመቶዎች የሚቆጠሩ ሰዎች እየጸለዩልኝ ነበር፤ ያንንም አውቄአለሁ:: ይሁን እንጂ እስከዚያ ጊዜ ድረስ ምንም ነገር ልዩነት የሚያመጣ አልነበረም::

ኢቫ እጅግ የቅርብ ጓደኛዬ የሆነውን ዴቪድ ጀንትልስን ጠራችው፤ በሳን አንቶኒዬ ቤተክርስቲያን በመጋቢነት ያገለግላል:: “እባክህ

አንድ ጊዜ ብቅ በል፤ ዶን ይፈልግሃል" የሚል መልዕክት አስተላለፈችለት::

ያለ ምንም ማቅማማት ጓደኛዬ ጉዳዮን ሁሉ ሰርዞ ወደ መኪና ውስጥ ዘሎ ገባ:: ሁለት መቶ ማይሎች የሚያህል መንገድ ተጉዞ ሊያየኝ መጣ:: የህክምና ባለሙያዎቹ በቀዶ ጥገና ክፍሉ ውስጥ እንዲቆይ የፈቀዱለት አምስት ደቂቃ ብቻ ነበር::

እነኛ ደቂቃዎች ሕይወቴን ቀየሩት::

ይህንን ውሳኔ የወሰንኩት ሆነ ብዬ አልነበረም፤ ነገር ግን ለመዳን ጥቂት ተስፋ ብቻ ቀርቶኝ በተኛሁበት በዚያ ሥፍራ እኔም ብቻ ሳልሆን ማንም ሰው እንደገና ወደ ጤንነቱ ይመለሳል ብሎ ተስፋ አላደረገም:: ለመኖር ፍላጎት አልነበረኝም:: ማለቂያ ማብቂያ የሌለውን ሥቃይ ብቻ አልነበረም ያየሁት፤ በመንግስተ ሰማይ ውስጥም ነበርኩ:: ታላቅ ፍጹምነት ወደተቀዳጀው ወደዚያ ሥፍራ ለመመለስ ፈለኩ:: "እግዚአብሔር ሆይ እንደገና መልሰኝ" ስል ጸለይኩ፤ "እባክህ መልሰህ ውሰደኝ::"

ትዝታዎች አዕምሮዬን ይሞሉት ጀመር፤ እናም እንደገና አንድ ጊዜ በዚያ በር ላይ ለመቆም ውስጤ ተነሣሣ:: "እባክህ እግዚአብሔር ሆይ!?"

ለጸሎቴ እግዚአብሔር የሰጠው ምላሽ፤ "አይሆንም" የሚል ነበር::

ዴቪድ የተኛሁበትን ክፍል በር ከፍቶ ሲገባ፤ ከህመሙ ስቃይና ከመድሃኒቱ ሃይል የተነሣ ብዥታ ውስጥ ነበርኩኝ:: የማየው ነገር እውነት መሆኑን ለማረጋገጥ መጀመሪያ ከሰመመን ውስጥ ወጥቼ



ትኩረቴን በነገሩ ላይ አደርግ ነበር:: እየቃዠሁኝ ነውን? ስል ራሴን ጠየቅኩ::

ከዚያ በኋላ ዴቪድ ጣቶቼን ከፍ አድርጎ አነሣቸው፤ እናም መነካቴን አወቅኩ:: አዎ በርግጥ ቅዥት ሳይሆን እውን ነበር::

ጣቶቼን ጨብጦ ያዛቸው፣ ምክንያቱም መያዝ የሚችለው የሰውነቴ አካል እርሱን ብቻ ነበር:: የደም ሥሮቼ እስኪኮራመቱ ድረስ በርካታ መርፌዎች በላዬ ላይ ተሰክተዋል፤ ረዘም ያለ የላስቲክ ቱቦ በደረቴ አልፎ በቀጥታ ከልቤ ጋር ተገናኝቷል:: እንደ ወታደር የተሰለፉት በመርፌ ወደ ሰውነቴ የሚላኩት መድሃኒቶች ይታወሱኛል:: መድሃኒቶቹ በእግሬ መዳፍ የላይኛው ክፍል ሳይቀር ይለቀቁልኝ ነበር:: ቁልቁል እየተመለከትኩ በእግሬ መዳፎች ላይ መርፌዎቹን የተከሏቸው ከሰውነቴ ክፍል ውስጥ ነፃ የሆነ ሥፍራ ባለማግኘታቸው ምክንያት እንደሆነ እገነዘባለሁ::

"እየተቋቋምከው ነው" አለ ዴቪድ:: "መቋቋምም አለብህ፤ እስከዚህ ሰዓት ድረስ ተቋቁመኸዋል::"

"ከዚህ በላይ መቋቋም አልችልም:: በፍጹም እርግጠኛ አይደለሁም ... መቋቋም መፈለጌን እንኳን እርግጠኛ አይደለሁም::"

"መቋቋም አለብህ:: ለራስህ እንኳን ብለህ ሳይሆን፤ ስለ እኛ ብለህ አድርገው"

"ኃይሌ ከውስጤ እያለቀ ነው" አልኩት:: "ማድረግ የምችለውን ሁሉ አድርጌአለሁ:: ማድረግ ባለብኝ አቅም ሁሉ አድርጌአለሁ:: አሁን መቋቋም የምችልበት እንዳች አቅም የለኝም" አረፍ አልኩና ደጋግሜ

አየር ሳብኩ፤ ሁለት ቃላት ለመናገር እንኳን በርካታ ሃይል ያስፈልግ ነበር።

"መበርታት መቻል አለብህ፤ እንድትሄድ እንፈቅድልህም"

"መቋቋም ካለብኝ፤ እናንተ ሁላችሁ ስለፈለጋችሁ ብቻ ነው። እኔ አልፈልገውም። በጣም ታክቶኛል። ባለኝ ጉልበት ሁሉ ታግያለሁ እናም አሁን ግን ለመሞት ዝግጁ ነኝ"

"ደህና፤ አሁን አንተ ምንም ማድረግ አይጠበቅብህም። ስለ አንተ እኛ ሁሉን እናደርጋለን። "

መግለጽ በሚያዳግተኝ ሁኔታ፤ በፊቱ ላይ በሚታየው የብርታት ስሜት ላይ አፈጠጥኩ።

"እንድትሞት እንፈቅድልህም። ይህንን ትረዳዋለህ ዶን? ተስፋ እንድትቆርጥ አንፈቅድልህም።"

"እባካችሁ እንድሄድ ተውኝ?!"

"በፍጹም በሕይወት መኖር አለብህ! ይህንን ትሰማለህ? መኖር አለብህ። እንድትሞት አንፈቅድም። "

"መኖር ካለብኝ . . ." በመጨረሻው እንዲህ አልኩ፤ ምክንያቱ እናንተ ስለፈለጋችሁ ብቻ ነው።

"እንጸልይልሃለን " አለ። እንደ እውነቱ ከሆነ ሰዎች አሁንም እየጸለዩልኝ እንደሆነ አውቃለሁ። ይሁን እንጂ እንዲህ የሚል ቃል ጨምሮ ተናገረ፤ "ሌሊቱን ሙሉ ስንጸልይልህ ነው የምናድረው። የማውቃቸውን መጸለይ የሚችሉ ሰዎች ሁሉ እጠራለሁ። አንድ ነገር እንድታውቅ እፈልጋለሁ፤ ስለ አንተ ግድ የሚለን ሰዎች ሁሉ ሌሊቱን ሙሉ ስለ አንተ ስንጸልይ እናነጋለን። "



"መልካም"

ይህንን የምናደርገው ስለ አንተ ስንል ነው ዶን። አንተ የምታደርገው አንዳች ነገር የለም። "

እንደ እውነቱ ከሆነ ቢጸልዩልኝም ባይጸልዩልኝም ግድ አልነበረኝም። እጅጉን ተጎድቻለሁ፤ በሕይወት መኖር አልፈለኩም ነበር።

"ከዚህ ሆነን መነጋገር እንችላለን፤ በሕይወት ለመቆየት ምንም ነገር ማድረግ አያስፈልግህም፣ አንዳች ነገር። ማድረግ የሚገባህ ነገር ቢኖር እዚያው እንደተኛህ ነገሮቹ እንዲፈጸሙ ፍቀድ። በዚህ ሁኔታ እኛ ስለ አንተ እንጸልያለን። "

ለአንድና ለሁለት ደቂቃዎች ያህል በፍጥነት አነጋገረኝ። ከዚያ በላይ የተናገርኩ አይመስለኝም። የህመም ስሜቱ እየጨመረ ሄደ፤ ይህ ቃል ሁኔታውን ገላጭ ከሆነ እናም ከዚያ በኋላ በተናገረው ነገር ላይ ትኩረት ማድረግ አልቻልኩም።

"ይህንን እኛ እንወጣዋለን" አለና ከግንባሬ ላይ ስሞኝ ወጣ። የሙሉ ሌሊት የጸሎት ተጋድሎ ሊያደርግ እርግጥ ነበር። ያ የጸሎት ተጋድሎ በህክምናዬ ላይ ጉልህ የሆነ ለውጥ አስከተለ፤ እናም ሌላ ተአምራቶች ደግሞ ተከታተሉ።

የሳንባ ምች በሽታው በሚቀጥለው ቀን ጠፋ። በጸሎታቸው ከእኔ እንዲነቀል ጠይቀው ነበር። እንደገናም የህክምና ቡድኑ በመተንፈሻ ቱቦዬ ላይ የነበረውን ችግር ምክንያት ደረሱበት።

በዚያ በሰባተኛው ቀን ዕለት፤ ረዥም ሰዓት በፈጀ የቀዶ ጥገና ህክምና ዶ/ር ግሪደር፣ ኤልዛሮቭ የተሰኘውን የህክምና መሣሪያ በእግሬ ላይ መግጠም በመቻሉ ቁጭ ብዬ የመተንፈሻ አካል ህክምናዬን መከታታል ቻልኩ። በተጨማሪም በሆዴ ውስጥ የነበረውን አየር አስወጡልኝ፤ ይህም ሳንባዎቼ አየር መሳብ እንዲችሉ ረዳቸው።

አግባብነት ባለው አሠራር፤ ሆስፒታሎች ኤልዛሮቭ ፍሬም የተሰኘውን የህክምና መገልገያ መሣሪያ ለመጠቀም ቢያንስ የስድስት ወር ምክር ይሰጣሉ። በእኔ ጉዳይ ግን፤ የህክምና ባለሙያዎቹ የሙከራ ተግባሩ ውጤታማ እንደሚሆን ምንም ዓይነት ዋስትና አልሰጧትም። በተጨማሪም ይህንን የህክምና መገልገያ መሣሪያ ብጠቀም የተወሰነ የአካል ስቃይና ያልተለመደ ስሜታዊና ሥነልቡናዊ ቀውስ ሊያስከትልብኝ እንደሚችል ነግረዋታል። እጅግ ተስፋ አስቆራጩ ነገር ደግሞ በዚህ ሁሉ ውስብስብ የህክምና ሂደት ካለፍኩ በኋላ እንኳን እግሬን ላጣ እንደምችል የተሰጠን ማስጠንቀቂያ ነበር።

"ይህ በጣም ስቃይ የሚያስከትል ህክምና ነው፤ ደግሞም ለመዳን ወራት ምናልባትም ዓመታት ያስፈልጋል" አላት ሃኪሙ ኢቫን። እንደገናም ሊደርስ የሚችለውን የመጨረሻውን ከባድ አደጋ ሲያስረዳት፤ እንዲህም ሆኖ እግሬ ሊቆረጥ እንደሚችል አሳሰባት። "ይሁን እንጂ በዚህኛው የህክምና መንገድ መሄድ የማንፈልግ ከሆነ፤ ሌላ ምርጫ አልነበረንም-መቆረጥ ብቻ።"

እግሬን የምቆርጡት ከሆነ ሌላ ተስማሚ ሰው ሠራሽ እግር እንደሚገጥሙልኝና በርሱም መሄድ እንደምለማመድ በዝግታ ገለጸ አደረገ።





ዶን፣ በአጥንት አስረዛሚው በኤልዛሮቭ መሣሪያ ውስጥ ሆኖ።

ኢቫ በእኔ ላይ የደረሰው አደጋ ከባድ እንደሆነ ጥርጥር አልነበራትም ወይም በዚህ አስቸጋሪ ሥቃይ ውስጥ ምን ያህል ጸንቼ መቆየት እንደምችል አታውቅም። በርካታ ጊዜ በጉዳዩ ላይ አወጣች አወረደች፤ እግዚአብሔር ምሪትን እንዲሰጣትም በውስጧ መጸለዩን ቀጠለች። በመጨረሻውም፤ የስምምነት ቅጹን እፈርማለሁ አለች።

በሚቀጥለው ሳምንት፤ ከሌላ አሥራ ሁለት ሰዓት ከፈጀ ህክምና በኋላ ስነቃ፤ የቀኝ እግሬ ባለበት በኩል ከሰበሰኩት ነገር በታች ትልቅ እብጠት የሚመስል ነገር ተመለከትኩ። እግሬን ገልጩ ስመለከት፤ ያየሁት ነገር ትንፋሼን በአጭር ቀረጠው። በግራ እግሬ ላይ አንዳች የሚያክል ከማይዝግ ብረት የተሠራ ክብነት ያለው መሣሪያ ከሙሃይቴ ጀምሮ ከጉልበቴ ዝቅ ብሎ እስከሚገኝ ሥፍራ ድረስ ተገጥሟል። ነርሷ ወደ ክፍሉ ገባችና ዙሪያውን መዞር ጀመረች፤ በእግሬ አካባቢ የሆነ ነገር እየሠራች ነበር፤ ምን ታደርግ እንደነበር ግን እርግጠኛ አልነበርኩም።

ኢቫ ከአልጋዬ አጠገብ ተቀምጣ እንደነበር አስተዋልኩ። "ይህ ደግሞ ምንድን ነው? ስል ጠየኳት። ምን እያደረገች ነው?"

"በዚህ ነገር ላይ መነጋገር ያስፈልገናል" አለች። "ትላንትና ተስማምቼ የፈረምኩት ይህ እንዲሆን ነው። አጥንት እያደገ እንዲሄድ የሚያደርግ መሣሪያ ነው። ፊክሳተር ተብሎ ነው የሚጠራው። ሃኪሞቹ የግራ እግርህን ለማቆየት ያላቸው የመጨረሻ እድል ይሄው ብቻ ነው" አለች። በመቀጠልም፤ "ሃላፊነቱን መውሰድ የግድ እንደሆነ አምናለሁ" ስትል ተናገረች።



መልስ ለመስጠቴም እርግጠኛ አልነበርኩም። ለመናገርስ ምን የቀረ ነገር ነበር? መወሰን የምትችለውን በጣም ጥሩ ውሳኔ ወስናለች፤ ብቻዋን እንድትወስንም ተገዳ ነበር።

ከዚያ በኋላ ደግሞ ከመሣሪያው የሚወጡ በርካታ የኤሌክትሪክ ገመዶችን ተመለከትኩ። "እነኚህ ገመዶች ሁሉ በእግሬ ውስጥ የሚያልፉ ናቸው?"

"አዎን"

ሳላውቀው ራሴን በሃዘኔታ ወዘወዝኩት፤ "በርግጥ በእግሬ ውስጥ የሚያልፉ ገመዶች ናቸው?"

"አዲስ የህክምና ዘዴ ነው። እግርህን ከመቆረጥ ለማትረፍ እየሞከሩ ነው።"

ከዚያ በኋላ አስተያየት ለመስጠት እውቀቱ አልነበረኝም። ራሴን በመስማማት አይነት ነቀነቅኩና ዘና ለማለት ሞከርኩ።

"እንደሚሠራ አምናለሁ።" አለች።

ትክክል እንደነበረች ተስፋ አደረግኩ። ዓመት ሊሞላ ጥቂት ሲቀረው ጊዜ ያህል መሣሪያው በሰውነቴ ላይ እንደሚሆን ግን በጊዜው የነበረኝ እውቀት ጥቂት ነበር።

# 7

# ውሳኔና ተግዳሮቶች

"ከክርስቶስ ፍቅር ማን ይለየናል? መከራ ወይስ ጭንቀት፣ ወይስ ስደት ወይስ ራብ፣ ወይስ ራቁትነት፣ ወይስ ፍርሃት ወይስ ሰይፍ ነውን? ስለ አንተ ቀኑን ሁሉ እንገደላለን፤ እንደሚታረዱ በጎች ተቆጠርን ተብሎ እንደተጻፈው ነው።"

1ዮሐ 8፥35-36

በአካል ከደረሰብኝ ጉዳት በተጨማሪ፤ እጅግ አስቸጋሪ ከሆኑብኝ ሁኔታዎች አንዱ፤ በቤተሰቦቼና በቅርብ ጓደኞቼ ፊት ላይ እመለከተው የነበረው የድንጋጤና የሃዘን ስሜት ነው። ወላጆቼ ከሃውስተን 250 ማይል ርቃ በምትገኘው ሉሲያና ውስጥ ነው የሚኖሩት። ይሁን እንጂ ወደ ሆስፒታሉ የደረሱት የመጀመሪያው ቀዶ ጥገና በተደረገልኝ ማግስት ነበር። እናቴ ጠንካራ ሴት ነች፤ ሁሉን ነገር መቋቋም ትችላለች ብዬ አስብ ነበር። ነገር ግን ወደ ህክምና መስጫ ክፍሉ በገባችበት ጊዜ ወደ እኔ ተመለከተች፤ እናም ራሷን ሳተችና ወደቀች። አባቴ ነበር ከመሬት አፍሶ ይዟት የወጣው።

የእርሷ ራሷን ስቶ መውደቅ ምን ያህል በአስቀያሚ ሁኔታ ውስጥ እንደምገኝ ግንዛቤ ሰጠኝ።

የመጀመሪያዎቹ ጥቂት ቀናቶች ብዙ ግራ የሚያጋቡ ነገሮችን ጥለውብኝ አልፈዋል። ሰዎች በእርግጥ ሊጠይቁኝ ይመጡ እንደነበር



ወይም በቅዠት ውስጥ ሆኜ እንደማያቸው እርግጠኛ አልነበርኩም። ኢቫና ነርሷ እንደነገሩኝ ከሆነ አንዳንድ ጊዜ አዕምሮዬን እስታለሁ።

ሆስፒታሉ፣ በየቀኑ ጠያቂዎች ጥቂት ጥቂት ሆነው እየገቡ እንዲጎበኙኝ ፈቀደ። ምንም እንኳን ቃል ባይናገሩም ሃዘናቸውን ርህራሄን የተሞሉ አይኖቻቸው ምን እንደተሰማቸው በግልጽ ይነግሩኝ ነበር። በአዕምሮዬ መዝገብ በግልጽ ጽፌአቸዋለሁ፣ ምክንያቱም በምን ዐይነት ሁኔታ እንደተቀበልኳቸው አውቃለሁና ነው። ወደ ኋላዬ ዘወር ብዬ ሳስበው፤ ምናልባት ተሳስቼ እንዳይሆን እሰጋለሁ። እንደምሞት ፈጽሞ እርግጠኛ ነበርኩ፣ ደግሞም ፈልጌው ነበር፣ በፊታቸው ላይ ከማየው ነገር ነበር ሥለ እራሴ የማስበው ነገር የሚመነጨው።

ትክክል ልሆንም ላልሆንም እችላለሁ፤ ነገር ግን እንዲህ እያልኩ አስባለሁ፤ አሁን እየተመለከቱ ያሉት ቅርጹን አጥቶ የተከመረ የሰው ሰውነት እንጂ ህያው የሆነ ሰው እየተመለከቱ አይደለም። ምንም እንኳን የሚያበረታታና የሚያጽናና ቃል ቢናገሩም በዚያው ሰዓት ውስጥ እንድሞት እንደሚፈልጉ ይመስለኝ ነበር። አንዳንድ ጊዜ ይገርመኛል፤ የሚመጡት አይኖቼን ጨፍኜ ለዘላለም ከማንቀላፋቴ በፊት ለእኔ ያላቸውን አክብሮት ለመግለጽና ለመሰናበት ነው ስል አስባለሁ።

የሳንባ ምች በሽታው ቢሄድም ቅሉ፤ ትቶት የሄደውን ሌላ ጉዳት ደግሞ ማከም ነበረብን። ነርሶቹ በየአራት ሰዓቱ ልዩነት ይመጡና የመተንፈሻ አካሎቼን አክመው ይሄዳሉ። ደረቴን መታመታ እያደረጉ በመጫን ጥሩ ጠረን፣ ጥሩ ጣዕም በማይሰጥ ሳንባዎቼን እንዲሸፍን በተደረገልኝ የህክምና መሣሪያ አማካይነት እንድተነፍስ ያደርጉኛል። እንዲህ አይነቱ ህክምና የሳንባዎች በሽታው ተመልሶ እንዳይጀምር የተከላከለው ሲሆን ሳንባዎቼ እንዲያገግሙም ረድቷል። እነቃና ሰዎች

ወደ ክፍሉ ሲገቡ እመለከታለሁ፤ እናም እንዲህ ሲል አስባለሁ፤ "አይ ደግሞ መጡ ... በዚያ ነገር አማካይነት እንድተነፍስ ሊያደርጉኝ ነው፤ ያንን ጭነት ይጭኑብኛል፤ በጉሮሮዬ አካባቢ የተከማቸውን ቆሻሻ ፈሳሽ መጥረጊያውን ደግሞ ሊነቅሉት ነው።" የእስቺጋሪ ህክምናነቱን ያህል ውጤታማ ሆነ። የሂርማነን ህክምና ማዕከል የህክምናው ቡድን መሪ የሆኑት ዶ/ር ሆቺንስ በቀን ውስጥ ብዙ ጊዜ ይመላለሳሉ። ዶ/ር ሆቺንስ ካላቸው መልካም ባህሪያት ጋር ተደምሮ አንድም በሽተኛቸው በሞት እንዳይወስድ እንደ አዳኝ ውሻ የመናጠቅ ቁርጠኛ የሆነ እልህ አላቸው።

መተንፈስ እንደሚገባኝ ነገሩኝ። "አሁን አታቋርጥ፣ አታቋርጥ። መሞከርህን ቀጥል" የሚናገሩት ቃሉን ብቻ አልነበረም፤ ይልቁንም ልክ እንደ እኔ ታማሚ የሆኑ ይመስል ከእኔ ጋር ሆነው ሲታገሉ ይሰማኛል። "ተስፋ አትቁረጥ፤ መሞከርህን ቀጥል"

ብዙውን ጊዜ ለመተንፈስ የሚያስፈልገኝ ሃይል ስላልነበረኝ መሞከሬን አቆም ነበር።

በፊታቸው ላይ ሃዘን የተሞላበት ስሜት እመለከታለሁ፤ ቆይቶም ያ የሃዘኔታ ስሜት እልህ ወደተሞላበት ንዴት ይለወጣል። "የምልህን ትሰማኛለህ? ተንፍስ! አሁን ተንፍስ! ተንፍስ! ደግሞ አስል! ቀጥል!"

ራሴን በአሉታ እወዛውዛለሁ። ከዚያ በላይ ለመንቀሳቀስ አንዳች ኃይል አልቀረኝም።

"ይሄ የምንደራደርበት ጉዳይ አይደለም። አሁኑኑ አድርገው! ተንፍስ!"



"አልችልም"

"ጥሩ፤ አታድርገው። በቃ እንደሞትክ እወቅ። የማታደርገው ከሆነ ትሞታለህ። የምናገረውን እየተረዳኸው ነው?"

እኔ መኖር አልፈልግም ነበር። እርሳቸው እየጮሁ ሲያበረታቱኝ ግን አንድ ነገር ሆነ።

መተንፈስ ጀመርኩ።

ከዚያ በኋላ ብዙም ሳይቆይ የህክምና ቡድኑ መቀመጥ እንድችል እግሬን እንዴት ማንሳት እንዳለባቸው መመካከር ጀመሩ። ቀና ብሎ መቀመጥ ደግሞ በራሱ በርካታ ደረጃዎች የሚጠይቅ ህክምናን የሚያካትት ነበር። ከዚያ በኋላ ባለው ሕይወቴ በጎኔ ጋደም እላለሁ ወይም በሆዴ እተኛለሁ ብዬ አላስብኩም ነበር።

አንድ ጊዜ በዚያው በቀዶ ጥገና ክፍሉ ውስጥ ሳለሁ፤ አይኔን ጨፍኜ በገለጥኩ ቁጥር በየሰኮንዱ ፍጥነት አንድ ሰው ስድስት ኢንች ያህል ርዝመት ያለውን ምግብ የተሞላ ማንኪያ ወደ አፌ እየሰደደ ያስገባል።

"አንድ ጊዜ ብቻ አፍህን ክፈት"

የወንድ ሰው ድምጽ እንደሆነ አወቅሁ።

አይኔን ገለጥኩና አተኩሬ ተመለከትኩ። አንድ ግዙፍ ሰው ማንኪያውን እንደጨበጠ ቆሟል። የኦክስጂን ጭንብሌን ከፊቴ ላይ

አንስቶ ማንኪያውን በዝግታ ወደ አፌ ያስገባል፤ “እንዲያ ነው እነጂ፤ ደግሞ አንድ ድገም ... ትንሽ”

እየታዘዘኩ እውጣለሁ፤ በዚያው ቅጽበት አዕምሮዬን እየሰበሰብኩ እየሆነ ያለው ነገር ምን እንደሆነ ለመገመት እሞክራለሁ::

ቀስ እያልኩ ያ ድምጽ በአሊቪን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ ባለብጫ ጃኬቶቹ የተሰኘው የእግር ኳስ ቡድን አሰልጣኝና የአትሌቲክስ ቡድን መሪ የሆነው የስታን ማውልዲን ድምጽ መሆኑን ተገነዘብኩ:: በህክምና በማገገም ላይ በነበርኩበት ጊዜ ሴት ልጃችን ከስታንና ከባለቤቱ ከሱዛን እንዲሁም ከሁለቱ ልጆቻቸው ጋር አብራ ነበር የምትኖረው:: አሰልጣኙ ማውልዲን ምግብ ባለመውሰዴ ምክንያት አሣሣቢ በሆነ ሁኔታ ክብደቴ እየቀነሰ መምጣቱን ስማ (ከዚያ በኋላ ከክብደቴ የቀነሰው ጥቂት ፓውንዶች ብቻ ቢሆንም፤ ሆስፒታል በገባሁባቸው በመጀመሪያዎቹ ስድስት ሳምንታት ወደ ሃምሳ ፓውንድ ያህል ክብደት ጥዬ ነበር)::

ስታን ሁኔታውን በሰማ ጊዜ፤ ወደ ሂርማንን ሆስፒታል የሚመጣበትን ጊዜ አመቻቸ:: የሚመጣው ግን ዝም ብሎ ጎብኝቶኝ ሊሄድ አልነበረም:: ምግቤን እንድትሰጠኝ ነርሷን ጠየቃት፤ እናም እስክነቃ ድረስ አጠገቤ ተቀምጦ መጠባበቁን ቀጠለ::

ሙሉ ለሙሉ መንቃቴን ካረጋገጠ በኋላ፤ ምግቡን በማንኪያው እየሰፈረ ወደ አፌ ይልክና መናገሩን ይቀጥላል ያ ደግሞ በተቻለኝ መጠን ምግቡን እንዳለምጥ ጊዜ ለመስጠት ነበር:: ያ በዚያ ሰው የተደረገው ትህትና የተሞላበት የመስዋእትነት ተግባር፤ በማገገሚያው ውስጥ በነበርኩበት ጊዜ ከማስታውሳቸው ማስተዋል ከተሞላባቸው



ሥራዎች አንዱ ነው:: የስታን ጥንካሬና ርህራሄ የተሞላበት የተዋሃደ ባህሪው የተለየ ሰው ያሰኘዋል::

ስለ ኢልዛሮቭ ፍሬም በገለጽኩበት ጊዜ ምናልባት የህክምና ሂደቱን ቀላል አድርጌ ገልጬው እንዳይሆን እሰጋለሁ:: ከዚያ በጣም የተለየ ነው:: ኢቫ የወሰነችው ውሳኔ አንድ ሰው ብቻውን ሊወስነው የሚችል ውሳኔ አልነበረም:: ኢልዛሮቭ የህክምና ሂደት በእኔ ላይ እንዲከናወን መወሰን ነበረባት::

በመጀመሪያ ላይ ይህ መሣሪያ የተሠራው እግርን ቀጥ አድርጎ ለማቆየት ነበር:: መሣሪያው አስቀድሞ ሲፈለሰፍ የተሠራው ገና ከውልደታቸው ጀምሮ አንደኛው እግራቸው ከሌላው እግራቸው ይልቅ አጭር ለሆነ ግለሰቦች ነበር:: እስከ አሥራ ሁለት ኢንች የእግር መበላለጥ ላጋጠማቸው ሰዎች ሁሉ የሚሠራ ነው:: ይልቁንም በተሽከርካሪ ብስክሌቶች ለሚንቀሳቀሱ፤ በብረት ድጋፍና በምርኩዝ ለሚሄዱ ሰዎች አገልግሎት ይሰጣል:: የኢልዛሮቭ ፍሬም በአካባቢ ያሉ ሌሎች የሰውነት አካላት ሳይጎዱ አጥንቱ እንዲያድግ የሚያደርግ መሣሪያ ነው:: በመሣሪያው አማካይነት ሰውነት በአጥንቶቹ መካከል ባለው ክፍት ስፍራ ላይ አጥንት ያበቅላል::

ኢልዛሮቭ የተሰኘው ይህ አጥንት አብቃይ መሣሪያ ውጫዊ አያያዥ (ማፅኛ) ተብሎ ይጠራል:: የሳይቤሪያ ዜግነት ያለው ኢልዛሮቭ የተባለ ዶክተር ነው የፈለሰፈው::

ዶ/ር ኢልዛሮቭ አስቀድሞ መሣሪያውን የሞከረው በበጎች ላይ ሲሆን፤ ያደጉና ተሰብረው የጠፉ አጥንቶች ወይም ገና ከውልደት ጀምሮ

እጥረው የተፈጠሩ አጥንቶች እንዲያድጉ የተደረገ ሙከራ ነው:: እንደኔ ያሉ የጠፉ አጥንቶችን ስማስተካከል ሂደቱ አጥንትን በትክክል መቁረጥን ይጠይቃል:: የፒያኖ ክር ያህል ውፍረት ያላቸው የኤሌትሪክ ሽቦዎች በቆዳና በአጥንቱ ውስጥ እንዲገቡና በኋላም በሌላኛው አቅጣጫ እንዲወጡ ይደረጋል::

መሣሪያው በእርሳስ ውፍረት ያህል ባላቸው ጠፍጣፋ ብረቶች አማካይነት ከወገብ በታች ካለው አጥንት ጋር እንዲያያዙ ይደረጋሉ:: ዶክተሮቹ አራት ረጃጅም ጠፍጣፋ ብረቶችን ወደ ውስጥ ማስገባት እንዲያስችላቸው በጭኔ ላይ ወደ መቀመጫዬ አቅጣጫ አራት ቀዳዳዎችን በሱ:: ይህንን ካደረጉ በኋላ፤ ቢያንስ ቢያንስ ሰላሣ ቀዳዳዎች በግራ እግሬ ላይ ተቀደዱ:: አብዛኞቹ ቀዳዳዎች በቀጥታ በአንደኛው የእግሬ አቅጣጫ ገብተው በሌላኛው ወገን የሚወጡ ናቸው:: ትልልቆቹ ቀዳዳዎች ሥጋ ለሥጋ ሄደው በትልቁ የጭን አጥንት ላይ ብረቶቹ እንዲታሠሩ የሚያደርጉ ናቸው:: ስድስት ወራት ካለፈ በኋላ ቁልቁል እግሬን በመመልከት ትናንሾቹ ቀዳዳዎች እየተለጠጡ እንደመጡ ማየት ችዬ ነበር::

በየቀኑ አንድ ሰው እየመጣ የመሳሪያውን ቡሎኖች ያጠብቃቸዋል፤ ይህም የሚደረገው አጥንቶቹ እንዲለጠጡ ለማድረግ ነበር:: አብዛኛውን ጊዜ ይህንን ተግባር የሚያከናውኑት ነርሶቹ ነበሩ:: ወደ ቤቴ ከገባሁ በኋላ ደግሞ ይህንን የማድረጉን ሃላፊነት ኢቫ ተረከበች:: አንድ አመት በሆነ ጊዜ ውስጥ የግራ እግሬ ትልቁ አጥንት እድጎ የጠፋውን የአጥንቴን ክፍል ሙሉ ለሙሉ ደፈነው:: በጥሩ የፈጠራ ክህሎት የተሠራ መሣሪያ ነው:: ምንም እንኳን ስቃይን የሚያስከትልና በርካታ ውስብስብ ችግሮች የሚያስከትል ቢሆንም፤



በአጥንት ላይ የሚፈጠርን እጥረት ስማራዘም የሚያስችል ነው:: እኔ፤ "እስቀያሚው ተአምረኛ" እያልኩ ነው የምጠራው::

ስድስት ቀጫጭን ብረቶችም ከግራ እጄ ክንድ አንስቶ ውስጥ ውስጡን በማስፍ በሌላው አቅጣጫ እንዲወጡ ተደርገዋል:: የመዛግ ባህሪ የሌላቸው ጠፍጣፋ ብረቶች በክንዴ ፊት ለፊትና ኋላ ግጥም ተደርገው ታስረዋል:: ምክንያቱም በክንዴ ውስጥ ያሉት ሁለቱም የመጀመሪያዎቹ የእጅ አጥንቶች በመጥፋታቸው ነው:: ጠፍጣፋዎቹ ብረቶች የእርሳስ ያህል መጠን ያላቸው ሲሆን፤ ዶ/ር ግሪደር በስተቀኝ ካለው መቀመጫዬ አካባቢ የወሰዱትና በእጄ ታችኛው ክፍል ላይ የተከሉት አጥንት ፀንቶ እንዲቆይ ለማድረግ ረድቷል:: ዶክተሩ ይህንን ነገር ሲያብራሩት፤ የነዳጅ ጉድጓድ በሚቆፈርበት ጊዜ ናሙና ከመውሰድ ጋር ያይዙታል:: በተጨማሪም ሰላሣ ሁስት ካሬ ኢንች የሚሆን ቆዳ ክቀኝ እግሬ ላይ በመላጥ በግራ እጄ ላይ በነበረ ትልቅ ቁስል ላይ ለጥፈውልኛል:: ከዚህ በኋላ ደግሞ በእጄ ላይ በተተከሉት ሁለት አጥንቶች መካከል ቴፍሎን ስትራይፕ የተባለ መለያ በእጄ ውስጥ እንዲቀበር ተደርጓል:: ይህም የሚረዳው አዲስ የተተከሉት አጥንቶች እርስ በእርስ እንዳይጠጋጉ እንዲረዳ ነው:: እንዲህ በመሆኑም አጥንቶቹ አቅጣጫቸውን ይዘው በአንድነት ለማደግ ይችላሉ::

እንደ አጋጣሚው ሆኖ ይሄኛው የህክምና ሂደት በእኔ ላይ ውጤታማ አልሆነም አጥንቶቹ ተፈውሰዋል፤ ይሁን እንጂ እርስ በእርሳቸው ተገናኝተው ነበር:: በዚሁ ሳቢያ የእጄን መዳፍ መጨበጥ ወይም የሆነ ነገር አንጠልጥዬ መያዝ አልችልም:: ክንዴን ቀጥ አድርጌ መዘርጋትም ይሁን የእጄን መዳፍ ማሽከርከር ወይም ላይና ታች ማድረግ አልችልም:: እጄን ቀጥ አድርጌ ስዘረጋ ሰዎችን ለመጨበጥ

እስከሚያስችለኝ ርቀት ብቻ ነው የሚነሣው:: እጄ በስተግራም ይሁን በስተቀኝ መዟዟር አይችልም:: ሁሉም ነገር አሰቃቂና ስቃይ የተሞላበት እንደሆነ አውቃለሁ፤ በጊዜውም የሚሰማው እንደዚያ ነው:: ይሁን እንጂ ለኤልዛሮቭ ምስጋና ይግባውና ነገሩ ተከናወነ::

አዎ የኤልዛሮቭ መሣሪያ ውጤታማ ሆነ፣ በህክምናው ሂደት ውስጥ በጽናት ከተቋቋምኳቸው ስቃይ ከተሞሉ ሂደቶች መካከል ዋነኛ ው ነው::

በእግሬ ውስጥ እንዲያልፉ የተደረጉት የኤልዛሮቭ ብረቶች ክብደት አሥራ ሦስት ኪሎ ተኩል ያህል ይሆናል፤ በተጨማሪ በክንዴ ላይ የታሠሩትና የገቡት ብረቶች ክብደት ዘጠኝ ኪ. ግራም ያህል ይሆናል:: ከስምንት ወራት በኋላ፤ በተሽከርካሪ ብስክሌቴ ላይ ተቀምጬም ይሁን እንደገና አራት ወራት ተጨምሮ በምርኩዝ ስንቀሳቀስ በድምሩ ለአንድ አመት ያህል ማለት ነው ያንን ተጨማሪ ክብደት መሸከም ግዴታ ነበር::

በደረስኩበት ሥፍራ ሁሉ የሚያጋጥመኝን በአግራሞት የፈጠጡ አይኖች መገመት ትችላላችሁ? በተሽከርካሪ ጎማ ላይ ተቀምጦ ያንን ሁሉ ብረታ ብረት በሰውነቱ የተሸከመ ሰው ሲመለከቱ ሰዎች ትንፋሻቸው ቁርጥ ይልና አፍጥጠው ይመለከቱኛል::

እዘውትሬ የተለመደ ጉብኝቴን በተሽከርካሪ ብስክሌቴ ላይ ሆኜ ወደ ዶ/ር ግሪደር ቢሮ አደርጋለሁ፤ በዚያ ያሉ ሌሎች ህመምተኞች እስተያየትም የተለመደ ነበር:: ምንም እንኳን እያንዳንዳቸው ጀሶ የተደረገላቸው፣ የብረት ማያያዣ የሚጠቀሙ ወይም በምርኩዝ የሚሄዱ ቢሆኑም፤ ሁሉም ወደ እኔ፣ ወደ ጠፍጣፋዎቹ ብረቶችና በእግሬ ላይ ወደጠለቀው ክብ ብረት አፍጥጠው ይመለከታሉ:: ከዚያ



በኋላ ያለ ምንም ማወላወል አንድ ሰው በሹፈት የሚናገረው "እ! እኔ ክፉኛ የተጎዳሁ መስሎኝ ነበር" የሚሉ ቃላትን ነው፤ አንዳንድ ጊዜም አንዳንዶች፤ "አንተን ከተመለከትኩ በኋላ እኔን ተሻለኝ" የሚሉኝ ሰዎች አሉ:: ለረዥም ጊዜ ስቃይ ያለው ጉዳት ምን ያህል እንደሆነ የመመዘኛ ደረጃው እኔ ሆንኩ:: በላዬ ላይ ከተከመረው የብረታብረት መዓት የተነሣ ከዓመታት በፊት የሥነ ምድር አጥኚዎች ቢያገኙኝ ኖሮ አዲስ ፍጥረት ያገኙ ይመስላቸው ነበር እያልኩ ለሌሎች አቀልድላቸዋለሁ:: የሰውነት አካሌ አደረጃጀት ሙሉ ለሙሉ ተለውጦ ነበር::

እንደገና ተመልሶ ቀላል የሆኑ የአካል እንቅስቃሴዎችን እንኳን ማድረግ ፈጽሞ የማይታሰብ ነገር ነው፤ ትንሽ የምትባል እንቅስቃሴ እንኳን እንደ ተአምር ትቆጠራለች:: ሁልጊዜም ነገሮችን እንዴት ማከናወን እለማመዳለሁ፤ ከተሳካ ልክ እንደ አንድ ታላቅ ድል ይቆጠራል::

ዶ/ር ግሪደር የግራ እግሬንና እጄን የሚተርፍበትን መንገድ ምን ያህል ተግተው ይፈልጉ እንደነበር የተረዳሁት በኋላ ላይ ነው:: በእኔ ጉዳይ ፈጥነው ተስፋ ባለመቁረጣቸው ሁል ጊዜም ምስጋናዬ ትልቅ ነው::

የቀኝ እግሬ ጉልበት ደቆ ነበር፤ ለተወሰነ ጊዜም በጀሶ ታስሬ ነበር:: የጉልበቴን ሎሚ የሚተካ ክብ ነገር ከተደረገልኝ በኋላ ችግሩ ተቃለለ:: ያልተሰበረው የአጥንቴ አካል ቢኖር የቀኝ እጄ ብቻ ነበር::

የኤልዛሮቭ ፍሬም ህክምናው ስኬታማ ቢሆንም ህመሙ ግን ትቶኝ አልሄደም፤ ለአንዲት ደቂቃ እንኳን::

“እስከመቼ?” እያልኩ ምን ያህል እንደጠየቅኩ በውል አላውቅም:: ማወቅ እፈልግ የነበረው ነገር በዚህ መሣሪያ በሚደርስብኝ ስቃይ ምን ያህል ጊዜ መታገስ እንደሚኖርብኝ ነበር:: መስራትና አለመስራቱን ለማወቅ ምን ያህል ጊዜ ይወስዳል? እንደገና ለመራመድ ምን ያህል ጊዜ ይጠይቀኛል?

ማንም ሰው መልስ አልሰጠኝም፤ መልስ ሊሰጠኝ የሚችልም አልነበረም፣ እኔ ግን መጠየቄን አላቋረጥኩም::

“ጥቂት ወራት” የሚለው የተለመደ መልስ ነበር::

“ጥቂት ሲባልስንት? ” ወጥሬ እይዛቸዋለሁ::

አንዱ ዶ/ር በመጨረሻው እንዲህ አለኝ፤ “ብዙ ወራት፤ ምናልባትም ረዥም ጊዜ::”

“ጥቂት አመታትም ሊወስድ ይችላል ማለትህ ነው?”

“አዎ፤ ምናልባትም ዓመታት”

“እናም እግሮቼንና እጆቼን እንደገና ለማንቀሳቀስ ዋስትና የለም ነው የምትለኝ?”

“ምንም ዋስትና የለም:: በድንገት የማመርቀዝ ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል፤ እናም እግርህን ለማስወገድ የምንገደድበት ሁኔታ ይከሰታል”

“ለወራት ያህል ይህን ስቃይ ታግሼ ከቆየሁም በኋላ ነገሬ ያለ እግር ይጠናቀቃል እያልከኝ ነው?”

በአዎንታ ራሱን ነቀነቀ::



እንደ እውነቱ ከሆነ መስማት የምፈልገው ያንን አልነበረም:: ምንም እንኳን ኢሻም ተመሳሳይ ነገር የነገረችኝ ቢሆንም ሙሉ ለሙሉ የለማሁትን መካድ ነበረብኝ:: ሙሉ ለሙሉ ጤናማ እንደምሆን የሚያረጋግጥልኝን ዋስትና ያለማቋረጥ መፈለግ ቀጠልኩ::

መልስ ማግኘት እፈልጋለሁ፤ ምናልባትም ከዚያም በላይ እንኳን ደህና እንደምሆን ዋስትና እፈልጋለሁ:: ከዚያ ሆስፒታል ውስጥ በሁለት እግሮቼ እየተራመድኩ መውጣት መቻልን እፈልግ ነበር፤ እናም ወደቀደመው የተለመደ የሕይወት እንቅስቃሴ መቀላቀል:: ይሁን እንጂ ያንን ዋስትና ሊሰጠኝ ፈቃደኛ የሆነ ወይም ችሎታ ያለው ማንም ሰው አልነበረም::

ብዙ ወራቶች አለፉ፤ አንድ ቀን ግን ወደዚያ ሆስፒታል ተመልሼ ሄድኩና በዚያ የነበሩትን ነርሶች እጅ እየጨበጥኩ ሰላምታ ሰጠኋቸው::

ያንን ኤልዛሮቭ ፍሬም የተሰኘ መሳሪያ ባደረኩባቸው ወራቶች ሌሎች ችግሮችም ነበሩብኝ:: ብዙ ጊዜ የማመርቀዝ ሁኔታ ያጋጥመኝ ነበር:: በእያንዳንዱ ጊዜም መመረዙ ወደ ሰውነቴ ሁሉ ይሰራጭና ያለ እግር እንድራመድ ሊያበቃኝ ይችላል በሚል ፍርሃት እጠመዳለሁ::

ከሃኪም ቤት ከወጣሁ በኋላም እንኳ የሰውነት መመረዝ ተከስቶብኝ ነበር:: ለሶስት ጊዜ ያህል ወደ ሆስፒታል ተመልሼ ገብቻለሁ፤ እናም መመረዙን ለመከላከል ቁጥር ስፍር የሌላቸው ፀረ ታዛስያን የሆኑ መድሃኒቶች ተጠቅሜአለሁ::

ከዚያ በኋላም እንኳን ለብዙ ሌሊቶች፤ “እግዚአብሔር ሆይ እንደገና ወደ መንግስተሰማይ ውሰደኝ:: ወደ ምድር ለምን መልስህ

እንዳመጣኸኝ ፈጽሞ አልገባኝም፤ እባክህ በዚህ አትተወኝ" እያልኩ ጸልዬአለሁ::

እግዚአብሔር ለጸሎቴ የሰጠው ምላሽ ቢኖር፤ "አይቻልም" የሚል ነበር::

ዛሬም ድረስ ምክንያቶቹን ሙሉ በሙሉ አላውቅም፤ ነገር ግን ወራቶቹ እያለፉ ዓመታቶችም እየነጎዱ በሄዱ ቁጥር በዝግታ አንድ ነገር ተገንዘብኩ፣ ቢያንስ ቢያንስ ወደ ምድር የተመለስኩባቸው ጥቂት ምክንያቶች ተገለጹልኝ::

የፈውስ ሂደቱ ጀመረ:: በዚያ ሆስፒታል አልጋ ላይ ዕለት ዕለት ተጋድሜ፤ እግዚአብሔር መልሶ ወደ ምድር እንደላከኝ በዝግታ መቀበል ጀመርኩ:: ያንን ሁሉ በአካሌ ላይ የደረሰ ስቃይ ለምን በጽናት መቀበል እንደነበረብኝ፣ ለምን እንደሆነ አላውቅም፤ ነገር ግን ዴቪድ ጃንቲሊስ የተናገራቸውን ቃላት ዝም ብዬ ማሰላሰሌን ቀጠልኩ:: እርሱና እጅግ ብዙዎች እኔ በሕይወት እንድኖር በጸሎት ወደ እግዚአብሔር ጮኸዋል:: እግዚአብሔር ጸሎታቸውን የሰማ በመሆኑ ምክንያት በሕይወት መቆየቴ የሆነ ዓላማ አለው::

በቀናት መካከል ባለፉ መጠነ ሰፊ ስቃዮች ውስጥ የዴቪድን ቃላት አስታውሳቸዋለሁ:: እንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር በሕይወት በመኖሬ ያለው ዓላማ ነው በሕይወት እንድቆይ ያደረገው ስል አስባለሁ::

በሄርማንን ሆስፒታል ቀዶ ጥገና ክፍል ውስጥ ለአሥራ ሁለት ቀናት ያህል ቆይቻለሁ:: ወደ ታችኛው የቅዱስ ሉቃስ ሆስፒታል



እስኪያዘዋውሩኝ ድረስ ሌላ አራትና አምስት ቀናት በዚያው በሄርማንን ሆስፒታል ውስጥ ቆይቻለሁ:: ሁለቱም ሆስፒታሎች በዓለም ላይ ከሚገኙ ታላላቅ የህክምና ማዕከሎች የሚመደቡ ናቸው:: በቅዱስ ሉቃስ ሆስፒታል ለ105 ቀናት ቆየሁ:: ወደ ቤት ከተመለስኩ በኋላ ለአሥራ ሦስት ወራት ያህል ተኛሁ:: ሰላሣ አራት የቀዶ ጥገና ህክምናዎች ተደረጉልኝ:: ያስምንም ጥያቄ ዛሬ በሕይወት ያለሁት ሰዎች ይጸልዮልኝ ስለነበር ነው::

ከዲክ ዋንሪከር ጀምሮ በሃገሬ ምድር የሚገኙ አብዛኛዎቹም የማላውቃቸው ሰዎች ስለ እኔ ወደ እግዚአብሔር አንብተዋል::

ምናልባትም ትልቁ ተአምር ያ ነበር:: ሰዎች ወደ እግዚአብሔር ጸለዩ፣ እግዚአብሔር ጸሎታቸውን አከበረ::

ዛሬ ወደ ኋላ ዘወር ብዬ ስመለከት፤ እግዚአብሔር እኔን ለማዳን ምን ያህል ሰዎች እንደተጠቀመ ይገርመኛል:: ዲክ ዋንሪከር ያላቋረጠ ፀሎቱን በመቀጠሉ ሕይወቴን ታደገ:: ዶ/ር ግሪደር ያንን የመጀመሪያ የቀዶ ጥገና ህክምና በማድረግ እጄና እግሬ እንዲተርፍ አደረገ:: ዶ/ር ሆቼንስ ከቀዶ ጥገናው ህክምና በኋላ ሕይወቴን አተረፈት፤ ምክንያቱም ልክ እንደ አዳኝ ውሻ ተናጣቂ በሆነ እልኸኝነት "መኖር አለብህ" የሚል ቁርጠኛ አቋም የነበራቸው በመሆኑ ነው:: በቅዱስ ሉቃስ ሆስፒታል ውስጥ ያሉ ሁልጊዜ የሚያበረታቱኝ የድንገተኛ አደጋ ክፍል ነርሶች ቀንና ሌሊት ይንከባከቡኝ ነበር:: እያንዳንዳቸው የተጫወቱት ሚና ቀላል አልነበረም::

የቀዶ ጥገና ህክምና ክፍሉን ለቅቄ የወጣሁት የዴቪድ ጆንቲሊስና በሌሎች ፀሎት ነበር:: “እኛ ይህንን እንወጣዋለን:: ለመኖር አንተ ማድረግ የሚገባህ ነገር የለም:: በዚህ ጉዳይ ላይ እኛ እንጸልያለን”

እንደማልሞት እያወቅኩ መጣሁ::

የእግዚአብሔር ሰዎች እንድሞት አልፈቀዱም::





“እኔ ከአንተ ጋር ነኝና አትፍራ፤ እኔ አምላክህ ነኝና አትደንግጥ፤ አበረታሃለሁ፤ እረዳሃማለሁ፤ በጽድቄም ቀኝ ደገፌ እይዝሃለሁ::”

ኢሣ 41፥10

ምንም እንኳን ሆን ብለው ባይሆንም፤ ጠያቂዎች ሁኔታዬ እንዲባባስ ምክንያት ሆኑ:: ስለ እኔ ግድ ያላቸው ነበሩ፤ እናም ያንን ስሜታቸውን ለመግለጽ ይፈልጉ ነበር:: ለእኔ ግድ ያላቸው በመሆኑ ምክንያት በዓለም ላይ የተለመደውን ነገር ነበር የሚያደርጉት:: ይነበኙኝ የነበረው በህክምናው ሆስፒታል ውስጥ በነበረው የመኝታ ክፍሌ ነው:: ችግሩ ደግሞ ያ ነበር::

በክፍሌ ውስጥ የሚፈጠረው የማያቋርጥ የመግባትና የመውጣት እንቅስቃሴ አሰልቺ ሆኖብኝ ነበር:: እዚያ ተኝቼ እንዲቀመጡ በማድረግ ላጫውታቸው አልችልም:: ምናልባትም እንደ ቤተክርስቲያን መጋቢነቴ መጫወት የሚገባኝን ሚና መጫወት ወይም እነርሱን ለማዝናናት የተወሰነ የሃላፊነት ስሜት ይሰማኝ ነበር:: ጠያቂዎቼን ክፍሉን ለቀው እንዲወጡ በመጠየቅ ወይም ዳግመኛ እንዳይመጡ በመናገር የማንንም ስሜት መጉዳት አልፈለግኩም::

የቀዶ ጥገና ህክምና ክፍሉን ለቅቄ የወጣሁት የዴቪድ ጀንቲሊስና በሌሎች ፀሎት ነበር:: "እኛ ይህንን እንወጣዋለን:: ለመኖር አንተ ማድረግ የሚገባህ ነገር የለም:: በዚህ ጉዳይ ላይ እኛ እንጸልያለን"

እንደማልሞት እያወቅኩ መጣሁ::

የእግዚአብሔር ሰዎች እንድሞት አልፈቀዱም::



# 8

# የሕመም ሥቃይና ማስተካከያዎች

"እኔ ከአንተ ጋር ነኝና አትፍራ፤ እኔ አምላክህ ነኝና አትደንግጥ፣ አበረታሃለሁ፤ እረዳህማለሁ፤ በጽድቄም ቀኝ ደግፌ እይዝሃለሁ::"

ኢሣ 41፥10

ምንም እንኳን ሆን ብለው ባይሆንም፤ ጠያቂዎች ሁኔታዬ እንዲባባስ ምክንያት ሆኑ:: ስለ እኔ ግድ ያላቸው ነበሩ፤ እናም ያንን ስሜታቸውን ለመግለጽ ይፈልጉ ነበር:: ለእኔ ግድ ያላቸው በመሆኑ ምክንያት በዓለም ላይ የተለመደውን ነገር ነበር የሚያደርጉት:: ይጎበኙኝ የነበረው በህክምናው ሆስፒታል ውስጥ በነበረው የመኝታ ክፍሌ ነው:: ችግሩ ደግሞ ያ ነበር::

በክፍሌ ውስጥ የሚፈጠረው የማያቋርጥ የመግባትና የመውጣት እንቅስቃሴ አሰልቺ ሆኖብኝ ነበር:: እዚያ ተኝቼ እንዲቀመጡ በማድረግ ላጫውታቸው አልችልም:: ምናልባትም እንደ ቤተክርስቲያን መጋቢነቴ መጫወት የሚገባኝን ሚና መጫወት ወይም እነርሱን ለማዝናናት የተወሰነ የሃላፊነት ስሜት ይሰማኝ ነበር:: ጠያቂዎቼን ክፍሉን ለቀው እንዲወጡ በመጠየቅ ወይም ዳግመኛ እንዳይመጡ በመናገር የማንንም ስሜት መጉዳት አልፈለግኩም::

ብዙ ጊዜ ምንም እንኳን ፍላጎቴ ጥቅልል ብሎ መተኛት ቢሆንም ያለውዴታ ፈገግታ አሳያቸዋለሁ ወይም አዋራቸዋለሁ። አንዳንድ ጊዜም እጅግ ከባድ የሆነው የህመም ስቃዬ መልካም እንግዳ ተቀባይ ልሆን እያስችለኝም፤ ይሁን እንጂ በዚያ ሁኔታ ውስጥ ሆኜም ደስተኛ ለመምሰል እጣጣራለሁ። ለእኔ እንደሚያስቡልኝና እኔን ለማየት ብዙ ዋጋ ከፍለው እንደመጡ ራሴን ማሳሰብ ቀጠልኩ።

በወዳጆቼ፣ በዘመዶቼና በቤተክርስቲያን አባላት ከሆስፒታሉ የመግቢያ በር እስከ መኝታ ክፍሌ ድረስ ያለው ሰልፍ እየተሳበ የሚሄድ ነው የሚመስለው። ኢቫ አንድ ቀን ከሰዓት በኋላ ስትመጣ ጠያቂዎቼ ምን ያህል ችግር እንደፈጠሩብኝ ተገነዘበች። እንዲህ እስኪሆን ድረስ ዝም በማለቴ ገሰጸችኝ።

እንደተረዳሁት ሰዎቹን ተመልሰው እንዳይመጡ እንዳልነገርኳቸው የገመተች ይመስለኛል፤ ስለዚህ ወደ ነርሶቹ በመሄድ የሚፈቅዱላቸውን ጠያቂዎች ቁጥር እንዲቀንሱ ጠየቀቻቸው። ሁሉንም ሰዎች ከመምጣት አላገዳቸውም፤ ይሁን እንጂ ወደክፍሉ የሚገባውንና የሚወጣውን የሰው ቁጥር በጥቂቱ ጋብ አደረገው።

በሰውነቴ ላይ ከደረሰው ስቃይና ህመም እንዲሁም ከገቢውና ከወጭው ህዝብ በተጨማሪም በድብርት ውስጥ ነበር የምኖረው። የዚህ ትልቁ ምክንያት በደረሰብኝ ድንገተኛ አደጋ ሊከሰት የሚችል ድብርት ሲሆን፤ በጥቂቱም የምወስዳቸው መድሃኒቶች ካስከተሉት ተጽእኖ ሊሆን ይችላል። ይሁን እንጂ እኔ እንደማምነው የውጤቱ መጨረሻ ያልታወቀና ማስቂያ የሌለው የህመም ስቃይ የተጋፈጥኩ በመሆኑ፤ ወደፊት ብሩህ ቀን ይጠብቀኛል የሚል ተስፋ ከውስጤ በመጥፋቱ



ይመስለኛል። ብዙውን ጊዜ በሕይወት ለመኖር በፍጹም አልፈልግም ነበር።

ፍጹምነት ከሞላው መንግስተ ሰማይ በምድር ወዳለ ስቃይ ወደሞላበት ሕይወት ለምንድነው ተመልሼ እንድመጣ የተደረገው? ምንም ያህል እጥብቄ ብሞክርም፤ ሕይወቴ እንደገና ደስተኛ ሊሆን አልቻለም፤ እንደገና ወደ መንግስተ ሰማይ መሄድ እፈልግ ነበር።

የህመም ስቃይ ከአደጋው በኋላ የሕይወቴ አንድ አካል ሆነ፤ እርግጠኛ ነኝ ይህ ነገር በብዙዎችም ላይ ደርሷል። በዚህ ሁኔታ ውስጥ መኖርን መለማመዳችን ደግሞ አስደናቂው ነገር ነው። አሁን እንኳን በአንዳንድ አጋጣሚዎች ሌሊቱን መልካም እንቅልፍ ተኝቼ ከነቃሁ በኋላ በአልጋዬ ላይ ተጋድሜ፤ የትኛውም ቦታ ላይ ያልተጎዳሁ መሆኔን በድንገት ማሰብ እጀምራለሁ። ከዚያ በኋላ ደግሞ የቀኑን ሃያ ሦስት ሰዓትና ሃምሣ አምስት ደቂቃዎች በማያቋርጥ የህመም ስቃይ ውስጥ እየኖርኩ እንደሆነ እንዳስብ እደረጋለሁ።

ያለሁበት ሁኔታዬ በስነልቡናዬ ላይ ያስከተለውን ከፍተኛ ተጽእኖ የተረዳሁት ጥቂት ዘግየት ብሎ ነበር።

እጸልያለሁ፤ ሰዎችም አብረውኝ ይጸልያሉ፤ ይሁን እንጂ ውስጤ ፈጥኖ ተስፋ ይቆርጥና፤ "አሁን ይሄ ሁሉ አስፈላጊ ነው?" እያልኩ በቀኑ ውስጥ ብዙ ጊዜ ራሴን እጠይቃለሁ።

ዶክተሮቹና ነርሶቹ ድብርቱን ከእኔ ላይ ለማስወገድ መድሃኒቶችን አብዝቼ እንድወስድ ያበረታቱኝ ነበር፤ እኔ ግን ተቃወምኩ። ለምን

እንደዚያ እንዳደረኩ እርግጠኛ አይደለሁም:: ምናልባትም በርካታ መድሃኒቶች የወሰድኩ በመሆኑ ከዚያ በላይ ባለመፈለጌ ሊሆን ይችላል:: ከዚህም በላይ ከዚያ በላይ ተጨማሪ መድሃኒት የሚፈይደው ነገር እንደሌለ አስባለሁ::

አሁን በሕይወቴ እየሆነ ካለው ውስብስቡ ከወጣ ሕይወት ነፃ መሆንና መሞት እፈልግ ነበር:: ነገሮች ስለሚለወጡበት ጉዳይ ለማሰላሰል ሙሉ ለሙሉ ብቃት እንዳልነበረኝ ግልጽ ነበር:: አሁን አንድ ነገር ደግሞ ተገነዘብኩ በድብርት ውስጥ ገብቻለሁ::

ፈጥኖ ሁሉም ሰው ያለሁበትን ይህንን ሁኔታ አወቀው::

"የስነ አዕምሮ ጠቢብ ማነጋገር ትፈልጋለህ? " ሲል ዶክተሬ ጠየቀኝ::

"አልፈልግም" ስል መለስኩለት::

ከጥቂት ቀናት በኋላ አንዷ ነርስ እንዲህ ስትል ጠየቀችኝ፤ "አማካሪ ሃኪም እንድጠራልህ ትፈልጋለህ? ሊያማክርህ የሚችል አንድ ሰው?"

የኔ መልስ የተለመደው ነበር::

ማንንም ሰው ማነጋገር የማልፈልግ በመሆኑ "አደጋ ጣይ የአዕምሮ ጠበብት" ብዬ የምጠራቸው ወደ ክፍሌ በዝግታ ይገቡ ጀመር::

"በጣም ከፍተኛ አደጋ እንዳጋጠመህ አያለሁ" አለኝ አንድ በስውር የመጣ የሥነ አዕምሮ ጠበብት የሐኪሙን ዘገባ ካነበበ በኋላ::



"ስለ አደጋው ምንም አይነት ነገር ማውራት አልፈልግም" አልኩት እውነቱ ደግሞ ስለማልችል ነበር:: ከዚህ ምድር ተለይቼ በሄድኩባቸው ዘጠና ደቂቃዎች ውስጥ የሆነውን ነገር ለእያንዳንዱ ሰው እንዴት መግለጽ እችል ነበር? የማይገለጸውን ነገር ለመግለጽ ቃላትን ከየት መፈለግ እችላለሁ? እውነታዊ በሆነ ቋንቋ መንግስተ ሰማይ ስለመሄዱ ጉዳይ እንዴት መግለጽ እንደምችል አላውቅም:: በዚያ መንገድ መናገር ጀምሬ ቢሆን ኖሮ በጣም እርግጠኛ ነኝ ወደ እብደት እንደማመራ አውቃለሁ::

እጅግ በሚያስከፋ ሁኔታ በአዕምሮዬ ላይ አንዳች ችግር እንደደረሰ ያስብ ነበር:: ይሄ ችግር ደግሞ ያልተፈጠረና የሌለን ነገር እንደሆነና እንደተፈጠረ አድርጎ በአዕምሮ የመሳልና የማሰብ ችግር በመሆኑ፤ ይህንን ቅዥት ለማስወገድ ብርቱ መድሃኒት መውሰድ እንደሚገባኝ ደምድሟል:: በሕይወት ዘመኔ ሁሉ ከተለማመድኩት ደስታ ይልቅ የላቀውንና ካየሁት ኃያል ነገር ሁሉ የበለጠውን ያንን እውነታ በምን ቃላት ልገልጸው እችላለሁ? ይህን ሁሉ ካየሁ በኋላ ሞት መምረጤን በመናገሬ እንዴት አዕምሮዬን እንደሳትኩ እቆጥራለሁ? እኔ ምን እንደሚጠብቀኝ አውቃለሁ፤ እርሱ ግን አያውቅም::

በእኔ ላይ ስለሆነው ነገር ከሥነ አዕምሮ ጠበብትም ይሁን ከማንኛውም ሰው ጋር ለመነጋገር ፍላጎት አልነበረኝም:: እንደዚያ አይነቱ ልምምድ ለሌሎች ሊያካፍሉት የሚከብድ እጅግ ኃይለኛና የጠለቀ ነገር መሆኑን ተመልክቻለሁ:: እኔና ኢቫ ምንም እንኳን እጅግ የተቀራረብን ብንሆንም በወቅቱ ግን ለእርሷ እንኳን ልነግራት አልችልም ነበር::

ወደ መንግስተ ሰማይ መሄድ እጅግ የተቀደሰ ነገር ነው፤ እጅግ የተለየም:: በመንግስተ ሰማይ ስሰነበረኝ የዘጠና ደቂቃዎች ቆይታ ማውራት እነኛን ድንቀኛ ጊዜያት ማንኳሰስ ይመስለኛል:: ወደ መንግስተ ሰማይ ስለነበረኝ ጉዞ እውነትነት በጭራሽ ተጠራጥሬም ይሁን ጥያቄ ኖሮኝ አያውቅም:: ያ በጭራሽ አስጨንቆኝ አያውቅም:: ሁሉም ነገር ግልጽና እውነታዊ ነበር፤ ልክድ ብፈልግ እንኳን ላደርገው አልችልም:: በጭራሽ:: ችግር የሆነው ነገር ግን ያንን ኃያል የሆነ ልምምዴን ከማንም ጋር ልጨዋወተው አለመፈለጌ ነበር::

ያ ሁኔታዬ የሥነ አእምሮ ጠቢባኑን ወደ መኝታ ክፍሌ ከመምጣትና እኔን ለመርዳት ከመሞከር አላገዳቸውም:: ከጥቂት ጊዜያት በኋላ፤ የሥነ አእምሮ ጠቢባን መሆናቸውን ለእኔ አይናገሩም ነበር:: አሁን ሲታሰብ ነገሩ ሁሉ አስቂኝ ነው፤ የሆስፒታሉ የሥነ አእምሮ ሀኪሞች እኔን ሊረዱኝ ወስነው ነበር:: እነርሱን ለማነጋገር ፈቃደኛ ባልሆንኩ ጊዜ፤ በድብቅ ወደ መኝታ ክፍሌ እየገቡ ሁኔታዬን ማጥናት ጀመሩ:: አንዳንድ ጊዜ የሚመጡት ነርሷ እርዳታ በምትሰጠኝ ሰዓት ነበር:: አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ወደ ክፍሌ ገብተው የሐኪሙን ሪፖርት ያጠኑና ምንም ሳይናገሩ ይሄዳሉ፤ እኔ ንግግሩን እንድጀምር ተስፋ አድርገው እንዲህ እንደሚያደርጉ እገምታለሁ::

ብዙውን ጊዜ ወደ ውስጥ ይገቡና እንደዚህ የመሰለ ንግግር ይናገራሉ፤ "እኔ ዶ/ር ጆንስ እባላለሁ" በቃ ይሄው ነው:: ዶክተሩ የደም ምቴን ያጣራል ከዚያም፤ "ዛሬ ሆድህ እንዴት ነው?" ሲል ይጠይቃል:: የሐኪም ሪፖርቱን ከተመሰከተ በኋላም ጠቃሚ ጥያቄዎችን ያስከትላል:: አዘወትሮ ንግግር የሚጀምረው "ዛሬ እንዴት ይሰማሃል?" በሚል ቀላል ጥያቄ ነው::



"ያው እንደተለመደው ነው"

"አሁን እየሆነ ስላለው ነገር ሁሉ የሚሰማህ ምንድን ነው?" ምንም ያህል አቀራረባቸውን ቢቀያይሩትም፤ ሁልጊዜም የሚጠይቁት ምን እንደሚሰማኝ ነው::

"አንተ የሥነ አዕምሮ ሃኪም ነህ፤ አይደለህም? " ስል እጠይቃለሁ::

"እ ... ማለት ... በእርግጥም ነኝ"

"ጥሩ፤ ማወቅ የምትፈልገው ነገር ምንድን ነው? በድብርት ውስጥ እንዳለሁ ለማወቅ ነው የምትፈልገው? መልሱን ማወቅ ከፈለግክ በታላቅ ድብርት ውስጥ ነው ያለሁት:: ስለእርሱ ደግሞ መነጋገር አልፈልግም:: "

የቃላት ልውውጡ ይቀጥላል፤ ይሁን እንጂ አብዛኞቹን ቃላት በአዕምሮዬ ወንፊት እያጣራሁ እጥላቸዋለሁ:: ዶ/ር ጆንስንም ይሁኑ ሌሎቹ የሥነ አዕምሮ ሃኪሞች ሊረዱኝ እንደሚሞክሩ ባውቅም ምንም ተስፋ ያለው ነገር እንዳለ አላምንም:: በድብርት ውስጥ መግባቴን ጠልቼዋለሁ፤ ነገር ግን በዚህ ጉዳይ ላይ ምን ማድረግ እንዳለብኝ አላውቅም::

በአልጋዬ ላይ ለረዥም ጊዜ በተኛሁ መጠን፤ ወደፊት ምንም ተስፋ እንደሌለኝ እራሴን ማሳመኔ እየጨመረ ይሄድ ነበር:: መንግስተ ሰማይ ፍጹም የሆነች፤ የተዋበችና ደስታ የሞላባት ነች:: ከዚህ ስቃይ ተላቅቄ ተመልሼ መሄድ እፈልግ ነበር::

"አንድ ሰው መንግስተ ሰማይን ከተመለከተ በኋላ በዚህ ለመቆየት ለምን ይፈልጋል? " ስል እግዚአብሔርን እጠይቀዋለሁ፤ "እባክህ ... እባክህ መልሰህ ውሰደኝ።"

አልሞትኩም፤ ከገባሁበት ድብርት ውስጥም አልወጣሁም።

መነጋገርን ያልፈለኩት ከሥነ አዕምሮ ሃኪሞቹ ጋር ብቻ አልነበረም፤ ስለ ምንም ነገር ከማንም ጋር መነጋገርን አልፈልግም ነበር።

ማንንም ማየት አልፈልግም። ጠያቂዎች በማይኖሩበት ጊዜ ጥሩ ስሜት ይሰማኛል ወይም እንደዚያ እያልኩ ራሴን አሳምናለሁ።

ድብርት ውስጥ በገባሁበት ጊዜ፤ ብቻዬን ሆኜ እንድሞት፤ ማንም ወደ አዕምሮዬ እንዳይመልሰኝ ብቻዬን መሆን እፈልግ ነበር።

በተጨማሪም እንደ ቤተክርስቲያን መጋቢነቴ በዚህ ሁኔታ ውስጥ ሆኜ ማንም ሊመለከተኝ አልፈልግም ነበር፣ ውስጣዊ የሆነ በቂ ኩራት ይሰማኛል። እንዲህ ስል አካላዊ ስለሆነው ጉዳቴ ብቻ አይደለም የምናገረው፤ ይልቁንም ስለነበርኩበት እጅግ የዘቀጠ ስሜታዊ ውድቀት ጭምር ማለቴ ነው።

ሰዎች ወደ ክፍሌ ገብተው ሊያዩኝ በመጡ ጊዜ ከሚናገሩት ቃላትና ከአስተያየታቸው እንዲህ እያሉ በውስጣቸው እንደሚናገሩ አስባለሁ፤ "በምድር ላይ ካየኋቸው ሰዎች ሁሉ ምስኪን ነህ"

እንደሆንኩም እገምታለሁ።

እናም ድብርቱ እየቀጠለ ሄደ። እግዚአብሔር ሌላ ተአምር እስኪያለማምደኝ ድረስ ረዥም ጊዜ ወስዶ ነበር።



የሦስት ልጆች አባትና የምትደነቅ ሚስት ባል ነበርኩ። አደጋው እስከደረሰብኝ ጊዜ ድረስ ታላቅና ብሩህ የሆነ መፃኢ የሕይወት ተስፋ የነበረኝም ሰው ነበርኩ። በአደጋው ወቅት የሰላሳ ስምንት ዓመት ጎልማሣና እስኪዚያም ጊዜ ድረስ የጤነኛ ሰው ምሳሌና መልካም ተክለ ቁመና የነበረኝ ሰው ነበርኩ። ከአደጋው በኋላ በጥቂት ቀናት ውስጥ እንደገና ጠንካራና ጤነኛ ሰው ልሆን እንደማልችል አወቅኩት። አሁን ሙሉ ለሙሉ ተስፋ የለሽ ሆኛለሁ። በራሴ ላደርገው የምችል ምንም ነገር የለም፤ እጄን ማንሣት እንኳን አልችልም። እስከ ሕይወት ዘመኔ መጨረሻም እንደዚሁ ተስፋ የለሽ ሆኜ እቀራለሁ የሚል ውስጣዊ ፍርሃት ነበረብኝ።

ተስፋ ቢስ እንደሆንኩ ጠቋሚ ከነበሩት ነገሮች መካከል አንዱ፤ በሆስፒታሉ ውስጥ በነበርኩባቸው የመጀመሪያዎቹ አሥራ ሁለት ቀናት ሰውነቴ አንዳችም አይነት እንቅስቃሴ አለማድረጉ ነበር። ውስጣዊ የሰውነት ክፍሎቼ እንደሚመረዙ በማወቃቸው፤ ወደ ትንሹ የአንጀቴ ክፍል ፈሳሽ መድሃኒት አስገቡ፤ ነገር ግን ምንም ያህል ጠቃሚ አልነበረም።

"ያን ያህል ጥሩ አይደለም" አልኩ፤ ይወጣ የነበረው ጥቂት ጥቂት ብቻ ነበር፤ ነርሷ ወይም የነርሷ ረዳት በደስታ ፈገግ አለች።

አንድ ቀን በመጠኑ ጨመር አድርጌ ማማጥ ተሳካልኝ። "እ! በጣም ጥሩ ነው። ስለ አንተ በጣም ደስተኞች ነን። እስኪ እንጠብቅ ምናልባት የሚወጣ ተጨማሪ ነገር ይኖራል። "

በድብርት ውስጥ በነበርኩበት ወቅት፤ በሕይወቴ የመጨረሻውን አሳዛኝ ክስተት ያየሁበት ሁኔታ ውስጥ የገባሁበት ጊዜ ነበር። ልክ እንደ

ህፃን ልጅ የሆንኩ ይመስል ነበር፤ እያንዳንዱ የእንጀቴ ትንሽ እንቅስቃሴ ሰዎችን ሁሉ ያስደስታቸዋል።

ለነርስ ረዳቷ ምን እንደተናገርኳት በትክክል አላስታውስም፤ ያም ቢሆን ደስተኛ እንዳልነበርኩ እርግጠኛ ነኝ።

ክፍሉን ለቃ ወጣች። ጠያቂ በአጠገቤ ካልነበረባቸው በጣም ጥቂት ጊዜያቶች አንዱ ወቅት ነበር። ሙሉ ለሙሉ ብቻዬን በመሆኔ ደስተኛ ነበርኩ፤ ሰላምና ውስጣዊ ጸጥታ ተሰማኝ።

ነርሷ በሄደች በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ በሆዴ ውስጥ ፈሳሹ መድሃኒት መሥራት ጀመረ።

ፈነዳ! በሕይወቴ አንጀቴ እንደዚያ ሲንቀሳቀስ ለመጀመሪያ ጊዜ ነበር። የወጣው ቆሻሻ ሽታ አንገሸገሸኝ።

ድንገተኛ በሆነው ሁኔታዬ ውስጥ ሆኜ እንደ ምንም ተንጠራረሁና የመጥሪያ ደወሉን በጣቴ ነካሁ። ከሰከንዶች በኋላ ወጣቷ የነርስ ረዳት ሮጣ ወደ ክፍሌ መጣች።

በጣም አዝናለሁ፤ እንዲህ አደርጋለሁ ብዬ አላሰብኩም አልኩ። "በማጽዳት እረዳሻለሁ።" እርሷን መርዳት አለመቻሌን ከመገንዘቤ በፊት ካሉ ጥቂት ሰኮንዶች በፊት ነበር ቃላቶቹ አፈትልከው የወጡት ምስኪንነቴ፣ አቅም አልባነቴና እድለቢስነቴ ተሰማኝ።

እናም ማልቀስ ጀመርኩ።

"በጭራሽ፣ በጭራሽ በምንም ነገር አትጨነቅ፤ ስለአደረከው እኛ እኮ ደስተኞች ነን። ይሄ እኮ ጥሩ ነው፤ ምክንያቱም ይህ ማለት ከእንግዲህ ሆድህ እንደገና በአግባቡ ይሠራል ማለት ነው።"



በፍጹም ትህትና ውስጥ ሆኜ እንደተጋደምኩ ወጣቷ ምስኪን ሴት ሁሉን ነገር ስትቀያይር እመለከት ነበር። ክፍሉን ለማጽዳት የወሰደባት ጊዜ ምን አልባት ግማሽ ሰዓት ያህል ይሆናል፤ ሽታው ከክፍሉ ለቆ ለመሄድም አንድ ሰዓት ያህል ጠይቋል።

ሃፍረቴ ጥሎኝ ሊሄድ አልቻለም፤ አዕምሮዬ ግን የተለየ ነገር ሊነግረኝ እየፈለገ ነበር። ላለፉት አስራ ሁለት ቀናት የቀመስኩት ነገር ጥቂት ነው፤ እናም ይህ የመጀመሪያው እፎይታ ነበር። ይሁን እንጂ እኔ አስበው የነበረው ነገር ይህ ሁኔታ በሕይወቴ እጅግ አሳፋሪው ክስተት እንደሆነ ነበር።

ለእኔ አስከፊ፤ በጣም አሳፋሪና ምስኪንነቴን የገለጠ ሁኔታ እንደነበረ ነው የተሰማኝ። የሽንት መቀበያ የፕላስቲክ ቱቦ ተደርጎልኛል፣ ራሴን ማጽዳት አልችልም፤ መላጨት አልችልም። የራሴን ጸጉር እንኳን መታጠብ አልችልም። ጭንቅላቴን ወደ ውስጥ የሚያስገባ የተለየ መሣሪያ አምጥተው ውሃውን በጸጉሬ ላይ ይለቁታል፤ ከዚያም በሆነ ቱቦ ውስጥ አሳልፈው ውሃውን ወደ ቆሻሻ ማጠራቀሚያው ቆርቆሮ ያፈሱታል። ከዚህ በተጨማሪ ታላቅ መልካምነቱን ያሳየኝ ሰው ካሮል ቢንፊልድ ሲሆን ይህ ሰው በአልጋ ላይ በነበርኩበት አንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ወደ እኔ እየመጣ ጸጉሬን ያስተካክለኝ ነበር። ስድሳ ማይሎች ያህል እያቆራረጠ መጥቶ ያገለግለኝ የነበረው ይህ ሰው ገንዘብም ሆነ ሌላ ነገር ለመቀበል ፈቃደኛ አልነበረም።

ጓደኞቼ፣ ቤተሰቦቼና የህክምና ባለሙያዎች ለሰውነቴ የሚያስፈልገውን ሁሉ ለማሟላት መንገዶችን ሁሉ ይፈልጉ ነበር፤ እኔ ግን ሙሉ ለሙሉ ፈጽሞ ዋጋ እንደሌለኝ አስባለሁ። ያልተሰበረው የቀኝ እጄ በርካታ መድሃኒቶችን ወደ ደም ስሮቼ የሚያስተላልፉ መርፌዎች

ተሰክተውበት ስለነበር እነርሱን ለመደገፍ አነስተኛ ጣውላ ከእጄ ጋር በማሰራቸው ላጥፈው አልችልም ነበር::

መርፌዎቹ በሰውነቴ ሁሉ ላይ ተተክለዋል:: ከደረቴ ጀምሮ ቁልቁል እስከ እግሬ መዳፍ ጫፍ ድረስ ይዘልቃሉ:: በደረቴ ላይ አቋርጦ በቀጥታ ወደ ልቤ የሚያልፍ አንድ ዋንኛ የመድሃኒት ማስተላለፊያ ቱቦ ተከትለው መስመራቸውን ይዘው ተደርድረዋል:: አብዛኛዎቹ የደም ስሮቼ ከጥቅም ውጭ ሆነዋል:: ፈጽሞ መላወስ የማልችል በመሆኔ፤ የቁስል ፋሻዎችን ለመቀየር፤ ለማንቀሳቀስ ወይም ከአልጋው ላይ ለማንሳት የሆነ ስንስለት መጠቀም ያስፈልጋቸው ነበር::

ዶክተሮቹን ስጋት ውስጥ በከተተ ሁኔታ ክብደቴ በሚያስገርም ፍጥነት ያሽቆለቁል ነበር:: ምንም ነገር መመገብ የማልችል በመሆኑ ምግብ የሚሰጠኝ በፈሳሽ መልክ በመርፌ ነበር:: በሆስፒታሉ በቆየሁበት የአራት ወራት ጊዜ ውስጥ ሃያ ስባት ኪሎ ያህል ቀንሻለሁ:: ከአደጋው በፊት ዘጠና አምስት ኪሎ እመዝን ነበር አሁን ወደ ስልሣ ስምንት ኪሎ ወርጃለሁ:: ክብደቴን የሚለኩት የህፃናትን ክብደት ለመለካት በሚጠቀሙበት ዘዴ ማለትም በተንጠልጣይ ሚዛን ከአልጋዬ ላይ ከፍ አድርገው በማንሳት ብቻ ነበር:: የምወዳቸውን የምግብ አይነቶች በማዘጋጀት እንድመገብ ያነሳሱኛል፤ ነገር ግን ምንም ነገር ጣእም አይሰጠኝም:: ገና የምግብ ሽታ ያንገሸግሸኛል:: የመብላት አንዳች ፍላጎት አልነበረኝም:: ለመብላት መሞከሬ አልቀረም፤ በርግጥ ብዙ ተጣጥሬአለሁ፤ ይሁን እንጂ ከጥቂት ጉርሻዎች በላይ መቀጠል አልችልም::

የድብርቱ ሁኔታ የምግብ ፍላጎቴን እንዳጠፋው እገምታለሁ፤ ይሁን እንጂ ችግሩ እርሱ ለመሆኑ እርግጠኛ አይደለሁም:: ለመመገብ



በሞከርኩ ጊዜ ምንም ነገር ለማኘክ እንደማልችል ነው የማውቀው:: ያላመጥኩትን ለመዋጥ አልፈልግም ነበር::

ፒሲ ተብሎ የሚጠራ የህመም ስሜትን የሚያስታግስ የሞርፊን መድሃኒት በመርፌ ወደ ሰውነቴ እንዲገባ ተደርጓል:: ህመሙ እየጨመረ በሄደ ጊዜ ሁሉ መድሃኒት እንዲሰጠኝ የመጥሪያውን ደወል እጫናለሁ:: ያለማቋረጥ የህመም ማስታገሻ መድሃኒቶችን መውሰድ ያስፈልገኝ ነበር:: በመጀመሪያ ላይ በርካታ የህመም ማስታገሻ መድሃኒቶችን መውሰዴን ተቃውሜ ነበር፤ ዶክተሩ ግን ያንን በማድረጌ ገሰጸኝ:: ሰውነቴ በህመሙ ስቃይ ምክንያት ችግር ውስጥ የሚገባ በመሆኑ፤ ፈውሴ እንዳይከናወን የሚያግድ መሆኑን ነገረኝ::

የሌሊት እንቅልፍ እንዲኖረኝ በማሰብ ምሽት ላይ ተጨማሪ መድሃኒቶች ይሰጡኛል:: ይሁን እንጂ መተኛት አልችልም ነበር፤ ምክንያቱም ተጨማሪ መድሃኒቶቹ አይሠሩም ነበር:: የእንቅልፍ እንክብሎችን፣ የህመም ማስታገሻ መርፌዎችን ወይም ተጨማሪ መርፌዎችን ቢሰጡኝም በፍጹም እንዳንቀላፋ አያደርጉኝም::

ዘና ለማለት ወይም የህመም ስቃዩ እንደለቀቀኝ ለማሰብና ከስቃዩ ወደ እፎይታ ለመሸጋገር ምንም መንገድ አልነበረኝም::

እንዲህ ብዬ ብገልጸው ሁኔታውን ያስረዳ ይሆን? "እንዲህ ባለ ሁኔታ ውስጥ እንዳለህ አስብ፤ በአልጋ ላይ ተጋድመሃል፣ በክንዶችህ ውስጥ ብረቶች እንዲያልፉ ተደርገዋል፣ የኤሌክትሪክ ሽቦዎች በእግሮችህ ውስጥ አልፈዋል፤ በዚህ ሁሉ ውስጥ የተኛኸው በጀርባህ ነው:: መገላበጥ እንኳን አትችልም:: ትንሽ ለመንቀሳቀስ እንኳን ከአልጋህ በላይ የተጋደመውን ብረት ካልያዝክ በስተቀር መነቃነቅ አይሞከርም:: እንደ

ምንም ብለህ ከተንቀሳቀስክ እንኳን መላውን ሰውነትህን የሚያዳርስ የህመም ስቃይ ይከተላል። ሙሉ በሙሉ ከእንቅስቃሴ ውጭ ነህ።"

በአንድ አቅጣጫ ማለትም በጀርባዬ ብቻ ለረዥም ጊዜ በመተኛቴ ጀርባዬ በመላጡ፤ በመጨረሻው ሆስፒታሉ ያለማቋረጥ የሚንቀሳቀስ በውሃ የተሞላና የፕላስተክ ሽፋን ያለው አልጋ እንዲዘጋጅልኝ አደረገ። ያ የጀርባዬ መላላጥ እንዲቀር አደረገው።

ያንን ክፍል ለቅቄ የምወጣው በተሽከርካሪ አልጋ ላይ አስተኝተው ወደ ራጂ ክፍል በሚወስዱኝ ጊዜ ብቻ ነው። ያ ለእኔ ሁልጊዜም እንደ ትልቅ ጀብድ የሚቆጠር ነበር። በላዬ ላይ ከተሸከምኩት የብረታ ብረት መአት የተነሣ እንዴት አድርገው ራጂ እንደሚያነሱኝ ይቸገሩ ነበር። ሦስትና አራት የሚሆኑ ሰዎች ጨረር መከላከያ ልብሳቸውን ለብሰው የራጂ ማንሻ መሣሪያውን ስስ፣ ጠፍጣፋ መስተዋት በብረት በተሞሉት እጆቼና እግሮቼ ዙሪያ እያሽከረከሩ ማንሳት ያስፈልጋቸው ነበር። ምክንያቱም እንደኔ ባለ ሁኔታ ውስጥ ላሉ ሰዎች ታቅዶ የተሰራ የራጂ መሣሪያ አልነበረም።

ይህም ማለት አንዳንድ ቀን የራጂ ቴክኒሺያኑ ሃኪም በተፈለገው መንገድ አጥንቶቼ መስተካከላቸውን መመልከት በሚችልበት ሁኔታ የራጂ ምስሎችን ለማዘጋጀት ሁለትና ሦስት ሰዓታትን ይወስድ ነበር ማለት ነው። እንደኔ ላለ ሁኔታ በመደበኛውና በተለመደው ሁኔታ ውስጥ መሥራት የሚችሉበት እድል አልነበራቸውም። ወደ ራጂ ክፍል እያሽከረከረ ሊወስደኝ የሚመጣው ሰው ሁልጊዜም፤ "በኮሪደሩ ላይ ረዥሙን ጉዟችንን እስኪ እንጀምር" ይላል።

ሁሉም የሚሉት ይሄንኑ ነው፤ ምክንያቱም ምን ማለታቸው እንደሆነ ስለሚገባኝ ነው። ተሽከርካሪው አልጋ በጥንቃቄና በዝግታ



እየተገፋ ረዥም መንገድ የሚሄድ ስለነበር፤ ሁኔታዬን ለመርሣት በጣሪያው ላይ ያሉትን የካሬ ቅርጽ ያላቸውን ጌጠኛ ነጠብጣቦች እያገጣጠምኩ እጫወታለሁ። ያንን የጀመርኩት በመጀመሪያው ቀን ከቀዶ ጥገና ክፍል ተመልሼ ስወጣ ነበር። ምናልባትም የሌለውን ነገር እያየሁ ስቃዥ የነበር ይሆናል፤ ይሁን እንጂ ያ የቀዶ ጥገና ክፍል ገና አዲስና እኔም የመጀመሪያው ሰው እንደነበርኩ አስታውሣለሁ። ወደ ውስጥ ሲያስገቡኝ በከፍተኛ ድምጽ እቃትታለሁ እናም ላቆመው አልቻልኩም። ከዚያ ቀና ብዬ በጣሪያው ላይ ያሉትን ጌጠኛ ነጠብጣቦች ተመለከትኩ፤ አተኩሬ ሳያቸው በውል ለይቼ ላውቀው ያልቻልኩትን ቅርጽ እየሠሩ በአንድ አቅጣጫ የሚጓዙ መሰለኝ። በአዕምሮዬ እነኝህን ነጠብጣቦች በመጠቀም ስዕሎችና ቅርጾችን መስራት ጀመርኩ። ያንን እያደረኩ እያለም፤ በቃ ፈጽሞ ወደ እብደት እያመራሁ ነው እያልኩ አስባለሁ። ይሁን እንጂ እንደዚያ ማድረጌን ቀጠልኩ። በመጨረሻውም፤ እነኝህን ነጠብጣቦች የማገጣጠሙ ነገር ያስሁብትን ሁኔታ እንድረሳና ስጊዜውም ቢሆን የሚሰማኝን የህመም ስቃይ ለመርሣት የምጠቀምበት መንገድ ሆነ።

የየዕለቱ ትልቁ ስቃዬ የሚጀምረው ነርሷ ኤሌክትሪክ ሽቦዎች ወደ ቆዳዬ የሚገቡበትን ቀዳዳዎች ማጽዳት ስትጀምር ነው። በቅዱስ ሉቃስ ሆስፒታል ውስጥ በሃያ ስባተኛው ፎቅ ላይ በሚገኘው የድንገተኛ አደጋ ክፍል የሚያክሙን ነርሶች ሁሉ እነኛን ቀዳዳዎች እንዴት እንደሚያፀዱ ተለማምደዋል። ቆዳው ከገመዶቹ ጋር እንዳይጣበቅ ስለሚፈልጉ፤ ቆዳው ከኤሌክትሪክ ገመዶቹ ጋር የተያያዘባቸውን ስፍራዎች ሁሉ ይፈለቅቋቸዋል-ይህ አንዳንድ ጊዜ የሚፈጠር ነው። ከዚያ በኋላ ነርሶቹ ቆዳዬ እንዳይመረዝ ሃይድሮጅን ፒርኦክሳይድ የተባለ

መድሃኒት በቀዳዳዎቹ ውስጥ ይጨምራሉ:: ይህንን ከመቋቋም የበለጠ ስቃይ እንደሌለ አስባለሁ፤ ይህ የሚሆነው ደግሞ በየቀኑ ነው::

ያም ብቻ አልነበረም:: በየስድስት ሰዓቱ በቀን አራት ጊዜ፤ አለን ሪንች የተባለ መፍቻ በመጠቀም በመሣሪያው ላይ ያሉትን ብሎኖች ይጠመዝዛሉ:: ይህንን የሚያደርጉት የአጥንቶቹ ጫፎች እንዲስጠጡ በማድረግ በጎደለው አጥንት ሥፍራ ላይ በትክክል እንዲገጥሙ በማሰብ ነው::

ብሎኖቹ በሚጠመዘዙ ጊዜ የሚሰማኝን ስቃይ ለመግለጽ አዳጋች ነው:: ምንም እንኳን እያንዳንዱ ጥምዘዛ በጥንቃቄና በዝግታ የሚደረግ ቢሆንም ህመሙ ግን አያድርስ ነው:: ቀንም ይሁን ሌሊት የሚያመጣው ለውጥ የለም፤ በየስድስት ሰዓቱ አንድ ሰው ወደ ክፍሌ ይገባና ብሎኖቹን መጠምዘዝ ይጀምራል::

እንደ ቤተክርስቲያን መጋቢነቴ፤ በርካታ የሆስፒታል ክፍሎችን ጎብኝቻለሁ፤ ይህም የቀዶ ህክምና መስጫ ክፍሎችን ያጠቃልላል:: በብዙዎች ፊት ላይ ጭንቀትን ተመልክቻለሁ፤ ያለማቋረጥም ያለኝን ሃዘኔታ በፊት ገጽታዬ ገልጩላቸዋለሁ:: ይህም ቢሆን በየቀኑ እንዲህ ባለው ሁኔታ ውስጥ ማለፍ ያለውን ስቃይ ገምቼውም አላውቅም ነበር::

ምናልባትም የእኔን ችግር ለየት ባለ ሁኔታ አስከፊ ያደረገው፤ አለመተኛቴ ነበር:: ለአሥራ አንድ ወራት ከተኩል እንቅልፍ የሚባል ነገር አላውቅም፤ ቀናቱንና ሌሊቱን እንዲሁ አሳልፋቸዋለሁ:: በርከት ያለ መጠን ያለው ሞርፊን የተባለውን መድሃኒት ብወስድም ህመም ተለይቶኝ አያውቅም:: የመተኛ ጊዜዬ ነው ብለው በገመቱበት ሰዓት ነርሷ ሞርፊን ወይም ሌላ መድሃኒት ሦስትና አራት ጊዜ እንድትወጋኝ ተወሰነ:: በአልጋዬ ላይ እንደተጋደምኩ ምንም ያህል ራሴን ዘና እንዲል



ብነግረውም፤ ፈጽሞ መሆን አይችልም:: ህመሙን ለመጋፈጥ እሞክራለሁ፤ ከዚያ በኋላ በግልጽ እንደሚሆነው አዕምሮዬን እስተዋለሁ:: ከዚያ በኋላ ወደአዕምሮዬ በምመለስበት ቅጽበት የማውቀው ነገር ቢኖር መጠነ ሰፊ የሆነ የህመም ስቃይ ውስጥ መሆኔን ነው::

በመጨረሻው፤ የቤተሰቤ አባላትና የሆስፒታሉ ሠራተኞች ብቻዬን ተውኝ፤ ምክንያቱም ከዚያ በኋላ መሥራት የሚችል አካል እንደማይኖረኝ በማወቃቸው ነበር:: የጊዜን ነገር ማሰብ አቁሜአለሁ፤ ዘና ማለትም አልችልም፤ ምክንያቱም በከፍተኛ ውጥረት ውስጥ ነበርኩ:: ለመንቀሳቀስ ትንሽ ጥረት ባደርግ፤ በውስጤ የተቀበረው የኤሌክትሪክ ገመድ ከመገናኛው ላይ ቆዳዬን ይስነጥቀዋል:: እኔ እንቀሳቀሳለሁ፤ ገመዶቹ ግን አይችሉም:: በጥቂቱ እንኳን ነቅነቅ ብል በመላው አካል ላይ የህመም ስቃይ የሚያስከትል ሁኔታ ይፈጠራል::

ከሆነ ጊዜ በኋላ፤ በዚያ ሁኔታ ውስጥ መኖርን ተማርኩ፤ ልላመደው ግን በፍጹም አልቻልኩም::

ምንም እንኳን በአካል አይን በአይን ባንተያይም፤ ኤልዛሮቭ ፍሬም የተባለው መሣሪያ መጀመሪያ ሲፈለሰፍ ለታቀደለት ዓላማ መዋሉን ያወቅኩት ክርስቲ በተባለች ወጣት ላይ ነው:: መሣሪያው ከመጀመሪያውም የተሠራው ገና ከእናታቸው ማህጸን ሲወጡ የአጥንት ችግር ላለባቸው ሰዎች ነው:: ይሁን እንጂ ኤልዛሮቭ ፍሬም፣ አጥንት እድገቱን ከማቆሙ በፊት በእግር ላይ አይገጠምም:: በተለይም የአጥንት እድገት ፈጣን በሆነባቸው የልጅነት ዓመታት መሣሪያውን መጠቀም

አይመከርም፤ በመሆኑም ዶክተሮች ትክክለኛውን ጊዜ በጥንቃቄ ይመርጣሉ::

ወጣቷ ልጃገረድ ክርስቲ እኔ ከተኛሁበት ክፍል አጠገብ ነበር የተኛችው:: የተወለደችው አንደኛው እግሯ ከሌላኛው አጥሮ ነው:: አጥንቶቿ እድገታቸውን ካቆሙ በኋላ፤ ሁለቱም እግሮቿ እኩል መጠን እንዲኖራቸው በኤልዛሮቭ ፍሬም ህክምና መጠቀም መረጠች::

ክርስቲ በዚህ ቀዶ ህክምና ስመታከም ራሷ የመረጠች በመሆኑ ስለሚያስከትለው ስቃይና ህክምናውን ለመጨረስ ስለሚወስደው የጊዜ መጠን የተወሰነ እውቀት ነበራት:: ለወራቶች ያህል አስፈላጊው ምክር ሲሰጣት የቆየ ሲሆን፤ ቤተሰቦቿም ቁስሉን እንዴት መንከባከብ እንደሚገባቸው እንዲያውቁ ተደርገዋል:: ህክምናው ምን ያህል ጊዜ እንደሚወስድ እንዲያውቁና በእነዚህ ጊዜያቶች ውስጥ እርሷን ለመንከባከብ ቁርጠኛ ፈቃደኝነት እንዲያደርጉ ተነግሯቸዋል::

በእኔና በክርስቲ መካከል ያለው ልዩነት፤ ቢያንስ ቢያንስ እርሷ ስለመሣሪያው ማንም ሰው ሊያውቅ የሚገባውን ያህል እንድታውቅና ስለምትገባበት ሁኔታ ግንዛቤ እንዲኖራት ተደርጓል:: እኔ ግን ከቀዶ ጥገና ህክምናው ስነቃ መሣሪያው በሰውነቴ ላይ ተገጥሞ ነው ያገኘሁት:: በድብርት ውስጥ በገባሁበት ጊዜ ይሄ ጉዳይ ችግሩን ይበልጥ አባባሰብኝ:: ምንም እንኳን የኤልዛሮቭ ፍሬሙን በእግሬ ላይ ያደረጉልኝ እግሬን ለማትረፍ ቢሆንም፤ የስቃዬ ሁሉ ትልቁ ምክንያት እርሱ ብቻ እንደነበረ አስባለሁ::

ቀላል ቢሆንም እንኳን ሌላ ችግር ደግሞ ተከሰተ:: ያሉን የተሰያዩ ዶክተሮች ቢሆኑም፤ ብሎኖቹን ስመጠምዘዝ ወደ እኔም ይሁን ወደ ክርስቲ የሚመጡት የተወሰኑ ሰዎች ናቸው:: አንዳንድ ጊዜ



መፍቻዎቹ ያለ ስፍራቸው ይቀመጡና ይጠፋሉ፤ በመሆኑም ተረኛው ሰው በእኔ ክፍል ውስጥ ባጣቸው ጊዜ የእርሷን መፍቻዎች ለመዋስ ወደ ክፍሏ ይሮጣል:: ወይም መጥተው የእኔን ይዋሳሉ:: እንደአጋጣሚ ሆኖ የአንዳችን መፍቻ የሌላችንን ብሎን ሊጠመዝዝ የሚችል ስለነበር፤ አንዳችን የአንዳችንን መፍቻ መዋዋስ እንችል ነበር::

በዚህ ምክንያት ነበር ለመጀመሪያ ጊዜ ስለ ክርስቲ ያወኩት- በመፍቻ ውስት ምክንያት:: ፊት ለፊት ተያይተን አናውቅም፤ አንዳችን የሌላውን ዶክተር ማየት ግን እንችል ነበር:: ይህና ሌሎች ተመሣሣይነት ያላቸው ችግሮቻችን በመካከላችን ግንኙነት እንዲፈጠር አደረጉ::

ክርስቲና እኔ የምንጋራው ሌላ ነገርም ነበረን - የህመም ስቃይ:: ብዙ ጊዜ ስትጮህ እሰማታለሁ:: ታለቅስ ነበር ማለቴ ሳይሆን ትጮህ ነበር ማለቴ ነው:: አንዳንድ ጊዜ ዝቅ ባለ ድምጽ ታቃስታለች:: ምናልባትም እርሷም የእኔን የስቃይ ድምጽ ከእኔ ክፍል ውስጥ ትሰማ ይሆናል:: እኔ እንደርሷ አልጮህም፤ ምክንያቱም በተፈጥሮዬ እንደዚያ ማድረግ አልችልም::

ከነርሶቹ አንዷቱ ልክ እንደርሷ ጩኸቴን እንድለቀው መከራኛ ለች:: ትክክል ልትሆን ብትችልም እንኳን ቢያንስ ቢያንስ በነቃ አዕምሮዬ ይህንን አድርጌው አላውቅም::

አዕምሮዬን መቆጣጠር እችል በነበረበት ጊዜ ሁሉ አልጮህም:: በስቃያቸው ምክንያት ሰዎች ሲጮሁ ለምቻለሁ፤ ጩኸታቸው ደግሞ እጅጉን ይረብሸኛል:: በተጨማሪም ልቤን መጠበቅና ስሜቴን መቆጣጠርን ተምሬአለሁ:: በዚያ ጊዜ እነኛ የጣር ድምጾች፣ ማቃሰቶችና ጩኸቶች መልካም እንዳልነበሩ አምን ነበር:: እጮህ የነበረባቸው ብቸኛ

ጊዜያት አንድም አዕምሮን በሳትኩ ጊዜ አለዚያም ከባድ መድኃኒቶች በሚሰጡኝ ጊዜ ነው። እጮህ እንደነበረ ያውቅኩትም ሰዎች ከነገሩኝ በኋላ ነበር።

ክርስቲና እኔ ምንም እንኳን ለአሥራ ሁለት ሳምንታት አጠገብ ለአጠገብ ያሉ ክፍሎች ውስጥ ብንተኛም ተገናኝተን አናውቅም። ደብዳቤዎችን በመላላክ ግንኙነት ጀመርን፤ ነርሶቹም ልክ እንደ ፖስተኞች ያገለግሉን ነበር።

ክርስቲን ላጽናናት ሞከርኩ። ታሪኳን ትነግረኛለች፤ ስለደረሰብኝ አደጋም በጣም እንዳዘነች ትጽፍልኛለች። እርሷም እንደ እኔው አማኝ ነበረች። ግንኙነታችን መስመሩን የጠበቀም ነበር።

ለራሴ ሃዘን በሚሰማኝ በጣም አስከፊ ጊዜያት፤ ክርስቲ እንደገና ጤነኛ ሴት ትሆናለች፤ እኔ ግን ዳግመኛ ጤነኛ አልሆንም እያልኩ አስባለሁ። ማንኛውም ወጣት ሊያደርግ የሚችለውን ማንኛውንም ጨዋታ መጫወትና መሮጥ ትችላለች። በዚያ ጊዜ እንኳን እኔ እንደገና መሮጥ እንደማልችል አውቃለሁ።

ስለራሴ የማዝንባቸው በርካታ ጊዜያት ነበሩ። እርሷ ስቃይ እንደሚያስከትል አውቃና ምርጫዋ ሆኖ ነው፤ እኔ ግን ምንም አይነት ማስጠንቃቂያ አልተሰጠኝም ምርጫም አልነበረኝ እያልኩ ራሴን አስታውሰዋለሁ። እርሷ ወደ ምን አይነት ሁኔታ ውስጥ እንደምትገባ አውቃዋለች፤ እኔ ግን ምንም ግንዛቤ አልነበረኝም። እርሷ በቀሪ የሕይወት ዘመኗ መልካም ውጤት የሚያስከትል ነገር እያደረገች ነው፤ እኔ ግን ሕይወቴን ለማትረፍ ብቻ የማደርገው ነገር ነው። አዎን እጅግ ብዙ ጊዜ ለራሴ አዝን ነበር።



ይሁን እንጂ ሁልጊዜም፤ ወደ አንድ ነገር ተመልሼ እመጣለሁ፤ እግዚአብሔር በሕይወት እንድኖር መርጧል። ከፍተኛ በሆነ የድብርትና ሃዘን ውስጥ በገባሁበት ጊዜ እንኳን ይህንን አልረሳውም።

እኔና ክርስቲ እንካፈል የነበረው ተመሳሳይ ስቃይ ነበር። ይህንን ብቻም አይደለም፤ እጅግ አስከፊ በሆነው የስቃያችን ጊዜ እንኳን ህያው የሆነ አምላካችን ከእኛ ጋር እንደሆነ ያለንን እምነት እንጋራ ነበር። እርሷ እኔ ካለሁበት ክፍሌ አጠገብ በመሆኗ፤ ስለእኔ ሁኔታ የማውቀው እኔ ብቻ አይደለሁም፤ ምን እንደሚሰማኝ የሚያውቅ ቢያንስ ሌላ አንድ ሰው አለ፤ እያልኩ አስባለሁ።

በዚያ ጊዜ ነው ከተገለሉት ወገኖች መካከል እንደሆንኩ ማሰብ የጀመርኩት። ከዚያ ሆስፒታል ከወጣሁ በኋላ እንኳን ከሌሎች ጋር መቀላቀልን የማይፈልጉ ጥቂት ሆነው ህብረት ከሚያደርጉ ቡድኖች ጋር ተገናኝቻለሁ። ስቃይ ማለት ምን እንደሆነ ስለማውቅ ህመማቸው ይሰማኛል-ልክ ክርስቲ የእኔን፣ እኔም የክርስቲን የህመም ስቃይ እናውቅ እንደነበረው ማለት ነው።

ስቃዩን መቋቋም ብቻ አይደለም፤ ዶክተሮች ከዚያ በኋላ ልታደርጋቸው አትችልም ያሏቸውን አንዳንድ ነገሮች ማድረግ ጀመርኩ። እንደገና መራመድን ተማርኩ። በራሴ እግሮች መቆም ቻልኩ፤ አንዱን እግሬን ከሌላኛው በማስቀደም መንቀሳቀስ ጀመርኩ።

በተሰበረው የቀኝ እግር ጉልበቴና ከግራ እግሬም ላይ ከጠፋው አጥንት የተነሣ (ምንም እንኳን የተተካልኝ አጥንት በመለጠጥ ክፍት የሆነውን ስፍራ ቢደፍነውም እንኳን) እንደገና መራመድ እንደማልችል

አስጠንቅቀውኝ ነበር:: ለመራመድ ብፈልግ ሰውነትን ደግፎ የሚይዝ መሣሪያ መጠቀም እንደሚገባኝ ነግረውኛል:: በዚህ ሙከራዬ ከአንድ ጊዜ በላይ የግራ እግሬን ለማጣት ተቃርቤ ነበር፤ ይሁን እንጂ በደረሱብኝ በሁሉም ችግሮች ውስጥ በእግዚአብሔር እርዳታ ለማለፍ ችያለሁ::

የተጎዱትን የሰውነቴን አካላት ለማፍታታት የተደረገው ህክምና በእጄ ላይ የተደረገው ዋናው ቀዶ ጥገና ከተደረገ ከአራት ሳምንታት በኋላ ሲሆን፤ በእግሬ ላይ የተደረገው ደግሞ ከዚያ በኋላ ሁለት ሳምንት ያህል ቆይቶ ነበር::

በዚያው ጊዜ ውስጥ፣ በተለየ አልጋ ላይ እንድተኛ ተደረገ! በዚህ አልጋ ላይ ሰውነቴ ጠበቅ ተደርጎ የሚታሰር ሲሆን፤ ከትራስጌው ከፍ እየተደረገ ሲሄድ እግሬ መሬት ይነካል፤ በመሆኑም በዚህ ሁኔታ መቆም እችል ነበር:: ሁለት የህክምና ሰዎች በወገቤ ዙሪያ ሁለት ቀበቶዎች አስታጥቀው በሁለት አቅጣጫዎች ይራመዳሉ:: ሁለቱም እግሮቼ ያለጥቅም በመቆየታቸው ጡንቻዎቼ በጣም ተዳክመው ነበር፤ በመሆኑም ሃኪሞቹ የመጀመሪያዎቹን እርምጃዎች እንድራመድ ይረዱኛል:: እንደገና መቆም ለመለማመድ ቀናት ወስደውብኛል፤ ስለዚህም የራሴን የእግር ጡንቻዎች ለመጠቀም ችያለሁ:: የሰውነት ሚዛኔን ለመጠበቅ አስቸግሮኝም ነበር፤ ምክንያቱም የብረቶቹ መጠን በጎን አቅጣጫ የሰፋ በመሆኑ ነው:: እንድቆም በሚደረግበት ጊዜ ሁሉ በማይታመን ሁኔታ ያስመልሰኝ ነበር:: በትክክለኛው እቋም ላይ ሆኜ የመጀመሪያዎቹን እርምጃዎች ለመራመድ ቀናት አስቆጥሬአለሁ::

ከሆስፒታሉ እስከወጣሁበት ጊዜ ድረስ በትክክል መራመድ አልተለማመድኩም ነበር:: በየዕለቱ የሰውነት አካል ህክምና ባለሙያ



እየመጣ ይረዳኛል:: ከጥቂት እርምጃዎች በላይ በራሴ መራመድን ለመለማመድ ስድስት ወራት ወስዶብኛል::

ዶክተሬ አደጋው ከደረሰብኝ ከአሥራ አንድ ወር ተኩል በኋላ ኢልዛሮቭ የተባለውን መሳሪያ ከሰውነቴ ላይ አወጣልኝ:: ከዚያ በኋላ በመራመጃ መርጃ መሣሪያ በመጨረሻውም ምርኩዝ መጠቀም አስፈልጎኝ ነበር:: ከአደጋው በኋላ እስከ አንድ ዓመት ከመንፈቅ ድረስ ያለ እግር መደገፊያ ብረትና ያለከዘራ መራመድ አልችልም ነበር::

አደጋው የደረሰብኝ በጥር ወር 1989 ነበር:: በክንዴ ላይ የነበሩትን ውጫዊ ብረቶች ያነሱልኝ በግንቦት ወር ላይ ነው፤ ይሁን እንጂ በክንዴ የመጀመሪያ አጥንቶች ላይ በውስጥ በኩል ብረቶች አድርገውልኝ ነበር:: እነኝህ ብረቶች ለብዙ ወራት በዚያው እንዲቆዩ ተደርገዋል::

በህዳር ወር መጨረሻ አካባቢ፤ የማፅኛ ብረቶቹን ከእግሮቼ ላይ አወጧቸው፤ ይሁን እንጂ ያ የመጨረሻው አልነበረም:: ከዚያ በኋላ ከጀሶ በተሰራ የአጥንት ማፅኛ ውስጥ ለረዥም ጊዜ ቆይቻለሁ፤ በዚያ ጊዜ ውስጥም ዝርግ ብረቶች በእግሬ ውስጥ እንዲገቡ ተደርጎ ነበር:: እነዚህ ብረቶችም ለዘጠኝ ዓመታት በእግሬ ውስጥ ቆይተዋል:: በዚያው እንዲተውአቸው ፈቃዴ ነበር፤ ይሁን እንጂ እንደሚያወጧቸው ነግረውኛል:: ዶክተሩ፤ እድሜዬ እየገፋ ሲሄድ እነዚህ ለአጥንቱ ጥንካሬ ሲባል የገቡ ብረቶች አጥንቱን ሊሰብሩት እንደሚችሉ ገልጾልኛል:: አጥንቶቻችን ጠንካሮች የሚሆኑትና በዚህ ጥንካሬያቸውም የሚቆዩት ስንንቀሳቀስባቸውና ስንጠቀምባቸው ብቻ መሆኑን ተረድቻለሁ::

የአጥንት ማፅኛ ብረቶች በውስጤ በተቀበሩባቸው በእነዚያ ዓመታት ውስጥ በአየር ትራንስፖርት መጠቀም ከነበረብኝ፣ ብረት ነክ

ነገሮችን ከሚጠቁመው መሣሪያ መራቅ ነበረብኝ:: ሌሎች መንገደኞች ብረት ነክ ነገሮችን እንዳልያዙ ለማስፈተሽ በሚያልፉበት መሣሪያው ባለበት መግቢያ አላልፍም፤ ይልቁንም ወደ ፍተሻ ሠራተኛው ጠጋ ብዬ፤ በቤትህ ውስጥ ካሉት የመመገቢያ ማንኪያዎች፣ ቢላዋዎችና ሹካዎች ይልቅ የበለጠ ክብደት ያለው ብረት በውስጤ ተሸክሜአለሁ ማለት ይጠበቅብኝ ነበር::

በመሣሪያው ዳበስ ያደርጉኝና "እውነት ነው" ብለው ፈገግ ይላሉ::

ልጆቼ "በሮቦት የሚንቀሳቀሰው ሰባኪ" እያሉ በመጥራት ኩራታቸውን ይገልጹልኛል: ይህን ስም የወሰዱት በፊልም ውስጥ ከሚታየው "ሮቦቱ ፓሊስ" ከተሰኘው ገጸ ባህሪ ነው:: ከአንድ አስጨናቂ ሁኔታን ከፈጠረ ክስተት በኋላ፤ ሃኪሞች ከፍተኛ ቴክኖሎጂ በመጠቀም በብረት ጥፍጥፎች ከጠጋገኑት በኋላ ፖሊሱ ወንጀልን ለመከላከል እንደገና ወደ ሥራው እንዲመለስ አስችለውታል::

ምንም እንኳን እነዚህ ብረቶች፣ የኤሌክትሪክ ገመዶችና ቆርቆሮዎች ዘመን ያለፈባቸው ቢመስሉም፤ የሚፈለገውን ውጤት አስገኝተው ነበር:: ሰዎች በሰውነቴ ላይ ተተክለው በሚያዩዋቸው ጊዜ ይደነግጡ ነበር:: ስንቀሳቀስ ያዩኝ እነዚያው ሰዎች አሁን ደግሞ በአግራሞት ይደነቃሉ:: ይሁን እንጂ በዚህ መጠነኛ የመጠገን ሁኔታ ውስጥ ብገባም፤ አሁንም ገና እንደገና በመስተካከል ሂደት ውስጥ እያለፍኩ ነው::



# 9

# ማስቂያ የሌለው ማስተካከያ

"ወዳጅ በዘመኑ ሁሉ ይወዳል፣ ወንድምም ስለመከራ ይወለዳል"

ምሳ 17፥17

ከአደጋው በኋላ ሰዎች በተለያየ መንገድ እንዴት እርዳታን እንዳደረጉልኝ የሚያስገርም ነው:: ከአደጋው በኋላ በነበሩት የመጀመሪያዎቹ አምስት ቀናት በርካታ ጓደኞቼ የሳውዝ ፓርክ ቤተክርስቲያን አባላት ጎብኝተውኛል:: ከእነዚሁ ሰዎች አብዛኞቹ በዴቪድ ጀንቲሊስ አስተባባሪነት ከተደረገው የሌሊት የምልጃ ጸሎት በኋላ እንደገና አይተውኛል:: እያንዳንዷን ጥቃቅን የማገገም ሁኔታዬን በተመለከቱ ቁጥር ይደሰቱ ነበር:: ወደዚያ ከባድ ድብርት ውስጥ የገባሁትም እያንዳንዱ የማገገም ሂደት እጅግ ዝግ ብሎ ይከናወን ስለነበር እንደሆነ አስተውያለሁ:: ከቀዶ ጥገና ክፍሉ ውስጥ ከወጣሁ በኋላ በሆስፒታሉ ውስጥ ለአንድ መቶ አምስት ቀናት ቆይቻለሁ:: ያን ያህል ጊዜ እኔ በነበርኩበት ሁኔታ ውስጥ የሚቆይ ሰው በቀላሉ በድብርት ውስጥ እንደሚገባ እገምታለሁ::

ማገገም በጀመርኩባቸው ወራት፤ እኔ እንደገና ጠቃሚ ሰው እንደሆንኩ እንዲሰማኝ ቤተክርስቲያን ተግታ እየሠራች ነበር:: ህጻናት ይጎበኙኝ ዘንድ ወደ ሆስፒታሉ ያመጧቸውም ነበር:: አንዳንድ ጊዜ ኮሚቴዎች እኔ በተኛሁበት የሆስፒታል ክፍል ውስጥ ስብሰባቸውን

ያደርጋሉ፤ ይህ የእኔ ውሳኔ ዋጋ ያሰው መሆኑ እንዲሰማኝ የተደረገ ነበር። ምንም መናገር ወይም ማድረግ እንደማልችል ያውቃሉ፤ ይሁን እንጂ እኔን ለማጽናናትና ለማነቃቃት የነበራቸው መንገድ ያ እንደሆነ በመገመታቸው ነው። እኔ ዋጋ ያለኝና የምጠቅም ሰው መሆኔን እንዳስብ ማድረግ የሚችሉትን ነገር ሁሉ አድርገዋል።

ይሁን እንጂ አብዛኛውን ጊዜ እኔ በድብርት ውስጥ ነበርኩ፤ ስለራሴም እጅግ አዝናለሁ። የነበረኝ ታላቅ መሻት ወደ መንግስተ ሰማይ መመለስ ነበር።

ከድብርቱ ሌላ፤ ሌላ ችግርም ነበረኝ። ማንም ሰው ለእኔ ምንም ነገር እንዲያደርግልኝ አልፈልግም። ያ ደግሞ ባህሪዬ ነበር።

አንድ ጊዜ ጄይ ቢ.ፐርኪንስ የተባሉ በእረፍት ላይ ያሉ አገልጋይ ሊጎበኙኝ መጡ። ጡረታ ከመውጣታቸው በፊት በደቡብ ቴክሳስ የሚገኙትን እብያተ ክርስቲያናት በመጋቢነት አገልግለዋል፤ በእኔ አገልግሎት ውስጥም ከፍተኛ ኃይል ያላቸው አባትና በጎ ተጽእኖም ያሳደሩ ሰው ናቸው። የሳውዝ ፓርክ ቤተክርስቲያንም፣ እኔ አደጋ በደረሰብኝ ወቅት በጊዜያዊነት በመቅጠር ለአገልግሎት አሰማርታቸው ነበር።

ጄይ በእምነት ይጎበኙኝ ነበር። ይህም ማለት በእያንዳንዱ ጉብኝት ከአርባ ማይሎች የበለጠ መኪናቸውን ያሽከርክሩ ነበር ማለት ነው። አንዳንድ ጊዜ በሳምንት ሁለት ወይም ሦስት ጊዜ ሊያዩኝ ይመጡ ነበር። ከእርሳቸው ጋር እኩያ አልነበርኩም፤ ይሁን እንጂ ሁልጊዜም ፈገግ እያልኩ እሸኛቸዋለሁ። በተኛሁበት አልጋ ላይ ሆኜ ስለራሴ ሃዘኔታ ይሰማኝ ነበር።



በፍቅር ይናገሩኛል፤ ሁልጊዜም ሊያጽናኑኝ የሚችሉ ቃላትን ይመርጣሉ፤ ምንም እንኳን ችግሩ ከእርሳቸው ባይሆንም፤ የሚናገሩኝ ነገር ሁሉ ምንም አይጠቅመኝም። ማንም ሰው ሊረዳኝ አይችልም ነበር። እኔ አስቸጋሪ ሰው ሆኜ ስለነበር ብቻ አልነበረም፤ በኋላ ላይ እንደተረዳሁት እኔ ሁሉንም ሰው እንደ አስቸጋሪ እቆጥር ስለነበረም ጭምር ነው።

የሚጎበኙኝ ሰዎች ሊረዱኝ ይሞክራሉ፤ አብዛኞቹ ደግም መርዳት በሚችሉበት አቅም ሁሉ ነበር ሊረዱኝ የሚፈልጉት። “የምታነበውን መጽሄት ላምጣልህን?” ሲል አንዱ ይጠይቀኛል። “ከወተት የተሠራ ጄላቲ ትወዳለህን? በእንግዳ መቀበያው ውስጥ ጣፋጭ ኬክ አለ። ወይስ ሃምበርገር ላምጣልህ ይሆን? ...”

“መጽሐፍ ቅዱስ ወይም ሌላ መጽሐፍ እንዳነብልህ ትፈልጋለህ?”

“ትንሽ ላንሸራሽርህ እችላለሁ?”

መልሴ ሁልጊዜም የማይለወጥ ነበር፤ “አመሰግናለሁ አልፈልግም” የሚል ነው።

ነገሮቹ ሳያስፈልጉኝ ቀርተው እንዳልነበር አስባለሁ፤ ነገር ግን መግባባትን ወይም መተባበርን አልፈልግም ነበር። ይሁን እንጂ ሁሉንም ሰው አሉታዊ በሆነ መንገድ እመለከት እንደነበር አይሰማኝም ነበር። ማንንም ማየት አልፈልግም። ከማንም ጋር መነጋገር አልፈልግም። እኔ እፈልግ የነበረው የህመም ስቃዩ እንዲወገድልኝና ቅርጹን ያጣው አካሌ እንደገና እንዲስተካከል ነበር። በምድር ላይ መቆየት ካለብኝ፤ እንዲሻለኝና እንደገና ወደ ተለመደው ሕይወት መመለስ እፈልጋለሁ።

ጄይ አዘውትረው ይጎበኙኝ ስለነበር፣ ከጎደኞቼና ከቤተሰቦቼም ጋር እንዴት እንደተራራቅኩ አስተዋሉ:: አንድ ቀን የሳውዝ ፓርክ ቤተክርስቲያን ዲያቆን የሆነ ሰው ሊጎበኘኝ ሲመጣ አጠገቤ ተቀምጠው ነበር:: ከአስር ደቂቃዎች በኋላ ሰውዬው ከመቀመጫው ተነስቶ፣ “መጥቼ ሁኔታህን መመልከት ስለፈለግኩ ነው በዚህ ያለሁት” አለ:: ቀጠል አድርጎም፣ “ከመሄዴ በፊት ላመጣልህ የሚያስፈልግህ ነገር ይኖራል?” ሲል የተለመደ ጥያቄ ጠየቀኝ::

“አመሰግናለሁ፣ አልፈልግም:: ጥያቄህን ተቀብያለሁ ግን ... ”

“እሽ የምትበላው ነገርስ ላምጣልህ፣ ታች ወርጄ ... ”

“በእውነት አልፈልግም:: ስለመጣህ አመስግናለሁ” ደህና ሁን ብሎ ተሰናበተኝና ሄደ::

ዲያቆኑ ከሄደ በኋላ ጄይ በጸጥታ ረዘም ላላ ጊዜ በመስኮቱ ወደ ውጭ አሻግረው ሲመለከቱ ቆዩ:: በኋላም ወደ አልጋዬ እየተራመዱ መጥተው ወደ ፊቴ ጎንበስ አሉና፣ “እያደረግክ ስላለው ነገር ልታውቅ የሚያስፈልግህ ይመስለኛል” አሉ::

“ምን አሉ ጌታዬ? ” አልኩ ማንም ሰው ለማንያ አመት እድሜ ላላቸው ሰባኪ የሚሰጠውን አክብሮት እየሰጠሁ::

“እያደረግክ ያለውን ነገር ልታውቅ ያስፈልግሃል” ሲሉ ደገሙልኝ::

“ጥሩ ነገር እያደረግክ አይደለም”

“ምን እያሉ እንደሆነ አልተረዳሁም... ”



“ከዚያም በላይ ደግሞ” አሉና አሻግሬ ማየት እስከማልችል ድረስ ወደ ፊቴ ተጠግተው፣ “ከዚህም በላይ ደግሞ፣ ድርጊትህ ሁሉ ልክ እንደቀደሙት ፈሪሣውያን ነው” አሉኝ::

“ስለምን እንደሚያወሩ አላውቅም”

“እነዚህ ሰዎች እኮ ስለ አንተ ግድ የሚላቸው ናቸው፣ አንተ ግን ምን ያህል ክልባቸው እንደሚወዱህ ልትገምት አልቻልክም”

“እንደሚወዱኝ አውቃለሁ”

“እርግጠኛ ነህ? እንደዚያ ከሆነ ይህንን እደምታውቅ እንዲያውቁ ለማድረግ ጥሩ ሥራ አልሠራህም:: በትክክለኛው ሁኔታ አይደለም የምታስተናግዳቸው:: እነርሱ እኮ ሊፈውሱህ አይችሉም:: ሊፈውሱህ ቢችሉ ኖሮ ፈጥነው ያደርጉት ነበር:: በአንተ ስፍራ መሆን የሚችሉ ቢሆን አብዛኞቹ ያደርጉት ነበር:: ምንም ነገር እንዲያደርጉልህ ብትጠይቃቸው ምንም ነገር ቢሆን ያለ አንዳች ማወላወል ያደርጉታል::”

“ያንን አውቃለሁ ... ”

“ነገር ግን ምንም ነገር እንዲያደርጉልህ አትፈቅድላቸውም:: ”

“ምንም ነገር እንዲያደርጉልኝ አልፈልግም” ምንም ነገር ሳልደብቅ በቻልኩት መጠን ሁሉ ድምጼን ከፍ አድርጌ፣ “እውነቱን ማወቅ ከፈለጉ እዚህ እንዲመጡ እንኳን አልፈልግም:: ሳይመጡ ቢቀሩ ነው የምመርጠው:: ደስ የማይል ነገር እየተናገርኩ እንደሆነ አውቃሁ:: ሥራቸውን ትተው እንደሚመጡ አውቃለሁ:: ያንን አውቃለሁ:: ማንም ሰው ወደዚህ እየመጣ እንደዚያ እንዲያየኝ ለምን እፈልጋለሁ? አስቀያሚ አስተያየት ነው:: እኔ የምጠቅም ሰው አይደለሁም:: ”

"እንግዲያስ ጥሩህ አይደለም"

በተናገሯቸው ቃላት እጅግ ደንግጬ ቀና አልኩ::

"ሌሎች ሰዎችን ለማገልገል የሕይወትህን መልካም ጊዜዎች ተጠቅመሃል:: ጉድለታቸውን ለመሙላት፣ በችግራቸው ጊዜ ልትረዳቸው፣ በአደጋ ጊዜ ..."

"አዎ ... እሞክር ነበር ..."

"እና አሁን ደግሞ እነዚያው ሰዎች አንተ ታደርግላቸው የነበረውን ነገር ሊያደርጉልህ ሲፈልጉ አንተ ግን ያልተገባ ሥራ ትሠራለህ"፣ የተናገሩትን ቀጣዮን ቃል በፍጹም አልረሳውም::

"ዶን፤ ሊያቀርቡልህ የሚችሉት ያላቸው ብቸኛው ነገር ያ ነው፤ አንተ ያንን ስጦታ ከእጃቸው ቀምተሃል"

ለመረታት ዝግጁ አልነበርኩም፤ በመቃወም ገለጻዬን ለመቀጠል ሞከርኩ:: እንደገና አቋርጠውኝ ጣልቃ ገቡ::

"እንዲያገለግሉህ አልፈቀድክላቸውም:: ሊያደርጉት የሚፈልጉት ያንን ነበር:: እንዴት ይህንን አትረዳም?"

ለተናገሩት ንግግር እጅግም ቦታ አልሰጠሁትም ነገር ግን፤ "አደንቃቸዋለሁ፤ ሊረዱኝ እንደሚፈልጉም አውቃለሁ:: እያደረጉ ያሉት ነገር ሁሉ ጥሩ ነው ... ግን ..."

"ግን ... ምንም የለም! ያላቸውን ፍቅር መግለጽ እንዳይችሉ መንገድ በመዝጋት እያጭበረበርካቸው ነው::"



የተናገሩት ቃል አስደነበረኝ:: እኔ ራስ ወዳድ ላለመሆንና በእነርሱ ላይ ምንም ጫና እንዳልጭንና ችግር እንዳልፈጥር እየሞከርኩ ነበር:: ከዚያ በኋላ የተናገሯቸው ቃላት አዕምሮዬን እየሰረሰሩ መግባት ጀመሩ:: እውነታው ራስ ወዳድ መሆኔን የሚያሳይ ነበር:: በዚያ ውስጥ ደግሞ የትእቢት ነገርም ነበረበት በጊዜው ልቀበለው ፍቃደኛ ባልሆንም:: ለሌሎች እንዴት ቸርነት አደርግ እንደነበር አውቃለሁ፤ ነገር ግን ኩራት የሌሎችን ቸርነት እንዳልቀበል አድርጎኝ ነበር::

ጂይ መልስ እንድሰጥ የእፎይታ ጊዜ አልሰጡኝም:: ለነገሩ ለመስማት እስረኛ የሆንኩ ሰው ነኝ:: ራሴን ከሌሎች ምን ያህል እንዳገለልኩ አምኜ እንድቀበል እስከገደድ ድረስ ስለራሴ ብዙ ነገር ተናገሩኝ:: እንደዚያም ሆኖ እንኳን ስመሟገት መፈለጌ አልቀረም፤ ጂይ ግን ስህተቴን አምኜ እንድቀበል ተጫኑኝ::

"እንዲረዱህ እንድትፈቅድላቸው እፈልጋለሁ:: እየሰማኸኝ ነው? እንዲረዱህ መፍቀድ አለብህ!"

"አልችልም-ብቃ እንዲረዱኝ ማድረግ አልችልም ..."

"ጥሩ፤ ዶን፤ ስለራስህ ስትል ይህንን ለማድረግ ባትፈልግ ስለ እኔ ስትል አድርገው" አሉ::

ስለእርሳቸው ማንኛውንም ነገር እንደማደርግ ያውቃሉ:: እናም በእሽታ ራሴን ነቀነቅኩ::

"ከዚህ በኋላ ማንም ሰው ወደዚህ መጥቶ አንድ ነገር እንዲያደርግልህ ቢጠይቅሁ- ምንም ነገር ይሁን-የፈለገው ነገር ይሁን እሽ እንድትል እፈልጋለሁ:: ምናልባትም ይህንን ለሁሉም ሰው ላታደርገው ትችላለህ፤ ነገር ግን በአንድና በሁለት ሰዎች መጀመር ትችላለህ::

አንተን በመርዳት ጥቂት ሰዎች እንኳን ፍቅራቸውን መግለጽ እንዲችሉ አድርግ:: ይህን እንደምታደርገው ቃል ግባልኝ::"

"ማድረግ እንደምችል እርግጠኛ አይደለሁም"

"አዎ፣ ማድረግ ትችላለህ"

"እሞክራለሁ፤ ያንን የማደርገው ግን ወድጄ አይደለም"

"ወደህ አድርገው" በመሰላቸት ወደ እኔ አትኩረው ሲመለከቱ ቆዩና፤ "አድርገው" አሉኝ::

ዛሬ ዛሬ ሳስበው ጄይ ለእኔ ያሳዩት ትእግስት ያስደንቀኛል:: ድምጻቸውን ልስልስ አድርገው፤ "ለእኔ ስትል ሞክረው:: ታደርገዋለህ? ከዚህ የተሻለ ነገር ማድረግ ትችላለህ:: አሁን እያደረክ ያለኸው ነገር ጥሩ አይደለም:: እግዚአብሔር ልትማራቸው ከሚፈልጋቸው ትምህርቶች አንደኛው ይህ ነው:: ይህን ባለማድረግህ ለረዥም ጊዜ ተጎድተሃል:: ሰዎች እንዳይረዱህ ብትቃወም ከዚህም በላይ ትጎዳለህ::"

"ጥሩ" አልኩ:: ከዚያ በላይ መቋቋም አልቻልኩም::

እናም ቃል ገባሁላቸው:: ይህንን ካላደረኩ በቀር ትተውኝ እንደማይሄዱ ነበር::

በጉዳዩ ላይ የመጀመሪያ የተሰማኝ ብስጭት ነበር እንዲያውም ቁጣ:: ከሚገባቸው በላይ አልፈው እንደተናገሩኝ አሰብኩ፤ አፍ አውጥቼ ግን አልተናገርኩም:: እርሳቸው ከወጡ በኋላ የተናገሯቸውን ነገሮች ሁሉ ማሰላሰል ጀመርኩ:: ቁጣዬን፣ ትእቢቴንና ራስ ወዳድነቴን ካሸነፍኩ በኋላ፤ ይናገሩት የነበረው ነገር ሁሉ እውነት እንደነበር ተገነዘብኩ- ማድመጥ ይገባኝ የነበረ እውነት::



ሁለት ቀናት አለፉ፤ ጄይ የጠየቁኝን ነገር ማድረግ አልቻልኩም::

በሦስተኛው ቀን አንድ የቤተክርስቲያናችን አባል ሊጠይቀኝ ወደ ክፍሌ ገባ:: ሰላምታ እየሰጠኝና እያጫወተኝ አምስት ደቂቃ ያህል ቆይቶ ሰመሄድ ከመነሣቱ በፊት፤ "እንደገና መምጣትና ሁኔታህን ለማየት እፈልጋለሁ" አለ:: "ዛሬ ደግሞ ደህና ነህ::"

ፈገግ አልኩ፤ አስከፊ ሁኔታ ውስጥ ነበርኩ፤ ነገር ግን ከእርሱ ጋር መከራከር አልፈለኩም::

ሰመሄድ ተነስቶ ቆመ:: "ከመሄዴ በፊት ላደርግልህ የምትፈልገው ነገር አለ?"

"አልፈልግም፤ አመሰግናለሁ" ለማለት ከናፍርቶቼን አንቀሳቀስኩ:: እናም የጄይ ምስል ወደ አዕምሮዬ መጣ:: "ጥሩ፤ የማነበው መጽሔት ባገኝ ደስ ይለኛል::"

"ትፈልጋለህ?" በፊቱ ላይ ታላቅ ፈገግታ ታየ፤ "በርግጥ ትፈልጋለህ?"

"ይመስለኛል:: ለረዥም ጊዜ አንድም መጽሔት አላነበብኩም"

"አሁን ተመልሼ መጣሁ!" ምን አይነት መጽሔት እንደምፈልግ እንኳን ሳልነግረው በሩን በፍጥነት ከፈተና እንደ ነፋስ በረረ:: ሃያ አንድ ፎቆችን ወደ ታች መውረድ ነበረበት:: ይሁን እንጂ ከደቂቃ ባነሰ ፍጥነት ተመልሶ የመጣ ይመስል ነበር:: ተመልሶ በመጣ ጊዜ በእቅፉ የመድሔት መአት ተሸክሟል:: ያመጣቸውን መጽሔቶች ሽፋን እያሳየኝ ሳለ እንኳን ያ ትልቅ ፈገግታው በፊቱ ላይ ይታይ ነበር::

አመሰገንኩትና "ትንሽ ቆይቼ አነባቸዋለሁ" አልኩት::

በጠረጴዛው ላይ አስቀመጣቸውና ፈገግ አለ፤ "ሌላስ የምትፈልገው ነገር አለ? "

"አይ፤ አይ፤ የምፈልገው ያንን ብቻ ነው፤ አመሰግናለሁ" አንድ ሰው መልካም ነገር እንዲያደርግልኝ አንድ ጊዜ በሩን ከከፈትኩ፤ ከዚያ በኋላ ያለው ነገር እንደማይከብደኝ ተገንዘብኩ:: እርሱ ከሄደ በኋላ መጽሔቶቹን ማገላበጥ ጀመርኩ:: እያነበብኳቸው አልነበረም፤ ምክንያቱም ስለሆነው ነገር እያሰላሰልኩ ነበር::

ጂይ ትክክል ነበሩ:: ሰዎች ለእኔ መግለጽ የሚፈልጉትን ፍቅራቸውንና ርህራሄአቸውን መግለጽ እንዳይችሉ መንገድ መዝጋቴ እውነት ነበር::

ከአርባ ደቂቃዎች በኋላ፤ ካላገቡት ቡድን መካከል የሆነች አንዲት ሴት ልትጎበኘኝ መጣች:: የተለመደውን ዐይነት የንግግር ጭውውት ስናደርግ ከቆየን በኋላ፤ "አሁን እንዴት ነህ" አለች::

"ደህና ነኝ"

"ላደርግልህ የምትፈልገው ነገር አለ? "

"የለም ... እኔ ... እኔ" እንደገና የጂይ ቃላት በአዕምሮ ውስጥ ማስተጋባት ጀመሩ::

"ጥሩ፤ ምናልባት የዝንጅብል ጣዕም ያለው ከወተት የተሠራ ጣፋጭ ልታመጪልኝ ትችያለሽ"

"የዝንጅብል ጣዕም ያለው ከወተት የተሠራ ጣፋጭ፤ ያንን ላመጣልህ በጣም ደስተኛ ነኝ::" ከዚያ በፊት ፊቷ እንደዚያ በደስታ



ሲያበራ ያየሁበት ጊዜ ትዝ አይለኝም:: "ተጨማሪ ነገርስ ትፈልጋለህ? የሆነ የተጠበሰ ነገር ምናልባት ያስፈልግሁ ይሆን "

"አልፈልግም"::

በሩን በፍጥነት ከፍታ ጣፋጩን ይዛ ተመለሰች:: "አ! ፓስተር እንደምትወደው አምናለሁ"::

"እወደዋለሁ" አልኳት፤ እንደ እውነቱ ከሆነ የዝንጅብል ጣዕም ያለው ከወተት የተሠራ ጣፋጭ እወዳለሁ

ከዚህ በኋላ የቤተክርስቲያኔ አባላት በተኛሁበት ክፍል በር ላይ ቆመው፤ "የዝንጅብል ጣዕም ያለው ከወተት የተሠራ ጣፋጭ እንዳመጣለት ጠይቆኝ ነበር" የሚል ማስታወቂያ አማርጠው እንዳነበቡ ገመትኩ::

"እም እንዳንሸራሸረው ፈቅዶልኝ ነበር"::

ከዚያ በኋላ ነበር ይህንን እድል ሳልጠቀምበት ማባከኔን የተገነዘብኩት:: የእኔንም ይሁን የእነሱን ዕድል ነበር የዘጋሁት:: በእነርሱ ላይ ጠንክር ለማለት በመሞከሬ እኔን ለማጽናናት የነበራቸውን እድል ሁሉ ነበር ጠርቅሜ የዘጋሁት:: የበደለኝነት ስሜት ተሰማኝ፤ ምክንያቱም ቢያንስ ቢያንስ ለእኔ ያላቸውን ስጦታ ማየት ችያለሁ::

ሃፍረቱ ውስጤን ሞላው፤ እናም ማልቀስ ጀመርኩ:: ይሄ የእነርሱ አገልግሎት ነው:: እኔ ግን ሁሉን ነገር አበላሸሁት ስል አሰብኩ:: እንዲረዱኝ ባለመፍቀዴ መጠኑ ለፊ የሆነ ሃፍረት ተሰማኝ:: በመጨረሻው መንገድን በከፈትኩላቸው ጊዜ በእንቅስቃሴያቸውና በፊታቸው ገጽታ ላይ አስገራሚ ለውጥ እንዳየሁ እመሰክራለሁ:: እኔን

መርዳታቸውን ወደውት ነበር:: ይፈልጉ የነበረው አንድ ነገር ለማድረግ የእድል በር እንዲከፈትላቸው ነበር፤ በመጨረሻው የሚፈልጉትን ሰጧቸው::

"እያደረክ ያለውን ነገር ልታውቅ ይገባሃል::" ይህ የጄይ ፍቅር የሞላበት የግሳጼ ቃል ለሚቀጥሉት በርካታ ሰዓታት ከእኔ አልተለየም ነበር:: እንባዬ ይወርድ ጀመር:: በዚያ ሁኔታ ውስጥ ለምን ያህል ሰዓታት እንደቆየሁ አላውቅም፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ይቅርታ እንዳደረገልኝ እስከገነዘብ ድረስ ሰዓታት የተቆጠሩ ይመስለኛል::

አደርገው የነበረው ነገር ጥሩ ባይሆንም ብዙ ሰዎች ጄይ ያደረጉትን ነገር አላደረጉም:: ያ ሁኔታ ባህሪዬን ቀየረው:: ከዓመታት በኋላ አሁን እንኳን ከሌሎች ሰዎች እርዳታን ላለመቀበል በብዙ እጣጣራለሁ፤ በመጨረሻው በሩ በጥቂቱ ገርበብ ብሎ ተከፍቷል:: እንደቀድሞው ሙሉ ለሙሉ ጥርቅም ተደርጎ አልተዘጋም::

አንዳንድ ጊዜ ስሜቱ ሲቀዘቅዝ ወይም የአካል መዳከም ሲያጋጥመኝ፤ ሰዎችን የማግለል አዝማሚያ ይሰማኛል ወይም ምንም ነገር እንደማያስፈልገኝ በመቃወም እናገራለሁ:: ይሁን እንጂ ራሴን መክፈት ስችልና ሰዎች ስጦታዎቻቸውን ተጠቅመው እንዲረዱኝ ስፈቅድ ትልቅ ልዩነት እንዲመጣ አደርግ ነበር:: የፊካ ፊታቸውን ስመለከት፤ "በእውነት ይህንን እንዳደርግልህ ትፈቅዳለህ? " የሚሉ ነው የሚመስለው::

እኔ ተቃውሞዬን ሁሉ የምመለከተው በእነርሱ ላይ ችግር ላለመፍጠር እንደፈለግሁ አድርጌ ነበር፤ እነርሱ ደግሞ አሁን ያለውን



ለውጤን የሚመለከቱት እንዲረዱኝ የእድል በር እንደከፈትኩላቸው አድርገው ነው::

ሰዎች ፍላጎቶቼን እንዲያሟሉልኝ ለመፍቀድ መማር በመቻሌ ትልቅ ውስጣዊ ደስታ ይሰማኛል:: ያንን ትምህርት የተማርኩት ደግሞ ምንም ማድረግ የማልችልበት የሆስፒታል መኝታ ክፍል ውስጥ ሆኜ በመሆኑ ደስታዬ የላቀ ነው::

አንድ ጊዜ አንድ ሰው ካማረ ሸክላ የተሠራ በላዩ ላይ ጽሁፍ የተጻፈበት ሰሌዳ ይዞ ወደ ሆስፒታል መጣ:: በመጀመሪያ የሆነ ቀልድ የመፍጠር ፍላጎት ኖሮት ያደረገው መስሎኝ ነበር፤ ምክንያቱም በላዩ ላይ፤ "እረፉ እኔም እምላክ እንደሆንኩ እወቁ" መዝ (46)፥10 የሚል ጥቅስ ነበር የተጻፈበት:: ምናልባትም ሰውዬው እኔን ለመምከር አስቦ ያደረገው ነገር ይሆናል:: ስጦታውን የሰጠኝ ሰው ማን እንደሆነ በትክክል አላስተውስም:: ያ ሰው ግን አንድ ነገር ስለእኔ ተገንዝቧል፤ ማድረግ የምችለው ነገር ማረፍ ብቻ ነበር::

ይሁን እንጂ ስጦታው የያዘው መልዕክት ለእኔ እጅግ አስፈላጊ የሆነ ነበር፤ ያንን ለመገንዘብ ግን ረዥም ጊዜ ወስዶብኛል::

ያስፈልገኝ የነበረው ነገር ውስጣዊ እረፍትና በደረሰብኝ ነገር ሁሉ እግዚአብሔር የሚያደርገውን የማናውቅ መሆኑን እውቁ መታመን እንደሆነ ለመገንዘብ ሳምንታት ተቆጥረዋል:: በምርጫዬ የመጣልኝ ባይሆንም እንኳን፤ በትክክል ለእኔ አስፈላጊ የነበረ ጥቅስ ነው::

እግዚአብሔር ዐርፌ እንድቀመጥ ግድ አለኝ:: በተፈጥሮዬ በተለየ ሁኔታ እራሴን በጽሞና የምፈትሽ ዐይነት ሰው አልነበርኩም፤ ይሁን እንጂ አመለካከቴን በጥልቀት መፈተሽ ጀመርኩ፤ ሌላ ምርጫ አልነበረኝም:: ለራሴ የነበረኝ የሃዘኔታ ስሜት እየቀነሰ መጣ:: ያለ አንዳች እንቅስቃሴ በአልጋዬ ላይ ተጋድሜ በቆየሁ መጠን፤ ጸጥታና ለውስጣዊ ዝምታ ለእግዚአብሔር ክፍት እየሆንኩለት መጣሁ::

ኢቫ ያንኑ ጥቅስ የያዘ በወርቅ የተቀረጸ እጅግ ያማረ ስጦታ አምጥታ ሰጠችኝ:: ያ ስሌዳ አሁን በቤተክርስቲያን ባለው ቢሮዬ ውስጥ ይገኛል:: ከመቀመጫየ ላይ ሆኜ ቀና ባልኩ ቁጥር ሁልጊዜም እመለከተዋሁ::

በአልጋዬ ላይ እንደተጋደምኩ ቀናት እየጨመሩ በሄዱ መጠን፤ መንቀሳቀስ አቃተኝ:: በሌላ አቅጣጫ ተገላብጬ መተኛት እስክችል ድረስ በድምሩ ለአሥራ ሦስት ወራት በጀርባዬ ለመተኛት ተገድጃለሁ:: በሌላ አቅጣጫ ተገላብጬ የተኛሁበት ያ ተራ የሚመስል እንቅስቃሴ ከፈውሶቼ ቀናት ታላቁ ቀን ነበር::

"ኦ! እንዲህ ተገላብጦ መተኛት ጥሩ ስሜት እንደሚፈጥር ረስቼው ነበር" አልኩ ጮክ ብዬ::

ረዥምም ጊዜ በወሰደው የፈውሴ ጊዜ፤ ስለራሴ፤ ስለጠባዬና ስለ ተፈጥሮዬ ብዙ ነገር ልማር ችያለሁ:: በዶን ፒፐር (በራሴ) ውስጥ ያየኋቸውን ብዙ ነገሮች አልወደድኳቸውም:: ይሁን እንጂ በዚህ የፍጹም ጸጥታ ጊዜ ውስጥም ድብርቱ እንደቀጠለ ነበር::

ያ ድብርት እስከ ፍጻሜው ይቀጥል ይሆን እያልኩ መገረም ጀመርኩ::

ከዚያ በኋላ እግዚአብሔር ሌላ ተአምር ወደ እኔ ላከ::



# 10

# ተጨማሪ ተአምራት

"እግዚአብሔርን ሁልጊዜ እባርከዋለሁ
ምስጋናውም ዘወትር በአፌ ነው::
ነፍሴ በእግዚአብሔር ትከብራለች
ገሮች ሰምተው ደስ ይላቸዋል::
እግዚብሔርን ከእኔ ጋር ታላቅ አድርጉት
በአንድነትም ስሙን ከፍ ከፍ እናድርግ::
እግዚአብሔርን ፈለግኩት መለሰልኝም
ከመከራዬ ሁሉ አዳነኝ "

መዝ (34) ፥ 1-4

አንዳንድ ጊዜ ድብርቱ በመጥፎ ሁኔታ ይበረታብኛል፤ እንዲህ ሲሆን መተንፈስ እንደምችል እንኳን አላስብም:: ወደ ኋላ መልሶ ገና ቀዶ ጥገና ክፍሉ ውስጥ በነበርኩበት ጊዜ መተንፈስ ባለመቻሌ የመተንፈሻ መሣሪያ እጠቀምበት ወደነበረው ሁኔታ ይወስደኛል:: ልዩነቱ አሁን ሳንባዎቼ በትክክል ይሠራሉ፤ በትክክል መስራት የማይችለው መንፈሴ ብቻ ነበር:: ተስፋ ቢስነትን የመሳሰሉ ጥቂት ነገሮች የሰውን መንፈስ እንዲዳከም ያደርጋሉ:: በጥቂት ሳምንታትና ወራቶች መቼ፣ ወይም ጭራሹን በቀረው ዘመኔ ተመልሼ ጤነኛ ልሆን እንደምችል

ሊነግረኝ የሚችል ሰው አልነበረም:: በዚህም ምክንያት ሙሉ ወደ ሆነ ድብርት ውስጥ ገባሁ::

ክፉኛ የተጎዳው ሰውነቴ እየተጠገነ እንደነበር፤ መንፈሳዊ ጥገናም ያስፈልገኝ ነበር:: እንዲህ እያልኩ ማሰብ ጀመርኩ፤ መንፈስ የሚለው ቃል የግሪክ ቋንቋ አቻ ትርጉም "ፕኑማ" ነው:: ቃሉ "ነፋስ" ወይም "እስትንፋስ" ተብሎ ሊተረጎምም ይችላል:: የግሪኩ ቃል ፕንዮሞኒያ ብለን ስምንጠራው ቃል ምንጩ ነው:: ልክ "ፕንዮሞኒያ" የተባለው በሽታ ሳንባዎቼን ባጠቃ ጊዜ፤ እርሱን ለመቋቋምና ሳንባዎቼን በአየር መሙላት አስፈላጊ እንደነበረው ሁሉ፤ የመንፈሴን ድብርት ለማስወገድ እንዲረዳኝ የእግዚአብሔር እስትንፋስ ያስፈልገኝ ነበር::

በድብርቱ እንደተያዝኩ ያወቅኩት መች እንደነበር አላውቅም:: ማገገም በጀመርኩባቸው የመጀመሪያዎቹ ጥቂት ሳምንታት ውስጥ ከባድ በሆነ የአካል ስቃይ ውስጥ ስለነበርኩ ለአንድና ለሁለት ደቂቃዎች ብቻ ካልሆነ በቀር በአዕምሮዬ ውስጥ አንድ የተወሰነ ሃሳብ ለረዥም ጊዜ ማሰብ አልችልም::

በእነዚያ የመጀመሪያዎቹ ሳምንታት በውስጤ ይፈጠር የነበረውን ቁጣ ለመግታት ታላቅ ጦርነት አድርጌአለሁ:: የምቆጣው በእግዚአብሔር ላይ አልነበረም፤ ይልቁንም እግዚአብሔር ከመንግስተ ሰማይ ወደ ምድር ለምን እንደመለሰኝና በዚህ አይነት የአካል ስቃይ ውስጥ እንዳልፍ እንዳደረገ ይደንቀኝ ነበር:: ይሁን እንጂ በስቃይ ውስጥ ማለፌ እንኳን ለእኔ ትልቁ ጉዳይ አልነበረም:: ወደ ሆስፒታል ከገባሁበት የመጀመሪያ ቀን አንስቶ ስቃይ ከእኔ የተለየ ነገር አልነበረም:: እንደ ሌሎች ብዙዎች ሁሉ፤ በዚያ እውነታ ውስጥ መኖርን ተምሬአለሁ:: "ለምን?" እያልኩ እታገል የነበረው፤ ያንን ታላቅ ክብርና



የመንግስተ ሰማይን ግርማ የተመለከትኩት "በቃ ወደምድር ለመመለስ ነው?" የሚል ነበር:: በአካሌ እጅግ ተዳክሜ በነበረበት ጊዜ እንደዚያ ባለ አስቃቂ ሁኔታ እግዚአብሔር ለምን ወደምድር እንደመለሰኝ አይገባኝም ነበር:: ብዙዎች ከዚያ በበለጠ ስቃይ ውስጥም ይኖራሉ፤ ነገር ግን በሕይወት ካሉ እንኳን ጥቂቶች ብቻ ናቸው መንግስተ ሰማይን ያዩ::

ከእግዚአብሔር ይልቅ ቀዳሚው ቁጣዬ የነበረው በህክምና ባለሙያዎች ላይ ነበር:: በምድር ላይ እንድቀር የሆነው እነርሱ ሁልጊዜም ከእኔ አጠገብ የማይለዩ በመሆኑ ምክንያት እንደሆነ እገምታለሁ:: በውስጤ ጥልቅ በሆነ ቁጣና ብስጭት እነዳለሁ፤ ምናልባትም ቁጣዬ በህክምና ባለሙያዎቹ ብቻ ሳይሆን በራሴም ጭምር ነበር:: ለምንድን ነው ፈጥኖ ሊሻለኝ ያልቻለው? ፈውሴ ያልፈጠነው በእነርሱ ምክንያት እንደሆነ አሳብባለሁ:: በትክክል ማሰብ በቻልኩባቸው ጊዜዎች ማድረግ የሚችሉትን ሁሉ እንዳደረጉልኝ አስባለሁ:: ምንም እንኳን እንደምቃወማቸውና እንደምበሳጭባቸው ቢረዱትም፤ ከአጠገቤ ሳይለዩ ያለማቋረጥ ያጽናኑኝ ነበር::

ምንም አይነት ማበረታታት አልፈልግም ነበር-የምፈልገው ውጤት ወይም ለውጥ ነበር:: እንደገና ጤነኛ መሆንን ነበር የምፈልገው:: ሕይወቴ ቀድሞ ወደነበረበት ሁኔታ የማይመለሰው ለምንድነው? በራሴ መራመድ እፈልጋለሁ፤ ሁልጊዜ በሌሎች ላይ መተማመንን አልፈልግም::

የህክምና ባለሙያዎቹ ግልጽ የሆነ መልስ አይሰጡኝም:: ያ ደግሞ አዲስ የሆነ የቁጣ ማዕበል በውስጤ እንዲገላበጥ ያደርጋል:: አሁን ወደ ኋላ ዘወር ብዬ ሳስበው እርግጠኛ ነኝ፣ ይነግሩኝ የነበረው መንገር ይችሉ የነበረውን ነው፤ ይሁን እንጂ የእኔ ጉዳይ ትልቁ ጉዳይ

እንደሆን አስብ ነበር:: ሁኔታዬን እንዲህ ይሆናል ብሎ ለመናገር ማንም አይችልም እንደ እውነቱ ከሆነ ለበርካታ ሳምንታት የተወሰኑት የሰውነት ክፍሎቼ ሊያገግሙ እንደሚችሉ መናገር ይቅርና፤ በሕይወት ለመቆየቴ እንኳን እርግጠኞች አልነበሩም::

ሌሎችን ሰዎች የመፍራትና የመጠራጠር ስሜት ይሰማኝም ነበር:: የተሻለ እንክብካቤ እንዲደረግልኝ ወይም የህመም ስቃዩ እንዲቀል ተጨማሪ መድሃኒቶች እንዲታዘዙልኝ ስጠይቅ እንኳን በመልካም መንፈስ ውስጥ ሆኜ አልነበረም:: ምንም ነገር አይስማማኝም:: የነገሮች ፍጥነት ሁሉ ተገትቶ ነበር:: ጥያቄዬን ለመመለስ ለረዥም ጊዜ እንደሚያስጠብቁኝ አስባለሁ:: ማንም ጥያቄዎቼን ለመመለስ አይፈልግም::

"ይህ ኤልዛሮቭ ፍሬም የተባለ መሣሪያ እስከመቼ ነው በላዬ ላይ የሚቆየው?" ወደ ክፍሌ የመጣውን የትኛውንም የህክምና ባለሙያ እጠይቀዋለሁ::

"እኔ አላውቅም" የሚለው የተለመደው መልስ ነው::

"ነገር ግን አንድ ነገር ማወቅ እፈልጋለሁ" እላለሁ በመጨረሻው::

"ረዥም ጊዜ፤ በጣም ለረዥም ጊዜ":: ነርሶቹ ወይም ዶክተሮቹ የሚሰጡኝ ሌላው መልስ ነበር::

ሁለት ጊዜ ያህል እርግጠኛ የሆነውን መልስ ማወቅ በመፈለግ ዶክተሩን ተጭኜ መጠየቅ ጀመርኩ::



"ሳምንታት ምናልባትም ወራት" አለኝ:: "እርግጠኛ የሆነውን ጊዜ ልንነግርህ አንችልም፤ ምክንያቱም ያንን ስለማናውቅ ነው:: የማውቀው ቢሆን ኖሮ እነግርህ ነበር::"

በትክክለኛው አሳቤ ሲገመገም ማድረግ የሚችሉትን የመጨረሻ ነገር እያደረጉ ነበር:: እኔ ግን በዚያ ጊዜ ትክክለኛ አስተሳሰብ አልነበረኝም:: የዚህ አንዱ ምክንያት የህመም ስቃዩ ነበር:: ምናልባትም የምወስዳቸው በርካታ መድሃኒቶች እንደዚያ እንድሆን ተጽእኖ አሳድረውብኝም ይሆናል፤ ያም ቢሆን እኔ የምመች በሽተኛ አልነበርኩም:: በነገሮች ሁሉ ከመርካት ይልቅ፤ "ለምንድን ነው የማይነግሩኝ? አውቀው የደበቁኝ ነገር ምንድን ነው? ሆን ብለው ያልነገሩኝ ነገሮች አሉ፤ በእኔ ላይ እየሆነ ያለውን ነገር የማወቅ መብት ደግሞ አለኝ" እያልኩ ራሴን እጠይቃለሁ::

እንቅልፍ ባጣሁባቸው በርካታ ሌሊቶች፤ በአልጋዬ ላይ እንደተጋደምኩ ነርሶቹ በእኔ ላይ ለከፋት ተማክረውብኛል እያልኩ ራሴን አሳምናለሁ:: እንደዚያ ለማድረግ ስለመፈለጋቸው የሚጠቁም አንዳች ነገር በእኔ ላይ ያለማድረጋቸው ደግሞ ያስደንቀኛል::

"እንደዚያ ካላሰቡ ታዲያ ለምንድን ነው ምንም ነገር የማይነግሩኝ፤ እዚህ ተኝቼ ብረቶቹ በእግሬ ውስጥ ተቀርቅርዋል:: ከዚህ በላይ በምን ሊጎዱኝ ይችላሉ?"

መልሱ "በምንም" የሚል ነበር:: በአደጋው በራሱ ከደረሰብኝ ስቃይ በተጨማሪ በፈውሱ ሂደት ውስጥ የደረሰብኝን ተጨማሪ ስቃይ ተቋቋምኩት:: ለምሳሌ ያህል ከቀኝ መቀመጫዬ አካባቢ ካለ ስፍራ አጥንት ወስደው በግራ እጄ ላይ በሚተክሉበት ጊዜ፤ በቆዳዬ ስድስት

ኢንች የሚያህል ስፍራ አንድጉደው ነበር:: ያንን ክፍተት የዘጉትም የብረት ማያያዣዎችን በመጠቀም ነበር:: የብረት ማያያዣዎችን የሚያወጡበት ቀን በደረሰ ጊዜ፤ ከስጋዬ ላይ እየነቀሉ አወጧቸው:: እያንዳንዱን ብረት በሚነቅሉበት ጊዜ፤ በሳንባዎቼ ምክንያት ድምጼን ከፍ አድርጌ መጮህ ባለመቻሌ ፊቴን በስቃዩ ስሜት አኮማትሬ በታላቅ ስቃዩን የመቻል ብርታት ተቋቋምኩት:: እንደዚያ በህመም ስቃይ የተጎዳሁበትን ጊዜ አላስታውስም:: ምናልባት ይኖር ይሆናል፤ ነገር ግን በአካሌ ላይ የተቀበልኩትን ስቃይ ሁሉ ምን ያህል እንደሆነ አረስቼዋለሁ::

ብረቶቹን ከሰውነቴ ላይ ትነቅል የነበረችዋ ምስኪን ነርስ፤ እያንዳንዱን ብረት ከነቀለች በኋላ ቆም ትል ነበር:: ሃዘን በአይኖቿ ውስጥ ሞልቶ ነበር፤ ሃዘኗ የህክምናው ሂደት ምን ያህል ክፉኛ እንደጎዳኝ በመሆኑ ምክንያት እንደሆነ አውቃለሁ:: ቁመናዋ ረዘም ያለ ሁልጊዜም በተቻላት መጠን በትህትና የምትከባከበኝ ሴት ነበረች:: “በጣም አዝናለሁ፤ መጋቢ” አለች ዝቅ ባለ ድምጽ “አውቃለሁ” ስል አጉተመተምኩ:: “ምንም ልታደርጊው አትችይም”:: ለአጭር ጊዜም ቢሆን ወደዚያው ወደ መጋቢነት ተግባሬ ተመልሼ አማክራት ጀመር:: እየተቀበልኩት ባለው ስቃይ ምክንያት እርሷ እንድታዝን አልፈለግኩም ነበር::

“መጋቢ፤ ለምን ትንፋሽህን አውጥተህ ጩኸትህን አትለቀውም?”

“የሚያመጣው አዲስ ነገር የለም”::

“እኔ አንተን ብሆን እንባርቀው ነበር”::



“አውቃለሁ፤ ታደርጊው ነበር” አልኳት:: ትንሽ ፈገግ እንድትልም “እናም በሆስፒታሉ ያሉ በሽተኞችን ሁሉ ትቀሰቅሻቸው ነበር”::

ሆን ብዬ በጭራሽ መጮህ አልችልም:: ምናልባትም ራሴን እስታለሁ ከሚል ፍርሃት የመነጨ ሊሆን ይችላል:: ምናልባትም ደግሞ ጩኸቴን ብለቀው እርሷም ሆነች ሌሎች እንደ ፈሪ ይቆጥሩኛል የሚል ስጋት ኖሮኝም ሊሆን ይችላል:: እስከ አሁን ድረስ እንኳን ስለ ምክንያቱ እርግጠኛ አይደለሁም:: የማውቀው ነገር ቢኖር በእኔ ፎቅ ላይ እንዳሉት ህመምተኞች መጮህ አለመቻሌን ነበር:: በሌሎች በርካታ ክፍሎች፣ በሽተኞች በየቀኑ በህመም ስቃይ ሲጮሁ እሰማቸዋለሁ:: እንደዚያ መጮህ እኔ አልችልም:: ከዚያ ይልቅ ለእኔ የሚቀለኝ ትንፋሼን ዋጥ አድርጌ እሰበስብና ከውስጤ በሚወጣ ቀዝቃዛ ላብ እገላገለዋለሁ፤ ይሁን እንጂ ሆን ብዬ መጮህ አልችልበትም ነበር::

ምንም እንኳን ጥሩ ጠባይ ያለኝ ወይም ለህክምና የምመች ቀላል በሽተኛ እንዳልሆንኩ ባውቅም፤ የድንገተኛ አደጋ ክፍል ነርሶች የሚንከባከቡኝ በከፍተኛ ትህትናና በርህራሄ ነበር:: ስለ እነርሱ ትልቅ አክብሮት እንዲኖረኝና ቁርጠኛ የነበረ ትጋታቸውን ማድነቅ እንደሚገባኝ ተምሬአለሁ:: በእኔ ላይ አንድ የተለየ ነገር እንዳዩ እገምታለሁ:: የነርሶች ቡድን አባላት ስለ እኔ ሲሉ አንዳንዶቹን የሆስፒታሉን ህጎች ያስተካክሏቸው ነበር፤ ለምሳሌም “እንኳን ደስ ያለህ” ሊሉኝ የሚመጡ ጠያቂዎቼ በቀንም ይሁን በሌሊት በየትኛውም ሰዓት ይምጡ እንዲገቡ ይፈቅዱላቸዋል:: ነገር ግን እጅግ ጣፋጭ የሆነችዋ ሰዓት የመጣችው ከአንድ መቶ አምስት ቀናት ቆይታ በኋላ ከቅዱስ ሉቃስ ሆስፒታል የወጣሁባት ዕለት ነች:: በግልጽ እንደታየው የነርስ ቡድን አባላት

እንዳንድ ዝግጅቶችን አድርገው ነበር፡፡ በሌሎች የሆስፒታሉ ፎቆች ውስጥ የሚኙትን በማስተባበር፤ ከመኝታ ክፍሌ እስከ አሳንሰሩ (ሊፍቱ) ድረስ ከዚያ ደግሞ ትጠብቀኝ እስከነበረች አምቡላንስ ድረስ በክብር ሸኝተውኛል፡፡ ሲመግቡኝ፤ ሲያክሙኝ፣ ሲያጥቡኝ ያደረጉልኝን ቀሪ ነገር የሚያውቀው ጌታ ብቻ ነው፤ በነበሩ ነርሶች ታጅቤ ወደ ቤቴ ያደረኩትን ጉዞ እጅግ አስደሳች አድርጎታል፡፡ "ማድረግ የምንችለውን ሁሉ አድርገናል፡፡ አሁን እየተሻለህ ነው፤ ወደ ሙሉ ጤንነትህ ተመልሰህ እንደገና ተመልሰህ በመምጣት ጠይቀን" የሚሉ ነበር የሚመስለኝ፡፡ በአደጋው ዕለት ወደ ሆስፒታሉ ስገባ የነበርኩበትን በሞትና በሕይወት መካከል የነበረ ሁኔታዬን፤ አሁን ወደ ቤቴ እየሄድኩ ካለሁበት ሁኔታ ጋር ያለውን ልዩነት ያነጻጽሩ እንደ ነበር እገምታለሁ፡፡

የቅዱስ ሉቃስን ሆስፒታል ለቅቄ ከመውጣቴ በፊት ግትርነትና፣ ሁሉን ነገር የመቃወም ስሜት አሳይ የነበር ቢሆንም፤ በእነኛ ወራቶች መካከል ያለፍኩባቸው ጠንካራ የስቃይ ጊዜያቶች መንፈስ ጠንካራነቴን አንበረከኩት፡፡ በእንባ ተሞልቼ እለቅሳለሁ፡፡ ዋጋ የሌለኝ የተጣልኩና ጥቅም አልባ እንደሆንኩ ይሰማኛል፡፡ ፈጽሞ መልሼ ደህና ልሆን እንደማልችል አድርጌ ራሴን አሳምኜውም ነበር፡፡

"እግዚአብሔር ሆይ፤ ነገሮች እንዲህ የሆኑት ለምንድን ነው? በዚህ ማለቂያ በሌለው ስቃይ ውስጥ እንዳልፍ የተደረገውና የማላገግመውስ?" እያልኩ እንደገና መልሶ እንዲወስደኝ ወደ እግዚአብሔር እጸልያለሁ፡፡ ከዚያ በላይ መኖር አልፈልግም ነበር፡፡



እንደገና ወደቤቴ መመለስን እፈልጋለሁ፤ አሁንም ቢሆን እኔ ቤቴ የምለው መንግስተ ሰማይን ነው፡፡

እንዲህ ያለውን ጸሎት ያለማቋረጥ በቀናት መካከል እጸልያለሁ፤ ብዙ ጊዜ እንዲህ ባለ ሁኔታ ውስጥ ተዳክሜ በእንቅልፍ እወሰዳለሁ፡፡ ከእንቅልፌ ስነቃ በተስፋ ቢስነት ተሞልቼ ራሴን አገኘዋለሁ፡፡ ሊረዳኝ የሚችል አንዳች ነገር አልነበረም፡፡

ከአደጋው ጥቂት ቀደም ብሎ፤ በ1960ዎቹና 70ዎቹ በኢምፔሪያልስና በእነ ዴቪድ ምስ የተዘመሩ ታዋቂ ክርስቲያናዊ ዝማሬዎችን ኦርጂናል በካሴት ቅጂዎች አዝገቼ ነበር፡፡ ኢቫ፣ እነዚህን ካሴቶች ከቴፕ መጫወቻ ጋር ወደ ሆስፒታሉ አምጥታቸው ነበር፤ ይሁን እንጂ እነርሱን ለማድመጥ ምንም ፍላጎት አላደረብኝም፡፡

ከዚያ ይልቅ ቴሌቭዥን እመለከት ነበር፡፡ አንድ ጊዜ ጓደኛዬ ለሆነ ሰው፤ "ብራዲ ባንች የተባለውን ተከታታይ ፊልም ቢያንስ ስምንት ጊዜ ያህል አይቼዋለሁ፤ በመሆኑም ገጸባህሪያቱ የሚጫወቱትን ቃለተውኔት በቃሌ አውቀዋለሁ" አልኩት፡፡

በአንድ ጠዋት ሰዓቱ ከ3:00 - 5:00 በሆነበት ጊዜ፤ ሌላ የቴሌቭዥን ፕሮግራም ለመመልከት አልፈለግኩም፤ በመሆኑም ካሴቶቹን ለማጫወት ወሰንኩ፡፡ ነርሷ መጥታ የመጀመሪያውን ካሴት በመክተት እንዳስጀምረው ረዳችኝ፡፡

የመጀመሪያው ካሴት የተቀረጸው በኢምፔሪያልስ የዝማሬ ቡድን ነበር፤ የዝማሬው ካሴት መጠሪያዋ "እግዚአብሔር ይመስገን" የሚል ነበር፡፡ የመዝሙሩ ግጥሞች፤ በሕይወት ውጣ ውረድ ትግል ውስጥ ካለንና ወደፊት መቀጠል እንደማንችል ከተሰማን እግዚአብሔርን

ማመስገን እንደሚያስፈልገን የሚመክሩ ስንኞችን ይዟል:: ዝማሬውን እያዳመጥኩ ብዙ ብቆይም ሰዓቱ አሁንም 3:00 የሆነ እስኪመስል ድረስ ሳይታወቅ መቆየቱ ሙሉ በሙሉ የማይታመን ነበር:: ጥልቅ ከሆነ ሃዘኔ የሚያላቅቀኝን አንዳች እርዳታ ፍለጋ ማድመጤን ቀጠልኩበት:: በቀጣዩ የግጥሙ ስንኝ ውስጥ፤ ወደ ምስጋና ስንመለስ በጽኑ ያሰረን የሚመስለው ሰንሰለት ከእኛ ላይ ወልቆ ይወድቃል የሚል ሃሣብ አሰበት:: ሙሉው ካሴት የያዘው የዝማሬ መልዕክት ያማከለው፤ ባለንበት ሁኔታ ውስጥ በመንፈስ እግዚአብሔርን ማመስገን እንደሚገባን ነው::

የዝማሬው ቡድን በሁለተኛው ቁጥር፣ ስለ ሰንሰለት ሲዘምሩ፤ ጎንበስ ብዬ የራሴን ሰንሰለት ተመለከትኩ:: ብዙ ኪሎ ግራም የሚመዝን ብረታ ብረት በእጄና በእግሬ ላይ ተከምሯል:: ከአደጋው በፊት ያንን ዝማሬ መቶ ጊዜ ያህል ሰምቼዋለሁ፣ ዘምሬዋለሁም:: እኔ ራሴም ተጫውቼዋለሁ:: ከዚያ በኋላ የዝማሬው ቃላት ከእግዚአብሔር ዘንድ የሆኑ መልዕክቶች እየሆኑ መጡ፤ ከላይ የወረደ ቀጥተኛ መልዕክት::

ዝማሬውን ከመጨረሳቸው በፊት፤ በተጋደምኩበት ስፍራ ሆኜ "እግዚአብሔር ይመስገን! " እያለ የሚዘምረውን የራሴን ድምጽ አዳመጥኩ::

ያ ዝማሬ እንዳበቃ የዴቪድ ምስ፤ "ምክንያቶቹ እኛ ነን" የሚለው ዝማሬ ቀጠለ:: የእርሱ ዝማሬ ደግሞ ኢየሱስ በመስቀል ላይ ያለቀሰበት፣ የተሠቃየበትና የሞተበት ምክንያቶቹ እኛ መሆናችንን የሚያስታውስ ነበር:: ዴቪድ በመጨረሻው እንዴት አድርጎ፤ እውነተኛው የሕይወት ዓላማ ሁለንተናን ለኢየሱስ ክርስቶስ መስጠት መሆኑን እንደተረዳ ይዘምራል:: ያ ለእኔ አዲስ ዝማሬ አልነበረም፤ እንደዚያ ባለ



ውድቀት ጊዜ ውስጥ ግን አንድ ነገር ሆነ:: ከሙዚቃው በስተቀር ሌላ ምንም ነገር አልሰማም ነበር- ከሌሎች ክፍሎች የሚወጣ የጣር ድምጽ ወይም በኮሪደሩ ላይ የሚተላለፉ የነርሶች ኮቴ ድምጽ የለም:: በአካባቢዬ ከነበረው ዓለም ፈጽሞ እንደተገለልኩ ተሰማኝ::

ከዚያ ግድቡ ተነደለ:: እንባ በጉንጮቼ ላይ መዝነብ ጀመረ፤ እናም ልጠርገው አልቻልኩም፤ ልጠርገውም መሞከር አልፈለግኩም:: ዝም ብሎ መፍሰሱን ቀጠለ:: እንባም ሊቆም አልቻለም፤ ከዚህ በፊት አልቅሼ በማላውቀው ሁኔታ ማልቀሴን ቀጠልኩ:: እርግጠኛ አይደለሁም፤ ይሁን እንጂ ያ ለቅሶ ለአንድ ሰዓት ያህል የቀጠለ ይመስለኛል::

በዝግታ እንባዬ እየቀነሰ መጣ:: መረጋጋት ውስጤን ሞላው፣ ዘና ብዬና በፍጹም ሰላም ውስጥ ተጋደምኩ:: ከዚያ ሌላ ተአምር እንደተከናወነ ተገነዘብኩ:: ድብርቱ ከላዬ ላይ ተነሳ:: ፈጽሞ ሄደ::

እንደገና ደግሞ ተፈወስኩ::

ግልጽና ቀላል የሆኑ ዝማሬዎቹ ሰወጡኝ:: ኢምፔሪያልስ፣ ሰይጣን ውሸታም መሆኑን እንዳስታውስ አደረጉኝ:: ሰይጣን ደስታችንን ሰርቆ በተስፋ ቢስነት ሊሞላን ይፈልጋል:: በሕይወት ፍልሚያ ውስጥ ከሆንንና በዚያ መቀጠል የማንችል መሆኑ ከተሰማን፤ ያንን ሁኔታ እግዚአብሔርን በማመስገን ልንሰውጠው እንችላለን:: ሰንሰለቶቻችን ከእኛ ላይ እየወለቁ ይወድቃሉ::

ዴቪድ ምስ፤ በዚህ ምድር ላይ ስንኖር ሙሉ የሆነው የሕይወት ምክንያት ምን እንደሆነ እንዳስታውስ አደረገኝ:: ያሰንን ሁሉ

ለእግዚአብሔር ማስረከብ - የልብ ስብረቶቻችንና ስቃያችንን እንኳን ሳይቀር። ለመኖራችን ምክንያቱ እግዚአብሔር ነው።

ከዚያ ጠዋት ጀምሮ በቀሪው የሕይወት ዘመኔ ሕይወትን በየትኛው ውም መልኩ ተቀብዬ ለመኖር ወሰንኩ። ያንን ውሳኔ የወሰንኩት ያለ የስነ አዕምሮ ጠበብት እርዳታ፣ ያለ ምንም መድሃኒትና ያለ ምንም የምክር አገልግሎት ነበር። እነኛን ሁለት ዝማሬዎች በማደምጥበት ጊዜ፤ እግዚአብሔር ራሱ ፈወሰኝ። ተስፋ ቢስነቴ ከላዬ ላይ ተነቀለ። በአዕምሮ ላይ የተተበተበው ሰንሰለት ተበጣጠሰ። በተጨማሪም ያለፍኩበት ማንኛውም ሁኔታ ወይም ስቃይ ኢየሱስ ያለፈበት ሰቆቃ እንደሆነ አወቅሁ።

የሥነ አዕምሮ ጠበብት የሚሰጡትን አገልግሎት እየተቃወምኩ አይደለም። ከአደጋው በፊትም ሆነ በኋላ ብዙ ሰዎች በእነርሱ ምክር እንዲያገኙ ልኬአለሁ። ነገር ግን እኔ ማንኛውንም እርዳታ ለመቀበል ፈቃደኛ ስላልነበርኩ፤ እግዚአብሔር አስደናቂና ለመግለጽ አስቸጋሪ በሆነ መንገድ ፈወሰኝ።

በዚያ ሥፍራ ተጋድሜ፤ ጠባዬ መቀየር ጀመረ። የአካል ስቃዬ መቼ ከእኔ እንደሚወገድ ወይም ኤልዛሮቭ ፍሬም የተሰኘው መሣሪያ መቼ ከእኔ እንደሚላቀቅ አላውቅም፤ ይሁን እንጂ ኢየሱስ ክርስቶስ ከኔ ጋር እንደነበር አውቄአለሁ። አሁንም ቢሆን እግዚአብሔር በዚህ ስቃይ ውስጥ እንድኖር ለምን መልሶ እንደላከኝ አላውቅም፤ ነገር ግን ያም ቢሆን ከዚያ በኋላ እጅግም ዋጋ የለጠሁት ጥያቄ አልሆነም።

አሁን ነፃ ሆኛለሁ። እርሱ እግዚአብሔር አዕምሮዬን ፈውሷል። ሰውነቴ እያገገመ ያለው በዝግታ ነው፤ ይሁን እንጂ ትልቁን ድል



ተቀዳጅቻለሁ። ከዚህ በኋላ በፍጹም ድብርት አያጠቃኝም። ከመንግስተ ሰማይ የሆነልኝ አንድ ተጨማሪ ተአምር ነበር።

# 11

# ወደ ቤተክርስቲያን መመለስ

"እንግዲህ በጊዜው ከፍ እንዲያደርጋችሁ ከኃይለኛው ከእግዚብሔር እጅ በታች እራሳችሁን አዋርዱ፣ እርሱ ስለ እናንተ ያስባልና የሚያስጨንቃችሁን ሁሉ በእርሱ ላይ ጣሉት "

1ጴጥ 5፥6-7

ስረኻርም ጊዜ የሚያውቁኝ አንዳንድ ሰዎች የመጽናናት ምሳሌ አድርገው ይመለከቱኛል:: እንደ እውነቱ ከሆነ እኔ እንደዚያ አድርጌ አይደለም ራሴን የምመለከተው:: ለአንዴም ቢሆን እንዲህ አስቤ አላውቅም፤ ምክንያቱም ስለእውነተኛው ማንነቴ ብዙ ነገር አውቃለሁ:: በተጨማሪም ከዚያ የመከራ ስቃይ ውስጥ ለመውጣት በራሴ ያደረኩት ነገር በጣም ጥቂት እንደሆነ አውቃለሁ::

እኔ ስለራሴ እንዲህ ባስብም፤ ጓደኞቼና የቤተክርስቲያን አባላት እንደዚያ ካለ ተስፋ አስቆራጭ ሁኔታ ውስጥ ወጥቼ ቀስ በቀስ ወደ መደበኛው ሕይወት ለመሸጋገር መቻሌን በማየታቸው እጅግ እንደተጽናኑ ይናገራሉ:: ብዙ ግለሰቦች ባሉበት ችግር ውስጥ እንዳሉ ወደ እኔ መጥተው፣ "ባለፍክበት በዚያ ሁኔታ ውስጥ አንተ ጸንተህ መቆም ከቻልክ፤ አሁን ባለሁበት ሁኔታ ውስጥ ማለፍ እችላለሁ" ብለውኛል::



በእኔ የሕይወት ልምምድ ሰዎች ልባቸው እንዲበረታታ በመሆኑ በጣም ደስተኛ ነኝ፤ ይሁን እንጂ እንደ ብርታትና የመጽናናት ምንጭ አድርጌ እራሴን ለመቀበል ታላቅ ችግር ይገጥመኛል::

አድናቆታቸውንና ምስጋናቸውን በምን ሁኔታ እንደምቀበል ይቸግረኛል፤ ምክንያቱም እኔ ያደረግኩት አንዳች ነገር የለም:: እኔ እፈልግ የነበረው መሞትን ነበር:: ያ እንዴት አድርጎ ሊያጽናና ይችላል::

ሰዎች ለሕይወታቸው እንዴት መጽናናት እንደሆንኩ ሲነግሩኝ በርግጥ አልከራከራቸውም፤ ነገር ግን ዴቪድ ጄንቲልስ ወደ እኔ መጥቶ ጤንነቴ እንዲመለስልኝ እርሱና ሌሎች እንደሚጸልዩልኝ የነገረኝን አስታውሳለሁ:: እኔ አሁን በሕይወት ያለሁት ሌሎች እንድሞት ባለመፍቀዳቸው ነው:: አድናቆት የሚገባቸው ይጸልዩልኝ የነበሩት እነዚያ ጓደኞቼ ናቸው::

አብዛኛውን ጊዜ ሰዎች - አንተ በዚያ ሁኔታ ውስጥ ማለፍ ከቻልክ የሚል ሃሣብ ሲሰነዝሩ፤ ራሴን በአዎንታ እነቀንቃለሁ፤ እየተናገሩ ያሉትን ነገር እደግፋለሁ፤ በተጨማሪም፤ ማድረግ የቻልኩትን አድናቂለሁ እላቸዋለሁ፣ በእውነትም ደግሞ አስቸጋሪ በሆኑት ቀናት ያደረኩት ያንን ነበር:: አንዳንድ ጊዜ ማድረግ የቻልኩት ትልቅ ነገር ሌላ ሳይሆን መጽናት ብቻ ነበር:: ከድብርት ውስጥ ለመውጣት እጣጣር በነበረበት ጊዜም ያደረኩት ትልቁ ነገር ይህንኑ ነው:: ምናልባት እግዚአብሔር ያከበረው እርሱን ሊሆን ይችላል:: እኔ የማውቀው ነገር የለም::

በተፈጥሮዬ፤ በነገሮች ላይ ቁርጥ አድርጌ የምወስን ሰው ነኝ፤ አንዳንድ ጊዜም የግትርነት የአጎቴ ልጅ እንደሆንኩ አምናለሁ:: ይሁን

እንጂ ብዙ ጊዜያት ብቸኛ የሆነ ሰው እንደሆንኩና ማንም ሰው ሊገነዘበኝ እንደማይችል ይሰማኛል:: አሁንም እንኳን ይህ እውነት እንደሆነ አስባለሁ:: ስቃያችን መጠነ ሰፊ ሲሆንና ያለ ምንም ዕረፍት ለሳምንታት ያህል በዚያ ሁኔታ ውስጥ ስንፀና ማንም ሰው ይህን አያውቅልንም:: በምን ሁኔታ ውስጥ እንዳለን ማወቃቸውና ስቃዩን መረዳታቸው ያን ያህል ጠቃሚ መሆኑንም አላውቅም:: ጠቃሚው ነገር ሁኔታው ግድ ያላቸው መሆኑን ነው::

በግንቦት ወር አጋማሽ ላይ ከሆስፒታል ወጥቼ ወደ ቤቴ የተመለስኩ ቢሆንም፤ እስከ የካቲት ወር 1990 ድረስ እንደገና ወደ ሆስፒታል አልጋ መመለስ ግድ ሆኖብኝ ነበር:: ያም ማለት ድፍን አሥራ ሦስት ወራት ማለት ነው:: ወደ ቤቴ ተመልሼ ከተኛሁ በኋላ እንኳን ቁስሉ እያመረቀዘ በተለያዩ ሁኔታዎች ተመርገፍ ነበር:: ወደ ሆስፒታል እየተመለስኩ ከሄድኩባቸው ጊዜያቶች አንዳንዶቹ ይልቁንም የመጀመሪያዎቹ ለሕይወት አስጊ በነበሩ መመረዞች የታጠቃሁባቸው ነበሩ:: አንዳንድ ጊዜ ሁለት እና ሦስት ሳምንታት እቆያለሁ:: አብዛኛውን ጊዜ ወደ ሆስፒታል በመኪና የምትወስደኝ ኢቫ ስትሆን፤ ወደ ቤቴ እመለስ የነበረው ግን ሁልጊዜም በአንቡላንስ ነበር::

በመጀመሪያ ከሆስፒታል እንድወጣ ከተደረገበት ቀን በኋላ፤ የቤተክርስቲያኔ አባላት ከደረሰብኝ ሁኔታ አንጻር አሁን ያለሁበትን ሁኔታ እያገናዘቡ፤ እየተሻለኝ እንደመጣና እንዳማረብኝ ይነግሩኝ ጀመር:: እርግጥ ነው ማንም አፍ አውጥቶ ይህን አልተናገረም፤ ነገር ግን "ለዶን እኮ ጸልየንለታል:: ሁኔታው እንዴት እንዲህ እንደተሰወጠ የማይታመን ነው:: እርሱ በሕይወት እንዲኖር ጸልየናል፤ ሁኔታው እንዲሰወጥም ጠይቀናል" እንደሚሉ አገምታለሁ:: በቃ እንደዚያ ነው፤ በአሳዛኝ ሁኔታ ውስጥ ነበርኩ፤ ይሁን እንጂ አሁን በሕይወት አለሁ፤ ይህ ደግሞ እነርሱ የጠየቁት ነው::

መንትያዎቹ ልጆቼ ጆይና ክሪስቶፎር በአደጋው ወቅት የስምንት ዓመት እድሜ ነበራቸው:: ሴት ልጃችን ኒኮል ደግሞ የአሥራ ሁለት ዓመት ልጅ ነበረች:: እያገገምኩ በነበርኩበት ጊዜ እጅግ የተጎዳሁበት ሁኔታ ቢኖር በልጆቼ ውስጥ የተፈጠረው የስቃይ ስሜት ነበር:: ብዙ ነገር አይናገሩም፤ ይሁን እንጂ ምን እንደተሰማቸው አውቃለሁ::

ከዚህ በታች ያሰፈርኩት ልጄ ጆይ በራሱ እጅ በሠራው ካርድ ላይ የጻፈልኝ ደብዳቤ ነው:: በዚህ ጊዜ ከአያቶቹ ጋር ሲኖር ሄዶ ነበር::

ሰላም አባ

አንተ እኮ የተለየህ ሰው ነህ:: እወድሃለሁ፤ ካርዱንም እንደምትወደው ተስፋ አደርጋለሁ:: እንደዚያ ያለ ሁኔታ ዳግመኛ እንደማያጋጥምህ ተስፋ አደርጋለሁ:: እወድሃለሁ አባ:: ጆይ

ከወራት በኋላ ወደ ቤቴ ስመለስ፤ የጆይ መንትያ የሆነው ክሪስ ከትምህርት ቤት በሚመለስባቸው በርካታ ከሰዓት በኋላ ጊዜያቶች፤ አልጋዬ ወደነበረበት ወደ ሰፊው ሳሎን ይመጣ ነበር:: አንዳች ቃል ሳይተነፍስ በጸጥታ ወደ እኔ ይመጣና ራሱን በደረቴ ላይ ያሳርፋል:: ምን ያህል ጊዜ በእንደዚህ ያለ ሁኔታ እንደሚቆይ አላውቅም፤ ምናልባትም ሙሉ ደቂቃ ላይቆይም ይችላል::

አንዳች ቃል አይናገርም::

ምንም ነገር ደግሞ አይፈልግም:፤ ጥቂት የፊት ገጽታው ስሜት በቂ ነበር:: ልጄ በጣም እንደሚወደኝ ይሰማኛል::

ከደቂቃዎች በኋላ፤ ክሪስ ወደ መኝታ ክፍሉ ይሄዳል፤ የትምህርት ቤት ልብሱን ያወልቅና የጨዋታ ልብሱን አጥልቆ ለመጫወት ወደ ውጭ ይወጣል:: እንዲህ ባለ ሁኔታ ነበር በየቀኑ ሰላምታ የሚያቀርብልኝ::

ሁኔታው ለእርሱ እጅግ የሚከብድ በእውነት እጅግ የሚከብድ ነበር፤ እናም እርሱ በሚያውቀው መንገድ የልቡን ውስጣዊ ሃዘን ይገልጻል::

ከአደጋው በኋላ ልክ በስድስተኛው ወር፤ ሰልጄ ለኒኮል እጅግ ልዩ በነበረው የደስታ ቀኗ ተሣትፎ ላደርግ ችዬ ነበር::

የደቡብ ባፕቲስት ቤተክርስቲያን ወጣቶችን የምታሳትፍበት ሚስዮናዊ ድርጅቶች አሏት:: ከነዚህ መካከል ታዋቂዎች የሆኑት ወንዶቹ የሚሳተፉበት፤ "የንጉስ አምባሳደሮች" የተሰኘው ሲሆን ልጃገረዶችን ያካተተው ደግሞ፤ "ልጃገረዶች በተግባራዊ ግዳጅ ላይ" የተሰኘው ይገኝባቸዋል፤ ዕድሜዋ በድርጅቱ ውስጥ ለመሳተፍ በቂ በሆነ ጊዜ፤ ኒኮል መሳተፍ ጀመረች:: አስፈላጊ የነበሩትን እንደ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ማስታወስ፣ በተለያዮ የአገልግሎት ፕሮጀክቶች መሳተፍንና የተልዕኮ ጉዞዎችን ሁሉ በሚገባ አሟላች::



ዕድሜዋ አስራ አራት አመት በሆነ ጊዜም፤ ሳውዝ ፓርክ ባፕቲስት ቤተክርስቲያን በሰኔ ወር 1989 በሚደረገው ክብረ በዓል ላይ የክብር ተሸላሚ ሆና እንደምትቀርብ ተነገራት::



ዶን፣ ከአደጋው በኋላ ሴት ልጄ በምትሳተፍበት የ "ልጃገረዶች በተግባር" የዘውድ በዓል ላይ ሲሳተፍ

ይህ ሽልማት ለላቀ ተሳትፎ የሚሰጥ ስጦታ ሲሆን የሚበረከተውም በቤተክርስቲያን ውስጥ በሚዘጋጅ ክብረ በዓል ላይ ነው። እርሷ ይህንን ሽልማት ልታገኝ የቻለችው ባደረገችው የተለየ ቁርጠኛ ውሳኔዋ ነው። በእነዚህ እንቅስቃሴዎች ለመሳተፍ ራሷን በሰጠችበት ጊዜ በቤት ውስጥ ለመኖር እድሉ አልነበራትም። ጓደኞቻችን የሆኑት ሱዘንና ስታን ማሃልዲን ነበሩ ቤታቸውን ከፍተው ያስጠጓት። እናም ከእነርሱ ጋር ነበር የምትኖረው። ኒኮል ከእኔ ምንም አይነት ስነልቡናዊም ሆነ አካላዊ እርዳታ አላገኘችም፤ ምክንያቱም እኔ በሆስፒታል ውስጥ በሞትና በሕይወት መካከል ነበርኩ። የሚያበረታቱ ደብዳቤዎችን ብቻ ከእናቷ ታገኝ ነበር፤ ምክንያቱም የኢቫም ሕይወት ቢሆን በአመቺ ሁኔታ ውስጥ አልነበረም፤ እስከ ከሰዓት በኋላ በትምህርት ቤት ውስጥ ታስተምራለች፤ ከዚያ እየሮጠች ወደ ሆስፒታል ትመጣለች፤ ወደ ቤቷ ተመልሳ ትንሽ ጋደም እስክትል ከእኔ ጋር ትቆያለች።

የነበሩብን ተግዳሮቶች በኒኮል ላይ ያለንን ኩራት እንዲጨምር አድርጎታል።

በሽልማቱ ሥነ ሥርዓት ወቅት ከተለመዱት ነገሮች አንዱ፣ አባቶች ልጆቻቸውን አጅበው በህዝቡ መካከል አልፈው ወደ ሽልማቱ ስፍራ ይሄዳሉ። ልጃገረዶቹ ወንድሞች ካሏቸውም ደግሞ እክሊሉንና ዘንባባውን ይዘው ከኋላ ይከተሏቸዋል።

የሳውዝ ፓርክ ቤተክርስቲያን ካወጣችው የሥነ ሥርዓቱ የጊዜ ሰሌዳ አንጻር ሲገመት፤ እንኳንስ አጅቤአት ወደ ሽልማቱ ሰገነት ልወጣ ይቅርና መገኘቴም አጠራጣሪ ነበር።



ዶክተሮቼ በሽልማት ሥነ ሥርዓቱ ላይ እንድገኝ ከሆስፒታል እንድወጣ ስለፈቀዱልኝ ምስጋናዬ ከፍተኛ ነው። በዚያ ለመገኘት ትልቅ መሻት ነበረኝ። እርግጥ ነው ያ የስርጓ ቀን አልነበረም፤ በወጣትነት ዕድሜዋ ውስጥ ግን ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ስፍራ ነው፤ እናም ያንን የደስታ ጊዜዋን አብሬአት ልካፈል በጣም እፈልግ ነበር።

በተሽከርካሪ ብስክሌቴ ላይ ተቀምጫለሁ፤ በሕዝቡ መካከል በማልፍበት ጊዜ ኒኮላ እጄን ይዛ ነበር። ክሪስና ጆይ ከኋላችን ነበሩ፤ የእርሷን አክሊል በትራስ ላይ አድርገው ይዘዋል። በተጨማሪም እኔ የተቀመጥኩበትን ብስክሌት በመግፋት እያገዟት ነበር። ሉፍ ኮት ለብሼ ከረባት አስሬአለሁ። ከአደጋው በኋላ ያ የመጀመሪያ ጊዜዬ ነበር። የለበስኩት ቱታ ሱሪ ለኤልዛሮቭ ፍሬሙ ሲባል የጎን ዚፕሮቹ ተፈተዋል።

ኒኮል እጅግ የተደሰተችው በሕይወቷ ወሳኝ በነበረው በዚያ ሥነ ሥርዓት ላይ አባቷ በመገኘቱ ብቻ ሳይሆን ይልቁን በአጠገቧ ሆኖ ወደ ሽልማቱ ሥፍራ አጅቧት እየሄደ ስለነበር ነው።

ከሽልማት መስጫ ሰገነቱ ላይ ሆኜ ቁልቁል ስመለከት እንባ በአይኖቼ ሞላ። ሌሎችም ሲያለቅሱ አዳምጥ ነበር። ይሁን እንጂ እናለቅስና እናፈስ የነበረው እንባ በኒኮል ሕይወት ወሳኝ ስለነበረው ጊዜ የደስታ እንደነበር አውቃለሁ።

ዶክተሮቼ በመጀመሪያ ወደ ቤቴ እንድሄድ ያደረጉበት ምክንያት ቤተሰቦቼ በዙሪያዬ ባሉበት ሁኔታ ውስጥ ቶሎ ያገግማል ብለው በማሰብ እንደሆነ አምናለሁ። በቤት መሆኔም የህክምና ወጭዬን በእጅጉ

የሚቀንስ ነበር። ለምን እንደሆነ እርግጠኛ ባልሆንም ከሆስፒታል በመውጣቴ በጣም ደስተኛ ነበርኩ። ለተደረገልኝ ህክምና ሁሉ ኢንሹራንስ አልነበረም ወጭዬን የሚሸፍነው። በመጀመሪያ የሠራተኞች ህብረት በኋላም የፌዴራሉ ፍርድ ቤት ጥፋተኞች እንደሆኑ ስለወሰነባቸው የቴክሳስ መንግስት ነበር ወጭውን የከፈሉት።

አሁንም እንኳን በራሴ ቤት ውስጥ እያለሁ ለእኔም ይሁን ለቤተሰቤ ይልቁንም ለኢቫ ሁኔታው ቀላል አልነበረም። በየቀኑ አንድ ሰው መርፌ ሊወጋኝ ያስፈልጋል። የሰውነት እንቅስቃሴ ልምምድን ማድረግ ይጠበቅብኛል ይህ ሁሉ በእኔ ላይ ሊደረግና ለእኔም ሊደረግልኝ ግድ ነበር። ሳሎናችን ወደ ሆስፒታልነት የተለወጠ ይመስላል። ያለ እንዳች እንቅስቃሴ ተቀምጬበት ከነበረው ከዚያ ሁኔታ ውስጥ በመውጣቴ ጥሩ እንደሆነ ተሰምቶኝ ነበር። በማውቃቸው ነገሮች መካከል መሆኔ መንፈሴን አነቃቃው። በአልጋዬ ላይ እንደሆንኩ በመስኮቱ አሻግሬ አካባቢዬን መመልከት ወይም ደግሞ ሊጠይቁኝ ወደ እኔ የሚመጡትን ነጭ ጋዋን ያልለበሱ ሰዎችን መመልከቱ ያስደስተኝ ነበር።

የህክምናው ቡድን እተኛበት የነበረውን አልጋና በላዩ ላይ ይተላለፍ የነበረውን ተደግፌ የምንቀስቀስበትን አግዳሚ ብረት ላኩልኝ - ሁኔታው ሁሉ ሆስፒታል ውስጥ በነበርኩበት ጊዜ እንደነበር እንዲሆን ተመቻቸ። ነርሶቹ በየዕለቱ ይጎበኙኛል፣ የአካል እንቅስቃሴዬን የሚከታተሉት ደግሞ አንድ ቀን እያለለሱ ይመጣሉ።

ፈጽሞ ከማይረሳኝ አስደሳች ትውስታዎቼ አንዱ ኢቫ ወደስራ በምትሄድበት ጊዜ ቀኑን ሙሉ ከእኔ ጋር ይውሉ የነበሩት መልካም ሰዎች ናቸው። የቤተክርስቲያናችን ሰዎች ኢቫ ወደ ማስተማር ሥራዋ



መመለስ ወይም ሥራዋን መልቀቅ እንዳለባት እንደተነገራት በሰሙ ጊዜ፣ ማድረግ የሚችሉትን ሁሉ ለማድረግ ወሰኑ።

የቤተክርስቲያናችን ቀዳሚ መጋቢ ሚስት የሆነችው ጂኒ ፎስተር በየቀኑ ከእኔ ጋር የሚውሉ ሰዎችን በማዘጋጀት እንዲረዱኝ አደረገች። ጂኒ፣ ያደራጀቻቸውን ሰዎች በቀልድ፣ "የደን ተቆጣጣሪዎች" እያለች ትጠራቸዋለች፣ አብዛኞቹ የቤተክርስቲያን ሴቶች ሲሆኑ ቀሪዎቹ ጥቂት ሰዎች ደግሞ ጡረተኞች ናቸው።

ኢቫ በማለዳ ከቤት ወጥታ የምትመለሰው ከለባት ሰዓታት በኋላ ነበር። የእንቅልፍ ሁኔታዬ የሚወሰነው የህመም ስቃዮን መቼ ተቋቁሚ እንደማሳልፈው ባለው ሁኔታ ላይ የተመሠረተ ነው - ከዚያ በኋላ አንቀላፋለሁ። በኋላ ላይ ግን ቀስ በቀስ ሁኔታው መልክ እየያዘ መጣ። በአጠቃላይ ከማለዳው ሁለት ወይም ሦስት ሰዓት ላይ እተኛለሁ፣ ከዚያ በአስር ሰዓት አካባቢ እነቃለሁ። "የደን ተቆጣጣሪዎች" በእንቅልፍ ላይ በምሆንበት በዘጠኝ ሰዓት አካባቢ ይመጣሉ። በቤቴ ውስጥ ምሣዬን ያዘጋጁልኛል ወይም ከቤታቸው ያዘጋጁትን ምግብ ያቀርቡልኛል።

አብዛኛውን ጊዜ ስነቃ አንድ ሩህሩህ ሴት ከአልጋዬ ግርጌ ተቀምጣ የእጅ ሥራዋን ስትሠራ ነው የማገኘው። ወይም ደግሞ አንድ በእድሜ ጠና ያለ ሰው ተቀምጦ ሀውስተን ክሮኒክል የተባለውን የአካባቢ ጋዜጣ ያነባል። በነቃሁ ጊዜ ጋዜጣውን ወደ ታች ዝቅዝቅ ያደርግና ፈገግ ብሎ፣ "እንዴት አደርክ፣ ምን ትፈልግ ይሆን?" ሲል ይጠይቀኛል።

በየዕለቱ የማየው ትህትና የተሞላው ፈገግ ያለ ፊት ይቀያየራል። በጎ ፈቃደኞቹ የተለያዩ ቢሆኑም እንኳን ዐላማቸው አንድ ነው። ዶንን መንከባከብና ብቻውን እንዳይሆን አብሮ መቆየት።

ከቀን ወደ ቀን አልጋዬ ላይ መሆኔ እየቀጠለ ሲሄድ፤ ሌሎች ለእኔ ምን ያህል እያደረጉ እንደሆነ ተገነዘብኩ:: በሆስፒታሉ ውስጥ በነበርኩበት ጊዜ፤ በአልቪን ቤተክርስቲያን የነበሩ ጓደኞቼ የቤት ዕቃዎቼን ወደ አዲሱ ቤት አንገዘውልኛል:: የቀድሞው ቤት ህንጻ ስለነበር ለአሁኑ ሁኔታዬ ወደሚመችበት ምድር ቤት ብቻ ወዳለው ቤት ተዘዋውረናል::

ቀን ቀን ካለሁበት የሳሎኔ የህክምና ክፍል ውስጥ ሆኜ በመስኮት ውጭ ውጭውን እመለከታለሁ:: ብዙውን ጊዜ ትኩረቴን የማደርገው በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ህንጻ ላይ እና አዋሳኞችን በነበሩት ማት ማለርና የእነርሱም ጓደኛ በሆነው በክሪስ አልስቶን አምሮ በተከረከመው የሳር አትክልት ስፍራ ላይ ነበር:: ክሪስ አንድ ቀን የዕቃ ማጓጓዣችንን ለመዋስ የመጣ አስመስሎ ወደ ፊልም ቤት ይዞኝ በመሄድ አስደሳች ጊዜ አደረገልኝ:: ፊልሙ ምን እንደነበር እንኳን አላስታውሰውም፤ ይሁን እንጂ ምን ያህል አስቦልኝ እንደ ነበር ግን ፈጽሞ እልረሳውም:: አንድ ጊዜ የቤታችን አጥር በከፍተኛ ንፋስ ተመትቶ በወደቀ ጊዜ፤ ማንንም ለእርዳታ ከመጥራታችን በፊት መልሶ እንዲስተካከል አድርገዋል:: በማገገም ላይ በነበርኩበት ጊዜ የተደረገልንን መልካምነት ሁሉ የሚያውቀው እግዚአብሔር ብቻ ነው::

ማለዳው ላይ ገና በአልጋዬ ውስጥ መንቀሳቀስ ስጀምር፤ ጠባቂዎቼ ተነስተው ጥርሶቼን እንዳጸዳና ፊቴን እንድታጠብ የጥርስ ቡርሹንና የመታጠቢያ ዕቃ ያቀርቡልኛል:: እስቀድመው ጭማቂውን በብርጭቆ ቀጥሎ ደግሞ ከበድ ያለ ምሣ ይመጣልኛል::



ከመገቡኝ፣ ካጣጠቡኝና አካላዊ ሁኔታዬ በፈቀደለኝ መጠን ዘና ማለቴን ካረጋገጡ በኋላ የተለመደውን ጥያቄ ይጠይቁኛል፤ "ከመሄዴ በፊት እንዳደረግልህ የምትፈልገው ተጨማሪ ነገር ይኖራል?"

የእኔም መልስ ሁልጊዜም አይለወጥም፤ "ምንም የለም አመሰግናለሁ" እላለሁ:: አለኝ የምለው የመጨረሻ ፈገግታ ነው ብዬ ተስፋ የማደርገውን ፈገግታዬን አሣያቸዋለሁ:: ምናልባትም አልተሳካልኝም ይሆን ይሆናል፤ እነርሱ ግን ሁልጊዜም በፈገግታ ይመልሱልኛል::

"ሁሉም ነገር ጥሩ ነው አሁን ይሻለኛል::"

የሰው ልጆች አንዳቸው ለሌላቸው የሚያደርጉት መስዋእትነትና የሚሰጡት አገልግሎት ስፋት ምንም ዐይነት ድንበር የለውም:: ከጉድለቶቻችን ሁሉ ጋር፤ በአደጋውና በማገገም ላይ በነበርኩበት ጊዜ ሰዎች ያደረጉልኝ መልካምነት፤ በእርግጥም እግዚአብሔር በመልኩ እኛ ን መፍጠሩን የሚያረጋግጥ ምሳሌ ነበር::

የዕለቱ የዶን ጠባቂ መላእክት ከቤት ከወጡ አንድ ሰዓት ያህል ጊዜ ቆይቶ በሩ ይከፈታል፤ ኢቫ ረዥሙን ጊዜ በት/ቤት ካሣለፈች በኋላ ወደ ቤት ትገባለች:: ሁልጊዜም ሞቅ ያለ ፈገግታ ካሳየችኝ በኋላ ትስመኛለች::

"እንዴት ነህ ዛሬ ... ሻል አለህ?" ስትል ትጠይቃለች::

"ደህና ነኝ" እላታለሁ የምሬን::

ከዚያ በኋላ ያለውን ስሜቴን በቃላት መግለጽ አልችልም፤ በዶን ጠባቂ መላእክት መኀብኘቴ የሚፈጥርብኝ እርግጠኝነት መንፈሴን ከፍ ያደርገዋል::

ወደ ቤቴ ከገባሁ ለወራት ያህል፤ መልካም ልብ ያላቸው የዶን ጠባቂዎች አባላት፤ በውሃ ውስጥ ለሚደረግልኝ የአካል ማፍታታት ህክምና በአሊቪን አካባቢ ወደሚገኘው ስፍራ ያመላልሱኝ ነበር:: በመጀመሪዎቹ አስራ ሦስት ወራት፤ በሆስፒታል ውስጥ ባልነበርኩባቸው ጊዜዎች ሁሉ በቤት ውስጥ በነበረው የሆስፒታል አልጋዬ ውስጥ እተኛ ነበር:: ለወራት ያህል ለህክምና ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር በቀን ውስጥ ከአምስት ደቂቃ በላይ ከአልጋ ውጭ የምሆንበት ሁኔታ አልነበረም:: አንዳንድ ቀን ጭራሹን ከአልጋዬ ውስጥ አልወጣም::

በጣም አስከፊው ነገር አንድ ጊዜ በሆስፒታሉ አልጋ ውስጥ ከገባሁ ሙሉ ለሙሉ ከእንቅስቃሴ ውጭ እሆናለሁ:: ቀና ማለት አልችልም ወይም በራሴ ማድረግ የምችለው ነገር የለም:: ከሃኪሞቹ እገዛ በስተቀር በጭራሽ ተነስቼ መቀመጥ ወይም በራሴ መንቀሳቀስ አልችልም::

በዝግታና ቀስ በቀስ እንደገና መራመድን ተለማመድኩ:: ከአልጋዬ ላይ በራሴ በወረድኩበት የመጀመሪያ ቀን እንደምንም ብዬ ሦስት እርምጃዎች ተራመድኩ:: ተመልሼ ወደ ኋላዬ በአልጋዬ ላይ ወደቅኩ፤ ድካሜ ወሰን አልነበረውም:፤ ይሁን እንጂ ፈገግ አልኩ::



መራመድ ቻልኩ:: ሦስት እርምጃ ማለት ትንሽ ማለት ይመስላል፤ ይሁን እንጂ የተሰማኝ ታላቅ የድል አድራጊነት ስሜት ነው::

በዚህ ዐይነቱ አደጋ ከደረሰ ችግር የማገገምን ሁኔታ አንድን ህፃን ከማለማመድ ጋር ተመሳሳይነት ያለው ነው:: ለረዥም ጊዜያት ተስፋ የለሽ ሆኜ ተቀምጬ ስኖር ሳለ በመጨረሻው በራሴ ወደ መጸዳጃ ቤት መሄድ ቻልኩ፤ ይህንንም እንደ ወሳኝ ድል ቆጠርኩት::

እንደገና መሄድ መቻሌ፤ አንድ ድል ብቻ አልነበረም፤ ይልቁንም እኔን ለመርዳት ያለ አንዳች ድካም ይሠሩ ለነበሩ በመቶ ለሚቆጠሩ የህክምና ባለሙያዎችም ክብር ነበር:: አንዱን እግሬን አንስቼ ከሌላ ፊት ማስቀደም ለእኔ ምን ያህል አስቸጋሪ እንደሆነ ባያውቁትም፤ በእኔ ይተማመኑ ለነበሩ ጓደኞቼና ቤተሰቦቼ ሁሉ ጭምር ታላቅ ክብርም ነው::

እኔ፣ መራመድ መቻልን የተወሰኑ ድሎችን እንደሚወክል አድርጌ ነው የምቆጥረው፤ ይህንንም ስል በመጠኑም ቢሆን እንደገና ወደ መደበኛው ሕይወት መመለሴን ነው የሚያሳየው:: ሁልጊዜም ወደ ኋላ መለስ ብዬ በትሪኒቲ ፒንስ የጉባኤ አዳራሽ ግቢ ውስጥ እኔና ጂ.ቪ. ቶማስ የነበረንን የመጨረሻውን የጉዞዬን ምሽት አስበዋለሁ:: ያ ከዚያ በኋላ ያልተራመድኩት የመጨረሻው የጤነኝነት እርምጃዬ ነበር:: ከአደጋው በኋላ ባሉ ለብዙ ወራት እንደገና ለመራመዴ ማንም ሰው እርግጠኛ አልነበረም:: በጣም ለረዥም ጊዜ እነኛን ሦስት እርምጃዎች የመራመዴ ጉዳይ ልክ ኤቨረስት ተራራን እንደወጣሁ ያህል የተቆጠረ ነበር::

"ተሳካልኝ!" ጸጥ ባለው ክፍል ውስጥ ጩኸቴን ለቀቅኩት::

"ተራመድኩ! ተራመድኩ እኮ!"

በቤቴ ውስጥ በራሴ እነዚያን ሦስት እርምጃዎች መራመዴ ቀስ በቀስ ከተፈጸመው የማገገሚያዬ ጊዜያቶች ሁሉ ትልቁን ስፍራ የያዘው ነው። እነዚያ ሦስት እርምጃዎች እንደገና ጤነኛ እንደምሆን አሳምነውኛል። አሁን ወደ ፊት ጠንክሬ ለመሥራት ዓላማ አለኝ። ያለፍኩበት የማገገም ሂደት እጅግ ዘግናኝ ነበር። ገናም ሁኔታዬ እየተሻሻለ እንደሚሄድ አውቃለሁ። በእያንዳንዱ ቀን ሌሎች ተጨማሪ እርምጃዎች አደረግኩ። በሳምንቱም መጨረሻ ላይ ሳሎኑን ሙሉ ለሙሉ መዞር ጀመርኩ።

ኢቫ ወደ ቤት መጥታ የእለቱን የተሻሻለ እንቅስቃሴዬን ሳደርግ በተመለከተች ጊዜ ያሳየችኝ ፈገግታ፤ የማራቶን ሩጫ ሮጬ ያሸነፍኩ ያህል እንዲሰመኝ ነው ያደረገኝ። በዚያ ከሰዓት በኋላ በፍጹም ደስታ ውስጥ ስትፍለቀለቅ ቆየች፤ እኔም በቤቱ ዙሪያ በራሴ መራመድ መቻሌን አሳየኋት።

ከሆስፒታሉ ወደ ቤት ከገባሁበት ከሳምንት በኋላ ወደ ቤተክርስቲያን ለመሄድና በእሁድ ማለዳ ፕሮግራም ለመሳተፍ ወሰንኩ።

ዛሬ ወደ ኋላ ዘወር ብዬ ሳስበው ያለጊዜው የተደረገ ውሳኔ ነበር፤ ነገር ግን ከምወዳቸው ሰዎች ጋር እንደገና አብሮ የመሆንና አብሮም የማምለክ በውስጤ የሚቀጣጠል መሻት ነበረኝ። ጥቂት ሰዎች ባሉበት ቡድን እረዳትነት ወደ ስፍራው እንዲወስዱኝ እቅድ አወጣን። ምን አልባት ሁኔታው የማይሳካ ከሆነ በሚል ስጋት ሌሎችን ሰዎች ግራ ላለማጋባት ለጉባኤው አስቀድመን ማስታወቂያ ላለመናገር ወሰንን።



አንድ ሰው ከአልጋዬ ውስጥ ሊያወጣኝና ሊያስገባኝ እስከቻለ ድረስ፤ በዚያን ጊዜ በተሽከርካሪው ብስክሌት ላይ በራሴ መቀመጥ እችላለሁ፤ ይሁን እንጂ ያኔም በራሴ መቆም አልችልም። ስድስት ሰዎች ከቤተክርስቲያን ወደ ቤታችን መጡ፤ ከቤተክርስቲያን ካሉ መኪናዎች አንዱን ይዘውም መጡ። በቤተክርስቲያን ውስጥም በበሮቹ ያለ ችግር መግባት የምችልበትን ሁኔታ አመቻችተውልኝ ነበር።

በእነዚህ ሰዎች' ላይ የጣልኩባቸውን ትልቅ ሃላፊነት ማሰብ ጀመርኩ፤ ደጋግሜም ይቅርታን እጠይቃቸው ነበር፤ እነርሱ ግን ይህን በማድረጋቸው ደስተኞች እንደሆኑ ይገልጹልኝ ነበር።

ከዚያ በኋላ የጂይን ቃላት ማሰብ ጀመርኩ። በአደጋው የመጀመሪያ ቀን ጓደኞቼና ቤተሰቦቼ መጥተው ተመለከቱኝ። ምን እመስል እንደነበረ በጭራሽ አላየሁም። ድንጋጤውንና ፍርሃቱን ሁሉ ታግሰው ተቋቋሙ። እንደምሞት ወይም እስከዘለቄታው አካለ ስንኩል ሆኖ ይቀራል በሚል ግምት መሪር ሃዘን አዘኑ። በተወሰነ መልኩ ይህ አሰቃቂ ክስተት ከእኔ ይልቅ አስቸጋሪነቱ ለቤተሰቦቼና ለጓደኞቼ ነበር። እኔን ለመርዳት ፍጹም ፈቃደኞች ነበሩ። በሌላ አቅጣጫ ከተመለከትነው፤ አሁን ያሳየሁት ለውጥ የእነርሱም ማገገም ነው፤ በመሆኑም ለእኔ አሁንም የተለየ ነገር ማድረጋቸውን እንደ ትልቅ ደስታ ነው የቆጠሩት።

በዚያ ማለዳ በአምልኮ ፕሮግራም ላይ ለመሳተፍ ከፍተኛ ፍላጎት ቢኖረኝም፤ ሰዎቼ ሁሉንም ነገር ለእኔ እንዲያደርጉልኝ ማድረግ አስቸጋሪ ነበር። ሙሉ ለሙሉ ምንም ማድረግ የማልችልና ሙሉ ለሙሉ በእነርሱ ላይ ራሴን የጣልኩኝ ነበርኩ። ያንን ሁኔታ ደግሜ ሳስታውሰው ፈገግ እላለሁ።

"እመሰግናለሁ" አልኳቸውና እንዲረዱኝ ሁሉን ነገር ተውኩላቸው።

በጥንቃቄ ከመኪናው ላይ አወጡኝ፤ እናም ወደ ቤተክርስቲያን ወስደው በኋላው በር በኩል አስገቡኝ። የመኪናውን በር አንድ ሰው ሲከፍት ወደ እምልኮው አዳራሽ ይሄዱ የነበሩ ሰዎች አዩኝ።

"ተመልከቱ! ፓስተር ዶን እኮ ነው!" ሲል አንድ ሰው ጮኸ።

ሰዎቹ በተንቀሳቃሹ ወንበር ላይ እየገፉ ሲወስዱኝ፤ መንገድ እየለቀቁ በምስጋናና በጭብጨባ ሲጮሁ እሰማቸው ነበር።

ከዚያ በኋላ ሁኔታዎች ሁሉ ድብልቅልቅ አሉ። ሰዎች እየሮጡ ወደ እኔ መጡ። እጅግ ብዙዎች እግዚአብሔርን ያመሰግኑ ነበር። እያንዳንዱ ሰው እኔን ለመንካት ወይ ለመጨበጥ የሚፈልግ ይመስል ነበር።

በመጨረሻው አንድ ሰው በተሽከርካሪው ብስክሌት እየገፋ ወስዶ በመድረክ ላይ ከኦርጋን መሣሪያው አጠገብ አስቀመጠኝ። እኔን ከብስክሌቱ ላይ ማንሳት የሚቻል ነገር አልነበረም።

ከዚያ በኋላ መላው የጉባኤ ተካፋይ በመድረኩ ላይ እንደወጣሁ አወቀ። ፈገግ እንዳልኩ እንዲህ ስል አሰብኩ፤ በትሪኒቲ ፒንስ ካደረጉት የመጨረሻ ጉባኤ ወደ ቤተክርስቲያኔ እስክቀላቀል ድረስ አምስት ወራት ፈጅተውብኛል። ምናልባት በጣም ዝግ ብዬ ይሆናል፤ ነገር ግን ታማኝ ነኝ።

ከዚህ በኋላ ደግሞ አንድ ሰው ወደ ጆሮዬ ጠጋ አለና፤ ለጉባኤው አንድ ነገር እንድትናገር እንፈልጋለን አለ። ወደ ኋላዬ ዞሮ ብስክሌቱን እየገፋ ወሰደና ከመድረኩ ፊት ለፊት አቆመኝ።



በዚያ ጊዜ ነበር የድካም ስሜት በውስጡ ሲፈስ የተሰማኝ። ምናልባትም ከቤቴ እሁን እስካለሁበት ስፍራ ባደረኩት ጉዞ ጉልበቴ አልቆ ይሆናል፤ ነገር ግን ተመልሼ በቤተክርስቲያን ለመገኘት ከነበረ ቁርጠኛነት የተነሳ፤ እየተሰማኝ የነበረውን የድካም ስሜት እምኜ አልተቀበልኩትም። ከአልጋ ውስጥ ከወጣሁ ከሁለት ሰዓት በላይ ተቆጥሯል። እስከዚያ ሰዓት ድረስ ከአልጋ ወጥቼ የቆየሁበት ረዥሙ ሰዓት ያ ነበር። በተጨማሪም በተሽከርካሪ ብስክሌት ላይ የቆየሁበትም ረዥሙ ጊዜ እርሱ ነው።

በዚያች ቅጽበት ወደ ቤተክርስቲያን ተመልሼ ለመምጣት በመወሰኔ የሞኝነት ሥራ እንደሠራሁ ተገነዘብኩ። ምክንያቱም ያን ለማድረግ በሰውነቴ አልጠነከርኩም ነበር። እልኸኝነቴ ቁርጠኝነቴን ከፍ አድርጌ እንዳይ አድርጎኝ ነበር።

ምናልባትም የዚያኑ ያህል ከፋ የሆነው ነገር፤ ጉባኤው የፍቅር ምላሹን የሰጠኝ ጊዜ ኃይለኛ በሆነ ስሜታዊ ማዕበል ውስጥ መግባቴ ነበር። መናገር መቻሌን እንኳን በእርግጠኝነት አላወቅኩም።

ለብዙ ሳምንታት በመካከላቸው ሳልገኝ ቆይቼና ደግሞም አሁን በማየውና በምሰማው ሁኔታ ውስጥ ሆኜ ምን ማለት እችል ነበር?

ይህንን ሁሉ በማገናዘብ ላይ በነበርኩበት ጊዜ አንድ ሰው የድምጽ ማጉያውን አምጥቶ በእጄ አስጨበጠኝ። መናገሪያውን አጥብቄ እንደያዝኩ እንዲህ ስል ማሰቤን ቀጠልኩ፤ እናንተ በዚህ ያላችሁ ሰዎች፤ እየተሻለኝ ለመሄዱና ለማገገሜ ያደረግኩት አስተዋጽኦ በጣም ጥቂት መሆኑን ገና አላውቃችሁም። እናንተ ድል እንዳደርኩ ቆጥራችሁታል። እኔ ግን የማየው በሕይወት መቆየት መቻሌን ብቻ ነው።

ከዚያ በኋላ ድንገት የፈነዳ የማያቋርጥ ጭብጨባ ተሰማ:: እኔን በማየታቸው የተሰማቸውን ደስታ ለመግለጽ ያደረጉት ነው የመሰለኝ:: እንደዚያ ባለ ሁኔታ ለእግዚአብሔር የቀረበውን ምስጋና ለመቀበል ዝግጁ አልነበርኩም:: በህንጻው ውስጥ የነበረው ሰው ሁሉ ቆሟል ጭብጨባውም ቀጥሏል ለረዥም ጊዜም ያለማቋረጥ ዘልቀዋል:: በመጨረሻም እንዲያቆሙ እጄን በማወዛወዝ ምልክት አሳየኋቸው::

ወደ እነርሱ ትኩር ብዬ ስመለከት፣ ስለጭብጨባቸውና ስለ ታላቁ ደስታቸው የህሊና ወቀሳ ተሰማኝ:: እነኛ ሰዎች ለእኔ ማጨብጨባቸውን ማመን አልቻልኩም:: ቢያውቁ ኖሮ . . . ቢያውቁ ኖሮ፣ ስል አሰብኩ::

ከዚያ እግዚአብሔር ተናገረኝ:: የእግዚአብሔርን ድምጽ በውስጤ በግልጽ ከሰማሁበት ጊዜዎች አንዱ ነበር::

"የሚያጨበጭቡት ለአንተ አይደለም"

የሰማሁት እነኝህን ቃላት ብቻ ነው፤ ነገር ግን ልዩነት ያመጡ ቃላት ነበሩ፤ እናም መናገር ቻልኩ:: በመጨረሻው ሁሉም ነገር ግልጽ ሆነልኝ:: እግዚአብሔር ለእኔ ስላደረገው ነገር ሁሉ ምስጋናን እያቀረቡ ነበር:: እግዚአብሔር እንደገና አንድ ጊዜ ከሞት ወደ ሕይወት መለሰኝ:: ትንሽ ዘና አልኩ:: ያ እግዚአብሔርን የማመስገን ጊዜ ነበር:: እኔን ለማግነስ የተደረገ ነገር አልነበረም::

ጭብጨባው እስኪቆም ድረስ ረዥም ለሚመስል ጊዜ መጠበቅ ነበረብኝ:: አራት ቃላትን ብቻ ነበር የተናገርኩት:: በዚያ የተከበረ ቀን በዚያ የነበረ ማንኛውም ሰው ቃላቶቹ ምን እንደነበሩ ይነግራችኋል፤ "እናንተ ስለጸለያችሁ በዚህ አለሁ::"



ጉባኤው እንደገና ጭብጨባውን አስተጋባው:: ሌላ ነገር ጨምሬ ብናገርም እንኳ ማንም ሰው እንደማይሰማኝ እርግጠኛ ነበርኩ::

ልናገረው አልቻልኩም፤ ይሁን እንጂ በዚያ ጊዜም ይሁን አሁን ድረስ፤ ልተርፍ የቻልኩት በርካታ ሰዎች እንድተርፍ በመፈለጋቸው ምክንያት መሆኑን አምናለሁ:: ድካም የማያውቁ፣ ፍቅርን የተሞሉና ተስፋን የማይቆርጡ እንዲሁም እግዚአብሔር እንደሚሰማቸው የሚያምኑ ሰዎች ነበሩ:: ከዚያ በፊት የምር ጸልየው የማያውቁ ሰዎች እንኳን ለእኔ ጸልየዋል:: አንዳንዶቹም ለዓመታት ያህል የምልጃን ጸሎት ጸልየው የማያውቁ ናቸው፣ እግዚአብሔር እንዲምረኝ ለእኔ ግን ይጮኹ ነበር:: በእኔ ላይ የደረሰው ነገር ሰዎችን በጉልበታቸው እንዲወድቁ አደረገ፤ እናም አብዛኞዎቹ በዚህ ሂደት ውስጥ ለእኔ በመጸለይ የጸሎት ሕይወታቸው ተቀይሯል::

በሕይወት መኖር በቻልኩ ጊዜ፤ የጸለዩልኝ እነዚያው ሰዎች፤ በተለይም አስቀድሞ እምብዛም የመጸለይ ልምድ ያልነበራቸው፤ ያ ልምምዳቸው የጸሎት ነገራቸውን ወደ አዲስ እመርታ እንደቀየረው ተናግረዋል:: አንዳንድ ሁኔታዎችን ስንመለከት፤ በኮተንውድ፣ በአሪዞና፣ በቡፋሎና በኒዬርክ የነበሩ፤ ፈጽሞ የማላውቃቸው የደረሰብኝን ነገር የሰሚ ሰሚ የሰሙ ናቸው:: ቀጥሎ በነበሩት ሦስት ዓመታት ሰዎች ወደ እኔ እየቀረቡ፤ "በቪዲዮ በተሠራጨ ቃለ ምልልስ ውስጥ ተመልክቼሃለሁ፤ እጸልይልህ የነበርከው ሰው አንተ ነህ!" ይሉኛል:: ወይም ደግሞ የእኔ ቤተክርስቲያን ያስራጨችውን ቴፕ ክር አድምጠው ከሆነ፤ "አንተ ነገሩ ምን እንደሆነ ላታውቅ ትችላለህ:: እግዚአብሔር ጸሎታችንን ሰምቷል፤ አንተም በሕይወት በመኖርህ በጣም ደስተኞች ነን" ይሉኛል::

አንዳንድ ግለሰቦች፤ እኔ ሰው ብቻ ሳልሆን ምሳሌ አድርገው ነው የሚ.ቆጥሩኝ:: ለእነርሱ እኔ የጸሎት መልስ ነኝ:: በሳውዝ ፓርክ ቤተክርስቲያን የነበረኝን አገልግሎት ያስታውሱ ይሆናል ወይም ደግሞ ምናልባት የሰብኳቸውን አንዳንድ ስብከቶችም አድምጠው ይሆናል:: ነገር ግን አብልጠው ያስታውሱ የነበረው ነገር የእግዚአብሔርን ፊት ለመፈለግ አጥብቀው፣ በትህትናና በቁርጠኝነት የጸለዩበትን ሁኔታ ነው:: እኔ በሕይወት እንድኖር ለእግዚአብሔር ልመናን አቀረቡ - እናም በሕይወት አለሁ:: እንዴት በሕይወት እንደኖርኩ አላውቅም፤ ማለት የምችለው ይህ ነገር ከእኔ ውጭ የሆነና ከእኔም አቅም በላይ የተከናወነ ነው::

እንደገናም ደግሞ ሰዎች እንዲመለሱላቸው ለሚፈልጓቸው ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት የተገባኝ ሰው እንደሆንኩም አስባለሁ::

በመንግስተ ሰማይ ስለነበረኝ ቆይታ ለሰዎች መናገር ከጀመርኩበት ጊዜ አንስቶ፤ ወደኔ እየመጡ፤ "መንግስተ ሰማይ በእርግጥ እውን ናት?" እያሉ የጠየቁኝን ሰዎች ቁጥር ማስላት አልችልም:: በእውነት መንግሥተ ሰማይ ምን ትመስላለች? እያሉ ይጠይቁኛል ወይም ደግሞ የተለዩ ጉዳዮችን ማለትም "ለእግዚአብሔር ይቀርብ ስለነበረው ምስጋና" ወይም "ከወርቅ ስለተሠሩት መንገዶች" ይጠይቁኛል አንዳንድ ሰዎች በቅርቡ የተለዩዋቸውን የሚወዷቸውን ሰዎች ሁልጊዜም ደጋግመው የሚጠቅሱዋቸው ይመስላሉ::

እኔ በእዚያ እንደነበርኩ ማወቃቸው፤ ወደ ምድር መመለሴና ከእነርሱም ጋር ለመነጋገር የመቻሌ ነገር ለብዙዎች ጥልቅ የሆነ መጽናናት ያመጣላቸው ይመስላል:: አንዳንዴ ለኔም ግርም ይለኛል::



ሌሎች ደግሞ ዛሬ ድረስ በሰውነቴ ላይ ያሉትን ጠባሳዎች ከተመለከቱ በኋላ፤ በዚህ ሁሉ ነገር እልፈህ በሕይወት በመቆየትህ፤ "አንተ ራስህ ተአምር ነህ!" "አንተ ተጓዥ ተአምር ነህ!" ይሉኛል::

# 12

# መንገዱ ተከፈተ

"ድንኳን የሚሆነው ምድራዊ መኖሪያችን ቢፈርስ በሰማይ ያለ በእጅ ያልተሠራ የዘላለም ቤት የሚሆን ከእግዚአብሔር የተሠራ ህንጻ እንዳለን እናውቃለን። በዚህ ውስጥ በእውነት እንቃተታለንና፤ ከሰማይም የሚሆነውን መኖሪያችንን እንድንለብስ እንናፍቃለን፤ ለብሰን ራቁታችንን አንገኝም። በእውነትም የሚሞተው በሕይወት ይዋጥ ዘንድ ልንለብስ እንጂ ልንገፈፍ የማንወድ ስለሆነ በድንኳኑ ያለን እኛ ከብዶን እንቃተታለን"

2ቆሮ 5፥1-4

እግዚአብሔር የቅርብ ጓደኛዬ የሆነውን ዴቪድ ጂንቲልስን ተጠቅሞ በሕይወት እንድኖር አደረገ፤ ስለዚህ ነገር አመሰግናለሁ። እንደገናም ደግሞ በግምት ከአደጋው ከሁለት ዓመታት በኋላ በሕይወቴ የተጠቀመበት ይህንኑ ሰው ነበር።

ከዚያ በፊት መንግስተ ሰማይ ስለመድረሴ ለማንም ሰው አልተናገርኩም። ጠቅለል ባለ መልኩ ለኢቫ ነግሬአለሁ፤ ነገር ግን ሁልጊዜም እርሷ ጥያቄ ከመጠየቋ በፊት ነበር ጭውውታችንን ፊጥኜ የምዘጋው። እርሷ እኔ ሳልናገራትም ያጋጠመኝ ነገር ከመታወቅ የሚያልፍ እንደነበረ ተረድታዋለች። ሌላ አንዳች ተጨማሪ ነገር እንድናገር ባለመጫኗ ላመሰግናት እወዳለሁ።

ከኢቫ ልደብቀው የምፈልገው ኖሮኝ አልነበረም፣ ጉዳዩ፤ ስለ መንግስተ ሰማይ ልምምዴ መናገር አልችልም ነበር። በዚያ ጊዜ



ሁኔታው እጅግ የሚያስፈራ በመሆኑና እርሱን ለመግለጽ መሞከር ክስተቱን ሊያሳንሰው ይችላል የሚል ስሜት ነበረኝ።

ከሆስፒታል ከወጣሁ ከአንድ ዓመት ተኩል በኋላ ዴቪድ ወደ ሀውስተን አካባቢ ለደቀመዝሙር ሳምንት ጉባኤ መጣ። ይህንን ያደረገው ሁኔታውን በመጠቀም ወደ ቤቴ መጥቶ ሊጎበኘኝና ጥቂት ሰዓቶችን አብረን እንድናሳልፍ በማሰብ ነው።

ሁለታችን ብቻችንን በሆንን ጊዜ፤ በቀዶ ህክምናው ክፍል ውስጥ በነበርኩበትና ከእርሱ ጋር በተገናኘን ጊዜ፣ ከዚያ በላይ መቀጠል እንደማልችል የነገርኩት ነገር ትዝ አለኝ። በዚያ ጊዜ ነበር በዚህ ጉዳይ ላይ እንደሚጸልይልኝ የነገረኝ ስለዚያን ቀኑ ነገር አወራን፤ ስለጓደኝነቱና ስላደረገልኝ ያላሰለሰ ፀሎት አመሰገንኩት።

"አሁን እንዴት ይሰማሃል?" ሲል ጠየቀኝ።

"የህመም ስሜት" ፈገግ ለማለት እየሞከርኩም፤ "እኔ ሁልጊዜም በህመም ስሜት ውስጥ ነኝ፤ ይሁን እንጂ አሁን የከፋው ችግሬ እርሱ አይደለም" አልኩት።

ወደ እኔ ጠጋ አለና፤ "የከፋው ችግር ምንድን ነው?" አለኝ። "በቃ ወዴት እየሄድኩ እንደሆነ አላውቅም፤ ስለ መጻኢ ሕይወቴ ጥርት ያለ መመሪያ አላገኘሁም።"

ዴቪድ ምን ማድረግ እንደምፈልግ፣ በአካል ጉዳቴ ምክንያት ማድረግ የማልችላቸውን ነገሮችና በሳውዝ ፓርክ ቤተክርስቲያን መቀጠሌን እግዚአብሔር ይፈልገው እንደሆነ እርግጠኛ አለመሆኑን ስነግረው ያደምጠኝ ነበር። በዚያ ተወዳጅና ተፈላጊም ሰው እንደሆንኩ፤

ነገር ግን መሆን የሚገባኝ በዚያ ስፍራ ስለመሆኑ እርግጠኛ እንዳልሆንኩ አጫወትኩት::

ለረዥም ጊዜ ዝም ብሎ ሲያዳምጠኝ ከቆዬ በኋላ፤ "ከአደጋውና ከማገገምህም የተማርከው ነገር ምን ነበር?" ሲል በትህትና ጠየቀኝ::

ለሦስትና ለአራት ደቂቃዎች ያህል ብዙ ነገሮችን በተለይ ደግሞ ሌሎች ሰዎች በእኔ ጉዳይ እንዲገቡ ስለመፍቀዴና እንዲረዱኝም መንገድ ስለመክፈቴ ነገርኩት:: በመቀጠልም፤ ነገር ግን በዚህ ሁሉ ስቃይና ተስፋ በመቁረጥ ሁኔታ ውስጥ፤ "መንግስተ ሰማይ እውን መሆኗን አውቄአለሁ" አልኩት::

ቅንድቦቹን በአግራሞት ከፍ አድርጎ "እንደዚህ ስትል ምን ማለትህ ነው?" ሲል ጠየቀኝ::

ቀስ በቀስ ፈራ ተባ እያልኩ በጥቂቱ በጣም ጥቂት - በመንግስተ ሰማይ ስለነበረኝ አጭር ቆይታ አጫወትኩት:: "እባክህ ጨምረህ ንገረኝ" አለ:: ጓደኛዬ ስለነበር ስለጉዳዩ እንዲያውቅ እፈልግ ነበር:: እንዲሁም ደግሞ ስለ መንግስተ ሰማይ ለዴቪድ ብነግረው እጅግ በርካታ ሰዎች ሊረዱኝ ከሚችሉት ይልቅ እርሱ ሊረዳኝ ይችላል ስል ገምቻለሁ::

"በአደጋው ወቅት ሞቼ ነበር:: ቀጥሎ በነበረው ቅጽበት ግን በመንግስተ ሰማይ ነበርኩ" አልኩት::

ወደ እኔ ተጠጋ፤ በጸጥታ ሆኖ ቀጣዩን ነገር እስክናገር ይጠብቅ ነበር:: በአይኖቹ ውስጥ የሚያበራው ደስታ ይታየኝ ነበር::

ብዙ በነገርኩት መጠን፤ ብዙ ለመስማት ያለው ጉጉት እየጨመረ ሄደ:: ዛሬ ሁኔታውን ወደ ኋላ መለስ ብዬ ሳስበው፤ ዴቪድ



በመንፈሱ ሃሴት ያደረገበት ምክንያት በሁለት ምክንያቶች ማለትም እኔ ደግሜ እያረጋገጥኩለት ስለነበረው የመንግስተ ሰማይ እውነታና ከረዥሙ የስቃይ ሁኔታዬ ውስጥ መልካም ነገር እንደወጣ በማወቁ እንደሆነ አምናለሁ::

በመንግስተ ሰማይ ስለነበረኝ ቆይታ ካጫወትኩት በኋላ ምንም ነገር አልተናገረም፤ በመሆኑም ስላም ያለው ጸጥታ ክፍሉን ሞላው:: በወዳጅነታችን መካከል ያለውን ክፍተት በቃላት ልንሞላው የምንችል ዐይነት አልነበረም::

በመጨረሻው ዴቪድ ራሱን በአዎንታ ነቀነቀና፤ "ስለዚህ ነገር አስቀድመህ ያልተናገርከው ለምንድን ነው?" ሲል ጠየቀኝ::

"ሁለት በጣም ጠንካራ የሆኑ ምክንያቶች አሉኝ:: አንደኛው በመንግስተ ሰማይ ስለነበረኝ ቆይታ እየዘርኩ ማውራት ብጀምር ሰዎች እንደ እብድ ይቆጥሩኛል:: "

"ግን ለምን እንደዚያ አሰብክ?" ለምሳሌ አሁን እኔ ሰማሁህ፤ እንደምትለው ግን አልቆጠርኩህም::

ሁለተኛው ምክንያቴ፤" አልኩት የጀመረውን አቋርጬው፤ "ስለዚያ ክስተት እንደገና መናገር ስለማልፈልግ ነው:: ... ማለቴ በጣም ግላዊ የሆነ ነገር ነው:: በጣም የተለየ:: ይህ ነገር እኔ ራሴ እንኳን ሙሉ በሙሉ ልረዳው የቻልኩት ነገር አይደለም:: እኔ ሁኔታውን ለመናገር ባለመፈለጌ ምክንያት አይደለም፤ ነገር ግን ይህን ማድረግ እንደምችል አላስብም::"

"ይህን ነገር ለሌሎች ማካፈል ካልቻልክ መንግስተ ሰማይን ያየኸው ታዲያ ለምን እንደሆነ ታስባለህ?"

"ለዚያ ጥያቄ መልስ የለኝም"

"ለምን?"

"ራሴን የጠየቅኩትን የተሻለ ጥያቄ ልነግርህ እችላለሁ፤ ለምን ወደ መንግስተ ሰማይ ገባሁ? ለምንስ እንደገና ከእኔ ተወሰደች? ያ ሁሉ ሁኔታ ለምን ተከሰተ? ምንስ ማለት ነው?" ለወራቶች በውስጤ ተቀብሮ የቆየ ልቆጣጠረው ያልቻልኩት ቁጣ ገንፍሎ ወጣ፤ ውስጣዊ ስቃዬ ሁሉ ገፍቶ ተገለጠ:: ጥሩ፤ በዚህ ሁሉ ነገር ውስጥ ያለፍኩት ለምንድን ነው? ክብሩንና ውበቱን ተመልከቻለሁ፤ እጅግ ኃይል፤ በሕይወት ሊታይ ከሚችለው ነገር ሁሉ እጅግ በላጭነት ያለው ልምምድ ነው - እና ከዚህ ሁሉ በኋላ ተመልሼ መጣሁ:: ለምን? ለዚህ?" ወደ እጄና ወደ እግሬ አመለከትኩት:: ስማ ሕይወቴን ነጥቆ በወሰደ አደጋ ውስጥ ነበርኩ:: ፈጥኜ ነበር ወደ መንግስተ ሰማይ የተጓዝኩት:: እናም ከምገምተው በላይ ሁሉም ነገር እጅግ ታላቅና አስደናቂ ነበር:: የመንግስተ ሰማይን አስገራሚ ውበት አይቻለሁ፤ እና እንደገና ተጎትቼ ወደዚህ ሕይወት መጥቻለሁ:: አካሌ በብዙ ተጎድቷል:: በማያቋርጥ የህመም ስቃይ ውስጥ ነኝ:: ከዚህ በኋላ እንደገና ሙሉ ጤነኛና እንደቀድሞው ጠንካራ ልሆን አልችልም:: አሁንም በዚህ ሁኔታ ውስጥ እያለፍኩ አለሁ፤ ምክንያቱም ... ምክንያቱም፤ እውነቱን ለመናገር ሁሉም ነገር ስቃይ ነው የሆነብኝ::"



ዴቪድ አትኩሮ ሲመለከተኝ ቆየና፤ "የመንግስተ ሰማይ ቆይታህን የማትናገር ከሆነ፤ ወደዚያ የሄድከው ለምን እንደሆነ ታስባለህ? ሲል ደገመና ጠየቀኝ::

"ቅድም እንደነገርኩህ ለዚህ ጥያቄ መልስ የለኝም" ::

"እግዚአብሔር ወደ መንግስተ ሰማያት የወሰደህና መልሶም ወደ ምድር ያመጣህ በአንተ የደረሰውን ነገር ሁሉ ለሰዎች እንድትናገር ሊሆን አይችልም? ለሌሎች ምን ያህል ታላቅ መጽናናት ልትሆን እንደምትችልስ አትገነዘብምን?"

የተናገራቸው ቃላት አስደነገጡኝ:: በጣም አትኩሬ የነበረው በራሴ ላይ ነበር፤ ስለማንም ሌላ ሰው አስቤ አላውቅም:: ምን እንደተሰማኝ ልነግረውና ለእራሴም ለማስረዳት በሞከርኩ ጊዜ ውስጤ ባዶ ሆኖ አገኘሁት:: እናም በእርሱ ፊት ማልቀስ ጀመርኩ፤ ደግሞ ትክክል እንደነበር አውቃለሁ::

ከዚያ በኋላ ለሃያ ደቂቃዎች ያህል ተወያየንበት:: ዴቪድ ይገፋፋኝ ጀመር፤ ምንም እንኳን ትክክል እንደሆነ ባውቅም፤ የመንግስተ ሰማይ ቆይታዬን ለመግለጽ ለእኔ ቀላል ነገር አልነበረም::

በመጨረሻው ዴቪድ፤ "ከእኔ ጋር ቃል ኪዳን እንድታደርግ እፈልጋለሁ" አለ::

"ምን አይነት ቃል ኪዳን?"

"በጣም ቀላል:: የምታምናቸውን ሁለት ሰዎች ምረጥ:: የመንግስተ ሰማይ ልምምድህን በጥቂቱ አጫውታቸው፤ ከዚያ በኋላ ምን እንደተሰማቸው የራስህን ግምገማ ውሰድ":: ሰዎቹ እንደ አብድ

ከቆጠሩኝ ወይም ቅዠታም እንደሆንኩ የሚቆጥሩኝ ከሆነ ከዚያ በኋላ ለማንም መናገር እንደማይገባኝ ገለጸልኝ።

"ነገር ግን በአንተ ደስ የሚላቸው ከሆነ" አለ፤ "ጨምረህ እንድትነግራቸው የሚጠይቁህ ከሆነ፤ ይህንን እንደምልክት እንድትቆጥረው እፈልጋለሁ፤ እግዚአብሔር በመንግስተ ሰማይ በቆየህባቸው ዘጠና ደቂቃዎች ያየኸውን ለሰዎች እንድትናገር መፈለጉን የሚያሣይ ምልክት።" ጉዳዮን በጥንቃቄ ካሰላሰልኩት በኋላ ከእርሱ ጋር ቃል ኪዳን አደረኩ፤ "ያንን ማድረግ እችላለሁ።"

"መቼ?"

"ፈጥኜ እንደማደርገው ቃል እገባለሁ"።

"በጣም ፈጥነህ እንደምታደርገው እርግጠኛ ነህ?" ።

"ጥሩ፤ እንደማይዘገይ ቃል እገባለሁ"።

ዴቪድ ጸለየልኝ፤ እናም ሲናገር አደምጠው ነበር፤ በእርግጠኝነት አሸንፎኛል። ጉዳዩ ከዚህ በኋላ የምርጫ ጉዳይ አይደለም፤ የግድ መናገር አለብኝ በራሴ መንገድ ላደርገው ግድ ነው።

በመጀመሪያ የተቀደሰውን ሚስጥሬን የማካፍላቸውን የማምናቸውን ሰዎች ወሰንኩ። አንድ ጊዜ ቁጥራቸው ጥቂት እንዲሆን ከወሰንኩ በኋላ፤ አቀራረቤን ጥንቃቄ የተሞላበት አደረኩ። የምነግራቸው ለእያንዳንዳቸው በግል መሆን እንደሚገባው አረጋግጫለሁ። ጤንነቴ ትንሽ እስኪሻሻል ድረስ ጠበቅኩ፤ ደግሞም እለት እለት እየተሻለኝ ነበር። ከዚያ በኋላ፤ "ታውቃለህ፤ በዚያ ቀን እኮ ሞቼ ነበር። የነቃሁት



ደግሞ በመንግስተ ሰማይ ነው" የመሳሰሉትን ቀለል ያሉ ነገሮች መናገር ጀመርኩ።

የሰዎቹ ምላሽ ሁልጊዜም ተመሳሳይ ነበር፤ "እባክህ ጨምረህ ንገረኝ"። ሁልጊዜም ይህንን ቃል ይናገሩት ነበር ማለቴ አይደለም፤ ይሁን እንጂ የሚፈልጉት ይህንን ነበር። ዓይኖቻቸው በአግራሞት ሲፈጡ እያለሁ፤ እናም ተጨማሪ መስማት ይፈልጋሉ።

ጥቂት ጨመር አድርጌ በነገርኳቸው ቁጥር፤ ስለ አእምሮዬ ጤንነት ተጠራጥሮ የጠየቀኝ ማንም የለም። ማናቸውም ቢሆኑ ቅዥታም እንደሆንኩ አልተናገሩም።

"ይህንን ነገር ለሰዎች መናገር ይገባሃል አለኝ" አንደኛው።

"ይህ ያየኸው ነገር ለአንተ ብቻ አይደለም" ሌላው ጓደኛዬ ደግሞ አስተያየቱን ሰጠ። "ለሁላችንም ነው። ለእኔ ነው"።

በቀጣዮቹ ሁለት ሳምንታት እያንዳንዳቸውን ባዳመጥኩ ጊዜ፤ ወደ ኋላ ተመልሼ በሆስፒታሉ ውስጥ ጂይ በገሰጹኝ ጊዜ የነበረውን ሁኔታ ማገናዘብ ጀመርኩ። በዚያ ጊዜ ማንም እንዲረዳኝ አልፈቀድኩም፤ ያ ደግሞ ራስ ወዳድነት ነበር። በዚህ ጊዜ ደግሞ በእኔ ሕይወት የሆነውን ነገር ለሌሎች አላካፈልኳቸውም ይህም ደግሞ ራስ ወዳድነት ነበር።

"ጥሩ፤ ስለዚህ ጉዳይ እናገራለሁ" ስል ለራሴ ቃል ገባሁ።

በአንጻሩ ደግሞ ሁሉም ሰው በመኪና አደጋ እንደደረሰብኝ ያውቅ ስለነበር፤ በመንግስተ ሰማይ የነበረኝን ቆይታ ለመናገር ውይይት እንደመክፈቻ አጋጣሚ ተጠቀምኩበት፤ በተለይም በመጀመሪያው አካባቢ

ስህተት ላለመፍጠር ጥንቃቄ አድርጌአለሁ። ሰዎች ፍጹም ደስተኞች መሆናቸውን በማሳየት የድጋፍ ምላሽ በሰጡኝ ጊዜ፤ ታሪኬን ለማካፍላቸው ለሰዎች ይበልጥ ግልጽ እየሆንኩ ጥንቃቄ ከማድረግ እየላላሁ መጣሁ። ነገሮችን ሁሉ ግልጽልጽ አድርጌ ማብራራት እንደሚጠበቅብኝ ስለማውቅ ሁሉን በግልጽ መናገር እፈልግ ነበር፤ ይሁን እንጅ ይህ ለእኔ ቀላል ነገር አልነበረም። አሁን እንኳን ከዓመታት በኋላ በሕይወቴ የሆነውን ነገር በጥልቀትና በግልም ለመናገር ከተፈጥሮ አቅሜ በላይ ይሆንብኛል። ዛሬ የመንግስተ ሰማይ ልምምዴን የምናገርበት ምክንያቶች አንደኛ ሰዎች ከጠየቁኝ ብቻ ነው፤ ይህም ብቻ ሳይሆን ያ ሰው በእርግጥ ሁኔታውን ለማወቅ መፈለጉ ከተለማኝ ጭምር ነው። እንዲህ ካልሆነ አሁንም ቢሆን ለማንም አልናገርም።

ይህኛው የምክንያቱ ክፍል ይህንን መጽሐፍ ለመጻፍ ለብዙ ዓመታት በውስጤ ጉዳዩ እንዲብላላ ያደረገ ነው። አሁን በሕይወት ያለሁበት ዋንኛ ምክንያት በመንግስተ ሰማይ የነበረኝ ልምምድና ወደ ምድርም የመመለሴ ነገር እንዲሆን አልፈለግኩም። ይልቁን በተቃራኒው፤ ይህ ከሕይወት የተለመደ ነገር የወጣ ግላዊና ለእኔ ብቻ እጅግ ቅርብ የሆነውን ልምምዴን ወደ ኋላ ተመልሼ እያስብኩ ደጋግሜ መናገሩ ለእኔ የሚመች ነገር አድርጌ አልቆጠርኩትም።

ያንን የሕይወት ልምምዴን በአደባባይና በግልም ለሰዎች ተናግሬአለሁ። የሆነውን ነገር አስመልክቼ ጽሑፍ አዘጋጅቻለሁ፤ ምክንያቱም በተለያዩ ምክንያቶቻቸው ታሪኬ ለእነርሱ ዋጋ ያለው ነገር መሆኑን በማወቄ ነው። ለምሳሌ ያህል፤ በርካታ ሰዎች ባሉበት ሥፍራ በተናገርኩ ጊዜ፤ ቢያንስ ቢያንስ በዚያ ስፍራ በቅርቡ የሚወደው ሰው



የሞተበት እናም የዚያ ወዳጁ ፍጻሜ ምን እንደሆነ ማረጋገጫ የሚፈልግ አንድ ሰው ይኖራል።

ንግግሬን በምጨርስበት ጊዜ፤ እኔን ለማነጋገር ሰዎች ፈጥነው የሚሰሯቸው ሰልፎች አሁን ድረስ ይገርመኛል። ወደ እኔ የሚመጡት እንባ በአይኖቻቸው ተሞልቶ ነው፤ በፊታቸውም ላይ የሃዘን ድባብ ያጠላበታል። እነርሱ በሰላም እንዲሞሉና እርግጠኞች እንዲሆኑ ማድረግ በመቻሌ ደስታ ይሰማኛል።

የምናገራቸው ቃላት ወደሰዎቹ መረጋጋትን እንደሚያመጣ አምኜ ተቀብያለሁ፤ ይሁን እንጂ ይህንን አደርገዋለሁ ብዬ በጭራሽ አስቤውም አላውቅም። ዴቪድ ጂንቲሊስ ባያበረታታኝ ኖሮ እርግጠኛ ነኝ እስከ ዛሬም ድረስ ቢሆን ለማንም አልናገርም ነበር።

እኔን በማነሳሳቱም ለእርሱ ምስጋና አቀርባለሁ፤ ምክንያቱም ውጤቱን በአምልኮ ጉባኤዎች ላይ ብቻ ሳይሆን በቀብር ስፍራዎች ላይ በተገኘሁባቸውም ሁኔታዎች ውስጥ ተመልክቼዋለሁ። እንደ እውነቱ ከሆነ፤ ያ የሕይወት ልምምዴ የእኔንም የሕይወት ገጽታ በእጅጉ ለውጦታል። በቀብር ሥፍራ ላይ አደርግ የነበረውን ነገር ቀይሬአለሁ። አሁን ስለመንግስተ ሰማይ የአይን ምስክር በመሆኔ እንደ ባለ ስልጣን እናገራለሁ።

ተአምራዊ ከሆነው የግል ልምምዴ በተጨማሪ፤ በመንግስተ ሰማይ ጉዞዬ አማካይነት አራት ነገሮች ጎልተው ሊታዩኝ ችለዋል። የመጀመሪያው በእርግጠኝነት እግዚአብሔር ጸሎትን እንደሚመልስ አምኛለሁ። እኔ አሁን በሕይወት ያለሁት እግዚአብሔር ጸሎትን በመመለሱ ምክንያት ነው። በሁለተኛ ደረጃ፤ እግዚአብሔር አሁንም ተአምራዊ በሆነ ሥራ ላይ መሆኑን ያለ አንዳች ተጠየቅ አምኛለሁ።

በጣም ብዙ ሰዎች በመጽሐፍ ቅዱስ የተጻፉትን ተአምራት ካነበቡ በኋላ፤ "ይሄማ መጽሐፍ ቅዱስ በተጻፈበት ዘመን እግዚአብሔር የሠራበት መንገድ ነው" እያሉ ያስባሉ። እግዚአብሔር መደበኛ ከሆነው ነገር በላይ መሥራት መቀጠሉን እምኛለሁ። በእያንዳንዱ ቀን በተአምር በሕይወት ስለመኖሬ፣ መራመድ ስለመቻሌና መናገር ስለመቻሌ እግዚአብሔርን አመሰግነዋለሁ።

ሦስተኛ፤ በተቻለ መጠን ሁሉ ሰዎች ወደ መንግስተ ሰማይ እንዲገቡ እፈልጋለሁ። ሁልጊዜም መንግስተ ሰማይ እውን እንደሆነና ለእግዚአብሔር ህዝብ የተዘጋጀ ሥፍራ መሆኑን በሚያስተምሩ ክርስቲያናዊ አስተምህሮዎች እምናለሁ።

እኔ በዚያ ተገኝቼ ይህን የተመለከትኩ በመሆኔ ምክንያት የነገሩን ፍጹም እርግጠኝነት በግልጽ የመናገር ጠንካራ የሃላፊነት ስሜት ይሰማኛል። ሰዎች ወደ መንግስተ ሰማይ እንዲገቡ በመፈለጌ ብቻ አይደለም፤ አሁን አሁን ሰዎች በሞቱ ጊዜ ወዴት እንደሚሄዱ እርግጠኞች ይሆኑ ዘንድ ሕይወታቸውን በመክፈት እንድረዳቸው የመቸኮል ስሜት ይሰማኛል።

እንደ እውነቱ ከሆነ በአውራ ጎዳናዎች ላይ በአደጋ ስለሞቱ ሰዎች አስባለሁ፤ በወንጌል አገልግሎት ወቅት ሰዎች ለኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወታቸውን እንዲሰጡ ለማግባባት የዚህን አስከፊና አሰቃቂ ክስተት ታሪክ አንዳንዶች ይጠቀሙበታል። ይሁን እንጂ እኔ ከተለማመድኩት ሁኔታ አንጻር ስመለከተው፤ እንደዚህ አይነት አደጋዎች በሕይወታችን ውስጥ በማንኛውም ቅጽበት ሊያጋጥሙን የሚችሉ የሞት ምክንያቶች እንደሆኑ አይቻለሁ። ሰዎች ያለ ክርስቶስ ሆነው ሲሞቱ ማየትን አልፈልግም።



በመጨረሻውም አንድ ጊዜ፤ ዲክ ዎንሪከርና እኔ ስለዚህ አጣዳፊነት ተወያየንበት። ለምን እንደዚያ እንደሚሰማኝ ገባው። ከዚያ በኋላ፤ "ዲክ፤ ነፍሴን ስላተርፍካት እንደገና ላመሰግንህ እፈልጋለሁ። በዚያ ዝናባማ ቀን እግዚአብሔርን ስለመታዘዝህ የሚገባውን ያህል እንዳላመሰገንኩህ ግልጽ ነው።"

"ማንም ሰው ቢሆን ሊያደርገው የማችለው ነገር ነበር።" አለኝ፤ ከዚያ በኋላ ማልቀስ ጀመረ።

"አንተ እንድታዝን ለማድረግ አልነበረም ይህን የተናገርኩት አልኩት። " እንደዚያ እንዲያለቅስ ያደረገውን ነገር ስለተናገርኩ በውስጤ ሀዘን ተሰማኝ። "በምድር ላይ ላደርገው ፈጽሞ የማልፈልገው ነገር ነው።"

"ያለቀስኩበት ምክንያት ያ አይደለም"

ሃሳቡን ለመሰብሰብ ረዥምም ጊዜ ነበር የወሰደበት።

"ያለቀስክበት ምክንያት ምንድነው" ስል ጠየኩት።

"የአደጋውን ሁኔታ እያስታወስኩ ነበር፤ በዚያ ጊዜ ፖሊሱን ለአንተ መጸለይ እችል እንደሆን ጠየቅኩት፤ ማንኛውም ክርስቲያን ሊያደርገው የሚችል ነገር እንደነበር አስባለሁ። ምንም እንኳን እንደሞትክ ቢናገርም፤ ለአንተ መጸለይ እንደነበረብኝ አውቀው ነበር በርግጥ አውቀው ነበር። ተጎድተህ እንደነበረ ብቻ ነው አስብ የነበረው፤ እናም ከዚያ ሁኔታ እንድትወጣ እፈልግ ነበር። ለዚህ ነው ያልተለመደ ነገር እንዳደረግኩ የማልቆጥረው።"

"ነገር ግን አድርገሃል። ፖሊሱ አስቀድሞ መሞቴን በነገረህ ጊዜ ..."

"አንድ ጊዜ አድምጠኝ፣ ዶን። አንድ ትንሽ ልጅ በአስፋልት ላይ ሲሮጥ ብታየው፣ ባለህ ፍጥነት ሁሉ ሮጠህ የልጁን ሕይወት ለማትረፍ ትሞክራለህ። የሰው ተፈጥሮው እንደዚያ ነው። ሕይወት ተጠብቃ እንድትቆይ እንፈልጋለን፣ እድሉን ባገኘህበት በየትኛውም ጊዜ አሁንም ቢሆን አደርገዋለህ። አንተም ብትሆን ታደርገዋለህ።"

ተቀምጠን የነበረው በአንድ ምግብ ቤት ውስጥ ነበር፣ እናም ዙሪያውን ለመቃኘት ንግግሩን አቋረጠ። "እዚህ ስፍራ ላይ በብዙ ሰዎች ተከበን ተቀምጠናል ይሁን እንጂ ምናልባትም ብዙዎቹ የጠፉና ወደ ሲኦል የሚሄዱ ሊሆኑ ይችላሉ። እኛ ግን እንዴት የዘላለምን ሕይወት እንደሚያገኙ አንዲትም ቃል አንናገራቸውም። እኛ ትልቅ ስህተት እየሠራን እኮ ነው"

"ሙሉ ለሙሉ ትክክል ነህ" አልኩት። በሚታይ ሁኔታ አደጋ ውስጥ ያለን ሰው ልናድነው ፈቃደኞች ነን፣ ይሁን እንጂ ብዙ ወገኖቻችን መንፈሳዊ በሆነ ቀውስ ውስጥ ናቸው፣ እናም ከዚያ ሁኔታቸው ውስጥ ስለሚወጡበት መንገድ አንዲት ቃል አንተነፍስም"።

"አለቅስ የነበረው ለዚህ ነበር። ስለዝምታዬ፣ ለሰዎች ወንጌልን መናገር ስለመፍራቴና፣ ነገሮችን ለማድረግ ስላለብኝ ፍርሃት እየተወቀስኩ ነበር።"

ከዚያ በኋላ ዲክ ደግሞ ደጋግሞ፣ እኔ ስላለፍኩበት ሁኔታ ማወቁና እኔ ወደ ምድር በመመለሴ ጉዳይ ላይ እርሱ የተጫወተው



ሚና ነፃ እንዳወጣው ይናገር ነበር። ከዚያ በኋላ ከዚያ በፊት አድርጎት በማያውቀው ሁኔታ ስለ ኢየሱስ በድፍረት መናገር ይሰማዋል።

# 13
# አጥብቆ የያዘኝ እጅ

"ዓይኖችህ ያዩትን እነዚህን ታላላቆች፣ የሚያስፈሩትንም ነገሮች ያደረገልህ፤ እርሱ ክብርህ ነው፤ እርሱም አምላክህ ነው"

ዘዳ 10፥21

አደጋው ከደረሰብኝ ከአንድ ዓመት በላይ ከሆነው በኋላ፤ በክሌን የመጀመሪያው መጥምቃውያን የዲክ ቤተክርስቲያን ውስጥ ታሪኬን ለማካፈል ዕድል አግኝቼ ነበር። የዲክ ባለቤት አኒታና የእኔም ቤተሰቦች በዚያ ተገኝተው ነበር። በእግር አጥንቶች መደገፊያውን ብረት አጥልቄ ስለነበር ወደ መድረኩ ላይ የወጣሁት በሁለት ሰዎች ተደግፌ ነው።

እዚያ ለነበሩት ሁሉ ስለአደጋውና የእኔን ወደ ምድር መመለስ አስመልክቶ ዲክ የነበረው ሚና ምን እንደነበር ተረኩላቸው። "ዛሬ በሕይወት ልኖር የቻልኩበት ምክንያት ዲክ ወደ ምድር እንድመለስ ስለጸለየልኝ እንደሆነ አምናለሁ" አልኳቸው። "ወደ አዕምሮዬ በተመለስኩባት የመጀመሪያዋ ቅጽበት ሁለት ነገሮች ሆነው ነበር። የመጀመሪያው፤ ከኢየሱስ ጋር ያለን ወዳጅነት እንዴት ድንቅ ነው። የሚለውን ዝማሬ እየዘመርኩ ነበር፡፤ ሁለተኛው ደግሞ የዴክ እጅ የእኔን እጅ አጥብቆ ጨብጦ ይዞ ነበር።"



ከጠዋቱ የአምልኮ ጊዜ በኋላ ብዙዎቻችን በአንድነት ሆነን ምሣችንን ለመብላት ወደ ቻይና ምግብ ቤት አመራን። አኒታ ከእኔ ፊት ለፊት ተቀምጣ ነበር። በዚያ የቀረበልኝን ሾርባ እየተመገብኩ ከቤተክርስቲያን አባላት ጋር የነበረኝን አስደሳች ጊዜ አስታውሳለሁ። የንግግር ልውውጣችን ለአፍታ ጋብ ሲል አኒታ ወደ ጠረጴዛው ተጠግታ ዝቅ ባለ ድምጽ፤ "በዚህ ጠዋት ስለተናገርካቸው ነገሮች ሁሉ ከልቤ አመሰግንሃለሁ" አለች።

"አመሰግናለሁ"

"አንድ ነገር ግን አለ ... በመልዕክትህ ውስጥ ከተናገርከው ነገር ላርምህ የሚገባው አንድ ነገር ግን አለ። "

"በእውነት?" የተናገረቻቸው ቃላት አስደንግጠውኝ ነበር። "በተቻለኝ መጠን በንግግሬ ሁሉንም በትክክል ለመግለጽ ሞክሬአለሁ። እንደ እውነቱ ከሆነ ምንም አይነት የተጋነነ ነገር አልጨመርኩም። የተናገርኩት የተሣሣተ ነገር ምን ነበር?"

"ዲክ ወደ መኪናው ውስጥ ገብቶ ከአንተ ጋር እንደነበር ተናግረሃል፤ በተጨማሪም እጅህን አጥብቆ እንደያዘ ይጸልይልህ እንደነበር ስትናገር ነበር።"

"አዎን፤ ያንን ነገር በተለይ በትክክል አስታውሰዋለሁ። ብዙ የማስታውሳቸው ነገሮች ነበሩ፤ እንዲያውም አብዛኛዎቹን ነገሮች አላስታውሳቸውም" በዚያ ጠዋት ስለሆኑት አንዳንድ ነገሮች መረጃ ያገኘሁት በስፍራው ከነበሩ ሰዎች ነው። "እጅግ ግልጽ የሆነው አንድ ነገር

ግን፤ ዲክ በመኪናው ውስጥ ተገኝቶ ከእኔ ጋር ይጸልይ እንደነበር ነው።"

"ያ ትክክል ነው። ወደ መኪናው ውስጥ ገብቷል። ከአንተም ጋር ጸልዮአል።" ወደ እኔ በጣም ቀረብ አለችና፤ "ነገር ግን ዶን፤ በጭራሽ እጅህን አልያዘም ነበር።"

"ግልጽ በሆነ ሁኔታ እጄን ይዤ እንደነበር አስታውሳለሁ"

"የሆነው እንደዚያ አልነበረም። በአካል ያንን ለማድረግ አይቻልም"

"ነገር ግን ያንን በትክክል አስታውሳለሁ፤ በጣም ግልጽ ከሆኑት ..."

"እስኪ አንድ ጊዜ አስበው። ዲክ ያደረገው በኋለኛው መቀመጫ በኩል ሆኖ በደረቱ በመጠጋትና እጁን በመዘርጋት በአንተ ትከሻ ላይ ነው ያሳረፈው። ፊትህ ወደፊት ተደፍቶ ነበር፤ የግራ እጅህ ደግሞ እርስ በእርሱ የተያያዘው ላመል ያህል ብቻ ነበር።"

"አዎ፤ ያ እውነት ነው"

"ያን ጊዜ ተዘርረህ የነበረው ከአሽከርካሪው አጠገብ ባለው የተሣፋሪ መቀመጫ ላይ እንደሆነ ዲክ ተናግሯል"

አይኖቼን ጨፈን አድርጌ እየተናገረች ያለችውን ነገር በአዕምሮዬ በመሳል ለመመልከት ሞከርኩ። እናም በአዎንታ ራሴን ነቀነቅኩ።

"ቀኝ እጅህ በተሣፋሪው መቀመጫ በኩል ባለው የመኪናው ወለል ላይ ነበር። ምንም እንኳን መኪናው የተሸፈነ ቢሆንም በዚያ



የተጋደመውን እጅህን ለማየት በቂ ብርሃን ነበር። ዲክ ያንን እጅህን ለመያዝ እጁ ሊደርስ የሚችልበት ምንም መንገድ የለም"

"ግን ... ግን ... ድምጼ በፍርሃት ይቆራረጥ ጀመር። "አንድ ሰው እጅህን ጨብጦ ይዞ ነበር። ነገር ግን ዲክ አልነበረም!"

"ያ እጅ የዲክ ካልነበረ፤ የማን እጅ ነበር?"

ፈገግ ብላ "እንደምታውቀው አስባለሁ" አለች። የሾርባውን ማንኪያ አስቀመጥኩና ለበርካታ ሰከንዶች አትኩሬ ተመለከትኳት። ማንም ይሁን ማን አንድ ሰው እጄን አጥብቆ ይዞ እንደነበር አልጠራጠርም። ከዚያ በኋላ ነገሩ ገባኝ። "አዎ፤ እኔም እንደ ማውቀው አስባለሁ።"

ወዲያውኑ በዕብራውያን መጽሐፍ ላይ አንዳንዶች ሳያውቁት መላእክትን በእንግድነት እንደተቀበሉ የሚናገረውን ጥቅስ አስላሰል ጀመር። በጥልቅ እያስላሰልኩ እያለሁ፤ መንፈሳዊ ገለጻ ብቻ ሊፈታቸው የሚችል ሌሎች ክስተቶችንም ማስታወስ ጀመርኩ። ለምሳሌ ያህል፤ በሆስፒታሉ ክፍል ውስጥ እጅግ ብዙ ጊዜ በውድቀት ሌሊት በከፍተኛ ስቃይ ውስጥ እሆናለሁ። ማንንም አላይም ወይም የማንንም ድምጽ አልሰማም - የሆነ ማንነት ህልውና ግን ይሰማኛል - የሆነ ነገር - የሆነ ስብእና - የሚደግፍ የሚያጽናና። ይህንንም ነገር ተናግሬው የማላውቀው ነገር ነበር። ልገልጸው የምችለው ነገር አልነበረም፤ በመሆኑም ሰዎች ሊረዱት አይችሉም ብዬ እገምት ነበር።

ይህ ሌላኛው ተአምር ነበር። እኒታ ባታርመኝ ኖሮ ሳውቀው አልችልም ነበር።

ከአደጋው በኋላ አምስት ዓመት ያህል ቆይቶ፤ እኔና ዲክ ሁለታችንም ፖት ሮበርትሰንስ 700 ክለብ በሚል የቴሌቭዥን ፕሮግራም ቀርበን ነበር:: የፊልም አንሺ ቡድን ወደ ቴክሳስ መጥቶ የነበረውን ክስተት እንደገና እንድንደግመው በማድረግ ፊልሙን አንስቶ ነበር:: በተጨማሪም በመንግስተ ሰማይ ስለነበረኝ ቆይታ ጠይቀውኛል:: የ700 ክለብ ከዚያ በኋላ በነበሩ ሁለት ዓመታት ውስጥ ያንን ታሪክ ብዙ ጊዜ ደጋግሞ በአየር ላይ ለቆታል::

በሕይወት እጅግ አስደናቂ ከሆኑት እንቆቅልሾች አንዱ ተከናወነ፤ በ2001 ዲክ በልብ ድካም በሽታ ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ:: ሞቱን በሰማሁ ጊዜ እጅግ ማዘኔን እናዘዛለሁ፤ ነገር ግን አሁን በክብር ስላለ ደስተኛ ነኝ:: ዲክ የእኔን ሕይወት አዳነ፤ እናም እግዚአብሔር እርሱን አስቀድሞ ወደ መንግስተ ሰማይ ወሰደው:: ወደ መንግስተ ሰማይ የሚያደርገውን ጉዞ ከመጀመሩ በፊት የእኔን ምስክርነት በመስማቱ ተደስቼ ነበር::

ከአደጋው በኋላ አንድ ዓመት በላይ ቆይቶ ከአኒታ ጋር ያንን ጭውውት ካደረግን ወዲህ፤ እግዚአብሔር ወደዚህ ምድር የመለሰኝ ለዐላማ መሆኑ ከመቼውም ይልቅ እያሳመነኝ መጣ:: መልአኩ የእኔን እጅ መያዙ፤ ምንም እንኳን ነገሮች ከባድ እየሆኑ ቢሄዱም እንደማይተወኝና እንደሚደግፈኝ እንዳውቅ የተጠቀመበት መንገድ ነበር::

ምናልባትም ያ እጅ በእያንዳንዱ ቀን እንደያዘኝ አይታወቀኝ ይሆናል፤ ነገር ግን ከእኔ ጋር እንዳለ አውቃለሁ::



# 14 አዲሱ ሕይወት

"እኔ ጤናህን እመልስልሃለሁ፤ ቁስልህንም እፈውሳለሁ፤ ይላል እግዚአብሔር ማንም የማይሻት፣ የተጣለች ጽዮን ብለው ጠርተውሻልና"

ኤር 30፥17

ፈጽሞ ልናገግም የማንችልባቸው አንዳንድ ነገሮች ወደ እኛ ይመጣሉ፤ እናም የተለመደውን የሕይወት ምልልስ ያናውጣሉ:: እንግዲህ ሕይወት እንዲህ ናት::

የሰው ተፈጥሯዊ ባህሪ የቀደሙ ነገሮችን መልሶ የመገንባትና የተውናቸውን ነገሮች ከጣልንበት ሥፍራ እንደገና የመሰብሰብ ዝንባሌ አለው:: እስተዋዮች ብንሆን ኖሮ ነገሮችን ቀድሞ ወደነበሩበት ሥፍራ ለመመለስ ጥረታችንን አንቀጥልም (ብንሞክርም አይሳካም):: ከዚያ ይልቅ የቀደመውን የተለመደ ነገር እየረሳን አዲሱን ሕይወት መቀበል ይገባናል::

ጤነኛ የነበርኩበትንና አንዳችም አካላዊ ችግር ባልነበረብኝ ጊዜ የነበረኝን ሁኔታዬን ብዙ ጊዜ በማሰብ እጅግ ብዙ ጊዜ አጥፍቻለሁ:: በአዕምሮዬም፤ ሕይወት ምን መምሰል እንደነበረባት እንደገና እቀርጻለሁ፤ እውነታው ግን ከዚያ በኋላ ሕይወት እንደቀደመው እንደማይቀጥል አውቅ ነበር:: አካላዊ ጉድለቶቼን እንደ አዲሱ ሕይወቴ

ከአደጋው በኋላ አምስት ዓመት ያህል ቆይቶ፤ እኔና ዲክ ሁለታችንም ፓት ሮበርትሰንስ 700 ክለብ በሚል የቴሌቭዥን ፕሮግራም ቀርበን ነበር:: የፊልም አንሺ ቡድን ወደ ቴክሳስ መጥቶ የነበረውን ክስተት እንደገና እንድንደግመው በማድረግ ፊልሙን አንስቶ ነበር:: በተጨማሪም በመንግስተ ሰማይ ስለነበረኝ ቆይታ ጠይቀውኛል:: የ700 ክለብ ከዚያ በኋላ በነበሩ ሁለት ዓመታት ውስጥ ያንን ታሪክ ብዙ ጊዜ ደጋግሞ በአየር ላይ ለቆታል::

በሕይወት እጅግ አስደናቂ ከሆኑት እንቆቅልሾች አንዱ ተከናወነ፤ በ2001 ዲክ በልብ ድካም በሽታ ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ:: ሞቱን በሰማሁ ጊዜ እጅግ ማዘኔን እናዘዛለሁ፤ ነገር ግን አሁን በክብር ስላለ ደስተኛ ነኝ:: ዲክ የእኔን ሕይወት አዳነ፤ እናም እግዚአብሔር እርሱን አስቀድሞ ወደ መንግስተ ሰማይ ወሰደው:: ወደ መንግስተ ሰማይ የሚያደርገውን ጉዞ ከመጀመሩ በፊት የእኔን ምስክርነት በመስማቱ ተደስቼ ነበር::

ከአደጋው በኋላ አንድ ዓመት በላይ ቆይቶ ከአኒታ ጋር ያንን ጭውውት ካደረግን ወዲህ፤ እግዚአብሔር ወደዚህ ምድር የመለሰኝ ለዐላማ መሆኑ ከመቼውም ይልቅ እያሳመነኝ መጣ:: መልአኩ የእኔን እጅ መያዙ፤ ምንም እንኳን ነገሮች ከባድ እየሆኑ ቢሄዱም እንደማይተወኝና እንደሚደግፈኝ እንዳውቅ የተጠቀመበት መንገድ ነበር::

ምናልባትም ያ እጅ በእያንዳንዱ ቀን እንደያዘኝ አይታወቀኝ ይሆናል፤ ነገር ግን ከእኔ ጋር እንዳለ አውቃለሁ::



# 14 አዲሱ ሕይወት

"እኔ ጤናህን እመልስልሃለሁ፤ ቁስልህንም እፈውሳለሁ፤ ይላል እግዚአብሔር ማንም የማይሻት፣ የተጣለች ጽዮን ብለው ጠርተውሻልና"

ኤር 30፥17

ፈጽሞ ልናገግም የማንችልባቸው አንዳንድ ነገሮች ወደ እኛ ይመጣሉ፤ እናም የተለመደውን የሕይወት ምልልስ ያናውጣሉ:: እንግዲህ ሕይወት እንዲህ ናት::

የሰው ተፈጥሯዊ ባህሪ የቀደሙ ነገሮችን መልሶ የመገንባትና የተውናቸውን ነገሮች ከጣልንበት ሥፍራ እንደገና የመሰብሰብ ዝንባሌ አለው:: አስተዋዮች ብንሆን ኖሮ ነገሮችን ቀድሞ ወደነበሩበት ሥፍራ ለመመለስ ጥረታችንን አንቀጥልም (ብንሞክርም አይሳካም):: ከዚያ ይልቅ የቀደመውን የተለመደ ነገር እየረሳን አዲሱን ሕይወት መቀበል ይገባናል::

ጤነኛ የነበርኩበትንና አንዳችም አካላዊ ችግር ባልነበረብኝ ጊዜ የነበረኝን ሁኔታዬን ብዙ ጊዜ በማሰብ እጅግ ብዙ ጊዜ አጥፍቻለሁ:: በአዕምሮዬም፤ ሕይወት ምን መምሰል እንደነበረባት እንደገና እቀርጻለሁ፤ እውነታው ግን ከዚያ በኋላ ሕይወት እንደቀደመው እንደማይቀጥል አውቅ ነበር:: አካላዊ ጉድለቶቼን እንደ አዲሱ ሕይወቴ

አንድ አካል አድርጌ መቀበልና ሁኔታዎችንም ከዚሁ አንጻር ማመቻቸት ነበረብኝ።

ልጅ በነበርኩበት ጊዜ በአያቶቼ ሳሎን ቤት በነበረ ቡና አይነት ምንጣፍ ላይ ከመሬት ተቀምጬ እነርሱ ስላሣለፏቸው መልካም ጊዜያቶች ሲያወሩ አዳምጥ ነበር። በርካታ ታሪኮችን ካዳመጥኩ በኋላ እንዲህ ስል አሰብኩ፤ እነኝህ የሚያወሩላቸው ዓመታት መልካም ዓመታት አልነበሩም፤ ቢያንስ ቢያንስ በትዝታቸው ውስጥ የሚያወሩት ነገር መልካም አይደለም። ምናልባትም ለእነርሱ በእውነትም መልካም ዓመታት ሆነውላቸው ይሆናል ወይም ደግሞ ምናልባት በጊዜያቸው የነበሩትን አሉታዊ ገጽታዎች እረስተዋቸው ይሆናል። በሕይወታችን ወደ ኋላ ተመልሰን ወደ አንዳንድ ስፍራዎች ነገሮች ቀላል ወደነበሩበት ሁኔታ፤ ጤናማ ወይም ደስተኞች ወደነበርንበት ሁኔታ መመለስ እንፈልጋለን። ልናደርገው አንችልም፣ ይሁን እንጂ አሁንም አንድ ጊዜ ሁኔታዎች እንዴት ጥሩ እንደነበሩ ማለማችንን እንቀጥላለን።

በሃያዎቹ የዕድሜ ክልል ውስጥ ሳለሁ፤ ዝማሬዎችን በምዘምርበት ጊዜ የቆዩ ግን ታዋቂ የነበሩ ዝማሬዎችን መዘመር እናዘወትር ነበር። እነኛን ዝማሬዎች እንዲዘመሩ የሚመርጡ ሰዎች አብዛኛውን ጊዜ መዝሙሮቹ አሁን ካሉት ዝማሬዎች ይልቅ የተሻሉ እንደሆኑ አስተያየት ይሰጣሉ። እውነታው ግን በቀደሙት ዓመታትም ቢሆን ጥሩም መጥፎም ዝማሬዎች ይዘመሩ ነበር፤ ይሁን እንጂ መጥፎዎቹ ዝማሬዎች አሁን እንደሚሆነው ሁሉ ከሰዎች አዕምሮ ውስጥ ፈጥነው ይደመሰሳሉ። ስኬት ያልነበራቸውን ዝማሬዎች እንድንዘምር ማንም ጠይቆንም አያውቅም። የቀደመውን ዘመን ተደናቂ የሚያደርጉት ጥሩዎቹ ዝማሬዎች ናቸው። በዚህም የቀደመው ዘመን



ዝማሬዎች ሁሉ ጥሩ እንደነበሩ ይገመታል። ተጨባጭ ሁኔታዎችን ካየን - ከሠላሣ ወይም ከሃምሳ ዓመታት በፊትም ጥሩ ያልሆኑ ዝማሬዎች ነበሩ። እንዲያውም አብዛኞቹ ጥሩ ያልሆኑ ናቸው። በሕይወት ልምምዶችም ሁኔታው ተመሳሳይ ነው። አሉታዊ ገጽታ የነበራቸውን ሁኔታዎች የመርሣትና አስደሣች ሁኔታዎችን ብቻ የማስላሰል አዝማሚያ እንወስዳለን። እውነታው ግን - እየመረጥን የምናስታውስና - እየመረጥንም የምንዘነጋ መሆኑ ነው።

ይህ ዐይነቱ አመለካከት አንድ ጊዜ ወደ ውስጤ ከገባ በኋላ፤ ከኋላዬ አልፌ የመጣሁትን እንደገና መያዝ እንደማልችል ወሰንኩ። ምንም ያህል በአዕምሮዬ እየደጋገምኩ ብሰለውም ያኛው የሕይወት ገጽታ ላይመለስ አልፎ ሄዷል፤ እንደገና ሙሉ ጤነኛ ወይም ጠንካራ ልሆን አልችልም። ለእኔ የቀረልኝ ብቸኛው ነገር የአዲሱን ሕይወቴን አዲስ አቅጣጫ መፈለግ ነው።

"አዎን"፤ አልኩኝ ለራሴ፤ እንደገና ላደርጋቸው ፈጽሞ የማልችላቸው ነገሮች አሉ። እንዲህ መሆኑን አልወደውም እንዲያውም እጠላዋለሁ፤ ይሁን እንጂ፣ ይህ ነገሮች ያሉበትን ሁኔታ አይለውጠውም። ፈጥኜ ከነባራዊው ሁኔታ ጋር ሰላም ስፈጥርና ያለሁበትን ሁኔታ ስቀበል፤ ፈጥኜ ሰላም ወደምላበት ሕይወት እገባለሁ፤ ያለሁበትንም አዲስ ሕይወት በደስታ ማጣጣም እጀምራለሁ።

እየተናገርኩ ያለሁትን ነገር በምሳሌ ልግለጸው።

እ.ኤ.አ. በ2000 መግቢያ ላይ፤ የተወሰኑ የኮሌጅ ተማሪዎችን በበረዶ ላይ እየተንሸራተቱ እንዲዝናኑ ለማድረግ ከሀውስተን ወደ ኮሎራዶ ይዣቸው መጥቼ ነበር። በበረዶ ላይ መንሸራተት በጣም ከምወዳቸው ነገሮች አንዱ ነበር። ከእነርሱ ጋር መሳተፍ ባለመቻሌ

ከተራራው በታች ባለች አንዲት ክፍል ውስጥ ተቀምጨ በመስኮቱ አሻግሬ ቁልቁል እየተምዘገዘጉ ሲወርዱ እመለከታቸው ነበር:: እናም ድንገት ውስጤ በንዴት ተሞላና፤ "ትልቅ ስህተት ነው የሠራሁት፤ ወደዚህ ስፍራ አብሬአቸው መምጣት አልነበረብኝም" አልኩ:: እነርሱ በበረዶው ላይ ሲንሸራተቱ ደስተኛ የሆንኩትን ያህል፤ እኔ ልንሸራተት ባለመቻሌ ደግሞ እጅግ ነበር ያዘንኩት::

ከዚያ በኋላ ላደርጋቸው የማልችላቸውን በሽህ የሚቆጠሩ ነገሮች ማሰብ ጀመርኩ:: በቤተክርስቲያኔ ዋነኛው መጋቢ በነበርኩበት ጊዜ፤ የእያንዳንዱ ማለዳ አገልግሎት ከተጠናቀቀ በኋላ፤ በእድሜ ከፍ ያሉት አባላት ከመግቢያው በር ላይ "በስብከትህ ደስተኞች ነበርን፤" "ታላቅ አገልግሎት ነበር" እያሉ ሰላምታ ሰጥተውኝ ይወጡ ነበር::

ልጆች ግን እንዲህ አይደሉም፤ ባህርያቸው የተለየ ነው:: በእጃቸው ሲለው ቀለም የቀቡትን ሥዕል ይዘው ወደ እኔ እየሮጡ ይመጡ ነበር:: ከአደጋው በፊት ህፃናቱ በዙሪያዬ ሲሰበሰቡ እደሰት ነበር፤ በጉልበቴ ተንበርክኬም ከእነርሱ ጋር አወራለሁ:: አሁን ከአካል ጉዳቴ ካገገምኩ በኋላ እንደቀድሞው በርከክ ብዬ ደስታ የተሞላ ብሩህ ፊታቸውን እየተመለከትኩ፤ "በጣም አመሰግናለሁ፤ ይህንን ስዕል በእውነት ወድጄዋለሁ:: በጣም ምርጥ ነው" ልላቸው አልችልም::

ከአደጋው በኋላ፤ ላደርግ የምችለው የተሻለ ነገር ወደ ፊት ጎንበስ ብዬ ከእነርሱ ጋር ማውራት ነው:: ምናልባት ይህ እምብዛም ትልቅ ነገር ላይመስል ይችላል፤ ለእኔ ግን ትልቅ ነገር ነው:: ከዚህ በኋላ መንበርከክ ፈጽሞ አልችልም:: ልጅ በነበርኩበት ዘመን አደርገው



እንደነበር ሁሉ አሁን መንበርከክ አልችልም፤ ምክንያቱም የእግሮቼ ሁኔታ ያንን እንዳደርግ አይፈቅድልኝም::

ሌላ ምሳሌ ደግሞ ልስጣችሁ፤ ቀላል ምግቦችን ለመመገብ በመኪናዬ ውስጥ ሆኜ በምግብ ቤቱ አካባቢ ስስተናገድ፤ መልስ ለመቀበል ግራ እጄን መዘርጋት አልችልም:: ማድረግ የምችለው የተሻለው ነገር ቀኝ እጄን በሰውነቴ ዙሪያ አሳልፌ መቀበል ነው:: እንግዳ ነገር ነው የሚሆንባቸው በፊታቸው፤ ላይ ግራ መጋባት አያለሁ፤ ይሁን እንጂ ማድረግ የምችለው በቃ ያንን ነው::

ምንም እንኳን እነዚህ ምሳሌዎች በተለይ ከእንቅስቃሴ ጋር የተያያዙ ቢሆንም ሁልጊዜም የሚያስታውሱኝ ነገር አለ:: አንዳንድ ጊዜ በዕለት ተዕለት እንቅስቃሴያችን በቀላሉ እናደርጋቸው የነበሩ ነገሮች እስከ ፍጻሜው ከእኛ ይወሰዳሉ፤ ነገሩ የሚሆነው ድንገት ነው፤ እናም ለዘላለም እንለወጣለን::

ሆስፒታል በቆየሁበት ረዥም ጊዜ፤ አንድ ሰው የአይኑን ብርሃን ስላጣ ስለ አንድ ወጣት የሚያትት መጽሔት አምጥቶ ሰጠኝ:: እጅግ መራራ በሆነና ድብርት በሞላበት ሁኔታ ውስጥ አለፈ:: ይህ ሰው በጻፈው ጽሁፍ እንደገለጸው፤ ለእርሱ በጣም ይጨነቅለት የነበረ ጓደኛ ው፤ ከዚህ ዐይነት ሁኔታህ ፈጥነህ መውጣት ይኖርብሃል" በማለት እውነቱን በነገረው ጊዜ ስሜቱ እጅግ ተጎዳ::

መጽሔቱን ከማንበብ ቆም አደረኩና፤ "እውነት ነው፤ ከአደጋው በኋላ እኔም ይሰማኝ የነበረው እንዲሁ ነበር" አልኩ:: ጽሑፉ እንዲህ ሲል ይቀጥላል፤ ይሁን እንጂ የአይነ ስውሩ ጓደኛ ተግባራዊ የሆነ

መመሪያዎችን ሊሰጠው ስለፈለገ፤ አሁንም ማድረግ የምትችላቸውን ነገሮች ዝርዝር ሁሉ እንድትገልጽልኝ እፈልጋለሁ አለው::

“እነዚህ የምትላቸው ዝርዝሮች ምን ምን ሊሆኑ ይችላሉ?” ሲል የተቆጣው አይነስውር ጠየቀ::

“በቃ ማድረግ የምትችላቸውን ነገሮች ለእኔ ንገረኝ:: መጻፍ አያስፈልግህም፤ ይሁን እንጂ በቴፕሪከርደሩ ላይ ዝርዝሩን መቅዳት ትችላለህ:: አሁንም ማድረግ የምትችላቸውን ነገሮች ሁሉ መዘርዝርህን አትርሣ:: እኔ እየተናገርኩ ያለሁት ቀላል ስለሆኑ ነገሮች ነው፤ አሁንም አበቦችን ማሽተት እችላለሁ የሚሉ ዐይነቶችን:: እስከቻልከው ድረስ ዝርዝሩን አርዝመው:: በጨረስክ ጊዜ ዝርዝሮቹን ማድመጥ እፈልጋለሁ::”

አይነ ስውሩ በመጨረሻው በነገሩ በመስማማት ዝርዝሮቹን ተናገረ:: ምን ያህል ጊዜ እንደወሰደ አይታወቅም፤ ነገር ግን ጓደኛው በተመለሰ ጊዜ አይነስውሩ ወጣት ፈገግ ብሏል፤ ውስጡም ሰላምን ተሞልቷል::

“ባለፈው ጊዜ ካየሁህ ይልቅ አሁን በተረጋጋ የአዕምሮ ሰላም ውስጥ ያለህ ትመስላለህ” አለ ጓደኛው::

“ትክክል ነው፤ በእርግጥም እንደዚያ ነኝ፤ ምክንያቱም የተሰጠኝን ዝርዝር እየሠራሁ ነበር::”

“በዝርዝርህ ውስጥ ስንት ነገሮች ናቸው ያሉት? ”

“ከአንድ ሺህ በላይ ይሆናሉ”::

“ይህ የሚያስደንቅ ነው”::



“አንዳንዶቹ በጣም ቀላል ነገሮች ናቸው:: የትኞቹም ትልልቅ ነገሮች አይደሉም፤ ነገር ግን አሁንም ላደርጋቸው የምችል በሺህ የሚቆጠሩ ነገሮች አሉ::”

አይነስውሩ ሰው ስርነቀል በሆነ ሁኔታ መለወጡን ያስተዋለው ጓደኛው፤ እስኪ እባክህ ንገረኝ፤ እንዲህ የለወጠህ ነገር ምንድን ነው?

“ማድረግ የምችላቸውን ነገሮች ሁሉ ለመዘርዘር ወስንኩ፤ ብዙ እያሰብኩበት በሄድኩ ቁጥር፤ የማልችላቸው ነገሮች ጥቂቶች መሆናቸውን አየሁ:: በሺህ የሚቆጠሩ ነገሮችን ማድረግ እችላለሁ፤ እነዚህን ሁሉ ነገሮች ደግሞ በቀሪው የሕይወት ዘመኔ ሁሉ አደርጋቸዋለሁ::”

ጽሑፉን ካነበብኩ በኋላ እንዲህ ስል አሰብኩ፤ አሁን በትክክል ለእኔ የሚያስፈልገኝ ይህ እንጂ፤ መሪር ሀዘን፣ ያለፈውን ደጋግሞ ማሰብ ወይም ከዚህ በኋላ ላደርጋቸው በማልችላቸው ነገሮች መቆጨት አይደለም:: ከዚህ ይልቅ አሁን ያለኝ ነገር ምን እንደሆነ መፈተሽ ያስፈልገኛል፤ ይህንንም የማደርገው በእርሱ ለመደሰት ብቻ ሳይሆን ተስፋ ቢስ እንዳልሆንኩ እንድገነዘብ ጭምር ነው::

ይህንን ሣሣብ በጥልቀት ሳስብ፤ ከማስበው በላይ በፊቴ በርካታ ሥራዎች እንዳሉ ተገነዘብኩ:: ትኩረቴን ጫን አድርጌ የነበረው ባጣኋቸው ነገሮች ላይ ስለነበር፤ የቀሩኝን ነገሮች ፈጽሞ ዘንግቻቸዋለሁ:: እንዲሁም ሞክሬያቸው የማላውቃቸውን ነገሮች ለመሞከር እድል እንዳለኝም አላስተዋልኩም ነበር::

ባነበብኩት ጽሑፍ ውስጥ፤ አይነ ስውሩ ሰው፤ አሁን ማድረግ ስለማልችላቸው ነገሮች አልጨነቅም:: አሁን በደንብ ማድረግ

የምችላቸውን ነገሮች አደርጋለሁ የሚል ሃሳብ ይሰነዝራል:: እነዚያ ቃላት ቀላል ይመስሉ ነበር::

ያንን ጽሑፍ ያነበብኩት በትክክለኛው አስፈላጊ ጊዜ ላይ ነበር:: እነዚያ ቃላት የማይታመኑና ጥልቀት ያላቸው ይመስላሉ:: ያንን መልዕክት የላከልኝ እግዚአብሔር ነበር፤ የሚያስፈልገኝ ወሳኝ ጊዜ "በሕይወት መቀጠል አለብኝ:: ያለኝን የትኛውም ነገር እጠቀምበታለሁ፣ ደግሞም ማድረግ እስከምችለው መጠን ሁሉ እሰፋዋለሁ::" እንድል ያስኘኝ እጅግ ታላቅ መነቃቃት ውስጥ ከገባሁባቸው ጊዜዎች አንዱ ነበር::

"አሁን ጊዜ እየቀደመኝ ሄዷል፤" ስል አሰብኩ፤ "ይሁን እንጂ ለእኔ ብቻ ሳይሆን ለሁሉም ነው":: እንዲያውም ከሌሎች ሰዎች ይልቅ በሁለት ምክንያቶች እኔ ስለ ጊዜ ያለኝ ግንዛቤ የተሻለ ነበር:: የመጀመሪያው፤ በአደጋው ምክንያት ከሕይወቴ ዋነኛውን ክፍል አጥቼዋለሁ:: ሁለተኛም፤ በዚህ ምድር ላይ ብዙ እንደማንቆይ አውቄአለሁ:: ብዙዎቹ የቀደሙ ዝማሬዎች እንደሚናገሩት፤ እኛ እንግዶችና ተላላፊ መንገደኞች ነን:: እነዚህን ነገሮች መጽሐፍ ቅዱስንና ሌሎች ጽሑፎችን በማንበብ ሁላችንም እናውቃቸዋለን፤ ይሁን እንጂ እነዚያ ማሳሰቢያዎች ለእኔ የማንቂያ ደወሎች ሆነውልኛል::

በተጨማሪም እነዚያ የምወዳቸው ሰዎች በመንግስተ ሰማይ መግቢያ በር ላይ እንደሚጠብቁኝ አውቃለሁ::

እንደገናም ደግሞ እግዚአብሔር እንደገና እስኪመልሰኝ ድረስ መጠበቅ ያስፈልገኛል::



እኔ በሆስፒታል ውስጥ በነበርኩበት ጊዜ የሳውዝ ፓርክ ቤተክርስቲያን አባላት ቤተሰባችንን ወደ ሌላ ሥፍራ አዛውረውት ነበር:: እኛ እንኖር የነበረው ፍሬንድስውድ በተባለ ከተማ ውስጥ ሲሆን፤ ከቤተክርስቲያናችን አስር ማይልስ ያህል ይርቃል:: ወደ ቤተክርስቲያናችን ቀረብ ያለ ቤት ብንፈልግም አላገኘንም:: በሆስፒታል በነበርኩበት ጊዜ የቤተክርስቲያናችን መሪዎች አንድ ቤት አገኙ፤ ተከራዩትም፣ ያለንን ንብረት ሁሉ ጭነው ወደአዲስ ቤት አዘዋወሩን:: ከሆስፒታሉ በወጣሁ ጊዜ የገባሁት አንቡላንሉ የሆስፒታል አልጋ ወዳለው አዲሱ ቤት ካደረሰኝ በኋላ፤ ተሽከርካሪ ጎማ ባለው ቃሬዛ እየተገፋሁ ገባሁ:: ያኔ ነበር ቤቱን ትኩር ብዬ መመልከት የጀመርኩት::

ፊጥኜ ከቤቱ ልዩ ልዩ ክፍሎች ጋር ተላመድኩ፤ ምክንያቱም ለረዥም ጊዜ ያየሁት የሆስፒታል አልጋውን ያኖሩበትን የሳሎኑን ክፍል ብቻ ነበር::

በአንዳንድ መንገዶች ወደ አዲሱ ቤት መዛወራችን ከእኔ ይልቅ ጫን ያለውን ችግር የፈጠረው በቤተሰቦቼ ላይ ነበር:: በእኔ ህመም ምክንያት ባለቤቴ ማስተካከል የነበረባትን አንዳንድ ሁኔታዎችና የምታልፍበትን ችግር ተረድቻለሁ:: ኢቫ አብዛኛውን ጊዜዋን ከእኔ ጋር ታሳልፍ ስለነበረ ሥራዋን ልታጣ ምንም ያህል አልቀራትም ነበር:: የስብሰባ ጊዜዎችን፤ የዕረፍትና የሕመም ፍቃዶቿን ሁሉ ከእኔው ጋር አሳልፋቸዋለች:: አንዳንድ አስተማሪዎች የራሳቸውን የህመም ፈቃዶች አሳልፈው ለእርሷ ይሰጧት ስለነበር ወደ ሆስፒታሉ መጥታ ከእኔ ጋር እንድትሆን ረድቷታል:: በመጨረሻው እነዚያ የፈቃድ ጊዜዎች ሁሉ በማለቃቸው ወደ ሥራዋ መመለስ ግድ ሆነባት:: በዚያ ላይ የመጀመሪያዋ የገቢ ምንጫችን እርሷ ነበረች::

በአልቪን ከተማ በሮበርት ሉዊስ ስቲቨንስን አንደኛ ደረጃ ት/ቤት የነበሩ የኢቫ ጓደኞች፣ ብዙውን ጊዜ የእርሷን ተማሪዎች የፈተና ወረቀቶች ያርሙላታል፤ ዕለታዊ የትምህርት እቅዷን ያዘጋጁላታል፤ እንዲሁም ማልዶ እኔን ለማየት ወደ ሆስፒታሉ በምትመጣበት ጊዜ የእርሷን ክፍሎች ይሸፍኑላታል። ከዚህም አልፎ የቅርብ ጓደኞቿ የሆኑት አስተማሪዎች ለልጆቻችን በየዕለቱ የምንሰጣቸውን ጥቃቅን ስጦታዎች ይሰጧታል፤ በመሆኑም ልጆቻችን ስለመጭዎቹ ቀናት ተስፋን የተሞሉ እንዲሆኑ አድርገዋል። ስጦታዎቹን "አስደናቂ ሳጥኖች ነው" የሚሏቸው። አስተማሪ ጓደኞቿ ከቤተክርስቲያን አባላት ጋር በመሆን ቤታችንን ለማጽዳትና ምግባችንንም ሊያዘጋጁልን ወደ ቤታችን ይመጣሉ። እንደ አስተማሪዎቹና እንደ ቤተክርስቲያን ትጋት ባይሆን ኖሮ ኢቫ ያለ ምንም ጥርጥር ሥራዋን ታጣ ነበር፤ የእኔም እጣ ይሄው ከዚህ አይዘልም። ይሁን እንጂ ከዚህ ሁሉ አስደናቂ መስዋእትነት የተሞላ ስጦታና ድጋፍ ጋር ያንን የ1989 የጸደይ ወር የትምህርት ወቅት ያሳለፍንበት ሁኔታ እንደ ተአምር የሚቆጠር ነው።

አንድ ጊዜ ኢቫ ለእኔ እየተሰጠኝ ስላለው የረዥም ጊዜ የህክምና ክትትል በጠየቀችበት ጊዜ፣ ነርሷ እንዲህ ስትል ተናገረች፤ "የኔ ወለላ፤ ይህንን ሁሉ ነገር ልታውቂ አያስፈልግሽም፤ አንቺ እኮ ሚስት ነሽ"።

ለዚያች ነርስ፤ እርሷ ምናልባትም "ሚስት ብቻ" ነች፤ ይሁን እንጂ ከአደጋው በኋላ ኢቫ የሁለታችንንም ሃላፊነት ደርባ እየተወጣች ነበር። ከአደጋው በፊት እኔ ሁልጊዜም የተለያዩ የውጭ ክፍያዎቻችንን፣ የባንክ ሂሣባችንን፣ የኢንሹራንስ ጉዳዮቻችንንና አብዛኛዎቹን ቤተሰባዊ ጉዳዮች እሸፍን ነበር። ምንም ምርጫ ስላልነበራት እነኝህን ሁሉ ተግባራት ደርባ ትሠራ ነበር፤ ደግሞም ሁሉንም ያለ ምንም እንከን አጠናቃቸዋለች። ኢቫ ጥንካሬን አዳብራለች፤ ወደ አዲስ በራስ የመተማመን እርከን አድጋለች። ቤተሰባዊ ጉዳዮቻችንን እንዴት መልክ ማስያዝ እንደምትችል እግዚአብሔር ጥበብን ሰጥቷት ነበር። ረዥም ጊዜ በወሰደው የማገገሚያዬ ጊዜ ውስጥ፣ አቀርባቸው የነበሩትን ብሶት የተሞላባቸው ጥያቄዎቼንና ማጉረምረሜን ሁሉ ታግሳ መቻልን ተምራለች።

ቤተክርስቲያን ወርሃዊ ቀለቤን መክፈሏን አላቋረጠችም፤ ይሁን እንጂ ማቋረጥ እንዳለባቸው ተገንዝበናል፣ የማልሠራ በመሆኔ ሊከፍሉኝ እንደማይገባም አውቀናል። ስለ ገንዘብ ጉዳይ ተነጋግረን እናውቅም፤ ነገር ግን በገንዘብ ምክንያት እጅና እግራችን ሊታሠር እንደሚችል አላጠነውም።

የቴክሳስ መንግስት በአደጋው ክስተት የእኔም ሃላፊነት እንዳለበት በመረዳታቸው፤ ህጉ ሊከፈለኝ የሚገባውን ክፍያ ወደ 250,000 ዶላር ዝቅ አደረገው፤ ይህም ገንዘብ በሙሉ ለሆስፒታል ወጪአችን መሸፈኛ ዋለ፤ እናም የአንድ ሚሊዮን ዶላር ሲሶ የሆነ ገንዘብ ብዙም ሊያንቀሳቅስ የሚችል አልነበረም።

የቴክሳስ መንግስት አቃቤ ሕግ የተገላቢጦሽ በሆነ መልኩ፤ የእኔን መኪና የገጫትን ከባድ መኪና ሊያሽከረክር ለነበረ ተከሳሽ "ችግረኛ እስረኛ ነው" በሚል ሰበብ ጥብቅና ቆመለት። በዚህም ምክንያት ከታክስ የተገኘው ገንዘብ የቴክሳስን መንግስትና አደጋ ያደረሰብኝን ሰው ለመከላከል ዋለ። ሕይወት አንዳንድ ጊዜ ግራ የምታጋባ አይደለችምን?

በሆስፒታል በቆየሁባቸው 105 ቀናት፤ ኢቫ በባለ ውጥረት ውስጥ ነበረች:: በቤት ውስጥ የነበረውን ሃላፊነት ሁሉ ብቻዋን በመሸከሟ ምክንያት ብቻ አልነበረም፤ በየዕለቱ ከማለዳው 12:00 ትነሣለች፤ በቤት ውስጥ ማከናወን ያለባትን ሥራ ሁሉ ከጨራረሰች በኋላ ወደ ትምህርት ቤት ትበራለች:: የትምህርቱ ጊዜ ካለቀ በኋላ ደግሞ ከአጠገቤ ለመሆን በጥድፊያ ትመጣለች:: ከዚያም እስከ ምሽቱ 4:30 ድረስ አብራኝ ትቆያለች:: ከቀን ወደ ቀን ውጥረት የሞላበት የማይለዋወጥ ሂደት::

እጅግ ፈታኝ ከሆኑት ገጠመኞቿ አንዱ - በራሷ የተፈጠረው ነበር:: ያም ሁኔታ በአደጋው ምክንያት ከጥቅም ውጭ በሆነችው መኪናዬ ምትክ፤ እኔን ለማመላለስ የሚያመች የአምቡላንስ ዓይነት መኪና ለመግዛት ያደረገችው ሙከራ ነው:: በዚያ ጊዜ እኔ ወደ ቤት የተመለስኩ ስሆን የኤልዛሮብ ፍሬሙ በእግሬ ላይ እንዳለ መራመድ ችዬ ነበር:: ይህም ማለት ወደ የትኛውም ስፍራ መሄድ የምፈልግ ቢሆን፤ ያንን አምቡላንስ መስል መኪና መጠቀም ይኖርብኛል ማለት ነው:: በመደበኛ የመኪና ወንበር ላይ በአግባቡ ለመቀመጥ ምን ያህል ጊዜ እንደሚወስድብኝ የምናውቀው ነገር አልነበረም::

ኢቫ በሕይወት ዘመኗ የመኪና ግዥ አከናውና አታውቅም፤ ይሁን እንጂ አልተነጫነጨችም:: ወደ መኪና ሻጩ ዘንድ ሄዳ አንዱን አምቡላንስ መሰል መኪና መረጠች፤ ከዚያም እያሽከረከረች ፈተነችው፤ ወደ ቤትም ይዛው መጣችና፤ "እነሆ መኪናችን አለች"::

በእውነት ኮራሁባት - ታላቅ ክብርም ተሰማኝ::

በዚያች መኪናዋ መሾፈርን እንደገና ተማርኩ:: አንድ ቀን ቤተሰቡ መኪናዋን ያጥቧት ነበር፤ ኤልዛሮቩ በእግሬ ላይ እንዳለ ወደ



ውጭ ወጣሁ:: ወደ መኪናዋ በዝግታ ስጠጋ፤ በሾፌሩ በኩል ያለው በር ክፍት እንደሆነ ተገነዘብኩ:: ወደ ውስጥ ስመለከት፤ የእኔንና በላዬ ላይ የተሸከምኩትን ለላሣ ፓውንድ የብረታ ብረት ክብደት ይዤ ከመሪ በስተኋላ ለመቀመጥ የሚበቃውን ስፍራ ገመትኩ:: ቤተሰቤ ትኩረታቸው በእኔ ላይ አልነበረም፤ ራሴን እንደ ምንም ከመቀመጫው ላይ አኖርኩና ሞተሩን አስነሣሁት:: ቤተሰቦቼ ደነገጡ::

ኢቫ ወደ በሩ ዞራ መጣችና "ምን እያደረክ ነው?" ስትል ጠየቀችኝ::

ፈገግ አልኩና፤ "እያሽከረከርኩ ልወጣ ነው!" አልኳት:: የምታየውን አላመነችም፤ ሳታስበው፤ "ልታደርገው ግን አትችልም" አለች::

ይሁን እንጂ፤ ለአንድ ዓመት ያህል መኪና ባላሽከረክርም፣ የመጨረሻው የመኪና ሾፌርነት ተግባሬ በሞት ቢጠናቀቅም አሁን ማሽከርከር ካልጀመርኩ ዳግመኛ የመኪና መሪ ይዤ እንደማላሽከረክር አንድ ነገር በጆሮዬ ሹክ አለኝ::

መኪናዋን በዝግታ ወደ ኋላ ነድቼ አወጣሁና በህንጻው ዙሪያ አሽከረከርኩ:: በእርግጥ ረዥም ጉዞ አልተጓዝኩም፤ ይሁን እንጂ እያገገምኩ ለመሄዴ ምስክር የሆነ መታሰቢያ ነበር:: አሁንም ቢሆን በሰዓት ለማንያ ኪሎ ሜትር ለመብረር ወይም ረዥም ርዝመት ባለው ድልድይ ላይ ለማሽከርከር ደስተኛ አይደለሁም:: ይሁን እንጂ መሄድ እስከምፈልግበት ርቀት ድረስ እያሽከረከርኩ እጓዛለሁ::

በእርግጥ አንዳንድ ቀጠሮዎቼን መከታተልና በሳምንት ሁለት ቀናት በዶክተሮች ቢሮ ያለኝን የጤና ምርመራ የመከታተሉ ጉዳይ የወደቀው በኢቫ ላይ ነው:: መጨመር የምፈልገው ነገር ቢኖር እኔ ለእንክብካቤ የምመች ቀላል ሰው አለመሆኔን ጭምር ነው:: አስቸጋሪ ሰው እንደነበርኩ እውነት ነው:: ጤንነቴ እየተሻሻለ ሲሄድ፤ በሆነ ባልሆነው የምነጫነጭና በጥቃቅን ነገሮች ሁሉ የማጉረመርም ሆንኩ (ይህ ግን በጊዜው ለእኔ አይታወቀኝም ነበር)፤ ኢቫም እኔን ለማስደሰት ብዙ ተጨንቃለች፤ ያም ሆኖ ተሳክቶላታል::

የችግሩ ሁሉ ምክንያት ደስተኛ ስላልነበርኩ ነው:: ብዙዎቹ ችግሮቼ ይመነጩ የነበሩት ፍጹም ተስፋ የለኝም ከሚል ስሜቴ ነበር:: በጣም ለረዥም ጊዜ አንዲት ብርጭቆ ውሃ በገዛ እጄ አንስቼ አልጠጣም:: ምንም እንኳን በራሴ መቅዳት ብችልም፤ ሰው መጥቶ ካልረዳኝ በቀር በፍጹም አልጠጣም:: እያንዳንዷ ትንሽ ድርጊት እንኳን ዋጋ እንደሌለው ሰው እንዲሰማኝ ታደርገኛለች::

አብዛኛውን ጊዜ ኢቫ በሁኔታው ላይ ወዲያውኑ እኔን ሳታናገር እርምጃ ትወስዳለች:: ማድረግ የምትችለውን ያህል ታደርግ ነበር:: አንዳንድ ጊዜ ኢቫ ነገሮችን በራሷ መንገድ በመስራት ላይ ሳለች፤ እኔ እንዴት እሠራው እንደነበር ለእርሷ ለመንገር እፈጥናለሁ:: ነገር ግን ወዲያውኑ ያንን በማድረግ ምን ያህል ስሜቷን እንደጎዳሁት እገነዘባለሁ:: ይሁን እንጂ ቃሎቼ አንድ ጊዜ አምልጠውኝ ወጥተዋል:: ስለአለሁበት ሁኔታና ስለእርሷም አስብና፤ በጣም አዝናለሁ:: "ማድረግ በምትችይው አቅም ሁሉ እያደረግሽ ነው" እላለሁ:: ራሴንም የማሳስበው ነገር ነበረኝ፤ ቁም ነገሩ ያንን ነገር እንዴት ማድረግ እችል እንደ ነበር ሳይሆን፤ አሁን ማድረግ አለመቻሌ ነው::



በነዚያ ጊዜያት እርሷ የምትናገረው ጥቂት ነገሮች ብቻ ቢሆንም በኋላ ላይ በዕለታዊ ውሎ እንቅስቃሴ ማስታወሻ ደብተሯ ላይ የጻፈችውን እንዳነብ አድርጋለች:: ከጻፈቻቸው አንዱ፤ "ዶን እኔ በማደርገው ነገር ሁሉ ላይ አቃቂር ያወጣል:: እየተሻለው በመሄዱ ምክንያት መሆን አለበት" የሚል ይገኝበታል::

ያ ለእኔ አሳዛኝም አስቂኝም ነው:: አንዳንድ ውሳኔዎችን እንደገና መስጠት በመጀመሬ እየተሻለኝ እንደሄደ አውቃለች:: ነገሮችን ለማድረግ የነበረኝ የነቃ ፍላጎት እየተሻለኝ ለመሄዱ የእርሷ መመዘኛ ነበር:: በሕይወት ዕለት ተዕለት እንቅስቃሴዎች ለመሣተፍና በዙሪያዬ እየሆነ ስላለው ነገር ለመጠየቅ የምፈልግ ይመስላል::

ጥሩ ባህሪ ያለው ታማሚ ሆኜ ነገሮችን ቀላል አድርጌላት ብሆን እመኝ ነበር::

እያገገምኩ በነበረበት ጊዜ አስቸጋሪ ሆኖብኝ የነበረው የቤተሰቦቼ ጉዳይ ሲሆን፤ ይኸውም የሦስቱ ልጆቻችን ከእኛ መለየታቸው ጉዳይ ነበር:: እናትና አባታቸውን ያጡ ልጆች አልነበሩም፤ ይሁን እንጂ ለሦስት ወራት ያህል ከሌሎች ሰዎች ጋር እየኖሩ ነው:: ሁለቱ መንታ ልጆቼ በሉሲኒያ ውስጥ ከሚኖሩት ከኢቫ ቤተሰቦች ጋር እንዲቆዩ ተደርጓል::

ከእኛ ያን ያህል መራቃቸውን የወደዱት እንዳልነበረ አውቃለሁ:: ርቀቱ ልጆቹ ከእኛ እንደራቁና እንደተለዩ እንዲሰማቸው አድርጓል፤ ይሁን እንጂ ሁሉንም ተቋቁመውታል:: ምናልባትም ገና አንደኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች በመሆናቸውና በዚያም ዕድሜ ከለወጡት ሥፍራ

ጋር ቶሎ መላመድ አላስቸገራቸው ይሆናል:: በዚያ ጊዜ ከመንትያዎቹ በአምስት አመት በላጭና አሥራ ሦስት ዓመት ዕድሜ የነበራት ኒኮል፤ ከሴት ጓደኛዋ ቤተሰቦች ጋር በመጠጋት በዚያው ቆይታ የመካከለኛ ደረጃ ትምህርቷን መከታተል ችላለች:: ከእኛ ተሰይታ መሄዷ ለእርሷ አጅግ አሳዛኝ ገጠመኝ ሳይሆን እንዳልቀረ አስባለሁ::

አደጋው የደረሰው በጥር ወር ውስጥ ሲሆን እስከ ሰኔ ወር ድረስ ልጆቹ ፈጽሞውኑ ወደ ቤት አልተመለሱም ነበር:: ለልጆቻችን አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮች ማቅረብ የማንችል በመሆናችን እጅግ ተሳቅቄና አዝኜ ነበር::

ሆስፒታል በነበርኩበት ጊዜ በሳምንቱ ማብቂያ ቀናት ልጆቹ ሊያዩኝ ይመጡ ነበር፤ ያ ደግሞ ለእነርሱ ከባዱ ጊዜ ነው:: ወደ ሆስፒታሉ መጥተው መጀመሪያ ያዩኝ ጊዜ፤ የክፍሉ የሥነ አዕምሮ ሃኪም መልካም ነገር አደረገላቸው:: ሦስቱንም ልጆች ወደ አንድ ክፍል ወሰደ፤ በሰው ቁመና ልክ የተሠራና ከመሣሪያ ጋር የተያያዘ የሰው ምስል አካል በማሳየት፤ በእኔ አካል ላይ የደረሰውን ጉዳት አሳያቸው:: በዚህ መንገድ እኔ ወዳለሁበት ክፍል ሲገቡ የሚያዩትን ነገር አስቀድሞ ገለጸላቸው::

ይህንን በማድረጉ ደስተኛ ነኝ፤ እንደዚያ ዐይነት ቅድመ ዝግጅት ያላደረጉ ብዙ አዋቂ ሰዎች እንኳን፤ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲያዩን በሚታይ ሁኔታ ድንጋጤአቸው ተገልጿል:: እነርሱ በሚያሳዮት ድርጊት እኔ የነበርኩበት ሁኔታ ምን ያህል አስከፊ እንደነበር አመዛዝናለሁ::

ልጆቹ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ክፍሌ በመጡ ጊዜ ሦስቱም ሊጨብጡኝ መቅረብ የሚችሉትን ያህል ርቀት ተጠግተውኝ ነበር:: በጣም ይወዱኝ ስለነበር ደህንነቴን በራሳቸው ማረጋገጥ ይፈልጉ ነበር::



እርግጥ ነው በዚያ ጊዜ በሞትና በሕይወት መካከል ነው የነበርኩት፤ ይሁን እንጂ እነርሱን በማየቴ ብቻ መልካም ሆኖልኝ ነበር:: ሀኪሞቹ ብዙ እንዲቆዩ አልፈቀዱላቸውም:: ምንም እንኳን አካሌ በአስቃቂ ሁኔታ መጎዳቱ የሚታይ ቢሆንም፤ በቅርቡ ደህና እንደምሆን በነገርኳቸው ጊዜ ልጆቹ አምነውኝ ነበር::

እነርሱ ከሄዱ በኋላ፤ ኢቫ ተመልሳ ወደ ቀዶ ጥገና ክፍሉ መጣች:: እኔ ይህንን አላስታውስም፤ በዚያ ጊዜ ስለሆኑት ነገሮች ብዙ የማስታውሰው ነገር የለም:: እርሷ እንደነገረችኝ፤ በአክስጂኑ ጭንብል ውስጥ አያየኋት፤ "በዓለም ላይ ምርጥ የሆኑ ልጆች አሉን" ብያለሁ::

ልጆቼ ምንም ነገር እንደጎደላቸው ይሰማቸዋል የሚል ስሜት ተሰምቶኝ አያውቅም፤ ይሁን እንጂ አንዳንድ ጊዜ ከልምድ ማጣት የተነሣ ስለአባታቸው የተሳሳተ አመለካከት ኖሯቸው ይታሰሉ ይሆናል የሚል ስጋት ነበረኝ::

በመጨረሻው ከሆስፒታል ከወጣሁና መራመድም በቻልኩ ጊዜ፤ ከልጆቹ ጋር የጎልፍ ጨዋታ ለመጫወት መሞከሬን አስታውሳለሁ፤ ከአንድና ከሁለት እርከኖች በላይ ማለፍ እንደማልችል አውቅ ነበር:: ከልጆቹ መካከል አንዱ ኳሷን ከእኔ በኋላ አሻግሮ ከመታት ተከትያት መሄድ አልችልም:: በዚህ ነገር በጣም ያዝኑና ይቸገሩ ነበር::

በጨዋታው ጊዜ አንዳንድ ነገሮችን ማድረግ ካለመቻሌ የተነሣ፣ በጨዋታው ሙሉ በሙሉ ከመደሰት ተቆጥበው ነበር፤ በመሆኑም ፈጥነን አቆምነው:: አፍ አውጥተው አይናገሩ እንጂ ለመሮጥ ሙከራ ሳደርግ ወይም ለመውደቅ አደጋ ተጋልጬ ለማየት አለመፈለጋቸውን አውቄአለሁ::

በተጨማሪም ከአደጋው በፊት ሁለቱም ወንዶች ልጆች በባህር ዳርቻው ውሃ ላይ የመንሳፈፍ ልማድ ነበራቸው፤ እኔም አብሬአቸው እንሳፈፍ ነበር:: አሁን መራመድና መኪና ማሽከርከር ከቻልኩ በኋላ፤ በብዙ አጋጣሚዎች የመጫወቻ መሳሪያዎቻቸውንና እነርሱን በመኪናዋ ጭኜ ወደ ጎልፍ መጫወቻ ሥፍራው እወስዳቸዋለሁ፤ ይሁን እንጂ ከእነርሱ ጋር እንዳች ነገር ማድረግ አልችልም:: ይህንን እነርሱ ሊረዱልኝ የቻሉ ይመስላሉ፤ ለእኔ ግን በዚያን ጊዜ ከባድ ነበር::

ልጆቼ ማድረግ የሚፈልጓቸው ሌሎች ነገሮች እንደሚኖሯቸው አልጠራጠርም፤ ነገር ግን ጠይቀውኝ አያውቁም:: ምክንያቱም እኔ ወደ ሁኔታዎች ውስጥ እንዳልገባና ጉዳት እንዳይደርስብኝ በመፍራት ነበር:: በዚህ ምክንያት ልጆቼ በማደጊያ ዕድሜያቸው ላይ ሳሉ እንደልብ ተጫውተው እንዳያድጉ ከአንዳንድ ሁኔታዎች እንዲገደቡ ተጽእኖ እንደተደረገባቸው ይሰማኛል::

ኒኮል ትልቋ ልጃችን የአባቷን ነገር በአግባቡ የምትረዳ ነበረች:: ስሜቷን የምትገልጸው ከጆይ ይልቅ በጣም በተለየ መንገድ ነው:: እርሱ በጣም ስሜታዊ ነው:: ክሪስ ደግሞ ምንም እንኳን ጠለቅ ባለ ሁኔታ ንቁ ቢሆንም ረጋ ያለ ልጅ ነው፤ በመሆኑም እንደ መንትያው ስሜቱን በቀላሉ መግለጽ አይሆንለትም::

ይህ መጽሐፍ በሚጻፍበት ጊዜ፤ ልጆቼን ሰብስቤ አደጋው እንዴት እድርጎ በእነርሱና በቤተሰባችን ላይ ተጽእኖ እንዳሳደረና ስለ እኔ የነበራቸውን አመለካከት እንዴት እንደለወጠው ጠይቄአቸው ነበር:: አደጋው በ1989 በተከሰተ ጊዜ ኒኮል የአስራ ሦስት ዓመት ልጅ ነበረች:: እርሷ እንዲህ ስትል መልስ ሰጠች::



"አደጋው በሕይወቴ ላይ ያሳደረው ትልቁ ተጽእኖ ለበርካታ ወራት ከቤተሰቦቼ ርቁ እንድኖር ማድረጉ ነው:: በዚያ ጊዜ እኖር የነበረው የእኛ ቤተክርስቲያን አባላት ከሆኑት ከጓደኛዬ ካማውልዲን ቤተሰቦች ጋር ነበር፤ አደጋው የራሴን ቤተሰቦች እንዳደንቃቸው አስተምሮኛል:: እኔ ለእነርሱ ሁሉ በጣም ቅርብ ነኝ፤ ምክንያቱም የዚህ አስደሳች ቤተሰብ አካል በመሆኔ ምን ያህል እድለኛ እንደሆንኩ ተረድቻለሁ:: በተጨማሪም ደግሞ ሰዎች ችግር በደረሰባቸው ጊዜ መረዳት እንደሚገባኝ ይሰማኛል፤ ምክንያቱም በዚህ በወጣትነት ዕድሜዬ በአስቸጋሪ ሁኔታ ወቅት ጸሎትንና ባልንጀሮችን እንዴት መጠቀም እንዳለብኝ ተምሬአለሁ:: በአጠቃላይ ሕይወትን በተለየ አቅጣጫ እንድመለከት አድርጎኛል:: በዚህ የወጣትነት እድሜዬ ሕይወት ምን ያህል ውድ እንደሆነችና እያንዳንዷን ቅጽበት በአግባቡ ልንጠቀምበት እንደሚገባ ልገነዘብ ችያለሁ::

በአደጋው ምክንያት ቤተሰቦቼ በጣም መቀራረብ እንዳቻሉ ይሰማኛል:: እንዳችን ለሌላችን እውነተኛ የሆነ ጥንቃቄ እናደርግ እንደነበረም ይሰማኛል፤ ለቤተሰባችን እባል ማድረግ የምንችለውን ሁሉ አድርገናል:: ወንዶቹ ልጆችና እኔ ብዙውን ጊዜ በወንድምና በእህቶች መካከል ከሚታየው መቀራረብ ይልቅ የቀረበና የጠበቀ ግንኙነት አደብረናል:: በአባቴ ላይ የደረሰው አደጋና ከዚያ በኋላ የሆነው ማገገሙ እርስ በእርሳችን እንድንተሳሰብ አስተምሮናል:: እማማ በጣም ጠንካራና በራሷ የምትተማመን ሆናለች፤ ምክንያቱም አባባ ሁልጊዜም ያደርጋቸው የነበሩትን ነገሮች ሊያደርጋቸው አይችልም ነበር:: ቤተሰቡ ሁሉ እንደገና እንዲሰበሰብ አባቴ በዚህ ሁኔታ ውስጥ ምነው ባለለፈ እያልኩ ብቻ እመኝ ነበር::

አባቴ ከፉኛ ከተጎዳ በኋላ፣ እርሱ እንደማንኛውም ሰው አደጋ ሊደርስበት ወይም ችግር ሊያጋጥመው የሚችል ሰው መሆኑን ለመጀመሪያ ጊዜ ተመለከትኩ፡፡ ከአደጋው በፊት፣ በምንም ዐይነት ሁኔታ ጉዳት ሊደርስበት የሚችል አይመስልም ነበር፡፡

ከእነዚያ ዓመታት በኋላ፣ አደጋው ይበልጡን ጠንካራ ሰው እንዳደረገው ተመልክቻለሁ፡፡ እርግጥ ነው ምናልባት አካሉ ተጎድቶ ሊሆን ይችላል፣ ነገር ግን በመንፈሳዊና ስሜታዊ ሁኔታዎች ጠንካሮች እንደሆኑ ከማውቃቸው ሰዎች ይልቅ ጠንክሯል፡፡ በዚያ ሁሉ ሁኔታ ውስጥ ካለፈ በኋላ፣ አሁንም ፍቅር የተሞላና ፍጹም የተሰጠ የእግዚአብሔር አገልጋይ መሆኑ ለእኔ አስደናቂ ነገር ነው፡፡

ስረኸርም ጊዜ ስለ አደጋው ባሰብኩ ቁጥር እናደድ ነበር፣ ነገር ግን ባደግኩ ጊዜ እርሱ በሕይወት ተርፎ ከእኛ ጋ በመሆኑና አደጋውም እጅግ እንድንቀራረብ በማድረጉ እድለኞች እንደሆንን ልገነዘብ ችያለሁ፡፡ በአደጋው ወቅት ሞቶ ቢሆን ኖሮ፣ በሕይወቴ ባጋጠሙኝ አስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ እንዴት ማለፍ እችል እንደነበር አላውቅም፡፡ በመንግስተ ሰማይ ከነበረ፣ ቁጥር ስፍር ከሌላቸው ቀዶ ጥገናዎች በኋላም በሕይወት መኖር ከቻለና ስለዚህም ለመናገር በመኖር ላይ ካለ ሰው በሚሰጠው ምክር ውስጥ በጣም የተለየ ነገር አለ፡፡ አሁን እርሱ የሚናገረውን ነገር በጥሞና ማድመጥ ጀምሬአለሁ፡፡"



ጆይ ደግሞ በአደጋው ወቅት የስምንት ዓመት ልጅ ነበር፤ እርሱ ደግሞ መልስ የሰጠው እንዲህ ሲል ነበር፤

"የመጀመሪያው ትውስታዬ የእናቴ ጓደኛ በሆነች አስተማሪ አማካይነት ከት/ቤት መወሰዴ ነው፡፡ እናቴ ስታለቅስ ባየኋት ጊዜ አንድ ጠንከር ያለ ችግር እንደተፈጠረ አውቄ ነበር፡፡

አባቴን ለማየት ወደ ሆስፒታል መሄዴንም አስታውሳለሁ፡፡

የአባባን አደጋ ሁኔታ እንድናውቅ በአሻንጉሊት ሠርተው አሳዩን፤ እናም ወደ ውስጥ የገባነው ተዘጋጅተን ነበር፡፡ አባባን በዚያ ሁኔታ ውስጥ ማየት የሚከብድ ነገር ነበር፡፡ በዚያ ብዙ አልቆየንም፤ እንዲዚያ ማድረጋቸው ለእኔ ጥሩ ነበር፤ ምክንያቱም እንደዚያ ሆኖ ላየው አልፈለግኩም፡፡ እኔና ክሪስ በሉሲያና ወደሚኖሩት አያቶቻችን ተወስደን በዚያ ተቀመጥን፡፡ በመጀመሪያ ላይ አካባቢው በጣም እንደሚቀዘቅዝ ተሰምቶኝ ነበር፤ በኋላ ግን ቤተሰቦቼ ይናፍቁኝ ጀመር፡፡ መንትያ ወንድሜ ከእኔ ጋር በመሆኑ በጣም ደስተኛ ነበርኩ፡፡ በየሣምንቱ መጨረሻ ላይ ከቦሲር ከተማ ወደ ሀውስቶን በመኪና እንወሰዳለን፡፡ ነገሩ ሁሉ በፍጥነት እንግዳ ሆኖብኝ ነበር፡፡

የአደጋው እጅግ አስከፊ ጎን የነበረው፣ ሌሎች ልጆች ከአባቶቻቸው ጋር ለሽርሽርና ዓሣ ለማጥመድ ሲወጡ እነዚያን ነገሮች ለማድረግ ፈጽሞ አለመቻሌ ነበር፡፡ እስከዛሬም ድረስ ስለዚያ ሁኔታ አብዝቼ አስባለሁ፡፡ አንዳንድ ጊዜ የብስጭት ሁኔታና ድብርት ውስጥ የመግባት ነገር ይሰማኝ ነበር፡፡ ነገር ግን ባለፉት ጥቂት ዓመታት ከአባባ ጋር ሽርሽር ለመውጣትና ዓሣ ለማጥመድ ችያለሁ፡፡ እነዚህ ነገሮች ምን ያህል እንደሚያስደስቱኝ ይገነዘበው እንደሆነ አላውቅም፡፡ እርሱ በአደጋ ውስጥ ባለፈበት ሁኔታ ምን ያህል ሰዎች እንደሚወዱንና ለእኛም

ቤተሰብ ግድ እንዳላቸው ለመገንዘብ ችያለሁ። እግዚአብሔር በሕይወታችን ባይኖርልን ኖሮ፤ በዚህ ሁሉ ነገር ውስጥ እንዴት እናልፍ እንደነበር አላውቅም።"

የክሪስ ምላሽ ደግሞ ይህንን ይመስላል።

"የዘጠኝ ዓመት ልጅ ሳለህ አባትህ ምን ጊዜ ለአንተ ትልቁ ጀግና ሰው ነው። በምንም ነገር ሊበገር የሚችል አይመስልህም። በአባቴ ላይ አደጋ እንደደረሰበት በመጀመሪያ ስሰማ፤ የደረሰበት ጉዳት ያንን ያህል ትልቅ ይሆናል ብዬ አላሰብኩኝም። እማማ ስለአደጋው በነገረችኝ ጊዜ እጅግ ተስፋ ቆርጣ ነበር፤ እናም የሚፈሰውን እንባዋን መደበቅ አልቻለችም። አባባ ግን ጠንካራ ነበር፤ እርሱ ሲያለቅስ በጭራሽ አይቼ አላውቅም።

በቀዶ ጥገና ክፍሉ ውስጥ በብዙ የህክምና ባለሙያዎች ተከቦ፣ በኦክስጂን እየተነፈሰና መናገር እንኳን ተስኖት እያየሁ፤ በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ ተሽሎት ወደ ቤት እንደሚመለስ ሙሉ ለሙሉ ጠብቄ ነበር።

አብዛኞቹ ዋነኛ የቀዶ ጥገና ህክምናዎቹ በተደረጉለት ጊዜ እኔ በዚያ አልነበርኩም። ከአደጋው በኋላ በነበሩት ጥቂት ቀናት ውስጥ ከአያቶቼ ጋር ለመኖር ሄድኩ። አባባን ለማየት የነበረኝ ዕድል በሳምንቱ መጨረሻ ቀናት ላይ ብቻ ነበር። እርሱን ማየት በቻልኩባቸው በእነኛ አጫጭር ጊዜዎች ምን ያህል ክፉኛ እንደተጎዳ መገንዘብ ጀመርኩ - በመንፈሱም በአካሉም። በእጁና በእግሩ ላይ የነበሩ እነኛ ብረታ ብረቶች ትኩረቴን ስበው ያስደንቁኝ ነበር፤ ይሁን እንጂ ክፉኛ የህመም ስቃይ እያደረሱበት እንዳሉ ተረድቻለሁ። እጅግ ተዳክሞ ስለነበር ሁኔታው ልክ



ገና ከእንቅልፉ እንደነቃ ወይም ፈጽሞ ተኝቶ እንዳላደረ ሰው ነበር የሚመስለው። አንዳንድ ጊዜ እኔ እገምታለሁ። ምንም እንኳን ስለ ድብርት የማውቀው በጥቂቱ ቢሆንም፤ በዚያ እንደተጠቃ አውቄ ነበር።

ልጠይቀው በሄድኩ ጊዜ አደርግ የነበረው የመጀመሪያ ነገር በዝግታ ወደ እርሱ መቅረብና እጄን በእርሱ አንገት ዙሪያ አድርጌ ማቀፍ ነበር። በቀስታ እጨብጠዋለሁ። በሕይወቴ ለመጀመሪያ ጊዜ አቅም የሌለው ተሰባሪ ነገር ሆኖ ተሰማኝ። ከሆስፒታል ወደ ቤት ከተመለሰ በኋላ እንኳን፤ ያንኑ ነገር ነበር ደጋግሜ የማደርገው - ከትምህርት ቤት ወደ ቤት ተመልሼ አባቴን መጨበጥ። ይህ ሁኔታዬ ለእኔ በእርሱ የመተማመንን ለእርሱ ደግሞ ምቾትን ይሰጠዋል። በሁለቱም መንገዶች እንደ ሠራ ተስፋ አደርጋለሁ።

ወንድሜ ጆይና እኔ እያደግን በሄድን መጠንና አባቴም እየተሻለው ሲመጣ፤ በእስፖርትና ከቤት ውጭ በሚዘወተሩ ጨዋታዎች ይበልጥ እየተሳብን ሄድን። አባባ ከእኛ ጋር ለመቀላቀል የተቻለውን ጥረት ያደርግ ነበር። አንድ ጊዜ ኳሷን አሻግሬ ስወረውራት ክፉኛ እንደወደቀ አስታውሳለሁ። በጨዋታው ላይ ሚዛኑን አጥቶ ይንገዳገዳል፤ አንዳንድ ጊዜም ይወድቃል። በብዙ ሁኔታዎች ውስጥ ስለዚህ ነገር እንባዬ እያመለጠኝ አልቅሻለሁ። እርሱም እንደ እኔ እንዳለቀሰ እርግጠኛ ነኝ። ስሜታዊ በሆኑት ሁኔታዎች ግን አባቴ ሁልጊዜም ከእኔ ጋር ነበር። ልጆቹ በሚሠሩት ነገር ላይ ከፍተኛ ትኩረትና ፍላጎት ነበረው። ከሁሉም በላይ ደግሞ፤ በአንዳንድ ሁኔታዎች ከገነት የመመለሱን ነገር ከፍተኛ ግምት የሰጠነው ይመስለኛል።

በአባቴ ላይ በደረሰው አደጋ ምክንያት ቤተሰባችን በጣም ተቀራረበ። ሁላችንም ሥራዎችን ከመከፋፈልም አልፈን የተለያዩ

ሚናዎችን እንጫወት ነበር። አባባ እያገገመ በነበረበት ወቅት እማማ ውሳኔ የምትሰጥና እኛንም ሥነ ሥርዓት የምታስይዝ ሆነች። እኔ ደግሞ የቤቱ አባወራ እንደሚያደርገው ለማድረግ የተቻለኝን ጥረት አደረግኩ። አንዳንድ ጊዜ እንደዚያ እንዳደርግ ራሴን አስጨንቅ ነበር፤ ነገር ግን በዚያው ነገር ውስጥ እየበሰልኩ ሄድኩ። ኒኮል በምትችለው አቅም ሁሉ ለእኔና ሰጆይ እንደ እናት ሆነችልን።

ከአደጋው በኋላ አባባ ሰዓመታት ያህል በድብርት ውስጥ ገባ፤ አሁንም እንኳን በጥቂቱ ምልክቶቹ ይታዩበታል። ምናልባትም ከአደጋውም በፊት እንኳን ሲታገለው ሳይቆይ አይቀርም። እንደዚያ እያደረገ ከቆየም እኔ ግን በጭራሽ አልተገነዘብኩትም። አባቴ እጅጉን በራሱ የሚተማመንና ውስጠኛውን ማንነቱን አልፎ አልፎ ብቻ ሰቤተሰቡ ግልጽ የሚያደርግ ሰው ነው። እኔም እንደርሱ እንደሆንኩ አስባለሁ።"

ከአደጋው ጋር በተያየዘ ኢቫ ስለ እኔ የነበራት አመለካከት መለወጡን ስትገልጽ እንዲህ ብላለች።

"ከአደጋው በኋላ በነበሩ የመጀመሪያዎቹ ቀናቶች ውስጥ ዶን አንዳንድ ውሳኔዎችን ለመወሰን ሲቸገር በማየቴ በጣም ተደንቄ ነበር። እርሱ ምን ጊዜም የሕይወትን ውጣ ውረድ የሚጋፈጥና እራሱንና ሌሎችን ጭምር ብዙ እንዲሠሩ የሚያደፋፍር ሰው ነበር። ለመናገር መሞከሩን ባቆመ ጊዜ ልክ የማላውቀው ዓይነት ሰው ሆኖ ይሰማኝ ጀመር። በድብርት ውስጥ መግባቱም አንድ አዲስ ጉዳይ ነበር። "ከፉው ጊዜ" እየቀረበ እንደመጣ ምልክቶቹን ማስተዋል ጀምሬ ነበር። የህመም ስቃዩ እየከፋ ሲሄድ ድብርቱ ይጨምራል፤ መተኛት አይችልም እናም ችግሩ እየከፋ ይሄዳል።



በዓመታት መካከል አንድ ነገር እየተገነዘብኩ መጣሁ፤ ዶንን በራሱ ነገሮችን እንዲያደርግ የምታወው ከሆነ በመጨረሻው እየተጠናከረ ይሄዳል ብዬ አስብ ነበር። መስማት የሚያስፈልገውን አንድ ነገር ልነግረው ስፈልግና እርሱ ግን ማወቅ ሳይፈልግ ሲቀር አንደበቴን እሰበስባለሁ፤ በጥቂት ሁኔታዎች ውስጥ ግን አልተሳካልኝም ነበር።

ምንም እንኳን ጉዳተኛ እንደሆነና ወደፊትም በዚሁ እንደሚቀጥል ባውቅም፤ ዛሬ ዛሬ ጉዳት እንደደረሰበት ሰው እንኳን አድርጌ አላስብም። ዶን ሰላም ያሰው ሰው ስለሆነ የነበረበትን ስቃይ እንኳን ልረሳውና ጉድለቶቹንም ላላስባቸው ችያለሁ። የእኔ ባሰቤት በርግጥ የተሰየ ሰው ነው።

ምናልባትም ከእኔ ይልቅ ልጆቼ ነበሩ ከጉዳቴ እንደማገግም እርግጠኞች የሆኑት። ህክምና ሲደረግልኝ፤ በስቃይ ሳቃስት ወይም ለሞት በተቃረብኩበት ሁኔታ ውስጥ ስገባ በጭራሽ አይተው አያውቁም፤ ምክንያቱም ያንን እንዲያዩ ባሰመፈለጌ ነበር። በተቻለው መጠን ነገሮችን እንሸፋፍንባቸዋለን። ኢቫ እጅግ አስከፊ በሆነው ሁኔታዬ ውስጥ አይታናለች፤ ልጆቼን ግን በተቻለ መጠን ሁኔታዬን እንዳያዩ ታሸሻቸው ነበር።

ምንም እንኳን እነርሱ ባይቀበሉትም በተለይ መንትያዎቹ ልጆች ከእኔ ጋር የነበራቸው ቅርርብ ተቋርጦ ነበር። ምክንያቱ ደግሞ እድሜያቸው ስምንት ዓመት መሙላቱ ነው። ይህ ዕድሜ የቡድን እስፖርቶችንና ሽርሽርን የመሳሰሉ ተግባራዊ እንቅስቃሴዎች

ለመለማመድ አስፈላጊ የሆነ የዕድገት ጊዜ በመሆኑ የእኔ በቅርብ ሆኖ ሁኔታዎችን የመከታተልና የማለማመድ ሚና አጥተውታል።

አሁን ወደ ኋላ ሳስብ፤ አደጋው ከማንም ይልቅ ወላጆቼን በዘላቂነት ጎድቷቸው እንደሄደ አስባለሁ። እንደ እውነቱ ከሆነ እድገን ለብሯቸዋል፤ ከሦስቱ ወንዶች ልጆቻቸው የመጀመሪያው እኔ ነኝ፤ ሁላችንም ደግሞ ጤነኞች ነበርን። ከዚያ ዕድሜዬ ሰላሳ ስምንት ዓመት ሲሞላ በድንገት ልባቸውን የሚሰብር ነገር ተከሰተ፤ ለእኔ ምንም ሊያደርጉልኝ እንደማይችሉ እስከሚያስቡ ድረስ ተስፋ ቆረጡ። ለረዥም ጊዜ ምናልባት አንድ ቀን ይሞታል ብለው ያስቡ ነበር።

አባቴ በዘመኑ ሁሉ በውትድርና ነው ያገለገለው፤ እናታችን ደግሞ ሌሎችን የቤት ጣጣዎች ቀጥ አድርጋ ይዛ ነበር። ይሁን እንጂ ሆስፒታል በገባሁባቸው የመጀመሪያ ሳምንታት ሊያዩኝ በመጡ ጊዜ እናቴ ራሷን ሳተች። አባቴ ከንዷን አፈፍ አድርጎ በመያዝ ክፍሉን ለቃ እንድትወጣ ረዳት። በእንደዚያ ያለ የተበላሸ የአካል ቅርጽ ሆኜ ልታየኝ አልተዘጋጀችም። ማንም ሰው እንደሷ ሲሆን ማየቴን እርግጠኛ አይደለሁም።

እስከ አሁንም ቢሆን ከእናቴ አዕምሮ ውስጥ የአደጋው ነገር መጥፋቱን እርግጠኛ አይደለሁም። ቤተሰቦቼ ለእኔ የነበራቸውን ፍቅር የሚገልጹ ሁለት ውብ ትውስታዎቼ የሚቀጥሉት ናቸው።

የመጀመሪያው፤ ከአደጋው ቀጥሎ በነበረው የበጋ ወራት የሆነው ነው። በዚያ ጊዜ ኢቫ ለራሷ እንዳች ነገር ለማድረግ ግድ አልነበራትም፤ እናም የሳውዝ ፓርክ ቤተክርስቲያን ወጣቶችን ወደ በጋው ሽርሽር ስፍራ ልትወስድ ወሰነች። በአካል ጤነኛ በነበርኩበት ጊዜ ያንን ማድረግ



የእኔ ሥራ ነበር። እንዲህ በሚሆንበት ጊዜ እርሷን ተክቶ ከእኔ ጋር የሚሆን የግድ አንድ ሰው መተካት ነበረበት።

እናቴ በደስታ ነገሩን ተቀበለችው። ወጣቶቹ ወደ ሽርሽሩ የሚሄዱበት ሳምንት ተቃረበ፤ እናም ኢቫ እኔን ለእናቴ ትታ ሄደች። በእያንዳንዱ ቀን እማማ ምግብ ታዘጋጅልኛለች፤ በእርሷ እዚያ መገኘ ትም በጣም ተደስቼ ነበር። ነገር ግን በአንድ ዕለታዊ ተግባር እጅግ ተሳቅቄ ነበር እናቴ የሽንትና የአይነምድር መቀበያ ዕቃዎችን ማጸዳዳት ነበረባት። አዎ በህፃንነቴ የሽንት ጨርቆቼን ትለውጥልኝ እንደነበረ አውቃለሁ፤ ይሁን እንጂ በአሁኑ ማንነቴና በህፃንነቴ ጊዜያት መካከል በርካታ ዓመታት አልፈዋል።

አስታውሳለሁ፤ በመጀመሪያው ቀን እኔን በመንከባከብ ላይ ሳለች የአይነ ምድር መቀበያውን እንድታቀርብልኝ ጠየቅኋት። ያ ድብቅ ያልሆነ የተለመደ ተፈጥሯዊ ግዳጅ እንደሆነ እንዳውቀው ለማድረግ ሞከረች። ከጨረስኩ በኋላ ለእርሷ ለመንገር ከፍተኛ የሆነ የውስጥ ጭንቀት ተሰማኝ።

እርሷ እንደጨረስኩ በመጠየቋ ምክንያት ከጭንቀቴ ገላገለችኝ። በአምንታ ራሴን አነቃነቅኩ። መቀበያውን አንስታ ወደ መታጠቢያ ቤቱ ይዛው ሄደች፤ ከዚያ በኋላ በሕይወት ዘመኔ ከሰማኋቸው ድምጾች ሁሉ ፈጽሜ የማልረሳውን ድምጽ ሰማሁ። ወደ መታጠቢያ ቤቱ አይነምድሩን ከደፋች በኋላ እማማ ስትዘምር እሰማት ነበር። የሰው ልጅ ለሌላው ሰው ማድረግ የሚችለውን የመጨረሻውን ዝቅተኛ ነገር እያደረገች ቢሆንም ዕቃውን እያጠበች ትዘምራለች። ነገሩ ሁሉ በልጅነቴ ታደርግልኝ የነበረው የእናትነት ተግባሯ እንደገና የተመለሰ ይመስላል። አንድ ጊዜ ታደርገው እንደነበረ ልጇ ሊያደርግ የማይችለውን ነገር

እያደረገችለት ነበረ፤ እናም ደስተኛና ሥራዋም የተሣካላት ነበረች:: ያንን ትዝታ ከአዕምሮዬ አላወጣውም፤ ምክንያቱም አንድ እናት ለልጇ ያላት ብቸኛ ፍቅር የተገለጸበት ድርጊት ስለነበረ ነው::

የማስታውሰው ሁለተኛው ነገር፤ ከአባቴ ጋር የነበረኝን የአጭር ጊዜ የግል ቆይታ ነው:: ይህም ከእናቴ ጋር እንደነበረኝ ቆይታ ሁሉ ልብ የሚነካና ተውኔታዊ የሚመስል ነበር:: አንድ ቀን ከሰዓት በኋላ ቤተሰቦቼ 250 ማይሎች ርቀት ተጉዘው ሲጠይቁኝ ወደ ቅዱስ ሉቃስ ሆስፒታል ከመጡ በኋላ ተመልሰው ወደ ቦሲር ከተማ ለመሄድ እየተዘጋጁ ነበር::

በማላስታውሰው የሆነ ምክንያት እናቴ ከክፍሉ ቀድማ ወጥታ ነበር:: እኔና አባቴ ብቻችንን በሆንን ጊዜ ወደ አልጋዬ መጥቶ ደህነኛ የነበረውን የቀኝ እጄን ጠንካራ በሆነው የእጅ መዳፍ ጨብጦ ያዘ:: ወደ እኔ እጅግ ተጠግቶ ከፍተኛ በሆነ ስሜትና ፍጹም ሐቀኝነት በተሞላበት ሁኔታ፤ "ያለኝን ነገር ሁሉ በመስጠት ከጎንህ እቆማለሁ፤ የአንተን ነገር በእኔ ጣለው" ሲል ተናገረ::

አዎን አባቴ ነው፤ ከዚያም በላይ ከሌሎች ጊዜዎች ሁሉ ይልቅ ምን ያህል እንደሚወደኝ ተገነዘብኩ::

ዶክተሩ በተደጋጋሚ "ለአንተ የምናደርገው ማንኛውም ነገር ማድረግ የምንችለውን የመጨረሻ ነገር ነው:: አረኛም እድሜና ስኬታማ የሆነ ሕይወት ሲኖርህ እንደሚችል አትቁጠር:: ቁርጥማትና በርካታ የሆኑ ውስብስብ ችግሮች ይከሰታሉ፤ በዚህም ታላቅ ጦርነት ከፊትህ ይጠብቅሃል" ሲል ነግሮኛል::



የሚናገረውን ነገር ያውቅ ነበር:: አሁን እደጋው ከደረሰብኝ አሥራ አምስት ዓመታት አልፈዋል:: የቁርጥማቱ ስሜት ይሰማኝ ጀምሯል:: ትንሿም ሰውጥ ብትሆን ትጎዳኛለች፤ ፈጥኜም እደክማለሁ:: አንዳንዶቹ ጉዳዮች ከእድሜ ጋር የተያያዙ ሊሆኑ ይችላሉ፤ ነገር ግን እግሮቼንና ጉልበቶችን እግዚአብሔር አስቀድሞ ሲፈጥራቸው እንድጠቀምባቸው ካቀደው ውጭ እየተገለገልኩባቸው የመሆኑ ውጤት እንደሆነ አስባለሁ::

አሁን እንኳን የግራው ጉልበቴ ከመጠን በላይ የተሰጠጠ ነው፤ በመሆኑም አንድ ሰው ከኋላዬ መጥቶ በድንገት ጀርባዬን መታ ቢያደርገኝ ፈጥኜ ራሴን ማቆም አሰብኝ፤ ካልሆነ ግን ዝም ብዬ ወደፊት መገስገሴን እቀጥላለሁ:: ወደ ከፍታ ስፍራ ወደፊት በምሄድበት ጊዜ ሚዛኔን ለመጠበቅ እንዲያስችለኝ ጉልበቴን መቆጣጠር አልችልም::

ነገሮችን ቀለል ለማድረግ እንዲህ እያልኩ እቀልዳለሁ፤ "በቴክሳስ ውስጥ በሚገኙ በአንዳንድ ምርጥ ስፍራዎች ላይ ወድቄአለሁ" ወይም፤ "ዶን ፒፐር እዚህ ወደቀ" ለሚል ማስታወቂያ ኮሚሽን እከፍላለሁ" እላለሁ::

አንድ ጊዜ በቴክሳስ ተራራማ ሀገር፣ ከቤት ውጭ የሚደረግ ኮንፍራንስ እሳተፍ ነበር:: ስፍራው ሜዳማ ስላልነበረ በምራመድበት ጊዜ ድንገት ወደቅኩ ጉዳት አልደረሰብኝም፤ ይሁን እንጂ ገና በመጀመሪያው ቀን ሦስት ጊዜ ነበር የወደቅኩት::

ምንም እንኳን የሚቻላቸውን ሁሉ ቢያደርጉልኝም፤ አንደኛው እግሬ ከሌላኛው ይልቅ በአንድ ኢንች ከግማሽ ያህል ያጠረ ነው:: ይህ በራሱ የጀርባ አጥንቴን እንዲጎብጥ አድርጎታል:: በጭኔ መገጣጠሚያ

ላይ እንደሆነው ሁሉ የጀርባ አጥንቴም መጎዳትና መለያየት ጀምሯል:: የቀኝ እጄ ክርን እጅጉን ስፍራውን በመልቀቁ ቀጥ አድርጌ ልዘረጋው አልችልም:: ዶክተሮቹ ማድረግ የሚችሉትን ሁሉ አድርገውልኛል፤ ይህም ብዙ ጊዜ ቀዶ ጥገና ማድረግን ይጨምራል:: ክርኔ የተሰነጠቀው ከውስጥ ነው፤ በመሆኑም ወደኋላ ካጠፍኩት በኋላ መልሼ ለመዘርጋት በጣም ያስቸግረኛል:: ዶክተሩ የሚጠቀምበትን ቋንቋ ልጠቀምና፤ "ፍጹም ሽባ" የሆነ መታጠፊያ ነው::

እንዲህ ያለ ጉዳት በቀላሉ ይቅርታ የሚያደርግ አይደለም፤" ሲል ተናግሮ ነበር:: አንድ ጊዜ ስፍራውን ከለቀቀ እንደገና ለማስተካከል ይከብዳል::

እንግዲህ ይህ አንዱ ልቀበለው የተገባ የአዲስ ሕይወቴ ገጽታ ነው::

አንድ ጊዜ በዶክተር ቶም ግሪደር ቢሮ ታክሜ ስጨርስ፤ ወደ ግል ቢሮው እንድገባ ጠየቀኝ:: ምንም እንኳን በርካታ የሥራ ጫና ቢኖርበትም፤ ከልቡ በእኔ ጉዳይ ላይ ትኩረት የሰጠ በመሆኑ ስለ ብዙ ነገሮች ተነጋገርን::

ድንገት እንዲህ ስል ጠየቅኩት:: "ቶም፤ በአደጋው ምሽት ወደዚህ ሥፍራ ሲያመጡኝ ምን ያህል ክፉኛ ተጎድቼ ነበር?"

ምንም ሳያንገራግር፤ "ከዚያ የከፋም ተመልክቻለሁ" ለአጭር ጊዜ ዝም አለና በደረቱ ወደ ጠረጴዛው ተጠግቶ፤ "ነገር ግን አንዳቸውም በሕይወት አልኖሩም" አለ::



አንዳንድ ነገሮችን ለማድረግ የተለያዩ መንገዶችን መጠቀም ነበረብኝ:: አዎ በሕይወት አለሁ፤ በሕይወት እስካለሁ ድረስም ኢየሱስ ክርስቶስን የማገልገል እቅድ አለኝ:: ይሁን እንጂ ከፊቴ የሚጠብቀኝን አስቀድሜ አውቄዋለሁ::

በየትኛውም ጊዜ ይህችን ዓለም ለቅቄ ለመሄድ ተዘጋጅቻለሁ::

# 15
# ነፍሳትን መድረስ

"የርህራሄ አባት የመጽናናትም ሁሉ አምላክ የሆነ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ። እርሱ በመከራችን ሁሉ ያጽናናናል፤ ስለዚህም እኛ ራሳችን በእግዚአብሔር በምንጽናናበት፤ በመከራ ሁሉ ያሉትን ማጽናናት እንችላለን" ፪ቆሮ 1፥3-4

አንዳንድ ጊዜ አሁንም እንኳን በመንግስተ ሰማይ እንድቆይ ያልተፈቀደልኝ ለምን እንደሆነ እግዚአብሔርን እጠይቃለሁ። ለዚህ ጥያቄዬ መልስ አልተሰጠኝም። ይሁን እንጂ እግዚአብሔር እኔን ወይም መልዕክቴን የሚፈልጉ ሰዎችን ወደ እኔ በመላክ ወደ ሕይወታቸው መድረስ እንድችል ዕድል እንደሰጠኝ ተምሬአለሁ።

በአደጋው ምክንያት ሰዎችን እንዳገለግል ለመጀመሪያ ጊዜ በሩ የተከፈተልኝ በአንድ ትልቅ ቤተክርስቲያን ውስጥ ተጋባዥ ሰባኪ ሆኜ በነበረበት ጊዜ ነው። የጋበዙኝ በተለይ ወደ መንግስተ ሰማይ ስላደረኩት ጉዞ እንድናገር ነበር። በአዳራሹ ውስጥ በመጀመሪያዎቹ ረድፎች ላይ ከእኔ በስተቀኝ በኩል የነበረች አንዲት ሴት ገና መናገር ከመጀመሬ አለቀሰች። የእንባ ዛላዎች ጉንጮቿን እያቋረጡ ሲወርዱ ማየት ችዬ ነበር። ልክ ስብሰባውን እንደጨረስን እየሮጠች መጣችና እጄን ጨበጠችኝ።

"እናቴ የሞተችው ባለፈው ሳምንት ነበር"።

"እናትሽን ስላጣሽ በጣም አዝናለሁ ..."



"አይደለም ... አይደለም ነገሩ አልገባህም። በዚህ ምሽት ወደዚህ የላከህ እግዚአብሔር ነው። እንዲህ አይነቱ ማረጋገጫ ያስፈልገኝ ነበር። ያላመንኩ ሴት ስለሆንኩ አይደለም፤ አምናለሁ፤ ይሁን እንጂ እናቴን በማጣቴ ልቤ በጣም አዝኖ ነበር። አሁን በጣም መረጋጋት ይሰማኛል። አሁን ያለችው በተሻለ ስፍራ ነው። አ! መጋቢ ፒፐር፤ የተናገርከው ቃል በዚህ ምሽት ያስፈልገኝ ነበር።"

አንዳች ቃል ጨምሬ ከመናገሬ በፊት እጄን አጥብቃ በመጨበጥ እንዲህ አለች፤ "እንደገናም ደግሞ በዚህ ምሽት እግዚአብሔር ወደዚህ የላከኝ፤ ይህ ማረጋገጫ የሚያስፈልገኝ በመሆኑ ምክንያት ነው። ስለማላምን ወይም የማላውቀው ጉዳይ ስለሆነ አይደለም፤ ምክንያቱም እኔም ሆንኩ እናቴ አማኞች ነን፤ ነገር ግን እነኛን ቃላት ዛሬ ምሽት መስማት ያስፈልገኝ ነበር። ስለመንግስተ ሰማይ በዚያ ከነበረ ከአንድ ሰው ማወቅ ያስፈልገኝ ነበር።"

እኔ እስከማስታውሰው ድረስ፤ በዚህ ዓይነት ሁኔታ ያናገረችኝ የመጀመሪያዋ ሰው ናት፤ በእርግጠኝነት የመጨረሻዋ ግን አልነበረችም። እንደዚህ ያሉ ምላሾችን ከመቶዎች ጊዜ በላይ ሰምቻለሁ። በዚያ የነበረኝን ቆይታዬን በመናገር ብቻ ለብዙዎች ባርኮት የመሆኑ ጉዳይ ያስደንቀኛል።

ለሚያምኑ ሰዎች ሁሉ ምስክርነቴ ማረጋገጫ ነው፤ ለሚጠራጠሩና ለማያምኑ ስለ እግዚአብሔር ትኩረት ሰጥተው እንዲያስቡ መንገድ የሚከፍት ነው።

ከአደጋው በኋላ ሁለት ዓመት ቆይቶ፤ ገና የእግር መደገፊያ ብረቶችንና ክራንቾችን እየተጠቀምኩ ሳለ፤ በቤተክርስቲያናችን ያሉት ወጣቶች ወደ ሃውስተን የመጀመሪያ መጥምቃውያን ቤተክርስቲያን ስብሰባ እየወሰድኳቸው ነበር:: ዳውሰን ማክሊስተር የወጣቶች ታዋቂ አስተማሪ የዕለቱ ተናጋሪ ነበር::

ከወጣቶች ጋር ስትሠሩ ሊያጋጥም እንደሚችለው፤ ያለንበትን የሳውዝ ፓርክ ቤተክርስቲያን በቶሎ ለቀን አልወጣንም ነበር:: ምንም ነገር አልተናገርኩም፤ ይሁን እንጂ በመዘግየታችን በጣም ነበር ያዘንኩት:: ቶሎ መድረስ የፈለኩበት ምክንያት፤ ቢያንስ ቢያንስ ስብሰባው ከመጀመሩ ከአንድ ሰዓት በፊት አስቀድመን ካልተገኘን ለእይታ ጥሩ የሆኑ መቀመጫዎች ሁሉ ቀድመው እንደሚያዙ ስለማውቅ ነበር::

ማዘኔ እንዲታወቅብኝ ስማድረግ ሞከርኩ፤ ነገር ግን ከጉባኤው ከሚካሄድበት የመጀመሪያው የመጥምቃውያን የሃውስተን ቤተክርስቲያን በደረስንም ጊዜ ተስፋ እንደቆረጥኩ ነበር:: ወደ ትልቁ የመሰብሰቢያ ህንጻ በገባንበት ጊዜ እንደ ፈራሁት በምድር ወለሉ ላይ የነበሩ መቀመጫዎች ሁሉ በሰዎች ተሞልተዋል:: ደረጃዎችን በመውጣት ወደ ፎቁ ማምራት ነበረብን::

ተጨማሪ እርምጃዎችን በደረጃዎቹ ላይ የመራመዴን ነገር ሳስበው ማጉረምረም ጀመርኩ:: መንቀሳቀስ የምችል ብሆንም እንኳን፤ እነዚያ የእግር መደገፊያ ብረቶችና በብብቶቼ ስር ይገቡ እራመድባቸው የነበሩ ክራንቾች በጣም አድክመውኝ ነበር:: ነገሩን እጅግ አስከፊ ያደረገው ደግሞ አሣንሰሩ አለመስራቱ ነበር:: ያ ሰው ዘግይቶ ባይመጣ ኖሮ፤ እነዚያን ደረጃዎች ሁሉ ስመውጣት እያስፈልገኝም ነበር እያልኩኝ ማሰቤን ቀጠልኩ::



ችግሩ ደረጃዎቹን መውጣት ብቻ አልነበረም፤ አዳራሹ ጥቅጥቅ ብሎ ሞልቶ ስለነበር የቀረው የመጨረሻ መቀመጫ መጨረሻ ላይ ያሉት ረድፎች ብቻ ነበሩ:: ወጣቶቹ አንድ መቀመጫ እንደሚይዙልኝ ቃል ገቡ:: እዚያ እስከደርስ 150 ደረጃዎችን ቆጠርኩ፤ በብዙ ጭንቅ ወደፍጻሜው ደረስኩ::

ጫፉ ላይ በደረስኩበት ጊዜ ፈጽሞ ተዳክሜ ነበር:: ከመቀመጫዎቹ የመጨረሻ ወደሆነው ልጆቹ ወደያዙልኝ ስፍራ ለመድረስ ጥቂት ሲቀረኝ መራመድ ተስኖኝ ነበር:: ከመቀመጤ በፊት - ያም በራሱ ብዙ ጥረት የሚጠይቅ ነበር:: የግንቡን ግድግዳ በመደገፍ ትንፋሼን ሰበሰብኩ:: ትንፋሼን እንደገና ስመመለስ እየሞከርኩ ራሴን እንዲህ ስል ጠየቅኩት፤ እዚህ ምን እያደረኩ ነው?

ወጣቶቹን ወደ ስፍራው የሚወስድ አዋቂ ሰው ማግኘት እችል ነበር፤ ነገር ግን ከእነርሱ ጋር መሆን እፈልግ ነበር:፤ እንደገና ጠቃሚ ሰው እንደሆንኩ ማሰብ እፈልግ ነበር:: በተጨማሪም ለወጣቶቹ ይህ አስደሳቹ ጊዜ እንደሆነም አውቅ ነበር፤ እናም የዚህ ደስታቸው ተካፋይ ለመሆን እፈልግ ነበር:: የሚያስተጋባ ሳቅና ጩኸት አዳራሹን ሞልቶታል:: ወጣቶቹ ለመባረክና ለመመከርም ዝግጁዎች ነበሩ፤ ነገር ግን በዚያ ጊዜ ውስጥ ስለወጣቶቹ እያሰብኩ አልነበረም ወይም ከስብሰባው ምን ያህል ተጠቃሚዎች እንደሚሆኑም እያሰላሰልኩ አልነበረም:: አስብ የነበረው ፈጽሞ ከጥቅም ውጭ እንደሆንኩ ነበር::

በዚያ ቅጽበት ስራሴ ማዘን ጀመርኩ:: ግድግዳውን ተደግፌ እንደቆምኩ በዓይኖቼ ጉባኤውን ቃኘሁት:: ከነበርኩበት ስፍራ ሁለት እርከኖች እልፍ ብሎ አንድ ወጣት ተሽከርካሪ ጎማ ባለው ብስክሌት ላይ ሆኖ አየሁት:: የተቀመጠው በእጆቹ ራሱን ይዞ ሲሆን የሚታየኝ

ጀርባው ነበር፡፡ ወደእርሱ ተጠግቼ ማነጋገር እንደሚገባኝ አወቅኩ፡፡ ለድርጊቴ ምክንያት መስጠት አላስፈለገኝም ነበር፤ መድከሜንም ሁሉ በድንገት ረሣሁ፡፡

ክራንቼን በግድግዳው ላይ አስደገፍኩና በዝግታ፤ ህመም እየተሰማኝ እርሱ ወደነበረበት ሥፍራ ደረጃዎቹን እየወረድኩ ሄድኩ፡፡ አካሉ ግዙፍና መልክ መልካም ወጣት ነው፤ ዕድሜው ምናልባት 16 ይሆናል፡፡ እየቀረብኩት ስሄድ እርሱን ማነጋገር የፈለኩበትን ምክንያት ተረዳሁ፡፡ ከርቀት ሆኜ ያላየሁትን ነገር ስቀርበው አየሁ፤ ልጁ የኤልዛሮቭ ፍሬም በእግሩ ላይ ተደርጎለታል፡፡ ድካሜ ሁሉ ጠፋ፤ ንዴቴና ለራሴ የነበረኝ የሃዘን ስሜት ተወገደ፡፡ ነገሩ ሁሉ እኔ ራሴ በዚያ ተሽከርካሪ ብስክሌት ላይ ተቀምጬ በነዚያ ጊዜያት ያየኋቸውን ስቃዮች ሁሉ እንደገና የማልፍባቸው ነው የሚመስለው፡፡

እጁን በትከሻው ላይ ጣል ሳደርግ ፊቱን ወደ ሌላ አቅጣጫ አዙሮ ነበር፡፡ ራሱን ዘወር አደረገና አትኩሮ ተመለከተኝ

“ይህ ነገር በጣም ያማል፤ አይደለም” ስል ጠየኩት፡፡

ትኩር ብሎ ማየቱን ቀጠለ፤ በውስጡ “እንዴት ያለ ሞኝ ሰው ነው?” የሚል ይመስላል፡፡ ነገር ግን፤ “አዎ፤ በጣም ነው የሚያሳምመው” አለኝ፡፡

“አውቃለሁ” አልኩና ትከሻውን መታመታ አደረግኩ፤ “እመነኝ ስቃዩን አውቀዋለሁ ዓይኖቹ በአግራሞት ፈጠጡ፤ “በዚህ ሁኔታ አልፈህበታል?”

“አዎን አልፌበታለሁ፤ እንዳንተው እንዴ ተደርጎልኝ ነበር”



“እጅግ አስጨናቂ ነው”፡፡

“አውቃለሁ፡፡ በጣም አስጨናቂ ነው፡፡ በግራ እግሬ ላይ አንድ ተደርጎልኝ ነበር፤ ለአሥራ አንድ ወራት ያህል፡፡”

“ማንም ሰው ሊረዳልህ አይችልም” አለ ሃዘን በሞላበት ድምጽ፡፡

“ሊረዱልህ አይችሉም፡፡ ይህ ችግር ለሰዎች ነግረሃቸው ሊረዱልህ የሚችሉት ዓይነት ችግር አይደለም፡፡”

ለመጀመሪያ ጊዜ በዓይኖቹ ውስጥ አንድ ነገር ተመለከትኩ፡፡ ምናልባትም ተስፋ ወይም ሰላም ሊሆን ይችላል፤ ምክንያቱም በመጨረሻው እያለፈበት ያለውን ስቃይ የሚረዳለትን አንድ ሰው አግኝቷል፡፡ አንድ የሚያደርገን ነገር ነበር፤ አጠገቡ ልቆም በመቻሌ ራሴን እንደ እድለኛ ቆጠርኩት፡፡

“ስሜ ዶን ይባላል” አልኩት፤ አሁን የተገናኘኸው እያለፍክበት ያለውን ስቃይህንና ሃዘንህን ሁሉ ከሚረዳልህ ሰው ጋር ነው፡፡

ትኩር ብሎ ሲያየኝ ቆየና አይኖቹ በእንባ ረጠቡ፤ “ከዚህ ሁኔታ ውስጥ በሰላም መውጣቴን እንኳን አላውቀም”፡፡

“ትወጣዋለህ፤ እመነኝ ትወጣዋለህ” ፡፡

“ምናልባት አለ”፡፡

“ምን ሆነህ ነበር?” ወዲያውኑ አንድ ነገር ተገነዘብኩ፤ በፍቃደኝነቱ የተደረገለት የቀዶ ጥገና ህክምና አይደለም፡፡

“በበረዶ መንሸራተት ጨዋታ ላይ ሳለሁ አደጋ ደርሶብኝ ነበር”፡፡

እንደገናም ደግሞ የስፖርት ጃኬት እንደለበሰ ተመለከትኩና

“የእግር ኳስ ተጫዋች ነህ” አልኩት።

“አዎን”

በእኔ ላይ ስለደረሰው አደጋ በአጭሩ ነገርኩት፤ እርሱም ያጋጠመውን ችግር በዝርዝር አጫወተኝ ... “አንድ ነገር ልነግርህ እፈልጋለሁ” አልኩት፤ “አንድ ቀን እንደገና ትራመዳለህ”።

ፊቱ ላይ ጥርጣሬ ሲያጠላበት አስተዋልኩ።

“ምናልባት እንደገና እግር ኳስ ልትጫወት ትችላለህ፤ ነገር ግን ትራመዳለህ”። ማንነቴን የሚገልጸውን ካርዴን ሰጠሁት፤ የስልክ ቁጥሬን በካርዱ ላይ ታገኛለህ፤ እናም በፈለክበት ሰዓት በቀን ይሁን በሌሊት፣ ባመቸህ በቀኑ የትኛውም ጊዜ ልትደውልልኝ ትችላለህ።

ካርዱን ተቀበለና ትኩር ብሎ ይመለከተው ጀመር።

“ይገርቸው ወደመጣሁት ልጆች መመለስ አለብኝ” አልኩና የተቀመጡበትን ስፍራ አመለከትኩት። “ስራመድ በደንብ እንድትመለከተኝ እፈልጋለሁ። እየተመለከትከኝ ሳለ አንተም አንድ ቀን እንደምትራመድ እንድታውቅ እፈልጋለሁ” አልኩትና ሳቅሁ።

“እውነቱን እነግርሃለሁ አንተ ደግሞ ከእኔ በተሻለ ሁኔታ ትራመዳለህ”።

ቀና ብሎ እጄን ጨበጠና እየወዘወዘ ሰላምታ ሰጠኝ። ለረዥም ጊዜ እጄን አጥብቆ ይዞ ነበር። ከእንባው ጋር እየተናነቀ የሚያሰማውን



የስቀይ ድምጽ ስሜት መረዳት ችያለሁ። በመጨረሻው እጄን ለቀቀና ምስጋናውን አዥጎደጎደው።

“ችግርህን የሚረዳልህን አንድ ሰው አግኝተሃል” አልኩት፤ “እባክህን ደውልልኝ”

ያ ልጅ የሚረዳለትን አንድ ሰው ይፈልግ ነበር። ምን ያህል ላግዘው እንደምችል አላወቅኩም፤ ነገር ግን ያለፍኩበት ልምምድ አለኝ፤ ስለ ህመም ስቃይ ልነግረውም እችላለሁ። እርሱ ባለፈበት ሁኔታ ውስጥ ያላለፍኩ ቢሆን ኖሮ፤ “እንደሚሻልህ ተስፋ አደርጋለሁ። ይሻልሃል ብቻ ብዬው አልፍ ነበር - ብዙ ሰዎች የሚጠቀሙባቸው የመልካም ምኞት መግለጫዎች - ነገር ግን ሁኔታውን በጥልቅ ያላገናዘቡ ቃላት ናቸው።

ወደስፍራዬ በደረስኩ ጊዜ ካደረኩት የመውጣትና መውረድ እንቅስቃሴዬ የተነሳ ሰውነቴ በላብ ተጠምቋል፤ ነገር ግን ግድ አልነበረኝም። ዘወር ብዬ ተመለከትኩ፤ አሁንም አትኩሮ ይመለከተኛል። ፈገግ አልኩና እጄን አወዛወዝኩለት፤ እርሱም አጸፋውን መለሰልኝ። ሃዘኑና የተስፋ መቁረጥ ስሜቱ ከላዩ ላይ ተወግዷል።

በቀጣዮቹ ስድስት ወራት፤ ሦስት ጊዜ ያህል የስልክ መልዕክቶቹን ተቀብያለሁ። ሁለቱ ጊዜያቶች በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ የተነጋገርንባቸው ሲሆኑ፤ ሦስተኛው ደግሞ ከአንድ እጅግ ተስፋ በቆረጠበት ሌሊት ያደረግነው የስልክ ንግግር ነበር። እነዚያ የስልክ ጥሪዎች ሁልጊዜም የምደስትባቸው ናቸው፤ ከአንዱ ወደሌላው ለማለፍ የሚደረግ የትግል ጉዞ ስለሆኑ።

አንድ ጊዜ የሃውስተን ቴሌቪዥን ጣቢያ በቀጥታ ስሚተላለፍ ቃለ ምልልስ ግብዣ አደረገልኝ:: ገና በእንግዳ ማረፊያው ክፍል እያለሁ፤ የፕሮግራሙ አዘጋጅ ወደ እኔ መጥቶ ፕሮግራሙ እንዴት እንደሚሠራና ልጠየቃቸው ስለሚችሉ አንዳንድ ጥያቄዎች ገለጻ አደረገልኝ::

"በጣም ጥሩ ነው" አልኩ፤ በተጨማሪ "ተጋባዥ እንግዳ ሆኖ የሚቀርበውስ ማን ነው?"

"አንተ ብቻ ነህ"::

"ምን ማለትህ ነው? የአንድ ሰዓት ፕሮግራም እየሠራችሁ፤ እኔ ብቻ ነኝ እንግዳችሁ?"

"አዎ፤ እንደዚያ ነው"::

ለአንድ ሰዓት ያህል ምን እንደምናገር ይገርመኝ ጀመር:: ገና ማገገም የጀመርኩበት ጊዜ ነበር፤ እናም በዚያ ወቅት የእኔን ታሪክ ለመስማት ሰዎች ምን ያህል ጉጉት እንዳላቸው አላውቅም:: ለቃለ ምልልሱ በቀረብኩት ጊዜ ዶክተሩ የኤልዛሮቭ ፍሬሙን ከእግሬ ላይ እንስቶልኝ፤ በአጥንት መደገፊያ ብረቶችና በክራንች እየተጠቀምኩ ነበር የምራመደው:: በሆስፒታል ውስጥ በነበርኩበት ጊዜ በአደጋው የደረሱብኝን ጉዳቶች የሚያሳዩ ፎቶግራፎች ይገኙ ነበር፤ በዚያ ቀን በተላለፈው ፕሮግራም ምስሎቹ ተላልፈዋል፤ ራሱን የኤልዛሮቭ ፍሬም መሳሪያውንም ጭምር ይገኙ ቀርቤ ነበር::

የቴሌቪዥን ቃለ ምልልሱ በተጀመረ ጊዜ፤ ታሪኬን በዝርዝር ተናገርኩ፤ ከዚያ ጋባዡ ጥያቄዎችን መጠየቅ ጀመረ:: ሰዓቱ በፍጥነት አለቀ:: ገና በቀጥታ የቴሌቪዥን ስርጭቱ ላይ እንዳለን አንድ ሴት ወደ



ቴሌቭዥን ጣቢያው ስልክ ደውላ፤ ከመጋቢ ፒፐር ጋር አሁኑኑ መነጋገር እፈልጋለሁ ስትል ጥያቄዋን አቀረበች::

ፕሮግራሙን አቋርጠው ጣልቃ እንድትገባ አልፈለጉም፤ ነገር ግን ፕሮግራሙ ከተፈጸመ በኋላ አንድ ሰው የሴትዮዋ አድራሻ የተጻፈበትን ወረቀት ሰጠኝ:: እናም ደወልኩላት::

"ወንድሜን ልታነጋግረው ይገባል" አለች::

"የወንድምሽ ችግር ምንድን ነው?"

"በአንድ መጠጥ ቤት በተደረገ ረብሻ ውስጥ ተካፍሎ ነበር፤ አንድ ሰው ሽጉጡን መዞ እግሩን በመምታት እንዲቆረጥ አደረገው:: በአንተ እግር ላይ እንደነበረው ነገር አይነት በእግሩ ላይ ተደርጎለታል::"

"በእርግጥ አነጋግረዋለሁ" አልኳት፤ አሁን የት ነው ያለው?

"በቤት ውስጥ አልጋ ላይ ነው"::

"አድራሻውን ስጭኝና ሄጄ ..."

"እረ በጭራሽ፤ እንደሱማ አይሆንም:: በታላቅ ቁጣ ውስጥ ነው ያለው:: ደግሞም አደጋ ሊያደርስ የሚችል እመጸኛ ነው:: እርሱን ለማየት የሚመጣውን ማንኛውንም ሰው አያናግርም አለችና የስልክ አድራሻውን ሰጠችን:: "እባክህን ደውልለት፤ አሁን በጥሩ ሁኔታ ውስጥ አይደለም ያለው፤ መልካም ንግግር እንደማይጠብቅህ" አረጋግጥልሃለሁ አለች:: በመጨረሻው ማስጠንቀቂያ ነገረችኝ፤ "ስልኩን ሊዘጋብህ ይችላል፤ ይሁን እንጂ እባክህ ሞክረው::"

ገና ወደ ቤቴ እንደደረስኩ፤ ወደ ወንድሟ ደወልኩና ራሴን አስተዋወቅኩት:: ሦስት ተጨማሪ ዐረፍተ ነገሮች ከመናገሬ በፊት፤ ልክ እህቱ የገመተችውን ነገር አደረገ:: በቁጣ ጮኸብኝ:: ድምፁን ከፍ አድርጎ ስሞቻቸውን የማላውቃቸውን የርግማን ቃላት ሁሉ አወረደብኝ:: ርግማኑንም ብዙ ጊዜ ደጋገመው::

ስድቡን ትንሽ ጋብ ባደረገበት ቅጽበት ተረጋግቼ፤ "አንተ ያደረግከውን ነገር እኔም በእግሬ ላይ አድርጌ ነበር ያንን የእግር አጥንት ማስተካከያ መሣሪያ" አልኩት::

ስሚቀጥሉት ጥቂት ሰኮንዶች ምንም አልተናገረም፤ እናም "ያንን የኤልዛሮቭ ፍሬም በግራ እግሬ ላይ አድርጌው ነበር እያስፍክበት ያሰውን ስቃይ አውቀዋለሁ"::

"አ! ሰውየው ... ስቃዮ ሊገድለኝ እኮ ነው:: ያስ እንዳች ፋታ ነው የሚያሰቃየኝ::" የተናገርኩትን እንዳልሰማ ያህል እንደገና ቁጣው ገነፈለ፤ ልቅ በሆነ ቋንቋና ባልተገራ አነጋገር ብስጭቱን መግለጽ ጀመረ::

እንደገና ከንግግሩ ትንሽ ጋብ ሲል "ያደረግከው የህክምና መሣሪያ የተደረገላቸው ሰዎች የሚሰማቸውን ስቃይ እረዳዋለሁ" አልኩት::

"አሁን በአንተ እግር ላይ የለም፤ አይደል?"

"የለም፤ በመጨረሻው አወጡልኝ፤ ማድረግ የሚገባህን ነገር የምታደርግ ከሆነ፤ ከአንተም ላይ አንድ ቀን ይወልቅልሃል":: ያ ንግግር ያን ያህል ዋጋ ያለው አልነበረም፤ ነገር ግን መናገር እችላለሁ ብዬ ያሰብኩት ብቸኛው ነገር ነበር::



"ከተደረጉልኝ ብረቶች አንዳንዶቹን አሁኑኑ ባወጣቸውስ?"

"የምታወጣቸው ከሆነ፤ እግርህን እንደቆረጥከው የሚቆጠር ነው፤ ምክንያቱም እነዚያ ብረቶች ናቸው የእግርህን አጥንቶች አገጣጥመው የያዙልህ::"

"ያንን አውቃለሁ፤ ነገር ግን እየገደለኝ እኮ ነው መተኛት አልችልም ... እና"፤ እንደገና በቁጣ ገነፈለ፤ በምን ያህል ስቃይ ውስጥ እንደሆነና ሁሉንም ነገር ምን ያህል እንደጠላ ነገረኝ::

ከዚያ በኋላ አንድ ነገር በእኔ ውስጥ ሲሆን ተሰማኝ፤ አቋረጥኩትና፤ "እግርህ ምንድን ነው የሚመስለው? ብረቶቹ በገቡበት አካባቢ በጣም ቀልቷል? በቆዳህ ላይ ከላይና ከታች ተመሳሳይ ቀለሞች አሉ? ከሌሎቹ ይልቅ ሃይለኛ ህመም እንዲሰማህ የሚያደርጉ የተለዩ ቀዳዳዎች አሉ?" ስል ጠየኩት::

"አዎ፤ ትክክል ነህ፤ በተለይ አንደኛው - ሰውየው - ክፉኛ የጎዳኝ እርሱ ነው::"

እህትህ አሁን በአካባቢህ አለች?" እንዳለች በነገረኝ ጊዜ፤ "ከእርሷ ጋር አገናኘኝ" ስል አዘዝኩት::

አልተከራከረም ነበር፤ እርሷም ቴሌፎኑን ያዘችና፤ "አመሰግንሃለሁ ... በጣም ነው የማደንቅህ ..." አለች::

"አሁን እኔን አድምጭኝ" አልኳት ንግግሯን አቋርጬ፤ "አሁኑኑ አምቡላንስ እንድትጠሪ እፈልጋለሁ፤ በተቻለ ፍጥነት ወንድምሽን ወደ ሆስፒታል እንድትወስጂው ይሁን:: በፍጥነት መድረስ ካልቻለ እግሩን ሊያጣ ይችላል::"

"እንደዚያ ይሆናል ብለህ ታስባለህ?"

"የምነግርሽን ስሚ:: ምልክቶቹ ሁሉ እየታዩበት ነው:: ምናልባትም ትኩሳት ጭምር ሊኖረው ይችላል:: ትኩሳቱን አይተሻል?"

"አዎን፤ ትክክል ነው:: ትኩሳትም አለው::"

"አሁኑኑ ወደ ሆስፒታል ውሰጂው:: ከዚያ በኋላ ደውይልኝ::"

በሚቀጥለው ቀን ደወለችልኝ:: "ኦ ትክክል ነበርክ! ሰውነቱ ተመርዞ ነበር፤ የሚያስፈራ የአካል ቅርጽም ነበረው:: ጸረ ተህዋስያን የሆኑ መድሃኒቶችን ሁሉ ሰጡት በጊዜው ወደ ሆስፒታል እንደመጣም ነገሩኝ፤ እናም ዛሬ ትንሽ ሻል ብሎታል::"

"አሁንም ሰዎች ሊገቡበት ባልተፈቀደ ክፍል ውስጥ ተለይቶ እንደተኛ እገምታለሁ" አልኳት:: ትክክል እንደሆነ ስትነግረኝ፤ "መጥቼ አየዋለሁ" ስል ጨምሬ ነገርኳት::

አገልጋይ ስለሆንኩ ገብቼ ላየው እችል ነበር:: እናም ወደ ሆስፒታሉ ሄድኩ፤ ተጫዋወትን አብረንም ጸለይን:: በመጨረሻው ያ ወጣት ወደ ጌታ መጣ::

በዚያ የቴሌቭዥን ፕሮግራም ባልቀርብ ኖሮና እህቱም ያንን ፕሮግራም ባትከታተል፤ ሰውየው እግሩን ማጣቱ ብቻ አይደለም ሕይወቱንም የማጣት ዕድሉ ሰፊ ነበር:: እግዚአብሔር የተጠቀመብኝ የወጣቱን አካላዊ ሕይወት ለማትረፍ ብቻ ሳይሆን ለደህንነቱም እንደ መሣሪያ ሆኛለሁ:: ይህ ደግሞ እግዚአብሔር አሁንም በምድር ላይ እንድሠራው ያዘጋጀው ነገር እንዳለ ካየሁባቸው ድርጊቶች ውስጥ አንደኛው ነበር::



ችግሩን ፈጥቼ ነበር የተገነዘብኩት፤ ምክንያቱም በሆስፒታል ውስጥ በነበርኩበት ጊዜ በእኔ ላይ የደረሰ ችግር ነበር:: ሰውነቴ ተመርዞ ክፉኛ የተጎዳሁበት ጊዜ ነበር:: ያን ጊዜ እንደ ሌሎቹ የስቃዩ ክፍሎች እንደ አንዱ ቆጥሬ በዚያ ውስጥ ማለፍ እንደሚገባኝ አስቤ ነበር:: ከዚያ በኋላ ግን ነርሷ ብረቱ ካለፈባቸው በእግሬ ላይ ካሉ ቀዳዳዎች አንደኛው መመረዙን ደረሰችበት::

ከዚያ በኋላ፤ ከአንድ ቀን በፊት ከነርሶቹ አንዷ በጥንቃቄ ጉድለት ለመመረዜ ምክንያት እንደሆነች በግልጽ አስታወስኩ:: ርህራሄ የማይታይባት ዐይነትና እንደሌሎቹ ፍቅርን የማታሳየኝ ሴት ነበረች:: ወደ ክፍሌ ትገባና ሥራዋን ትሠራለች፤ ይሁን እንጂ እኔን በምታክምበት ጊዜ ምሬት እንደሚሰማት ዐይነት ትሆናለች::

ኪው ቲፕስ የተባለ ቀዳዳዎቹን የማጽጃ ዕቃ እንዲጠቀሙና ለእያንዳንዱ ቀዳዳ አዳዲስ ኪው ቲፕስ እንዲጠቀሙ ትእዛዝ ተሰጥቷቸው ነበር:: ነርሷ ታክመኝ በነበረ ጊዜ ለእያንዳንዱ ቀዳዳ አዳዲስ ኪው ቲፕስ እንዳልተጠቀመች አስታውሳለሁ:: እንዲህ ያደረገችበት ምክንያት ምናልባትም አዲስ ኪው ቲፕስ ለማምጣት ጊዜ የሚወስድባት በመሆኑ ይሆናል:: ቀዳዳው ከመመረዙ በፊት እንዲህ ዐይነት ችግር ይከሰታል ብዬ አላሰብኩም ነበር:: በእርሷ ስንፍና ምክንያት ለተጨማሪ ስቃይ ተዳረግኩ:: የሰውነቴን መመረዝና የትኩሳቴ መጠን መጨመሩን ካወቁ በኋላ፤ ማንም ወደማይደርስበት ወደተለየ ክፍል ፈጥነው ወሰዱኝ፤ በዚያም ለሁለት ሳምንታት ቆይቻለሁ:: እዚያ በነበርኩበት ጊዜ ማንም ሰው እንዲጎበኘኝ አይፈቀድም ነበር::

ኢቫ አቤቱታ አቀረበች፤ የሆነውንም ለዶክተሮቹ ነገረቻቸው። ከዚያ በኋላ ያችን ነርስ አላየኋትም፤ ከሥራ ያሰናብቷት ወይም ወደ ሌላ ክፍል ያዘዋውሯት አላውቅም።

ታሪኬን በአደባባይ መናገር ያስደስተኛል፤ በጥቂት አጋጣሚዎች ግን ከመጠን በላይ ሃሴት ለማድረግ ችያለሁ። ከእነዚህ አንዱ በሉሲያና ግዛት ዩኒቨርስቲ ያደረግኩት ንግግር ነበር። በዚያ ጉባኤ እኔና ባለቤቴ የተገኘን ሲሆን፤ ኮሌጁ ከሦስቱ ልጆቻችን ሁለቱ የሚማሩበትም ስፍራ ነበር።

በተደጋጋሚ ካገለገልኩባቸው በኮሌጅ ውስጥ ካሉ ድርጅቶች አንዱ የባፕቲስት ኮሌጅ አገልግሎት (ቢ.ሲ. ኤም) ነው። ኒኮል በሉሲያና ግዛት ዩኒቨርስቲ ተማሪ በነበረችበትና በአንድ ቡድን ውስጥም መሪ ሆና ታገለግል በነበረበት ጊዜ፤ የባፕቲስት ኮሌጅ አገልግሎት ንግግር እንዳደረግ ጋበዘኝ። ኒኮል ከጉባኤው ተሳታፊዎች አንዷ መሆኗን ማወቄ፤ ጊዜውን እጅግ የደስታ አደረገልኝ።

የባፕቲስት ኮሌጅ አገልግሎት ከሚያዘጋጃቸው በርካታ የኮሌጅ እንቅስቃሴዎች መካከል የማክሰኞ ምሽት የምስጋናና የአምልኮ አገልግሎት ይገኝበታል። ኮሚቴው የጋበዘኝ ለስደረሰብኝ አደጋ ንግግር እንዳደርግ ነው።

ተማሪዎቹ በግቢያቸው ውስጥ፤ "የሞተው ሰው ሲናገር" በሚል ርዕስ ስለማደርገው ንግግር ማስታወቂያ አሰራጩ። የተገኙት ሰዎች ቁጥር ብዛት ስለነበረው ስብሰባው በሁለት ጊዜያት ተከፍሎ እንዲደረግ ነበር የታቀደው። እየተናገርኩ አድማጮቹ በሞተውና ወደ ሕይወት



በተመለሰው ሰው ታሪክ በፍጹም የተማረኩ ይመስል ነበር። ስለመንግሥተ ሰማይ ተናገርኩ፤ ስለተመለሰ ጸሎትና ስለተአምራቶቹም ጨመርኩ። "በክርስቶስ ያለን ባልንጀርነት እንዴት ያለ ነው" የሚለውን ዝማሬ ከዲክ ዋንሪከር ጋር በመኪናው ውስጥ እንደዘመርነው ተናገርኩ።

እያንዳንዱ አገልግሎት በተፈጸመ ጊዜ የምስጋናው ዝማሬ ቡድን ከታሪኬ ጋር የተያያዘ ዝማሬ በማቅረብ ይመሩን ነበር። እንደዚያ እንደሚያደርጉ አላወቅኩም' ነበር። እንዲያደርጉ የተመሩት በመንፈስ እንደሆነ ግን ምንም ጥርጥር የለኝም። "በክርስቶስ ያለን ባልንጀርነት እንዴት ያለ ነው" የሚለው ዝማሬ ለእኔ ለመስማትም ይሁን ለመዘመር አስቸጋሪ የሆነ ዝማሬ ነበር።

በመጨረሻው ቁጥራቸው በርካታ የሆነ ተማሪዎች ጥያቄዎችን ለመጠየቅ ተሰልፈው ነበር። ከእነርሱም መካከል ዋልተር ፎስተር የተባለ አፍሪካ - አሜሪካዊ ተማሪ ይገኝበታል። እርሱ ራሱ በርካታ ጥያቄዎችን ከጠየቀ በኋላ በዚያ ቆይቶ ሌሎች ተማሪዎች የሚጠይቋቸውን ጥያቄዎችም ያደምጥ ነበር። መድረኩን ለቅቄ ስወርድ ዋልተር ከኋላዬ ተከተለኝ። እኔ እጅግም ትኩረት ባልሰጠውም እርሱ ፍጹም ቁርጠኛ በሆነ ውሳኔ ይከተለኝ እንደነበር ተሰማኝ። ነገሩ ሁሉ ስለመንግስተ ሰማይ ዝርዝር ጉዳዮች በበቂ ሁኔታ መረጃ ያላገኘ ወይም ስላልፍኩበት ሁኔታ በበቂ ስምቶ ያልጠገበ ይመስላል።

ከጥቂት ወራቶች በኋላ፤ ኒኮል ደወለችልኝ። "ዋልተር ፎስተርን ታስታውሰዋለህ?" ስትል ጠየቀችኝ። በድምጿ ውስጥ ሃዘን ነበር፤

ቀጥላም ማልቀስ ጀመረች:: ልክ ማስታወሴን ስነግራት፤ "ሞተኮ ... ሞተ፤ በልብ ድካም ህመም ሞተ! በቃ በዚያ ምክንያት ... ሄደ"

ዋልተር ከባድ በሆነ የልብ ድካም ህመምተኝነቱ በግልጽ የሚታወቅና በህክምና ክትትል ሥር የነበረ ተማሪ ነው:: በዚህ ምክንያት ሁሉም ሰው ጤንነቱ በደህና ሁኔታ እንደሚገኝ ይገምት ነበር:: የእርሱ ሞት የሚያውቁትን ተማሪዎች ሁሉ እጅግ ማስደንገጡ በግልጽ ታየ::

"የሃያ ዓመት ዕድሜ ያለው ተማሪ ይሞታል ተብሎ አይገመትም" ሲል ከጓደኞቹ መካከል አንደኛው ተናገረ::

ስልኩን ከዘጋሁ በኋላ እኔና ዋልተር ስለተገናኘንበት ቀን ወደ ኋላ ሄጄ ማሰብ ጀመርኩ:: ስለ ሞቱ ቀደም ያለ ስጋት ይኖረው ይሆን ስል እገረም ጀመር:: በሉሲያና ግዛት ዩኒቨርስቲ ውስጥ ባገለገልኩበት ጊዜ፤ ያን ያህል ጊዜ ይከተለኝ የነበረውና ስለ መንግስተ ሰማይ ቁጥር ስፍር የሌላቸውን ጥያቄዎች የጠየቀበት ምክንያት ያስገርመኝ ጀመር::

ጥያቄዎቹ በቀላሉ ከተገረመ ሰው ከሚወጡት ጥያቄዎች በላይ ትኩረት የነበራቸው ነበሩ:: ምናልባት በዚያን ጊዜ እግዚአብሔር ወደ ዘላለም ቤቱ ለሚያደርገው ጉዞ እያዘጋጀው ነበር ስል አሰብኩ:: ድንገተኛ የሆነው ሞቱ ጓደኞቹን ይልቁን ደግሞ በባፕቲስት ኮሌጅ አገልግሎት ውስጥ ይሳተፉ የነበሩትን ተማሪዎች ክፉኛ ስሜታቸውን ጎዳ:: አብሮ አደጋቸው በመሆኑ ምክንያት ተወዳጅ በነበረው ጓደኛቸው ሞት መሪር ሀዘን አዘኑ:: በሞቱ ማግስት ዋልተር በጣም ይወደው በነበረው በባፕቲስት ኮሌጅ አገልግሎት ህንጻ ውስጥ ተሰበሰቡ::



በዚያ ምሽት በነበረው ስሜት በፈነቀሰው ስብሰባ፤ በርካታ ጓደኞቹ እየተነሱ ስለ መንግስተ ሰማይ ስላደረግኩት ንግግር ዋልተር እጅግ ከብደት ሰጥቶት የነበረ ንግግር እንደሆነ በሰፊው ተናገሩ:: ብዙዎችም ዋልተር በሰማው ነገር እጅግ መደሰቱን ገልጾላቸው እንደነበረ አስታውሰው ተናገሩ:: ከስብሰባው በኋላ በነበሩት ቀናት ስለዚያ ስብሰባ ደጋግሞ ይናገር ነበር::

"መጋቢ ፒፐር እዚህ ከመጡ በኋላ በቀን ውስጥ እጅግ ብዙ ጊዜ" አለ ከተማሪዎቹ መካከል አንዱ፤ "ዋልተር አንድ ቀን እኔ ራሴ ወደ መንግስተ ሰማይ እሄዳለሁ!" ሲል ነግሮኛል አለ::

በርካታ የቤተክርስቲያን ጉዳዮች ወጥረው ይዘውኝ ስለነበር፤ በባቶን ሮጅ በሚገኘው የመጀመሪያው የመጥምቃውያን ቤተክርስቲያን ለዋልተር ሞት በተዘጋጀው የመታሰቢያ አገልግሎት ላይ ለመገኘት አልቻልኩም:: ኒኮል ቤተሰባችንን ወክላ የተገኘች ከመሆኑም በላይ በዚያ ምሽት ስለዋልተር ሕይወት በተደረገው የመታሰቢያ ስብሰባ ላይ የተከናወኑትን ነገሮች ሪፖርት አድርጋልናለች:: ከጓደኞቹ ቀርበው ከነበሩት ሁለት የተለዩ ጥያቄዎች አንደኛው ለባኪው የወንጌል መልዕክት እንዲያቀርብና አንድ ሰው አንድ የተለየ ዝማሬ እንዲዘምር ነበር:: እርግጥ ነው ዝማሬው፤ "በክርስቶስ ያለን ባልንጀርነት እንዴት ያለ ነው" የሚለው ዝማሬ ነበር:: በዚያ የነበሩ የስብሰባው ተካፋዮች ያ ዝማሬ በዋልተር ዘንድ ከፍተኛ ስፍራ የነበረው ዝማሬ እንደነበር ተነገራቸው::

በሉሲኒያ ግዛት ዩኒቨርስቲ ሙዚቃ የምታጠናውና የተዋጣላት ሶሎ ዘማሪ የሆነችው ኒኮል መዝሙሩን ለሃዘኑ ለተሰበሰቡ ሰዎች ዘመረችላቸው:: ዝማሬውን የተቀበሉት በታላቅ ሃዘንና በታላቅ ተስፋ

ነበር:: እንባዎች ይዘንቡ ነበር፤ የብዙዎችም ፊት ሰላም የተሞላ ፈገግታ አጥልቶበታል::

ስብሰባው ካበቃ በኋላ፤ ስለመንግስተ ሰማይ የነበረው የማይናወጥ እምነት ምን ያህል እንዳጽናናቸውና እንዳበረታታቸው ለመወያየት ወደ ኋላ ቀርተው ነበር::

ከእኔ ምስክርነትና ይህንንም ተከትሎ ከመጣው የዋልተር ሞት የወጣው ሌላው አስደሳች ነገር፤ በሉሲያና ግዛት ዩኒቨርስቲ ውስጥ በሚገኘው የባፕቲስት ኮሌጅ አገልግሎት ክልል ጸሎት የሚደረግበት የመናፈሻ ሥፍራ እንዲገነባ መደረጉ ነው:: እኔ ይህ ትክክለኛ ነገር ይመስለኛል፤ ምክንያቱም ታሪኬን ባካፈልኩባቸው ጊዜያቶች ሁሉ የጸሎትን ወሳኝ የሆነ አስፈላጊነት አበክሬ ገልጫለሁ:: ከሁሉም በላይ እኔም እኮ አሁን በሕይወት ያለሁት በተመለሰ ጸሎት አማካይነት ነው::

ከደረሰብኝ አደጋና ከመንግስተ ሰማይም ከተመለስኩ በኋላ መለኮታዊ በሆነ ጣልቃ ገብነት ሕይወታቸው ከእኔ ጋር እንደ ተያያዘ እጅግ ብዙ ሰዎች ሁሉ፤ እግዚአብሔር ለሁለተኛ ግዜ ወደ ቤቱ እስኪጠራኝ ድረስ ዋልተር እኔን የሚጠብቁትን ሁሉ የሚወክል ነው::

ሱ ፋይሌ የተባለች የመጀመሪያ ባሏ የሞተው በካንሰር በሽታ ነበር:: ለረዥም ጊዜያት ካለፈበት ከዚህ አስከፊ በሽታው የተነሳ እርሷ በብዙ ተጎድታ ነበር:: ቀሪ ሕይወቷንም መበለት ሆና እንደምትጨርሰው ገምታ ነበር:: ይሁን እንጂ ጎረቤቷና ያለ ትዳር የነበረው ቻርልስ ይህን ግምቷን ቀየረው:: ጎረቤታሞች ብቻ አልነበሩም፤ ይልቁንም ሁለቱም የትዳር ጓደኞቻቸውን ያጡ በመሆናቸው ምክንያት ጥሩ ጓደኞችም እየሆኑ መጡ::

ጊዜው እያለፈ ሲሄድ፤ አንድ ጊዜ ሰዎችን ወደው የሚወዷቸውን እነዚያን ሰዎች ያጡ ብቻ ሊገነዘቡት በሚችሉበት ሁኔታ አንዳቸው የአንዳቸውን ፍላጎት ማሟላት መቻላቸውን ተገነዘቡ:: ጓደኝነታቸው ወደ ፍቅር በማምራቱ በአደገኛ ሁኔታ የጋብቻን ጉዳይ ማሰብ ጀመሩ::

ሱ ቻርልስን የማግባቱን ነገር ገደብ አበጅታለታለች፤ ምክንያቱም ቻርልስ አስቸጋሪና የማይመቹ የሠራተኛ መደብ አባላት ብላ ከምትጠራቸው ጎረቤቶቿ አንዱ ነው:: ሃይለኛ ጠጭ እንደነበር የሚነገር ታሪክ አለው፤ እናም እርሷ፤ "ከዚህ አይነት አመል ጋር አብሮ መኖር አልችልም" ትላላች::

ይሁን እንጂ ፍቅራቸው እየጨመረ ሲሄድ፤ ሱ ጋብቻውን ለመቀበል አንድ ቀላል ቅድመ ሁኔታ ብቻ አቀረበች፤ "ጠጪ የሆነ ሰው አላገባም::"

ቻርልስ ስካራምነቱን ብቻ አይደለም፤ መጠጡንም ቁርጥ አድርጎ ተወ:: አሁን ስለጋብቻ ለመነጋገር ዝግጅዎች ሆኑ::

አንድ ቀን ስለትዳር ጓደኞቻቸው ሞት መነጋገር ጀመሩ ሁለቱም የሞቱት በካንሰር በሽታ ነበር:: "እኔ ካንሰር እንዳለብኝ በህክምና ቢረጋገጥ" አለ፤ "ራሴን አጠፋለሁ::" ቻርልስ አንድ ነገር ያውቃል፤ በበሽታው የሚሰቃየው ታማሚው ብቻ ሳይሆን፤ ፍቅረኞቻቸውም ጥልቅ በሆነ ችግር ውስጥ ማለፋቸው ግድ ነው:: "እኔ ማንንም ቢሆን በዚያ አይነት ችግር ውስጥ አብሮኝ እንዲሰቃይ አልፈልግም::"

ተጋቡ፤ ጥሩ ትዳር ሆነላቸው፤ ቻርልስም ዳግመኛ መጠጥ አልጠጣም። ስ ቀድሞውንም በቤተክርስቲያናችን ትጉህ ተሳታፊ ነች። ከጋብቻቸው በኋላ ግን ቻርልስም ንቁ ተሳታፊ ሆነ።

ይሁን እንጂ አንድ ቀን ካደረጋቸው የህክምና ምርመራዎች በአንዱ ከሁሉም በላይ የሚፈራው ነገር ተከሰተ፤ ቻርልስ ካንሰር አለበት። አሁን ወደ ውስጥ ጠልቆ ከገባ ፍርሃት ጋር መፋጠጥ ግድ ሆነበት። ስ ካለፈው ባለቤቷ ጋር ያሳለፈችውን ስቃይ እንደገና ደግማ ልታልፍበት ነው በሚል ፍርሃት ተዋጠ።

የህክምና ምርመራውን ካደረገ በኋላ ሌላም ፍርሃት ከፊቱ ተጋርጦ ነበር፤ ይህ ክፉ ዜና ሞራሉንም ተገዳድሮታል፤ በመሆኑም ሞቴ እጅግ አስፈርቶኛል ሲል ተናገረ። ምንም እንኳን ቻርልስ የቤተክርስቲያን አባል የሆነና እንደሚያምን የሚናገር ቢሆንም፤ ደህንነታቸውን ከሚጠራጠሩ ሰዎች አንዱ ነው። ቻርልስ ከዚህ በሽታ ነፃ ወጥቶ እስኪታየው ድረስ ስ የታቻላትን ሁሉ እንደምታደርግ አረጋገጠችለት። ያሳሰባት ሌላው ነገር ግን ስለድነቱ እርግጠኝነት የማጣቱ ጉዳይ ነው። በተለያዩ ጊዜያቶች ስለመንግስተ ሰማይ የሰጠኋቸውን ምስክርነቶች አዳምጣለች፤ እንዲያውም የእኔን ታሪክ ስሌሎች ሰዎችም ደግማ ተናግራዋለች።

"ቻርልስን ልታነጋግረው ትችላለህ?" ስትል ጠየቀችኝ "አንድ ቀን ምስክርነትህን ከራስህ መስማት ይፈልጋል።"

በዚያ ጊዜ አሁን ባለሁበት ስፍራ ማለትም በፓሳድና የምትገኘው የመጀመሪያዋ የመጥምቃውያን ቤተክርስቲያን የአዋቂዎች ብቸኛው



መጋቢ ሆኜ ነበር። እኔና ስ በተለያዩ አጋጣሚዎች በተወሰኑ ፕሮጀክቶች ላይ አብረን ሠርተናል።

"እባክህ ድነትን በሚመለከት አነጋግረው፤ ይሁን እንጂ ጨምረህ ከምድራዊው ሕይወት ፍጻሜ በኋላ ሕይወት ምን እንደሚመስል አስረዳው" አለችኝ።

እንደ እውነቱ ከሆነ ቻርልስን አውቀዋለሁ፤ ካለፈ ሕይወቱ አስከፊነት የተነሣ ለእግዚአብሔር ጥሩ ሰው እንዳልሆነለት ያስብ እንደነበር እጠረጥራለሁ።

እኔና ቻርልስ ወዲያውኑ ቀጠሮ ያዝን። በጣም ጥሩ ሰውና ፈጥኖ ለመግባባትም ቀላል የሆነ ነው። መደበኛ በሆኑ ቀላል ጉዳዮች ከእርሱ ጋር መነጋገር እንደምፈልግ አመካኘቼ ነበር ቀጠሮ የምይዘው። ወደ ቤታቸው በምሄድበት ጊዜ ሁሉ ስ ይቅርታ ጠይቃ ከክፍሉ ትወጣና ለመሄድ እስከምዘጋጅ ድረስ በዚያው ትቆያለች።

ምንም እንኳን የቻርልስ ጤንነት እያሽቆለቆለ ቢሄድም፤ እንዳችም አይነት የንዴት ወይም የድብርት ምልክት አላሳየም። በጣም ግላዊ የሆኑ ነገሮችን ለምሳሌም በአልጋ ላይ ሆኖ በመቀበያው እቃ ላይ ለመጸዳዳት፣ ሽንትን ለመሽናትና ለመታጠብም ቢሆን በሌሎች ላይ ለመተማመን በጣም አስቸጋሪ መሆኑንም እንኳን ተነጋግረናል።

በአራተኛው ጉብኝቴ ወቅት፤ ቻርልስ በመጨረሻው በግልጽ መናገር ጀመረ፤ "እኔ ፈርቻለሁ። ወደ መንግስተ ሰማይ መሄድ እፈልጋለሁ፤ ነገር ግን ማረጋገጫ እሻለሁ በሞትኩ ጊዜ በቀጥታ ወደ መንግስተ ሰማይ እንደምሄድ ማረጋገጫ እፈልጋለሁ ..." አለ።

እርሱ ስለሕይወቱ እንደሚናገረው ከሆነ፤ ከእግዚአብሔር ጋር አሁን ያለው ግንኙነት በግልጽ እውነተኝነት ላይ የተመሠረተ ነው። ብዙ ጊዜ እንደሚያጋጥመው ሉን ከማግባቱ አስቀድሞ ለብዙ ዓመታት፤ የክርስቶስ ታማኝ የሆነ ተከታይ አልነበረም። እየደጋገምኩ መንግስተ ሰማይ የሁሉም አማኞች የመጨረሻ ቤት መሆኗን የሚገልፁትን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች እንዲያስታውስ አደረግኩ።

"አውቃለሁ፤ አውቃለሁ" አለ። "ድነትን ከማግኘቴ በፊት ወደ መንግስተ ሰማይ እንደማልሄድ አውቅ ነበር። ወደ ሲኦል እየሄድኩ ነበር። አሁን ስለ መንግስተ ሰማይ እርግጠኛ መሆን እፈልጋለሁ።"

ስለ መንግስተ ሰማይ የሰጠሁት ስዕላዊ መግለጫ አጽናናው። "አዎ ... አዎ፤ የምፈልገው ይህንን ነው" አለ።

በሌላው ጉብኝቴ ጊዜ፤ በጭውውታችን መካከል፤ "አሁን ተዘጋጅቻለሁ። አሁን ሰላም ይሰማኛል። በመጨረሻው ወደ መንግስተ ሰማይ እንደምሄድ አወቅኩ" አለ በፈገግታ።

ለመጨረሻ ጊዜ ባደረኳቸው ሁለት ጉብኝቶች፤ ቻርልስ እንዲህ አለ፤ "እንደገና ንገረኝ፤ መንግስተ ሰማይ ምን እንደምትመስል አንድ ጊዜ ደግመህ ንገረኝ።"

ምንም እንኳን የምነግረውን ነገር ሁሉ ሰምቶ የጨረሰው ቢሆንም እንደገና ደግሜ ነገርኩት። ስለ መንግስተ ሰማይ በነገርኩት ቁጥር እርግጠኝነቱ በየጊዜው እየጨመረ የሚሄድ ይመስል ነበር።



ከመሞቱ ጥቂት ቀደም ብሎ፤ ሉ ወደ ሃውስተን የክህምና ማዕከል ሆስፒታል ወስዳው ነበር፤ ያ ስፍራ እኔ ለረዥም ጊዜ ከተኛሁበት ክፍል ጥቂት በሮች ብቻ ነበር የሚርቀው።

በምድር ላይ በኖረባት የመጨረሻዋ ቀን፤ ቻርልስ ለሉ እንዲህ ሲል ተናገረ፤ "ሁሉም ነገር ጥሩ ይሆናል፤ አንድ ቀን እንደገና አብረን እንሆናለን።"

ሉ ስልክ ደውላ ስትነግረኝ፤ "ሲሞት ፈጽሞ ፍርሃት አይታይበትም ነበር" ስትል ሁኔታውን ገልጻልኛለች።

የቻርልስ የተረጋጋ እርግጠኝነትና ነገሮችን አምኖ መቀበል፤ ከሃዘኗና እርሱን በማጣቷ ከደረሰባት ጉዳት ፈጥና እንድትወጣ ለሉን ሰጣት። እርሷ እንደነገረችኝ፤ ከመሞቱ አንድ ሳምንት ብቻ ቀደም ብሎ፣ የእኔን ታሪክ ማድመጡና በሕይወቱ ያየው አምንታዊ የሆነ ብሩህ ገጽታ ልዮነቱን እንደፈጠረ ነግሯታል። አሁን ሁሉም ነገር ተረጋግቷል አለ። ወደ ተሻለ ስፍራ እንደምሄድ አውቃለሁ።"

ሉ ስለቻርልስ የነበራትን ትውስታ ስታጫውተኝ፤ እየሳቀች እንዲህ አለች፤ "እኔ በጣም እድለኛ ሴት አይደለሁምን? በላይ እኮ ሁለት ሰዎች ይጠባበቁኛል። አንድ ቀን የእኔ ጊዜ ሲመጣ፤ እያንዳንዳቸው አንዳንድ እጆቼን ይይዛሉ፤ የቀድሞው ባለቤቴም በጌታ ወንድም ነበር። እናም በወርቁ ጎዳና ላይ ቁልቁለቱን እያዘገሙ ይሸኙኛል።"

ከልጆቻችን አንዱ የሆነው ጆይ ዕድሜው ወደ ወጣትነት በደረሰ ጊዜ፤ አንድ የሠራች መኪና ልንገዛለት ፈለግን። እርሱ የፈለገው የዕቃ

መጫኛ ያላት መኪና በመሆኑ፤ የፈለጋትን አይነት እስክናገኝ ድረስ አፈላለግን፤ በመጨረሻውም የ1993 ፎርድ ሬንጀር አገኘንለት።

የመኪና ነጋዴው ስም ጋሪ ኢሞንስ ይባላል፤ በእኛ አካባቢ በዚህ ሥራው ለረዥም ጊዜ የታወቀ ነው። ጆይ የፈለጋትን መኪና ለመግዛት ከወሰንን በኋላ፤ ዋጋውን ለመነጋገር ወደ ውስጥ ገባን። ሚስተር ኢሞንስ ጥሩ ዋጋ ሰጡን፤ በመሆኑም ጆይ መኪናዋን ገዛት።

በዚህ አጋጣሚ ምክንያት በሚስተር ኢሞንስና በእኔ ቤተሰብ መካከል ጥሩ ግንኙነት ተመሠረተ። ከዚያ በኋላ ከእርሳቸው ላይ ተጨማሪ ሦስት ወይም አራት መኪናዎች ገዝተናል።

ጋሪ በእኔ ላይ ስለደረሰው ነገር በጥቂቱ ያውቃሉ፤ ይሁን እንጂ ዝርዝር ነገሮችን አያውቁም። እኚህ ሰው ከመኪና ነጋዴነታቸው በተጨማሪ የመኪና ተወዳዳሪም ናቸው። በእኔ ታሪክ በጣም የተማረኩም ይመስላሉ። ሙሉውን ታሪክ ለመስማት እንደሚፈልጉ ነግረውኛል፤ ይሁን እንጂ እርሳቸው በሥራ ብዛት ይጠመዳሉ ወይም እኔ በአጣዳፊ ሥራ እሯሯጣለሁ።

አንድ ቀን ጆይ ገንዘብ ለመክፈል ወደ መኪና መሸጫው ድርጅት ይሄዳል። ጋሪ እጃቸውን እየወዘወዙ ሰላምታ ከሰጡት በኋላ፤ "ይህን ብነግርህ ጭራሽ አታምንም" አሉ በፈገግታ። "ትላንትና አስደናቂ ነገር ተከሰተ።"

"ምን"

"ገና ገዝተን ያስገባናትን መኪና እየፈተሽኩ ነበር። ሁልጊዜም የማደርገውን ነገር ለማድረግ ወደ መኪናዋ ውስጥ ገባሁ። ሁሉም ነገሮች በአግባቡ መሥራታቸውን ለማረጋገጥ የተለያዩ ቁልፎችን



መነካካቴን ቀጠልኩ የመኪናው ሞተር ችግር ያለው መሆኑን ለማየት የሞተሩን ድምጽ አዳመጥኩ፤ የአየር ማቀዝቀዣውን ተመለከትኩ፤ በመጨረሻም ሬዲዮው መሥራቱን ሞከርኩ። ድንገት በቴፕ ሪኮርደሩ ውስጥ ካሴት መኖሩን አየሁ። የማፈናጠሪያ ቁልፍን ተጭኜ ካሴቱን አወጣሁት።"

ንግግራቸውን ቆም አድርገው ፈገግ ሉ፤ "በቴፑ ውስጥ ይናገር የነበረው ሰው ማን እንደሆነ እስኪ ገምት"

"ይህን መገመት አልችልም" አለ ጆይ።

"የአባትህ ታሪክ ነበር። መኪናዋን የገዛናት በይፋ ጨረታ ነበር፤ በመሆኑም የቴፕ ክሩን መልሰን ለመስጠት ባለቤት አልነበረውም። ቴፑን ወስጄ አዳመጥኩት ታሪኩን አዳምጥ በነበረበት ጊዜ ሁሉ እሰላስል የነበረው አንድ ቃል ነበር የሚደንቅ ነው! የሚል"

ዘወር ብዬ ሁኔታውን ሳስበው፤ የሚደንቅ ነው። ጋሪ ታሪኬን ለመስማት ይፈልጉ ነበር፤ ይሁን እንጂ ተገናኝተን መነጋገር አልቻልንም።

"በሽህ ከሚቆጠሩ ለጨረታ ከቀረቡ መኪናዎች ውስጥ ይህችን መኪና መግዛቴ እንግዳ ነገር አይደለምን?" ሲሉ ጋሪ ጆይን ጠየቁት፤ ከዚያ በኋላ በመኪናው ውስጥ እንደተቀመጥኩ፤ የማጫወቻውን ቁልፍ ተጭኜ አባትህ የሚናገረውን ሁሉ ሰማሁ።

ከዚያ በኋላ ባሉት ቀናት፤ ጋሪ ላገኟቸው ሰዎች ሁሉ በእኔ ላይ ስለደረሰው አደጋ ሳይናገሩ እንዳልቀሩ እስባለሁ።

እርግጥ ነው በዚያ ምስክርነት ተደስቻለሁ:: ከዚህም ሌላ እግዚአብሔር የእኔን ታሪክ ስለተጠቀመባቸው መንገዶች ሌሎች ታሪኮችን ሰምቻለሁ::

በቤተክርስቲያኔ ውስጥ በምሰብክበት ጊዜ በመንግስተ ሰማይ ስለነበረኝ ቆይታም በመተረክ በቴፕ ቀድቼ እንዲባዛ አድርጌው ነበር:: በሺህ የሚቆጠሩ ቅጅዎችን ሳላሰራጭ አልቀረሁም:: በተጨማሪም ሰዎች እነዚያን የቴፕ ክሮች እያባዙ ለቤተሰቦቻቸው እንደሚሰጡ አውቃለሁ:: በአንድ ወር ጊዜ ውስጥም እስከ ሃያ ቅጅዎች ያዘዙ ሰዎችንም አውቃለሁ::

ያ የምስክርነቴን ታሪክ የያዘ ቴፕ እስከ አሁንም ድረስ እየተባዛ በመከፋፈል ላይ ይገኛል:: እጅግ ብዙ ሰዎች ታሪኬን ካደመጡ በኋላ ክሩን በማባዛት አካል ጉዳት ለደረሰባቸውና በስቃይ ላይ ላሉ ሰዎች እንዲሁም በሚወዷቸው ሰዎች ምክንያት በብርቱ ሃዘን ላይ ላሉ ሰዎች ይሰጧቸዋል::

እግዚአብሔር ጋሪ ኢሞንስ ያንን ቴፕ እንዲያደምጥ የፈለገበት ምክንያት አለው ብዬ ድምዳሜ ላይ ደርሻለሁ በርግጥ ምክንያት እንዳለው እርግጠኛ ነኝ::

---

አንድ ቀን ፓሳድና የመጀመሪያው የመጥምቃውያን ቤተክርስቲያን የመተላለፊያ ኮሪደር ላይ በመጓዝ ላይ ሳለሁ፤ አንዲት ሴት አስቆመችኝ:: እንደ እውነቱ ከሆነ ያ ደግሞ የተለመደ አልነበረም:: ባለቤቴ እያንዳንዱ ሰው ወንድ ይሁን ሴት እኔን የሚጠይቀው ወይም ለእኔ የሚነግረው አንዳች ነገር የማያጣ በመሆኑ "ስድስት ሜትር ለመጓዝ ሰላሳ ደቂቃ ይፈጅብሃል" እያለች ትቀልዳለች:: እኛ ያሉን አስር ሺህ ያህል አባላት ናቸው፤ እያንዳንዱን ሰው ለማነጋገር ብዛቱ አስቸጋሪ ነው::

"ኦ! መጋቢ ፒፐር፤ ወደዚህ የመጣሁት አንተን ለማግኘት ነው:: አንድ ነገር ልነግርህ እፈልጋለሁ:: አንተ መስማት ያለብህ ነገር እንደሆነ አስባለሁ::"

አብዛኛውን ጊዜ አንድ ሰው እንዲህ ብሎ ነገሩን ከጀመረ፤ "ለራስህ ጥቅም ነው" የሚል ቃል አብሮ ይጨምርበታል:: ብዙ ጊዜ እንዳስተዋልኩት ያ ነገር እኔ ልሰማው የሚያስፈልገኝ ነገር አይሆንም:: ብዙ ሰዎች ከእኔ ጋር ስለነበሩ ምን ብዬ እንደምመልስ አላወቅኩም ነበር:: ይሁን እንጂ ትኩር ብዬ ስመለከታት በፊቷ ላይ የሆነ አጣዳፊ ነገርና ውጥረት እንዳለ ስሜቷን ማንበብ ቻልኩ:: ወደ ሌሎቹ ሰዎች ዞወር አልኩና፤ አንድ ጊዜ ትፈቅዱልኛላችሁ? ስል ጠየቅኳቸው::

በርግጥም ፈቃደኞች ነበሩ::

"እኔ ፈቃድ ያለኝ ነርስ ነኝ፤ ምን እንደተፈጠረ ብነግርህ ልታምን አትችልም"

"በእኔ ሕይወት ብዙ የማይታመኑ ነገሮች ደርሰዋል:: ንገሪኝና ማመን አለማመኔን ሞክሪ:: "

"ይህ የሆነው በሆስፒታል ውስጥ ነው:: በጠና ታማ ሆስፒታል የገባች አንዲት ሴት የአንተን ቴፕ ለማዳመጥ ችላ ነበር፤ እናም ሕይወቷን ለወጠው::"

"እንዲህ ያሉ ነገሮችን አስቀድሜ ስምቻለሁ፤ አዳዲስ ታሪኮችን ለመስማት ግን ፈቃደኛ በመሆኔ፤ ሰፋ አድርገሽ ንገሪኝ አልኳት::"

"ሴትዮዋ አማኝ አልነበረችም፤ ይሁን እንጂ አንድ ሰው አምጥቶ የአንተን ቴፕ ክር እንድታዳምጠው ሰጣት:: ጓደኞቿ ስለ እግዚአብሔር ሊያነጋግሯት ሞክረው ነበር:: መጽሐፍ ቅዱስ፤ ብዙ ዓይነት መጻሕፍትና ትራክቶችን ጭምር ሰጥተዋታል፤ ነገር ግን አንዳቸውም አልበገሯትም:: ስለ እግዚአብሔር ጉዳይ፤ ስለሃይማኖትም ይሁን ስለ ድነት ነገር መነጋገር አልፈልግም ትላለች:: እስከ ሞት ድረስ ቀርባ የታመመች ቢሆንም፤ የዘላለም ሕይወትን በሚመለከት ለየትኛውም ዐይነት መልዕክት ውስጧ ክፍት አልነበረም::"

ከመቀጠሏ በፊት በዓይኖቿ ላይ የሚወርደውን እንባ ለማበስ ንግግሯን አቋረጠች:: "አንድ ሰው የቴፕ ክሩን አመጣላት፤ ያንን ስለ መንግስተ ሰማይ የሚናገረውን የቴፕ ክር ማለቴ ነው ማድመጥ ትፈልግ እንደሆነም ጠየቃት:: ያ ጓደኛዋ ምንም አይነት ተጽእኖ አላደረገባትም፤ በቃ ቀለል አድርጎ ምናልባት ጠቃሚ የሆነ ነገር በዚህ ውስጥ ታገኚ ይሆናል:: ታሪኩ የሚያወስው ሞቶ ስለነበረ፣ ወደ መንግስተ ሰማይ ስለሄደና እንደገና ወደ ሕይወት ስለተመለሰ ሰው ነው" አላት::

ሴትየዋ በነገሩ ላይ አስባበት ልታደምጠው እንደምትችል መግለጿን ነርሷ ነገረችኝ:: ጓደኛዋም ተሰናብቷት ሄደ:: የቴፕ ክሩ ሳይደመጥ ከአልጋዋ አጠገብ በነበረ መለስተኛ ጠረጴዛ ላይ ተቀምጦ ቆየ:: ወዲያውኑ የጤንነቷ ጉዳይ ከፉኛ እያሽቆለቆለ ይሄድ ጀመር::



ዶክተሮቿ የሴትየዋን ልጅ ጠርተው እናቷ ከዚያ በኋላ በሕይወት ብትኖር ለአንድ ግፋ ቢልም ለሁለት ሳምንት እንደሆነ ነገሯት::

አማኝ የሆነችው ልጇ የእኔን ክር እናቷ እንድታዳምጠው አጥብቃ ትፈልግ ነበር:: የቴፕ ክሩ የያዘው ሁለት መልዕክቶችን ነው:: የመጀመሪያው ክፍል እኔ በሕይወት እኖር ዘንድ ስለአስቻለኝ ተአምርና ስለተመለሰው ጸሎት የሚያወሳ ሲሆን ይህንኑ ታሪክ በዚሁ መጽሐፍ የመጀመሪያዎቹ ምዕራፎች ላይ ጠቅሼዋለሁ:: ሁለተኛው ክፍል ደግሞ መንግስተ ሰማይ ምን እንደምትመስል ይተርካል:: እኔ፤ "የልብ ህመም ፈውስ" ስል ርዕስ ለጥቼዋለሁ:: ልጅቱ እናቷ እንድትሰማው የፈለገችውም ክፍል ይሄኛው ነበር::

ሴትዬዋ ግን መስማት ባለመፈለጓ ተቃወመች:: በዚህ የቴፕ ክር ውስጥ ያለውን ነገር ሁሉ መስማት አልፈልግም ስትል ተቃውሞዋን ገለጸች::

ቀናቶች እያለፉ ሄዱ፤ የአሮጊቷም ሁኔታ ወደ አስከፊ ሁኔታ ተሸጋገረ:: ከእኔ ጋር የምትነጋገረውና ክርስቲያን የሆነችው ነርስ፤ በዚያ እየሆነ ያለውን ነገር ተገነዘበች:: ከልጅቱ ጋር ከተነጋገረች በኋላ፤ ነርሷ በሽተኛዋን ስለ ሕይወቷ ጉዳይ ራሷ ልታነጋግራት ወሰነች:: ከዚህ ቀደም እንዲህ አድርጋ አታውቅም::

እንደ ምክንያት አድርጋ የወሰደችው፤ አንዳንድ ጊዜ ከቤተሰብ አባላት ይልቅ አሉታዊ የሆነ ምስክርነት ለመስጠት እንግዳ ለሆነ ወይም በመጠኑ ብቻ ለሚያውቁት ሰው ይቀላል የሚል ግምት ነው::

የሥራ ጊዜዋን ከጨረሰች በኋላ፣ ነርሷ ወደ ሴትየዋ ክፍል ሄዳ፣ "አጠገብሽ ተቀምጬ ጥቂት ጊዜ ላጫውትሽ እችላለሁ?" ስትል ጠየቀቻት::

በመሞት ላይ ያለችው ሴት ራሷን በአዎንታ ነቀነቀች:: በፍጹም ትህትናና በታላቅ ጥንቃቄ ስለ እምነትና ስለ እግዚአብሔር ሰላም እንዲሁም ኢየሱስ ክርስቶስ በእራሷ ሕይወት ስላመጣው ታላቅ ለውጥ ተረከችላት::

በዚህ ሁሉ ውስጥ ግን ሴትየዋ አንዳች ቃል አልተነፈሰችም:: ነርሷ፣ "ይህንን የቴፕ ክር አድምጬዋለሁ፣ አንቺም ልታውቂው የሚገባ ነገር በውስጡ እንዳለ አስባለሁ፣ የቴፕ ክሩን ማድመጥ ትፈልጊያለሽን? " ስትል ጠየቀቻት::

አሮጊቷ ሴት ራሷን በአዎንታ ነቀነቀች፣ ስለዚህም ነርሷ ቴፑን ከፈታችላትና ሄደች::

በሚቀጥለው ቀን በሞት መንገድ ላይ ያለችው ሴት ለልጇና ለነርሷ ቴፑን እንዳደመጠችው ከነገረቻቸው በኋላ፣ "በጣም አስደሳች ሆኖ አግኝቼዋለሁ አሁን ክርስቲያን ስለመሆን ጉዳይ አጥብቄ አስቤበታለሁ" አለች::

ምንም እንኳን ልጅቷና ነርሷ በዚህ ነገር እጅግ ቢደሰቱም ከዚያ በላይ ሄደው ምንም ነገር አልጠየቋትም:: ከሁለት ቀን በኋላ ሴትየዋ፣ "እኔ አሁን አማኝ ሆኛለሁ" ስትል ተናገረች:: ይህንን በመጀመሪያ የተናገረችው ለልጇ ሲሆን ቀጥሎ ደግሞ ለነርሷ ነበር:: ከዚያ በኋላ ማንም ሊጠይቃት ወደ ክፍሏ ይምጣ፣ "እኔ ክርስቲያን ሆኛለሁ::



ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ አዳኜ አድርጌ ተቀብያለሁ፣ እናም ወደ መንግስተ ሰማይ እሄዳለሁ እያለች" ትነግረዋለች::

ሴትዮዋ በግልጽ ለሌሎች መለወጧን ከተናገረች ከጥቂት ሰዓታት በኋላ የጤንነቷ ጉዳይ ከፊቱ ይልቅ እያሽቆለቆለ ሄደ:: ቀይቶም ህሊናዋን ሳተች:: በሚቀጥለው ቀን ነርሷ ወደ ሥራ ገበታዋ ስትገባ፣ አሮጊቷ ሴት ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት መሞቷን ሰማች::

ነርሷ ይህንን ሁሉ ከነገረችኝ በኋላ፣ "ሴትዮዋ እየሞተች በነበረችበት ጊዜ የሆነውን ነገር ማመን አትችልም" አለች::

ጥያቄ ከመጠየቄ በፊት ነርሷ እንዲህ አለች፣ "ቴፕ ሪከርደሩ በአልጋው ላይ አጠገቧ ተቀምጦ ነበር:: ልጇ አንተ መንግስተ ሰማይ ምን እንደምትመስል የገለጽክበትን ሁለተኛውን የቴፑን ክፍል ከፈተችላት:: ሕይወቷ እየተወሰደ በነበረበት ጊዜ መንግስተ ሰማይ ምን እንደምትመስል የተረከውን ገለጻ እያዳመጠች ነበር:: ከዚህ ምድር ከመሰናበቷና በመንግስተ ሰማይ እግዚአብሔርን ከማግኘቷ በፊት የሰማችው የመጨረሻ ነገር መንግስተ ሰማይ ምን እንደምትመስል ነው::"

ስሜቴን ለመቆጣጠር ብታገልም፣ እንባ ከዓይኔ ጠርዞች ላይ መፍለቅ ጀመረ::

"ይህንን ማወቅ እንዳለብህ ስላሰብኩ ነው::"

"አዎ" አልኳት:: "ስለነገርሽኝ አመሰግናለሁ:: ያ ለእኔ ትልቅ መጽናናት ነው::"

ነርሷ ከእኔ ጋር ለነበሩት ሰዎች ታሪኩን ደግማ ስትናገር ወደ ምድር መልሶ ስላመጣኝ እግዚአብሔርን አመሰገንኩ:: "አ! እግዚአብሔር ሆይ እዚህ ያለሁበትን ዐላማ አንዳንድ ምክንያቶች አውቄአለሁ:: ይህንን ታሪክ እሰማ ዘንድ ስለፈቀድክልኝ አመሰግንሃለሁ::"

አንድ ጊዜ በሃውስተን በምትገኘው በቾክላት ባዮ መጥምቃውያን ቤተክርስቲያን ሰብኬ ነበር:: የጋበዙኝም የሞቴንና በመንግስተ ሰማይ የመገኘቴን ተሞክሮ እንዳካፍላቸው ነበር::

ከመድረኩ በታች ሆኜ ሃሳቤን ሰብሰብ አድርጌ በመጠባበቅ ላይ ነበርኩ:: በተለይ የመጥምቃውያን አብያተክርስቲያናት፣ ተጋባዥ እንግዳ ወደ መድረኩ ከመውጣቱ በፊት በነጠላ የሚዘምር ዘማሪ ወይም የተለየ ሙዚቃ የማቅረብ ልምድ አላቸው:: አገልግሎቱ ሲጀመር ያልነበረች በምን እርዕስ ላይ ቃል እንደማቀርብም የማታውቅ አንዲት ሴት በስተጉን ባለ በር በኩል አልፋ ለመዘመር ወደ መድረኩ ወጣች::

እጅግ ማራኪ የሆነ ድምጽ ነው ያላት፣ የዘመረችው የኢየሱስን እግር በእንባዋ ያጠበችው ሴት ስለሰበረችው የአልባስጥሮስ ሽቱ ብልቃት ሲሆን፣ የዝማሬው መጠሪያ "ተሰብሮ መፍሰስ" የሚል ነበር::

አገልግሎቷን ጨርሳ እንደተቀመጠች፣ እኔ ደግሞ ተነስቼ ስለደረሰብኝ አደጋ መናገር ጀመርኩ:: በእርሷ ዝማሬና በእኔ መልዕክት መካከል አንዳችም ግንኙነት እንዲኖር አላደረግኩም፣ ይሁን እንጂ በርካታ ሰዎች ጥሩ ባልሆነ ስሜት ወደርሷ ሲመለከቱ አስተዋልኩ::



አገልግሎቱ ካበቃ በኋላ፣ አንድ ሰው ዘማሪዋን፣ "ዶን ንግግር ከማድረጉ በፊት፣ 'ተሰብሮ መፍሰስ' የሚለውን ዝማሬ መዘመርሽ አስደሳች ነው" ብሎ ሲናገራት ሰማሁ:: አስደሳች የሚለውን ቃል ሲናገር የነበረው ስሜት ባዶ ነበር::

"አ!" አለች ዘማሪዋ በፊቷ ላይ ካየሁት ድንጋጤ ልናገርበት የነበረውን ሃሳብ አስቀድማ እንደማታውቅ ተገነዘብኩ:: እውነቱን ለመናገር፣ እርሷም ብትሆን ዝማሬዋና የእኔ ምስክርነት ግንኙነት እንዲኖረው አላደረገችም:: ዓይኖቻችን ተገጣጠሙ፣ እናም ማልቀስ ጀመረች፣ "በጣም አዝናለሁ ... አዝናለሁ::"

ጥሩ እኮ ነው" አልኳት:: "በእውነት በጣም ጥሩ ነበር" አልኳትና ወደ እርሷ መራመዴን ቀጠልኩ፤፤

"ተሰብሮ መፍሰስ" አለ አንድ ሰው:: "ይሄ እኮ የሆነው በአንተ ላይ ነው፣ አይደለም እንዴ?" ቢያንስ ቢያንስ ደርዘን የሚሞሉ ሰዎች ተመሳሳይ አስተያየት ሰንዝረዋል:: አንዳንዶች ደግሞ እኛ በተለይ ይህንን መዝሙር እንድትዘምር ሆን ብለን ያደረግነው እንደሆነ ገምተዋል::

ቆም አልኩና ወደ ኋላዬ ተመለከትኩ:: ዘማሪዋ ከፒያኖው አጠገብ ቆማ ታለቅሳለች:: ራሴን ይቅርታ ጠይቄ ወደ እርሷ ተመልሼ ሄድኩ:: "በመጽሐፍ ቅዱስ ከተከናወኑት አስደናቂ ታሪኮች አንዱን የሚዘክር አስደናቂ ዝማሬ ነው የዘመርሽው እኔ ልናገርበት የነበረውን ጉዳይ አንቺ አላወቅሽም ነበር፣ ነገር ግን ጥሩ ዝማሬ ነበር፣ ምክንያቱም ከዚህ የተሻለ ዝማሬ እንደሚኖር አላስብም::"

ይቅርታን ለመጠየቅ በደስታ ተሞልታ ፈገግ አለች::

"በጣም ጥሩ ዝማሬ ነው፤ ጥሩ ነበር" ስል አረጋገጥኩላት።

አልፌአት እየሄድኩ ሳለ፤ ምናልባትም እኔ ተሰብሬ የፈሰስኩ ነኝ ስል አሰብኩ። ነገር ግን ወዲያው ደግሞ በሌላ ሃሳብ ፈገግ አልኩ፤ እንደገና ከስብራቴ ተጠግኜ ወደ ስፍራዬ ተመልሻለሁ።



# 16

# ዓላማን ማወቅ

"ይህንን ተረድቼ በእናንተ ዘንድ እንደገና ስለመሆኔ በእኔ መመካታችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ ይበዛ ዘንድ በእምነት ታድጉና ደስ ይላችሁ ዘንድ እንድኖር ከሁላችሁም ጋር እንድቆይ አውቃለሁ"

ፊል 1፥25-27

በሃውስተን የፓሳድና ክፍለ ከተማ ፖሊስ የሆነው ብራድ ቱርፒን በአደጋ ምክንያት እግሩን ሊያጣ ምንም ያህል አልቀረውም ነበር። የሚያሽከረክራት ሞተር ብስክሌት ከአንድ የጭነት መኪና የጀርባ ክፍል ጋር ተጋጨች። የህክምና ባለሙያዎች ፈጥነው በመድረስ ደሙ እንዳይፈስ ባያደርጉ ኖሮ በዚያው ስፍራ ደሙ ፈሶ ያልቅ ነበር።

ሶኒ ስቲድ የተባሉት በቤተክርስቲያናችን የቀድሞ የትምህርት አገልግሎት ሠራተኛ ደግሞ ብራድን በግል ያውቁት ስለነበር ሄጄ እንዳየው ጠየቁኝ። "በርግጥ ሄጄ አየዋለሁ" አልኩ፤ በተለይ ደግሞ ያ የእግር አጥንት ማፅኛ መሣሪያ እንደተደረገለት ከሰማሁ በኋላ መሄዴ አይቀሬ ሆነ። ደወልኩና ሊያነጋግረኝ እንደሚችል ፈቃድ ጠየኩት። ለምን እንደሆን ባላውቅም ከመሄዴ በፊት በእኔ ላይ የደረሰውን አደጋና ከዚያ በኋላም የሆነውን ማገገሜን የሚያሳዩ ፎቶግራፎቼን ይዤ ሄድኩ።

ሶኒ በመኪናቸው ወደ ፖሊሱ ቤት ወሰዱኝ። ወደ ውስጥ ከገባን በኋላ ያየሁት ነገር ልክ የእኔ ቤት ለወራቶች ያህል የነበረበትን ሁኔታ

ዓይነት ነው:: ብራድ የመደገፊያ የብረት ዘንግ በተዘረጋበት የሆስፒታል አልጋ ላይ ተኝቷል:: በእግሩ ላይ የተደረገለት መሣሪያ ለእኔ ተደርጎ ከነበረው ጋር ተመሳሳይነት አለው፤ ይሁን እንጂ ልክ የእኔ ዐይነት አልነበረም፤ ምክንያቱም ከእኔ አደጋ በኋላ በነበሩት ደርዘን በሚሞሉ ዓመታት ውስጥ ቴክኖሎጂው መሣሪያውን አሻሽሎታል::

ሌሎች ሰዎች በክፍሉ ውስጥ በመኖራቸው ተቀመጥኩና በሌሎች ጉዳዮች ላይ አብሬአቸው ጨዋታ ጀመርኩ:: በደህና ሁኔታ ላይ ነው ያለው፤ ይሁን እንጂ ብዙ ሰዎች ይጎበኙት ስለነበር በጠያቂዎች ምክንያት እንደሚሰላች አውቀአለሁ:: ልክ የመጨረሻው ሰው ክፍሉን ለቆ እንደወጣ፤ "ከሰዎች ጋር መነጋገር አሰልችቶሃል፤ አይደለም?" ስል ጠየኩት::

ብራድ በአዎንታ ራሱን ነቀነቀ::

"አውቃለሁ:: በዚህ ለፍራ ተኝተህ ልክ እንደ ኢግዚቪዥን እንደሆንክ እንደሚሰማህ አውቃለሁ:: ስልኩ መጮሁን አያቆምም:: እያንዳንዱ ሰው አንተን መጥቶ ማየት ይፈልጋል::"

እንደገና ራሱን ነቀነቀ፤ "በመምጣታቸው ደስ ይለኛል፤ ነገር ግን ጥቂት ሰላምና እፎይታ እፈልጋለሁ::"

"መጥቼ ከእረፍትህ ስላናጠብኩህ ይቅርታ እጠይቃለሁ፤ ነገር ግን ወደዚህ አንተን እንዳይ ያመጣኝ ሶኒ ነው፤ ምክንያቱም ምን ማድረግ እንደሚጠበቅብህ ከአንተ ጋር መነጋገር እፈልጋለሁ:: በእግሩ ላይ ወደ ታሰረው ኤልዛሮቭ ፍሬም በጣቴ እየጠቆምኩ፡ እንደዚህ በእግርህ ላይ እንዳለው መሣሪያ ዐይነት እኔም አድርጌ ነበር" አልኩት::



"አ! አንተም አድርገህ ነበር?"

በእጁ የያዝኳቸውን ፎቶግራፎች አውጥቼ መሣሪያውን ካደረጉልኝ ቀን ጀምሮ የተነሱትን ፎቶዎች በቅደም ተከተል አሳየሁት:: እያንዳንዱን ፎቶ በትኩረት ይመለከት ጀመር ከዚያም እኔ ከእርሱ በባሰ ሁኔታ እንደነበርኩ አየ::

"እና ተሻለህ፤ አይደለም?"

"አዎ ተሽሎኛል፤ አንተም ደግሞ ይሻልሃል::"

"አንተ የተሻለህ በመሆኑ በጣም ጥሩ ነው፤ ነገር ግን እኔ እንዳንተ የሚሻለኝ አይመስለኝም:: ይሄ እግሬ እንደማይቆረጥ እንዳችም ዋስትና ሊሰጡኝ አልቻሉም:: ዶክተሮቹ በእኔ ነገር ጨለምተኞች ናቸው፤ እናም ይሄ ነው ነገሩን ያከበደብኝ::"

"ጥሩ ነው፤ እነርሱ እኮ እንዲሁ ናቸው" አልኩት በእነዚያ አስቸጋሪ ጊዜዎች የነበረኝን ስሜት ወደ ኋላ ሄጄ አጥብቄ እያስታወስኩ "በዚህ ረገድ ወግ አጥባቂ የመሆንን ስህተት ነው የሚፈጽሙት፤ ተስፋህ ፈጽሞ እንዳይንሰራራ ነው የሚያደርጉት:: ከዚህ በኋላ በወራት ውስጥ ይሄ በእግርህ ላይ ያለ መሣሪያና ሁሉም ነገር ጥሩ እንደሚሆን ያውቃሉ ነገር ግን የሚነግሩህ እግርህ ሊመረዝ የሚችልና ሊቆረጥም እንደሚችል አድርገው ነው::"

"እኔም ያልኩህ ይህንኑ ነው:: በዚህ ሁሉ ስቃይ ውስጥ ማለፌ ዋጋ እንዳለው ነገር አልቆጥረውም::"

"መልካም ዜና እያገገምክ ስትሄድ የህመም ስቃዩ እየቀነሰ መሄዱ ነው::"

ይህንን እየተጫዋወትን ሳለ ሚስቱ ወደ ክፍሉ እየገባች ስለ ነበር ንግግራችንን አዳምጣለች::

"ምንም ዐይነት መሻሻል ባለመኖሩ' በጣም አስልችቶኛል፤ ደግሞም ማንም ሰው ስለዚህ ነገርም ምንም አይነግረንም" አለች:: "እንዲያውም ዶክተሮችን ለመለወጥ በዝግጅት ላይ ነን::"

"የተሻለ ዶክተር ልታገኙ ትችላላችሁ" አልኳት፤ "ነገር ግን ጥቂት ቆዩ ትዕግስትም ይኑራችሁ:: እርግጠኛ ነኝ ዶክተራችሁ የሚቻለውን ሁሉ እያደረገ ነው::"

ከዚያ በኋላም ፍጹም ተስፋ ቆርጬና ትዕግስቴ አልቆ ስለነበረበት ጊዜ አጫወትኳቸው::

"ዶክተሬ ሊጎበኘኝ በመጣ ጊዜ ንዴቴ ግሎ ነበር"

"ተቀመጥ" ስል ጭንቀት በሞላው ድምጽ ጮኹበት::

"ተቀመጠ፤ ከዚያ በኋላ ላሉት ቢያንስ አምስት ደቂቃዎች የተቸገርኩበትንና ተስፋ ያስቆረጠኝን ነገር እዘረዝረለት ጀመር:: ፊቱን ትክ ብዬ ስመለከት ስሜቱን እንደጎዳሁት ተገነዘብኩ:: በርግጥ ለራሱ እያሰብኩ አልነበረም:: ተጎድቼ ነበር፣ ስቃዩ ማቆሚያ አልነበረውም፣ መተኛት አልችልም፤ ለዚህ ሁሉ ደግሞ መልስ እፈልግ ነበር:: ነገሮችን ማወቅ ባለመቻሌ ስልችቶኛል:: አሁንም ምን ያህል ጊዜ ይህ ብረት በእግሬ ላይ እንደሚቆይ ጠይቄሃለሁ፤ ምናልባትም አንድ ወር ወይም ሁለትና ሦስት ወራት ነበር ያልከኝ ያልካቸው ወራቶች ካለፉ በኋላም እንኳን ያገኘሁት ለውጥ የለም:: ቀጣዩን ዙር አቤቱታዬን ለማቅረብ እንደገና ንዴቴ እየገነፈለ ነበር:: ነገሬን ያጠቃለልኩት፤ ቀጥተኛ የሆነ መልስ ለምን አትሰጠኝም በማለት ነበር::"

"ራሱን ቁልቁል ጣል አደረገና፤ ማድረግ የምችለውን ሁሉ እያደረግኩ ነው:: እኔም መልሱን አላውቀውም:: የማልነግርህም ለዚህ ነው" አለኝ::

"እኔ አሁን የምፈልገው ..."

"የምትፈልገውን አውቃለሁ፤ ይሁን እንጂ ይህ እርግጠኛ የሆነ ሳይንስ አይደለም: መሣሪያውን እንደ ገና ነው የፈለሰፍነው:: በዚህ አቅጣጫ ብዙም ልምድ የለንም፤ ከዚህም በላይ ይህ ለእኛ አዲስ ቴክኖሎጂ ነው:: ማድረግ የምንችለውን ሁሉ እያደረግን ነው::"

ለስዚያ አደጋ ለብራድና ለሚስቱ በነገርኳቸው ጊዜ፤ "እባካችሁ ለዶክተራችሁ ትዕግስት ይኑራችሁ:: የሌለውን መልስ ሊሰጣችሁ አይችልም:: ማድረግ የሚገባችሁን ነገር እንድታደርጉ ይነግራችኋል፤ የመድሃኒት ትዕዛዝ ወረቀት ያሽክማችኋል:: በበርካታ የህክምና ሂደቶች ውስጥ እንድታልፉ ያደርጋል፤ በእነዚህ ነገሮች ሁሉ ውስጥ እንዴት ማለፍ እንደምትችሉ መማር አለባችሁ በሁሉም ውስጥ::"

"አዎ፤ አውቃለሁ" አለ:: ይሁን እንጂ ከዚህ በኋላ ስሜቴን ለመቆጣጠር አልችልም:: እኔ ፖሊስ ነኝ:: ብዙ ችግሮችን አይቻለሁ፤ በጣም መጥፎና አስቸጋሪ ሁኔታዎችን:: ውስጤ ስብርብር ብሎ ነው ያገኘሁት ማለቴ ስሜቴ ወድቋል:: የምለውን ታውቃለህ?"

"በትክክል:: ዝም ብለህ በመለባበርህ ቀጥል:: ነገሮቹ ሁሉ እንደገና ይስተካከላሉ::"

"ከቁጥጥር ውጭ እንደሆንኩ ይሰማኛል"

"አሁንም ከቁጥጥር ውጭ ነህ!"

ብራድ ትኩር ብሎ ተመለከተኝ::

"ነገሩን እስኪ አስበው፤ ልትቆጣጠረው የቻልከው ነገር ምንድነው? ምንም የለም::"

"ራሴን ማጽዳት እንኳን አልችልም"

"ትክክል ነው:: ሙሉ ለሙሉ ተስፋ ቢስ ነህ:: ልታደርገው ወይም ልትቆጣጠረው የምትችለው አንዳች ነገር የለም::"

"እንዲህ ከመሆኔ በፊት ክብደት አነሣና የሰውነት ማዳበሪያ እንቅስቃሴ አደርግ ነበር" አለ:: "ማመን ከሚያቅትህ በላይ ክብደትና ቅርጽ ነበረኝ"

"ስለዚያ ምንም ጥርጥር የለኝም::" አንድ ጊዜ ጥሩ ቅርጽና ጡንቻ እንደነበረው ማየት ችያለሁ:: አሁን ግን እነዚህ ነገሮች የሉህም:: አንድ ቀን ግን እንደ ቀድሞው ግዙፍ ሰውነት ይኖርሃል፤ ነገር ግን ተነስተህ ቀድሞ የምታደርጋቸውን ነገሮች ለማድረግ አለመቻልህ እንድትለወጥ ያደርግሃል:: ለመለወጥ ተዘጋጅ:: ክብደትህን ትቀንሳለህ፤ ጡንቻዎችህም ይላላሉ:: ቀድሞ ታዳርገው እንደነበረው ሰውነትህን መቆጣጠር አትችልም::"

ሚስቱ በአዕምሮው ላይ የደረሰውን ዝለት ሁሉ በግልጽ በስሜቷ የተረዳች በመሆኑ ለማልቀስ እየተዘጋጀች ነበር:: "መጥፎ ስሜት ነው



የሚሰማው፤ በራሱ በህክምናው እንኳን ደስተኛ አይደለም:: ምን ማድረግ እንደምችል አላውቅም::"

"ጥቂት ነገሮች ልጠቁምሽ እችላለሁ:: ከሁሉም በፊት፤ ለጎብኚዎችና ለምትቀበሏቸው የስልክ መልዕክቶች ቁጥር ወሰን አብጁ:: ማንም ሰው በፈለገ ጊዜ ሁሉ እንዲገባ አትፍቀዱ" አልኩ:: "ጠበቅ በሉ:: ሁሉም ሰው እንዲገባ የምትፈቅዱ ከሆነ እየተሰላቻችሁ ትመጣላችሁ፤ ከፊታችሁ ላይ መልካም ስሜት መነበቡን ያቆማል:: ጓደኞቻችሁም ይህንን ይረዱታል::"

እንደገናም ወደ ብራድ ዘወር አልኩና፤ "ሁሉንም ህክምናዎች ለማድረግ ራስህን አዘጋጅ:: ምክንያቱም አስቸጋሪ የሆኑ ነገሮችን ሁሉ ታደርጋቸው ዘንድ ከፊትህ ይጠብቁሃል:: እንድትራመድ የሚረዱህ እስከሆኑ ድረስ አድርጋቸው ትዕግስት ይኑርህ፤ ምክንያቱም ህክምናው የሚወስደው ረዥም ጊዜ ነው:: ምናልባትም ልነግርህ የምችለው እጅግ የተሻለው ነገር ብቸኛ እንደ ሆንክ እንዳታስብ ነው::" ለአጭር ጊዜ ንግግሬን አቋርጬ ፈገግ አልኩ፤ ምክንያቱም እኔ ራሴ እንዴት እንደነበርኩ አስታውሼ ነው:: "የት ስፍራ እንደተጎዳህ ሰዎች እንዲያውቁ ፍቀድ፤ እንዴትስ ሊረዱህ እንደሚችሉ መንገድ ክፈት፤ በተለይም ለምታምናቸው ሰዎች አንዳንድ ነገሮችን ሊያደርጉልህ እንዲችሉ ችግሮችህን እንዲያውቁ አድርግ:: እንዲጸልዩልህ አድርግ:: ወደዚህ የሚመጡ እጅግ በርካታ መልካም ወገኖች ልታገኝ ትችላለህ፤ እነርሱም ኬክ፤ ኮካ ወይም ምግብ ሊያመጡልህ ወይም አንድ ነገር ሊያደርጉልህ ይፈልጋሉ:: ባልንጀርነታቸውንና ፍቅራቸውን እንዲገልጹልህ አድርግ::"

ለጥቂት ጊዜያት ካነጋገርኳቸው በኋላ፤ ለመሄድ ተነሳሁ:: የስልክ ቁጥሬን ጻፍኩና፤ "ደውልልኝ፤ ገና ከጠዋቱ ሦስት ሰዓት ላይ እንቅልፍ እንቅልፍ ካለህ ወይም ከተበሳጨህ ደውልልኝ:: አደምጥሃለሁ:: ችግርህን እረዳልሃለሁ፤ ምክንያቱም መረዳት እንድችል ሆኛለሁ:: አንድ የሚያደርገን ትንሽ ወዳጅነት በመካከላችን ተፈጥሯል፤ እያንዳንዳችን እጅ ለእጅ ልንያያዝ የቻልነው በምርጫችን ብቻ አይደለም" አልኩት::

ከመሄዴ በፊት፤ ብራድ እንዲህ አለ፤ "ወደዚህ በመምጣትህ ምን ያህል እንደተደሰትኩ ልነግርህ አልችልም:: እኔ እያየሁ ያለሁትን ስቃይ በሚያውቅ ሰው መጎብኘቴ በጣም ረድቶኛል:: በቀን ውስጥ ለሃያ አራት ሰዓት በማያቋርጥ ስቃይ ውስጥ ማለፍ ምን ማለት እንደሆነ ከሚያውቅ ሰው ጋር ስገናኝ አንተ የመጀመሪያ ነህ ..."

"እኔ በነበርኩበት ሁኔታ ውስጥ ያሉትን ሰዎች መጎብኘት፤ እኔ ራሴ በገዛ ፍቃዴ አስቤ የማደርገው ነገር አይደለም" አልኩት፤ "ይሁን እንጂ አደርገው ዘንድ ፈቃደኛ ነኝ:: መረዳት እፈልጋለሁ፤ ነገር ግን አንተ ወደ እኔ በመደወል የመጀመሪያውን ጥረት ማሣየት አለብህ:: አስታውስ ብቻህን የምትዘልቀው ነገር አድርገህ እንዳትገምት::"

የብራድ ሚስት መኪናችን ድረስ እየሸኘችን እንዲህ አለች፤ "የሚያስፈልገው ይህ ነበር:: ለሰዎች ሲታይ ልክ የኃይል ሁሉ ምንጭ እርሱ እንደሆነ ይመስላል፤ አሉታዊ የሆኑ ነገሮችንም ይናገራል:: በጥቂት ደቂቃዎች ልዩነት ውስጥ በፍርሃት ይዋጣል፣ ስሜቱ ይቀዘቅዛል፤ እናም በቀላሉ ውስጡ ተሰባብሮ ይወድቃል:: ስለ እርሱ በጣም መጨነቅ ጀምሬአለሁ:: አብረን በኖርንባቸው ዓመታት ሁሉ እንደዚህ ሲሆን አይቼው አላውቅም::"



"ሚስቴ ቀኑን ሙሉ በትምህርት ቤት ስትለፋ ቆይታ ምሽቱን ከእኔ ጋር ለማሳለፍ ስትመጣ የነበረችበትን ሁኔታ አስታውሳለሁ" አልኳት:: "ዝም ብለሽ ከእርሱ ጋር ቆይ:: እየተሻለው ይሄዳል::"

አንድ ጊዜ እጅግ አስከፊ ሁኔታ ውስጥ በነበርኩበት ጊዜ፤ ኢቫ እኔን ልታጽናናኝ ፈልጋ፤ "ጊዜ ስጠው:: ደህና ትሆናለህ" እንዳለችኝ አጫወትኳት::

በጭንቀትና በቁጣ ፈነዳሁና፤ "እኔ ደህና እንደምሆን ምን አስበሽ ነው የምትናገሪው? እነዚህ ሁሉ ምስቅልቅል ነገሮች እንዴት ነው ደህና የሚሆኑት? ማንም እንዲህ ብሎ ሊነግረኝ አይችልም:: ማንም ሰው ይህንን ቃል ሊገባልኝ አይችልም::"

ምስጋና ይግባትና ኢቫ አልተከራከረችኝም:: እጆቿን ዘርግታ አቀፈችኝ:: አለቀስኩ:: በእርሷ ፊት ያንን አድርጌው አላውቅም::

ለብራድ ሚስት ይህንን ታሪክ ከነገርኳት በኋላ፤ እንዲህ አልኩ፤ "በእርሱና በአንቺም ሕይወት ሊመጣ ስላለው ለወጥ ተዘጋጂ:: እርሱ ስሜቱን መቆጣጠር አይችልም፤ ይሁን እንጂ በሚጮህብሽና በሚቆጣ ጊዜ በግል በአንቺ ላይ የተነሳ አድርገሽ አትውሰጂው:: በአንቺ ላይ ሳይሆን ከስቃዩና ከስጋቱ የተነሣ ነው":: እጇን ጨብጬም እንዲህ አልኳት "ነገሮች መልካም እንዲሆኑ ከፈለግሽ በምትፈልጊኝ ጊዜ ደውይልኝ:: ብራድም እንዲደውልልኝ ገፋፊው::"

ከዚያ በኋላ ብራድን ሦስት ወይም አራት ጊዜ ያህል ጎብኝቼዋለሁ:: በመራመጃው እየተረዳ መራመድ ከቻለ ከሳምንታት በኋላ በአንድ ምግብ ቤት ውስጥ አይቼዋለሁ:: እርሱ ወደነበረበት ጠረጴዛ ሄጄ ተቀመጥኩ:: "እሺ ሁሉ ነገር እንዴት ነው?" ስል ጠየቅኩት::

"አሁን ደህና ሆኛለሁ፤ በርግጥ ደህና ነኝ":: እጅግ አስቸጋሪ በሆነ ሁኔታ ውስጥ በነበረበት ጊዜ መጥቼ ስለጎበኘሁት አመሰገነኝ:: በዚያን ጊዜም የሰውነት አቋሙ ሙሉ ስሙሉ አልተመለሰለትም፤ ይሁን እንጂ እንደገና ጤነኛ ሰው ሆኗል:: እጄን ጨብጦ ለረዥም ጊዜ እንደያዘ ቆየ፤ በቃላት ሊገልጽ ያልቻለውን አድናቆቱን የሚገልጽበት መንገድ መሆኑን አላጣሁትም::

የሕይወቱ ጨለማ እጅግ በጠቆረበት ወቅት ብራድን ለመርዳት በመቻሌ ለእግዚአብሔር ምስጋና አስጣለሁ::

አደጋው ከደረሰብኝ ከሁለት ዓመታት በኋላ፤ ቻድ ቮውል ከባድ የሆነ የመኪና አደጋ እንደደረሰበት ሰማሁ:: በሳውዝ ፓርክ የሚገኘው የወጣቶች አገልግሎት አባል የነበረ ሲሆን ቤተሰቦቹም በቤተክርስቲያን ከነበሩ ከፍተኛ እገዛ ከሚያደርጉልኝ ወገኖች መካከል ናቸው:: እናቱ ካሮል ሆስፒታል በነበርኩበት ጊዜ ስለ ወጣቶች የእረፍት መዝናኛ ጉዳይ ለመወያየት ወደ እኔ ዘንድ ይመጡ ከነበሩት የኮሚቴ አባላት መካከል አንዷ ናት:: በዚያን ጊዜ ወደ እኔ ዘንድ የሚመጡት እኔ ያን ያህል እገዛ ላደርግላቸው የምችል ሆኜ ሳይሆን እነርሱ እኔ ጠቃሚ ሰው እንደሆንኩ እንዲሰማኝ የተጠቀሙበት መንገድ ነበር::

ቻድ በጣም የተዋጣለት የሶከር ተጫዋችና በቤተክርስቲያናችን የወጣቶች ህብረት ውስጥ ወደ ኮሌጅ እስከገባበት ጊዜ ድረስ ይሳተፍ ነበር::

ለእናትዬው በደወልኩላት ጊዜ፤ በጋልቭስቶን ወደሚገኘው የስኦሴይ ሆስፒታል በሂሊኮፕተር እንደወሰዱት ነገረችኝ:: ጉዳቱ



የደረሰበት በታችኛው እግሩ ላይ እንደሆነ ሪፖርት ደርሷል፤ የአጥንት ማጽኛ ብረትም ተደርጎለታል ብላ እስክትነግረኝ ድረስ ምን ያህል ከባድ አደጋ እንዳጋጠመው አላወቅኩም ነበር:: የአጥንት ማጽኛ የሚለውን ቃል ስሰማ የግድ ሄጄ ማየት እንዳለብኝ ተሰማኝ ደግሞም የወጣቶች ህብረት አባላችን በመሆኑ መሄዴም አይቀርም:: ይሁን እንጂ የአጥንት ማጽኛ የሚለው ቃል ለሁኔታው አጣዳፊነት ትኩረት እንድሰጥ አደረገኝ::

ወደ ተኛበት ክፍል በገባሁበት ጊዜ፤ ቻድ ተደብሮ ተጋድሟል፤ ማንንም ሰው ማናገር እንደማይፈልግ በግልጽ ይታያል:: ይህ ቀድሞ የማውቀው ቻድ አይደለም:: ከዚያ ቀደም ባሉት ጊዜያት፤ እኔን ለማየት ሁል ጊዜም የሚፈልግ ነበር፤ ፊቱም እኔን በማክበር ይፈካል:: በዚህ ጊዜ የእኔን በዚያ መገኘት አውቋል፤ ይሁን እንጂ ከእኔ ጋር ውይይት ለመጀመር ምንም አይነት ፍላጎት አልታየበትም::

"ደህና ነህ ወይ? ትንሽ የመሻል ስሜት ይሰማሃል? " ስል ጠየኩትና ወደ እግሩ ተመለከትኩ፤ "የአጥንት ማጽኛውን እንዳደረጉልህ ደግሞ አያለሁ::"

"አዎ አድርገውልኛል" አለ::

"ቻድ፤ እኔ አደጋ የደረሰብኝ ጊዜ ታስታውሳለህ? ያንኑ በእኔ ላይ ያደረጉትን መሣሪያ ነው ለአንተም ያደረጉልህ:: "

"በእውነት?" ሲል ጠየቀኝ:: ለመጀመሪያ ጊዜ በእኔ ላይ ፍላጎት እንዳሳደረ በሚገልጽ ሁኔታ ተመለከተኝ:: እኔ መሣሪያውን በእግሬ ላይ አጥልቄ በጭራሽ አላየኝ ይሁን ወይም ሁኔታውን ዘንግቶት እንደሆነ አላውቅም:: ወደ እርሱ ቀረብ አልኩና፤ "እስኪ ይህንን አስታውስ፤

እንዲህ ያሰውን መሣሪያ ያጠሰቀ ሰው ምን እንደሚሰማው አውቃለሁ” አልኩት።

ጉዳቱ የደረሰበት በታችኛው የእግሩ ክፍል ላይ ነበር። በታችኛው እግራችን ላይ ሁሰት አጥንቶች በመኖራቸው ምክንያት ስመፈወስ ቀለል ይላል። ከዚያ ከመውጣቴ በፊት እንደተረዳሁት የመዳን እድሉ ሰፊ እንደሆነ በሀክምናው ምርመራ ተረጋግጧል።

ከዚያ ልጅ ጋር ስመነጋገር፣ እጁን ስመያዝና አብሬው ስመጸሰይ ችዬ ነበር፣ በዚህም መንገድ ባጋጠመው ችግር ውስጥ እኔም አልፌበት እንደነበር እንዲገነዘበው አድርጌአለሁ። ሰመጀመሪያ ጊዜ፣ ወደፊት ማየት ያስበት ዋነኛው ነገር የሚደረግለትን የሀክምና ክትትል መሆኑን የመገንዘብ ስሜት አደረበት። ከዚያ በፊት እኔ አደጋው ካጋጠመኝ በኋላ በእኔ ላይ እንደደረሰው ሰቻድ ዝርዝር የሆነ መረጃ የሰጠው ማንም ሰው አልነበረም። ልክ እንደእኔው ሁሉ ሰብስጭትና ሰድብርት ተሰጥቶ ነበር።

“የሀመም ስቃዩ ረዥም ጊዜ ይፈጃል። የማገገም ሂደቱም ዘላለም የሚቆይ ነው የሚመስለው፣ ነገር ግን ከሀመሙ ትድናሰህ። ይህን አንድ ነገር አስታውስ፣ ትድናሰህ።”

እናም ዳነ።

ጆይስ ፔንትክስት ዕድሜዋ ሰላሣ ዘጠኝ ዓመት ሲሞላ አንድ ሳምንት ሲቀረው ካንሰር እንዳሰባት ታወቀ። በጣም ነበር የምወዳት። ያገባችው የኢቫን ወንድም ሲሆን ባሰቀያይ ጠጉር የሆኑ ጆርዳንና ኮልቶን የተባሉ ሁሰት ልጆችን ትታ አልፋለች።



ጆይስ ከማውቃቸው እጅግ ተወዳጅ ከሆኑ ሰዎች መካከል አንዷና ኃይለኛ ዘማሪ ብቻ አልነበረችም፤ ይልቁንም ገና ወደ አንድ ክፍል ውስጥ በመግባቷ ብቻ ክፍሉን በብርሃን የምታደምቅም ጭምር ናት። የምትዘምረው አልፎ አልፎ ብቻ ነበር።

ሰሞቷ መታሰቢያ በአርካንሰስ በምትገኘው ፎርሬስት ከተማ በመጀመሪያዋ የባፕቲስት ቤተክርስቲያን በተዘጋጀው ሥነ ሥርዓት ላይ ንግግር እንዳደርግ በመጋበዜ ክብር ነበር የተሰማኝ። በጉባኤው አዳራሽ ውስጥ ከስድስት መቶ ሰዎች በላይ ነበሩ። ጆይስ በርካታ ክርስቲያናዊ ዝማሬዎችን በሲዲ አሳትማ ስስነበር በምድር ሰቀረነው ብዙ መንፈሳዊ ውርስ ትታልን ነው ያሰፈችው። በዚያ ፀሃያማ ከሰዓት በኋላ የተባረኩ ዝማሬዎቿን ከራሷ እየሰማን ነበር።

ከሰማናቸው የተቀዱ ዝማሬዎቿ በኋላ አባቷ መጋቢ ቻርልስ ብራድሌይ ተስፋንና ድነትን አስመልክቶ ቃል አቀረቡ። በዚያ ስተሰበሰብነውም፤ “ከዓመታት በፊት እኔና ጆይስ ቃል ኪዳን አድርገን ነበር። እኔ ቀድሜ የምሄድ ከሆነ በመቃብሬ ስፍራ እርሷ እንድትዘምር፣ እርሷ ቀድማ የምትሄድ ከሆነ ደግሞ በእርሷ የቀብር ሥነ ሥርዓት ላይ እኔ እንድሰብክ ነበር። ዛሬ ሰትንሿ ልጄ የገባሁላትን ቃል ፈጸምኩ” ሲሉ ተናገሩ።

ያች ቅጽበት ዛሬም ድረስ ከውስጤ አልጠፋችም።

ሃዘን ያረገዙ ፈገግታዎች ብልጭ ብልጭ አሉ፣ እንባዎች ተከትትሰዋቸው ወረዱ፣ ይሁን እንጂ ማንም በዚያ የተገኘ ንዴት ወይም ተስፋ መቁረጥ የተሰማው አይመስለኝም።

የጆይስ አባት መልዕክታቸውን ከጨረሱ በኋላ ቀጣዩ ተናጋሪ እኔ ነበርኩ።

"ዛሬ ከመካከላችሁ አንዳንዶች ጆይስ እንዴት ልትሞት ቻለች? ብላችሁ ትጠይቁ ይሆናል" ስል ተናገርኩ። "ነገር ግን ልትጠይቁ የሚገባችሁን የተሻለ ጥያቄ ልንገራችሁ፤ የኖረችው እንዴት ነበር? ጥሩ ኑሮ ኖራለች፤ የተወደደችም ነበረች። የሕይወቷን ሩጫ በመልካም ጨርሳለች።"

ጆይስ ለቅጽበት ጊዜ በሕይወት መድረክ ላይ ውልብ ብላ እንዳለፈች ጅራታም ኮከብ የምትመስል ነች፤ የኖረችው ለሰዎች ደስታ ለመስጠት በነበራት ፍቅር ነው፤ ልብ የሚጣልባት ባልንጀራ፤ የተለየች ውድ ልጅ፣ ተወዳጅ እህት አስደናቂ ሚስት ነበረች። በዚህ ቤት ውስጥ ባላችሁት የብዙዎቻችሁን ልብ ለንጥቆ የገባውን 'ለምን?' የሚለውን ጥያቄያችሁን ለመመለስ እንደማልችል ግን በፍጹም ትህትና አገልጽላችኋለሁ" ስል በዚያ ለተሰበሰቡ ልባቸው ላዘነባቸው ህዝብ ተናገርኩ።

"መልስ ባልመጣ ጊዜ መጽናናት" አለ ስል ጨምሬ ተናገርኩ። "ጆይስ ብሞት ወዲያውኑ ከእግዚብሔር ጋር እሆናለሁ የሚል ጽኑ እምነት ነበራት። ደግሞም በሕይወት ብትኖር እግዚአብሔር ከእርሷ ጋር እንደሚሆን ታምን ነበር። ለመኖሯ ምክንያት የነበረው ነገር ይህ ነበር። እኛም ሲኖረን የሚገባው ምክንያት ይሄው መሆን አለበት።"

ንግግሬን አንድ የግል ገጠመኜን በማካፈል ደመደምኩ። ይህ ገጠመኜ ጆይስ ወደ ቤቷ ከመመለሷ በፊት በሆስፒታል ውስጥ ሳለች



ለመጨረሻ ጊዜ ያደረግነው የቃላት ምልልስ ሲሆን፤ ይህም ስለመንግስተ ሰማይ ነበር።

"ወደ መንግስተ ሰማይ ያደረኩትን ጉዞ ሳጫውታት በፍጹም ለምታ አትጠግብም ነበር። በዚህም ለመጨረሻ ጊዜ አብረን መንግስተ ሰማይን በሃሣባችን ጎበኘናት። ስለመላእክቱ አወራን፤ ስለ መንግስተ ሰማይ ደጆች ተጫወትን፣ እንወዳቸው ስለነበሩ በዚያ ስላሉ ለዎች ተነጋገርን (የጆይስ እናትም የሞቱት በካንሰር ምክንያት ነበር)። ጆይስ ሁልጊዜም ስለዝማሬው እንድተርክላት ትፈልግ ነበር። የነበረን የመጨረሻው የንግግር ልውውጥም ከዚህ የተለየ አልነበረም።"

"ከጥቂት ቀናት በፊት"፣ ንግግሬን ለጉባኤው ቀጠልኩ፤ "እግዚአብሔር በእነዚያ በመንግስተ ሰማያት ደጆች ላይ ተቀምጦ፣ መላእክቱን በዚህ አካባቢ አሁን የሚያስፈልገን ጥሩ ባለቀይ ጠጉር ዘማሪ ነው ሳይላቸው እንዳልቀረ እምናለሁ። መላዕክቱ፣ ያች ዘማሪ ጆይስ ፔንትኮስት መሆን አለባት!" ብለው እንደ ተናገሩ እምናለሁ።

"እግዚአብሔር ወደ ጆይስ መልእክተኛ ላከ። እርሷም ለጥሪው ምላሽ ሰጠች። አሁን ከመላእክቱ ተቀባዮቿ ጋር በመዘመር ላይ ትገኛለች። ጆይስ ፔንትኮስት አሁን በአካል የለችም፤ ይሁን እንጂ ከጌታ ጋር ናት።"

የሃሣቤ ማጠቃለያ ለሕዝቡ የቀረበ ጥያቄ ነበር።

"የት እንዳለች የምታውቋትን ሴት፣ እንዳጣችኋት ትቆጥራላችሁን?"

በመኪና አደጋ በሞትኩበት ጊዜ የሰላሳ ዘጠኝ ዓመት ጎልማሣ ነበርኩ። ጆይስም የካንሰር በሽታ እንዳለባት ሲነገራት በዚሁ ዕድሜ ላይ

ነበረች። እኔ ከደረሰብኝ ዘግናኝ ጉዳት እንደገና ማገገም ቻልኩ። ጆይስ ግን አልቻለችም። ነገር ግን አንድ ነገር አውቃለሁ፤ እኔ መንግስተ ሰማይን ስላየሁ፤ እርሷንና ተወዳጆቿን ሁሉ ለዚያ ክብር ላዘጋጃቸው ችዬ ነበር። አሁን ደግሞ እናንተን እያዘጋጀኋችሁ ነው።

አደጋ ከደረሰብኝ በኋላ ብዙ ጊዜ በአደጋ ምክንያት በእግሩ ላይ የአጥንት ማጽኛ መሣሪያ ተገጥሞለት ለወራት ያህል ያሳለፈ ሰው ወደ ሆስፒታሉ መጥቶ እንዲጎበኘኝ እናፍቅ ነበር። እንደዚያ ቢሆን አብዛኛው ጭንቀቴ እንደሚቃለልልኝ አውቅ ነበር።

አሁን ደግሞ በእግራቸው ላይ መሣሪያው ስለተደረገላቸው ሰዎች በሰማሁ ቁጥር፤ ልገናኛቸው እሞክራለሁ። ረዥም የሥቃይ ጊዜ በማሳለፍ ላይ ያሉ ሰዎችን ሳነጋግር ሙሉ ለሙሉ ግልጽ ልሆንላቸው እሞክራለሁ። ከዚያ የህክምና ሂደት በቀላሉ የሚወጣበት መንገድ የለም፤ ይሄንንም እንዲያውቁ ደግሞ ያስፈልጋቸዋል። እኔ በዚያ ሂደት ውስጥ ስላለፍኩ ልነግራቸው እችላለሁ (እነርሱም ያደምጡኛል)፤ ምንም እንኳን የማገገም ሂደቱ ረዥም ጊዜ የሚወስድ ቢሆንም በመጨረሻው ይሻላቸዋል። በተጨማሪም አጫጭር ለሆኑ ጊዜያት ሊያጋጥሟቸው የሚችሉ ችግሮችን እነግራቸዋለሁ።

ከቻድና ከብራድ እንዲሁም ከሌሎች ጋር የነበረኝ የጉብኝት ጊዜ እግዚአብሔር በምድር ላይ ለመቆየቴ ዓላማ እንዳለው እንዳስታውስ አድርገውኛል። በነበረኝ በዚያ ረዥም የማገገም ጊዜ አንዳንድ ጊዜ መንግስተ ሰማይን እናፍቅ ነበር። ዛሬ ዘወር ብዬ ስመለከተው ግን፤ ዛሬ ለሌሎች ሰዎች ያካፈልኳቸው የመንግስተ ሰማይ ልምምዶ መንግስተ



ሰማይ ከነበርኩበት በዝግታ ወደ ምድር ያወረደኝ እንደሆነ እመለከታለሁ። "እግዚአብሔር ሊወስደኝ በተዘጋጀ ጊዜ" በመጨረሻው "እግዚአብሔር ይለቀኛል" ለማለት እችላለሁ። እስከዚያው ግን የተቻለኝን ያህል ለሌሎች የተመቸ አገልግሎት ለመስጠት እሞክራለሁ።

እንደኔው ሁሉ፤ አደጋው የደረሰባቸው ሌሎች በመጀመሪያ ጊዜ የአጥንት ማጽኛ መሣሪያውን በእግራቸው ላይ ሲመለከቱ፤ በተለይም ደግሞ አስቃቂ የሆነውን የስቃይ ስሜቱንና ለመራመድ አለመቻላቸውን ሲያውቁ ድብርት በውስጣቸው ይለቀቃል። ቀጥሎ የሚሆነው ነገር ምን እንደሆነ አያውቁም። ምንም እንኳን ዶክተሮቹ እንደሚሻላቸው ሊያረጋግጡላቸው ቢሞክሩም፤ ከዶክተሮቹ ቃል መጽናናትን ለማግኘት ስለሚከብዳቸው በብዙ ይጎዳሉ።

ይሁን እንጂ አንዳንድ ጊዜ፤ ህመምተኛው ባለማስተዋል፤ "ከዚህ ችግር በፍጥነት ወጥቻለሁ" ብዬ እንደተናገርኩ በማሰብ ወደ ተሳሳተ ድምዳሜ ሊደርስ ይችላል።

"ካለህበት ችግር ልትወጣ ትችላለህ፤ ይሁን እንጂ ፈጥኖ የሚሆን ነገር አይደለም" ብዬ እነግረዋለሁ። "ይህ በረዥም ጊዜ ልትወጣው የምትችለው የህክምና ሂደት ነው፤ ሂደቱንም ለማፋጠን የሚያስችል አንዳችም አማራጭ መንገድ የለም። በዚህ አይነት የከፋ ደረጃ ጉዳት የሚያጋጥምህ ከሆነ፤ ፈጥኖ ለመውጣት ቀላል መንገድ የለም። ለጊዜው አብረኸው ልትኖር ግድ ነው።"

ሌሎች ታሪኮችንም ላጫውታችሁ እችላለሁ፤ ይሁን እንጂ በሕይወቴ እጅግ በጨለሙ አንዳንድ ጊዜዎቼ ውስጥ እንዳልፍባቸው

ያስቻሉኝ ገጠመኞቼ እነዚህ ናቸው:: በዚህ ምድር ለመኖሬ እንደገና ዓላማዬን አውቄአለሁ:: አሁንም ወደ መንግስተ ሰማይ ለመመለስ እናፍቃለሁ፤ ይሁን እንጂ ለጊዜው ልሆን የተገባኝ ስፍራ ይህ ነው:: በምድር የተሰጠኝን የሕይወት ግዳጅ እየተወጣሁ ነው::



# 17

# ወደ ቤቴ እናፍቃለሁ

“ስለ እናንተ ስንጸልይ፤ በሰማይ ከተዘጋጀላችሁ ተስፋ የተነሳ በክርስቶስ ኢየሱስ ስለ እምነታችሁ፤ ለቅዱሳንም ሁሉ ስላላችሁ ፍቅር ሰምተን፤ የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን አባት እግዚአብሔርን ሁልጊዜ እናመሰግናለን:: ስለዚህም ተስፋ በወንጌል እውነት ቃል አስቀድማችሁ ሰማችሁ”

ቆላ 1፥5-6

ደጋግሜ ከምናገራቸው ተወዳጅ ታሪኮች አንዱ፤ ከቤቷ ወጥታ የት እንደሄደችና እንደደረሰኝ እናቷ ያላወቀቻት የትንሿ ልጃገረድ ታሪክ ነው:: እናቷ የልጇን መጥፋት ካወቀች በኋላ በልጇ ላይ አንድ ነገር ሳይደርስ አይቀርም ስትል በጭንቀት ተዋጠች:: በቤቷ መግቢያ በር ላይ ቆማ የልጇን ስም ደጋግማ ተጣራች::

ወዲያውኑ ልጅቷ አጠገባቸው ከነበረው ቤት ወጥታ እየሮጠች ወደ ቤቷ መጣች:: እናቷ የልጅቱን እጅ ይዛ፤ እንደተጨነቀች ከነገረቻት በኋላ፤ “የት ነበርሽ?” ስትል ጠየቀቻት::

“አገጠባችን ካለው ቤት ከሚስተር ስሚዝ ጋር ነበርኩ::”

“ደግሞ እዚያ ምን ታደርጊያለሽ?”

“ሚስቱ በመሞቷ ምክንያት በጣም አዝኗል::”

"እ! ምጣም አዝናለሁ፤ ያንን አላውቅኩም ነበር አለች" እናቷ። "ይሁንና አንቺ እዚያ ምን እያደረግሽ ነበር?"

"አይ በቃ ሲያለቅስ አላቅሰው ነበር።"

በነገራችን ላይ እኔም ይህንኑ እያደረግኩ ነው። ልምምዴን ሳካፍላቸው በጭንቀት ያሉትን እብሬ እያላቀስኳቸው ነው።

ራሳቸው ወደ ሞት ለተቃረቡትና በሚወዷቸው ሰዎች ሞት ምክንያት እጅግ ላዘኑ ሰዎች መጽናናትን ማምጣት የቻልኩበትን አንድ ምክንያት ልገነዘብ ችያለሁ። እጠገባቸው በመገኘት መንግስተ ሰማይ እቻ የሌለውና ሊገለጽ የማይችል ደስታ ያለበት ስፍራ መሆኑን ላረጋግጥላቸው መቻሌ ነው።

ያለ አንዳች ጥርጥር፤ መንግስተ ሰማይ እውን መሆኑን አውቂአለሁ። በሕይወቴ ከተለማመድኳቸው ልምምዶቼ ሁሉ የበለጠ እውን ነው። እንዳንድ ጊዜ፤ "በእናንተ ላይ የደረሰውን የትኛውንም የከፋ ነገር አስቡ፤ ደግሞም ያጋጠማችሁን ከፍተኛ ደስታ አስቡ፤ እንደገናም በእነዚህ መካከል ያጋጠሟችሁንም ነገሮች ሁሉ አስቡ፤ ከነኝህ ነገሮች ሁሉ ይበልጥ መንግስተ ሰማይ እውን ነው" እያልኩ እናገራለሁ።

ወደ ምድር ከተመለስኩ በኋላ፤ ሁላችንም በጉዞ ላይ መሆናችንን ልረዳ ችያለሁ። ይህንን የሕይወት ዘመናችንን በጨረስን ጊዜ የምንሄድበት ሕይወት ወደ መንግስተ ሰማይ ወይም ወደ ሲኦል፤ አሁን ከምንኖረው ኑሮ ይልቅ እጅግ እርግጠኛ ነው።



አደጋው በእኔ ላይ ከመድረሱ በፊት በፍጹም አስቤው አላውቅም ነበር። ለኔ መንግስተ ሰማይ እንደ ሀሳብ ነበር፤ የማምነውም እንደዚያ ነበር፤ ደጋግሜም የማላስበው ነገር ነበር።

ከአደጋው በኋላ ባሉት ዓመታት፤ ኢየሱስ ክርስቶስ ከመሸጡና ከመሰቀሉ በፊት ከደቀመዛሙርቱ ጋር ያደረገውን የመጨረሻ ምሽት ደጋግሜ አስበዋለሁ። ወደ መንግስተ ሰማይ ጉዞ ለመጀመር ጥቂት ሰዓታት ብቻ ሲቀረው በላይኛው ክፍል ውስጥ ከደቀመዛሙርቱ ጋር ተቀመጠ። በምንም ነገር እንዳይጨነቁና በእርሱ እንዲያምኑ ለመናቸው። እንደሚሄድ ከነገራቸው በኋላ "በአባቴ ቤት ብዙ መኖሪያ አለ፤ እንዲህስ ባይሆን ባልኋችሁ ነበር፤ ስፍራ አዘጋጅላችሁ ዘንድ እሄዳለሁና ሄጄም ስፍራ ባዘጋጅላችሁ፤ እኔ ባለሁበት እናንተ ደግሞ እንድትሆኑ ሁለተኛ እመጣለሁ ወደ እኔም እወስዳችኋለሁ" (ዮሐ 14፥2-3)

ከዚያ በፊት ይህን በእውነት አስተውዬው አላውቅም፤ ይሁን እንጂ ኢየሱስ ሁለት ጊዜ "ስፍራ" የሚል ቃል ተጠቅሟል፤ አድራሻን ያመለክታል። ምናልባት ይህ ብዙ ሰዎችን ላያነቃቃቸው ይችላል፤ ነገር ግን ይህን ቃል ደጋግሜ አስበዋለሁ። እውነተኛ የሆነ ስፍራ ነው፤ ደግሞም ያንን ስፍራ እንደማውቀው ላረጋግጥላችሁ እችላለሁ። እዚያ ነበርኩ። መንግስተ ሰማይ እውን እንደሆነ አውቃለሁ።

ከደረሰብኝ አደጋ በኋላ፤ ከመቼውም ጊዜ ይልቅ ትኩረትን መስጠትና በጥልቀት ማሰብ ይሰማኛል። አንድ ዓመት ያህል በሆስፒታል የቆየ ማንም ሰው እንደዚያ ሊሰማው ይችላል፤ ነገር ግን ይህ ከዚያም የዘለለ ነገር ነው። እነዚያ የዘጠና ደቂቃ ቆይታዎቼ ደግሜ የቀደመውን አይነት ሰው እንደማልሆን የሚያስረግጡ ስሜቶችን ትተውብኝ

አልፈዋል:: በዚህ ምድር ላይ ሙሉ ለሙሉ ራሴን ጥዬ ዳግመኛ አልኖርም፤ ምክንያቱም አሁን የምኖረው መጭውን እየተጠባበቅኩ ነው::

የሰው ልጅ ሊቋቋመው ከሚችለው በላይ ስቃይ እንደተቀበልኩ አስባለሁ፤ ዛሬም የምኖረው ስለዚያው ነገር ለመናገር ነው:: በነዚያ ወራት ወሰን የሌለው ስቃይ ቢደርስብኝም እንኳን እኔ ከተቀበልኩት መከራ ይልቅ የመንግስተ ሰማይ እውነታ እጅግ እጅግ በላጭ መሆኑ ይሰማኛል::

እጅጉን በስሜቱ የምነዳና ዝግ ሰማለት በጣም የምቸገር ሰው በመሆኔ ምክንያት፤ ብዙ ጊዜ የተወሰኑ ነገሮችን ማድረግ ያልቻልኩበትን ምክንያት መግለጽ መቻል እንደሚኖርብኝ ይሰማኛል:: ሙሉ ልብስ በለበስኩ ጊዜ፤ አብዛኞቹ ወገኖች በከባድ አደጋ ምክንያት የአካል ጉዳት የደረሰብኝ ፈጽሞ አይመስላቸውም:: ይሁን እንጂ ይህ እንደገና የተጠጋገነ አካሌ ማድረግ የማይችላቸው አንዳንድ እንቅስቃሴዎች ሲያጋጥሙኝ አብዛኛውን ጊዜ ምላሼ ያልተለመደ ነው የሚሆነው:: አብዛኛዎቹ እነዚህ እንቅስቃሴዎች በጣም ቀላል የሆኑ በመሆናቸው ብዙ ሰዎች ይደነቃሉ::

"ጤነኛ ትመስላለህ፤ ምንድን ነው እሱ ችግርህ? " ብዙ ሰዎች እንዲህ ይናገሩኛል::

አልፎ አልፎ፤ ከአንድ ሰው ኋላ ኋላ እየተከተልኩ ደረጃ የምወርድ ከሆነ፤ አንድ አስቸጋሪ ነገር ይፈጠራል፤ ጉልበቶቼ እርስ በእርስ እየተፋጩ ሲንገጫገጩ ድምጽ ይሰማል:: እናም ዘወር ብለው፤ "እንዲህ አይነቱ የሚረብሽ ድምጽ የሚወጣው ከአንተ ነው?" ይሉኛል::



"አዎ እላለሁ" ፈገግ እልና፤ "አስደናቂ ድምጽ አይደለም፣!"

አንጻራዊ በሆነ መልኩ እንቅስቃሴዬ ግራ የሚያጋባ ነው:: ምንም እንኳን የማደርጋቸው ነገሮች ውስንነት ያላቸው መሆኑ ለሌሎች ባይታወቅም፤ ማንም ሰው ያደርገዋል ብሎ ከሚገምተው በላይ እንቀሳቀሳለሁ:: በአግባቡ ለመራመድ ጠንክሬ እሠራለሁ፤ ምክንያቱም የሌሎችን ትኩረት ወደራሴ መሳብ ስለማልፈልግ ነው:: ያንን የአጥንት ማጽኛ አድርጌ በነበርኩበት ጊዜ ብዙዎች ወደ እኔ አፍጥጠው እንዲመለከቱ በሚያደርግ ሁኔታ ውስጥ ነበርኩ::

ጤነኛ እንደሆነ ሰው ነገሮችን ለማድረግና ለመምሰልም እንዲሁም ራሴን ወደ ፊት መግፋት አካላዊ ድካሜንና ጉድለቴን ለማሸነፍ የተጠቀምኩባቸው መንገዶች ነበሩ:: ከልምዴ እንዳገኘሁት፤ ራሴን በሥራ በምጠምድበት ይልቁንም ሌሎችን በምረዳበት ሥራ ላይ በሆንኩ ጊዜ ህመሜን እረሳዋለሁ:: ግራ በሚገባ መንገድ የህመም ስቃዬ ህክምና ያገኛል:: መራመድ እስኪሳነኝ ድረስም መሄድን አቅዳለሁ::

ምድራዊ በሆነ ንድፈ ሃሳብ ስለ ጊዜ ባለን ተፈጥሯዊ አመለካከት ተጽእኖ ሥር የወደቅን ነን - ሥርአታችን እንደዚያ ነው:: አስረግጬ ልናገርበት የምፈልገው ጠቃሚ ሃሳብ ይሄ ነው:: ተፈጥሯዊ በሆነ አመለካከቴ ስቃኘው በመንግስተ ሰማይ ደጃፍ ላይ የተቀበሉኝ እነዚያ የመስተንግዶ አባላት እኔ ወደ ምድር በተመለስኩባቸው በእነዚህ ዓመታት ውስጥ ምን እያደረጉ እንደሆነ እደነቃለሁ::

ይህንን በአንክሮ ሳስተውለው፤ አቀባበል ያደረገልኝ ቡድን "ኦ! ያሳዝናል በዚህ አልቆየም" ብለው እንደተናገሩ አላምንም:: አሁንም

በዚያው በመግቢያው በር ላይ ናቸው። አሁንም ይጠብቃሉ። ለእነርሱ ጊዜ የሚያልፍ ነገር አይደለም። አሁን ሁሉም ነገር በዘላለም ውስጥ ነው - እርግጥ ነው ይህንን በቃላት መግለጽ አልችልም፤ ምንም እንኳን አሥር ወይም ሰላሳ ዓመታት ቢያልፉም እንኳን በመንግስተ ሰማይ፤ እንደገና ወደዚያው እስከመለስ ድረስ ያለው ጊዜ የቅጽበት ያህል ጊዜ ነው።

የዚያ የጥር ወር ማለዳ ወደ መንግስተ ሰማይ ያደረግኩት ጉዞ በራሴ ምርጫ አልነበረም። በዚህ ሁሉ ውስጥ ያደረግኩት አንድ ምርጫ፤ አንድ ቀን ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ቀርቤ እንደ አዳኜ አድርጌ እርሱን መቀበሌ ነው። ምንም እንኳን የማልጠቅም ሰው ብሆንም ወደ መንግስተ ሰማይ እንድገባ ፈቀደ። እናም ዳግመኛ ወደዚያ በሄድኩ ጊዜ በዚያው እንድቆይ አውቃለሁ።

የመሞት ምኞት የለኝም። ራሴን ለማጥፋት እንደሚፈልግ ሰውም አይደለሁም፤ ይሁን እንጂ ሁልጊዜም ተመልሼ ስለመሄድ አስባለሁ። ለመመለስ እናፍቃለሁ። በእግዚአብሔር በራሱ ጊዜ፤ በፍጹም እርግጠኝነት ይህ እንደሚሆን አውቃለሁ። አሁን ያንን ጊዜ እናፍቃለሁ፤ በታላቅ ጉጉት እጠባበቀዋለሁ።

በፍጹም የሞት ፍርሃት የለኝም። ለምን እፈራዋለሁ? የሚያስፈራ አንዳች ነገር የለም በሞት ውስጥ ያለው ደስታ ብቻ ነው።

ቀደም ሲል ገልጬዋለሁ፤ ወደ ምድር ተመልሼ አዕምሮዬ በነቃ ጊዜ ልቆጣጠረው የማልችል ትልቅ ቁጣ በውስጤ አልፎ ሄደ። ወደ ምድር መመለስ አልፈለግኩም፤ ይሁን እንጂ ያም ቢሆን የእኔ ምርጫ አልነበረም።



ለረዥም ጊዜ፤ እግዚአብሔር ወደ ምድር መልሶ የላከኝ አይመስለኝም ነበር። ነገር ግን ግራ በሚያጋቡኝ ሁኔታዎች ውስጥ እንኳን በሆነው ነገር ሁሉ እግዚአብሔር ዓላማ እንዳለው አውቃለሁ። ወደ መንግስተ ሰማይ ስሄድ ምክንያት ነበረው፤ ወደ ምድር መመለሴም ዓላማ አለው። በመጨረሻው፤ እግዚአብሔር ልዩ በሆነ ሁኔታ ውስጥ እንዳሳለፈኝና ዘላለም ምን እንደሚመስል በከፊል እንዳይ ማድረጉን አውቄአለሁ።

ምንም እንኳን ሰማያዊ የሆነውን ቤቴን ብናፍቅም፤ የመጨረሻው ሰአላዊ ጥሪ ወደ እኔ እስኪመጣ ድረስ ለመጠበቅ ተዘጋጅቻለሁ።

በሰላሣ አራት የቀዶ ጥገና ህክምናዎች ውስጥና በብዙ ዓመታት ስቃይ ውስጥ ማለፌ፤ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች፤ "የርኅራኄ አባት የመጽናናትም ሁሉ አምላክ የሆነ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ። እርሱ በመከራችን ያጽናናናል፤ ስለዚህም እኛ እራሳችን በእግዚአብሔር በምንጽናናበት መጽናናት በመከራ ሁሉ ያሉትን ማጽናናት እንችላለን" (2ቆሮ 1፥3-4)

በዚህ ምድር ላይ እስከቆየሁ ድረስ፤ እግዚአብሔር አሁንም ለእኔ ዓላማ አለው። ያንን እውነት ማወቁ ስቃዬን ታግሼ ለመቋቋምና አካላዊ ጉድለቴን ተቀብዬው እንድኖር አስችሎኛል።

እጅግ አስቸጋሪ በሆኑት ጊዜዎች ቀደም ካሉ ዝማሬዎች አንድ መስመር ትዝ ይለኛል። "ኢየሱስን ባየነው ጊዜ ሁሉም መልካም ይሆናል" እንደሚሆንም አውቃለሁ።

# 18

## ስምን?

"ዛሬስ በመስተዋት በድንግዝግዝ እንደምናይ ነን፤ በዚያን ጊዜ ግን ፊት ለፊት እናያለን፤ ዛሬስ ከእውቀት ከፍዬ አውቃለሁ በዚያን ጊዜ ግን እኔ ደግሞ እንደታወቅሁ አውቃለሁ።"

1ቆሮ 13፥12

ብዙ ጊዜ ሰዎች በቴሌቪዥን መስኮት ውስጥ ወደ ሞት እጅግ ተቃርበው እንደነበረ ሲናገሩ አዳምጫለሁ። በነገራቸው መማረኬ እውነት ቢሆንም ጥርጣሬ ግን አለኝ። እንደ እውነቱ ከሆነ በጣም ነው የምጠራጠረው። እነዚህ ሰዎች ንግግር ከማድረጋቸው በፊትም ሆነ በኋላ እንዲህ እያልኩ አስባለሁ፤ "ምናልባት እነዚህ ሰዎች አንጎላቸው ቀስ በቀስ ሥራውን አቁሞ ሊሆን ይችላል። ወይም ምናልባት በትውስታቸው ካዝና ውስጥ ተቀብሮ የኖረ አንድ ነገር ይኖርና ያንኑ ደግመው እያስታወሱት ይሆናል" እላለሁ። በሰዎቹ ቅንነት ጥርጥር የለኝም፤ የተናገሩትን ለማመን እንደፈለጉም አውቃለሁ።

በቴሌቪዥን በርካታ ቃለ ምልልሶችን ተመልክቻለሁ፤ በአስደናቂ መንገድ የሞት ሰለባዎች ስለነበሩና ከሞት ስለተመለሱ (ትንፋሻቸው ስለተመለሰች) ሰዎች የተጻፉ ጽሑፎችን አንብቤአለሁ። ከሞት ጋር ስላደረጉት ትንንቅ የሚያቀርቡት ገለጻቸው ብዙውን ጊዜ በጣም የተጠናና በሚረብሽ መልኩ ልክ አንድ ሰው የመጨረሻው ሰው የተናገረውን በትክክል ገልብጦ የተናገረው እስኪመስል ድረስ



ተመሳሳይነቱ የሚረብሽ ነው። ከሃያ አራት ሰዓት በላይ ሞቶ እንደነበር የሚናገር አንድ ሰው፤ በጻፈው መጽሐፉ ላይ ከአዳምና ከሄዋን ጋር እንደተነጋገረ ተርኳል። የመጀመሪያዎቹ ባልና ሚስት ነግረውኛል የሚላቸው አንዳንድ ነገሮች በመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ሲመዘኑ እውነት ያላቸው አይደሉም።

ዛሬም ድረስ አብዛኞዎቹን ምስክርነታቸውን ብጠራጠርም፤ የገዛ ራሴን ሞት ግን በጭራሽ ተጠራጥሬው አላውቅም። እንደ እውነቱ ከሆነ እጅግ ሃያልና ሕይወትንም የሚለወጥ ስለነበር ከዴቪድ ጀንቲልስ ጋር አደጋው ከደረሰ ከሁለት ዓመት በኋላ በግል ባደረግነው ጭውውት ከመግለጼ በፊት በጭራሽ ለማንም አልተናገርኩም።

ወደ ሞት ተቃርበው ስለነበሩ ሰዎች የተደረገውን ጥናት ተመልክቼ፤ ለዓመታት ያህል በጉዳዩ ላይ ሳስብበት ቆይቻለሁ። በቅርቡ በታህሳስ ወር በ2001 በርካታ የሳይንስና የህክምና ሊቃውንት፤ እነዚህን ተውኔታዊ የሆኑ ገጠመኞችን "በምኞት የተሞሉ ሃሳቦች ወይም የኦክስጂን እጥረት ከገጠመው አንጎል የመነጩ የተሳሳቱ እሳቤዎች ናቸው" ሲሉ ውድቅ አድርገዋቸዋል።

በኔዘርላንድስ የተደረገው ጥናት የመጀመሪያው ሳይንሳዊ ጥናት ነው። አንድ ጊዜ ሞተው ነበር ተብሎ ከተነገረላቸው ሰዎች ጋር ቃለ ምልልስ ከማድረግ ይልቅ የተጠቀሙት፤ በሆስፒታል ውስጥ የሞቱትንና ከሞት የተነሱትን በመቶዎች የሚቆጠሩ ህመምተኞች ማነጋገርን ሲሆን እነዚህም የልብ ምታቸው ፈጽሞ ቆሞ የነበሩ ናቸው። ይህን አይነቱን መንገድ የመረጡበት ምክንያት፤ ከሞት ከተነሱ ከረዥም ጊዜ በኋላ ያጋጠማቸውን ነገር እያስታወሱ እንዲናገሩ ከማድረግ ይልቅ፤ ሁኔታው

እንደተከሰተ ወዲያውኑ ሁኔታውን እንዲዘግቡ ማድረግ በተሻለ መንገድ ትክክለኛ መረጃን መስጠት ይችላሉ ብለው ተስፋ በማድረጋቸው ነው።

ውጤቱም ይሄ ነበር፤ አስራ ስምንት በመቶ የሚሆኑ በሽተኞች በሆስፒታል ውስጥ በሞቱበት ጊዜ የነበረውን ሁኔታ እንደሚያስታውሱ ተናግረዋል። ከስምንት እስከ አስራ ሁለት በመቶ የሚያህሉቱ ወደ ሞት ተቃርበው የነበሩ ሰዎች እዘውትረው የሚናገሩትን ለምሳሌ ያህል አንጸባራቂ የሆነ ብርሃን ማየታቸውን፤ በሆነ ሸለቆ ውስጥ ማለፋቸውን ወይም ወደ መንግስተ ሰማይ ተሻግረው ከሞቱ ዘመዶቻቸው ወይም ጓደኞቻቸው ጋር መነጋገራቸውን ገልጸዋል። አጥኚዎቹ ከሞት በኋላ ወይም ወደ ሞት ተቃርበው የነበሩ ሰዎች ልምምድ፤ "ሌሎች አማራጮችን ሁሉ ፈትሸን ተስፋ ስንቆርጥ ልንቀበለው የምንችል እውነት ብቻ" ሲሉ ጥናታቸውን ደምድመዋል።

በሌላ ወገን፤ ሌሎች ተመራማሪዎች ሞተው በተነሱ በ344፣ ዕድሜያቸው ከሃያ ስድስት እስከ ዘጠና ሁለት በደረሱ ሰዎች ላይ ባካሄዱት ጥናት ላይ ተመርኩዘው የራሳቸውን ድምዳሜ ሰጥተዋል። አብዛኞቹ ቃለ ምልልሱን ያደረጉት ክስተቱ ከተፈጸመ ከአምስት ቀናት በኋላ ነበር። አጥኚዎቹ እነኛኑ ሰዎች ከሁለት ዓመት በኋላና ከስምንት ዓመት በኋላ አግኝተው አነጋግረዋቸዋል።

አጥኚዎቹ በዚሁ ፍተሻቸው የእነዚህ ሰዎች ልምምድ ከተሰመዱት ሥነ አካላዊ፣ ስነልቡናዊ ወይም የህክምና መመዘኛዎች አንጻር ሲታይ እየሞተ ያለ የሰው አንጎል ከሚያሳየው ሁኔታ ጋር የማይመሳሰል መሆኑን ደርሰውበታል። አጥኚዎቹ፣ አብዛኞቹ በሽተኞች ስለ ክስተቶቹ አስደናቂ ትውስታ አላቸው ያሉት ትውስታዎቹ ሀሰት ናቸው የሚለውን ሀሳብ ይሸረሽረዋል።



ለእኔ እጅግ ጠቃሚው ነገር በእንዲህ ያለ ሁኔታ ውስጥ ያለፉ ሰዎች በስብእናቸው ላይ የተገለጠ ለውጥ መታየቱ ተዘግቧል። ለሞት የነበራቸው ፍርሃት ጠፍቷል። ርህራሄን የሚያሳዩ፣ ቸርነት የሚያደርጉና ፍቅር ያላቸው ሆነዋል።

ዘገባው ወደ ሞት ተቃርበው ስለነበሩ ሰዎች እውነታ ያረጋገጠው ምንም ነገር የለም። ከጥናቱ በፊት አንዱ ቡድን፤ ወደ ሞት ተቃርበው የነበሩ ሰዎች፤ በመሞት ላይ ያሉ ሰዎች ባሉበት ሁኔታ ውስጥ የነበሩ ብቻ ናቸው ብሏል።

ሌላው ቡድን ደግሞ ጠንካራ የሆኑ ማስረጃዎች ወደ ሞት የመቃረብን ክስተት የሚያረጋግጡ በመሆኑ፤ ሳይንቲስቶቹ ከአካል ተለይቶ የመውጣትን ጽንሰ ሃሳብ እንደገና እንዲያጤኑት ሃሳቡን አቅርቧል።

በዚህ ጉዳይ ላይ የሚነሱትን ክርክሮች ለመደገፍ አልሞክርም። እኔ ነገሮችን የማየው በራሴ ላይ ከደረሰው ነገር አኳያ ነው። አጥኚዎቹ ምንም ነገር ሊነግሩኝ ወይም ላይነግሩኝ ቢሞክሩም፤ እኔ መንግስተ ሰማይ ሄጄ እንደነበር አውቃለሁ።

በእኔ ላይ የደረሰውን ነገር በአንክሮ ስመገንዘብ፤ የደረሰብኝ ነገር ምንድነው? ከሚለው ጥያቄ ይልቅ በእኔ ላይ የደረሰው ለምንድን ነው? የሚለውን ጥያቄ ለማሰላሰል ሰፊ ጊዜ ሰጥቻለሁ። የደረስኩበት አንድ ጠንካራ መደምደሚያ ብቻ ነው፤ በመኪና አደጋ ከመገደሌ በፊት ወደ ሞት ስለተቃረቡ ሰዎች ዘገባ በጥርጥር ውስጥ እንዳለሁ ቆይቻለሁ። በቀላሉ አንድ ሰው ሞቶ ወደ መንግስተ ሰማይ ሄዶ እንደገና ተመልሶ ስላየው ነገር መናገር የሚችልበት ሁኔታ እንዴት እንደሆነ አይታየኝም ነበር። መሞትን፣ የመንግስተ ሰማይን እርግጠኛነት ወይም ከሞት በኋላ

ሕይወት መኖሩን አልጠራጠርም። ግን "ወደ ሞት ተቃርቤ" የሚሉ ዘገባዎችን ተጠራጥሬአለሁ። ታሪኮቹ ሁሉ የተጠኑና ተመሳሳይ ድምፀት ያላቸው ይመስላሉ። ከዚያም እኔ ራሴ ሞትኩ፣ ወደ መንግስተ ሰማይ ሄድኩ፣ ተመለስኩም። መናገር የምችለው በእኔ ላይ የሆነውን ነገር ብቻ ነው።

ይህ ለቅጽበት ያህል ያሰብኩት ራዕይ ወይም ህልም አይደለም፣ በአእምሮዬ የተመሰሱ ክስተቶች አይደሉም፣ ወይም የሰማኋቸው ታሪኮች ውጤት አይደለም። መንግስተ ሰማይ እውን እንደሆነ አውቃለሁ። እዚያ ነበርኩ፣ ተመልሼም መጥቻለሁ።

ነገሩ እንዲህ ሊቋጭ ይችላል፤ አንድ ሰው ለተወሰነ ጊዜ ያህል ይሞታል፣ ከዚያ ቀጥሎ ደግሞ በተጨባጭ ሁኔታ ከሞት በኋላ ያለውን ሕይወት ከተመለከተ በኋላ ወደ ሕይወት ይመለሳል። በዚህም ወደ ሞት ተቃርቦ የነበረው ሕይወት የእምነት ጉዳይ ሆኖ ይቀጥላል ወይም ደግሞ ቢያንስ ቢያንስ በተጨባጭ መንገድ መግለጽ የማይቻል ክስተት ይሆናል። ይሁን እንጂ ከዚያ በኋላ፣ አንድ ጓደኛዬ ተናግሮ እንደነበረው፤ "እንግዲህ አዲሱ ነገር ምንድን ነው?"

አንድ ጊዜ የባለቤቴ ቤተሰቦች ኢልዶንና ኢቴል ፔንትኮስት በነበሩበት በአንድ ትልቅ ጉባኤ መካከል የሕይወት ልምምዴን አካፍል ነበር። እነኝህ ዘመዶቻችን አደጋው በደረሰብኝና ከዚያም በኋላ ረዥም ጊዜ በወሰደው የሕክምና ጊዜዬ የደገፉንና ትልቅ መስዋእትነት የከፈሉልን ናቸው።



ከአገልግሎቴ በኋላ፤ ወደ ቤታቸው ሄድን። በዚያ ወቅት እኔና ኢልዶን ብቻችንን የሆንበት አጋጣሚ ተፈጠረ፤ እናም እንዲህ ሲል ተናገረ፤ "ወደ መንግስተ ሰማይ ስላደረግከው ጉዞ ስትናገር ለመጀመሪያ ጊዜ ስሰማ ተናድጄ ነበር" አለኝ።

ለምን እንደዚያ እንደተሰማው ምንም አይነት ግምት አልነበረኝም።

"ንግግርህን የጨረስከው ወደ ምድር መመለስህን በፍጹም እንዳልፈለግከው በመግለጽ ነበር።"

በአዎንታ ራሴን ነቀነቅኩ፤ ነገሩ ወዴት እንደሚያመራ አላወቅኩም ነበር።

"በዚያን ጊዜ ምን ማለትህ እንደሆነ አልገባኝም፤ አሁን ግን ተለውጫለሁ።" አሁን አሁን ስለ መንግስተ ሰማይ ውበት ስታወራ፤ ከልጆና ከልጅ ልጆቼ ጋር እስከጊዜውም ቢሆን ለመለያየት ፈቃደኛ የሆንክበትን ምክንያት በጥቂቱም ቢሆን ተረድቼዋለሁ። ታውቃለህ - በእውነት ታውቃለህ - አንድ ቀን መጥተው እንደሚገናኙህ አታውቅም?

"ያለ አንዳች ጥርጥር" አልኩ።

የኢልዶን መገለጥ አስደነቀኝ። እንደ እውነቱ ከሆነ ትክክል ነበር። የራሴን ልጆች ሳጠምቃቸውና ባለቤቴም ስትጠመቅ ቆሜ የመመልከት ዕድል ነበረኝ። እምነታቸውም እውነተኛ የሆነ እምነት እንደሆነም አውቃለሁ። በእምነት አንድ ቀን የመንግስተ ሰማይ ነዋሪዎች እንደሚሆኑ አውቃለሁ። በመንግስተ ሰማይ በነበርኩበት ጊዜ ከእነርሱ የመለየቴ ጉዳይ በፍጹም አላሳሰበኝም። በመንግስተ ሰማይ ያሉ ሰዎች

በቀላሉ አገላለጽ በዚያ ስለሌሉ ሰዎች ግንዛቤ የላቸውም:: የሚያውቁት ነገር ማን እንደሚመጣ ነው::

ዛሬ እንኳን ቢሆን፤ በእውነት እናገራለሁ በመንግስተ ሰማይ ቀርቼ ቢሆን እያልኩ እመኛለሁ፤ ይሁን እንጂ የመጨረሻዋ ቀኔ ገና አልመጣችም:: መንግስተ ሰማይን ለቅቄ ከወጣሁ በኋላ፤ ሁለት ሳምንት በቀዶ ጥገና ክፍል ውስጥ እንደምቆይ፣ በሆስፒታል አንድ ዓመት እንደምተኛና ሰላሣ አራት የቀዶ ጥገና ህክምና እንደሚደረግልኝ ባውቅ ኖሮ በርግጥ በበለጠ በሁኔታው አዝኜ ልቤ በወደቀ ነበር:: ይሁን እንጂ ይህ የእኔ ምርጫ አልነበረም፤ እናም በአንድ የጸሎት ድምጽ እንደገና ተመለስኩ፣ በሰዎች እግር ወደሚፈጭ የደቀቀ መስተዋት ድምጽ፣ ደግሞም በአደጋ ምክንያት ከተጨፈላለቁ መኪናዎች ውስጥ ሰዎችን የሚያወጣው ጀው ኦፍ ላይፍ (ሕይወት አድን መሳሪያ) በተባለው መሣሪያ አማካይነት በረቀቀ ጥበብ ከመኪናዋ ውስጥ ወጣሁ::

አንድ ጥያቄ ደጋግሞ ይረብሸኛል፤ "ለምን? " የሚመጣው ብዙ መልክ ይዞ ነው::

በመኪና አደጋ የሞትኩት ለምንድን ነው?

ወደ መንግስተ ሰማይ ለመሄድ የተለየ ዕድል ያገኘሁት ለምንድን ነው?

እንደገና ወደ ምድር ለመመለስና መንግስተ ሰማይን በጥቂቱ (ውልብታ ብቻ) እንዳይ የሆነው ለምንድን ነው?



በሆስፒታሉ ውስጥ እንደገና ከመሞት በጥቂቱ ያመለጥኩት ለምንድን ነው?

እግዚአብሔር፣ ከጥር 18 ቀን 1989 አደጋ ጀምሮ በማያቋርጥ የህመም ስቃይ ውስጥ እንዳልፍ ለምን ፈቀደ?

አጭሩ መልስ፤ "እኔ አላውቅም" የሚል ነው:: እንደዚያም ሆኖ ለምን? የምትለዋ አንዲት ቃል የሰው ልጅ የተሟላ ጥያቄ ሆና ትቀጥላለች:: በተፈጥሯችን ነገሮችን የማወቅ ከፍተኛ ጉጉት አለን:: ማወቅ እንፈልጋለን::

ከእነዚህ ሁሉ ዓመታት በኋላ፤ አሁንም ቢሆን የሆነውን ነገር አገናዝቤ ለመመልከት ለእኔ ቀላል አይደለም:: ብዙ ጊዜ ይህንን ታሪኬን ራሴ ልጽፈው ሞክሬአለሁ፤ ነገር ግን አልቻልኩም:: ስለዚህም ነው በዚህ መጽሐፍ ዝግጅት እንዲረዳኝ ወዳጄን ሰሲል ሙርፌን የጠየቅኩት - እንደ እኔማ ቢሆን፤ ይህ መጽሐፍ ጭራሹን ባልተጻፈ ነበር:: ድርጊቶቹን ሁሉ እንደገና ማስታወስ መሞከሩ የሚያስከትለው ስነልቡናዊ ጉዳት አስቸጋሪ ነው:: ከዚህ አስቸጋሪ ስቃይ በመጨረሻው መትረፍ የሚቻለው ከአንድ ሌላ ሰው ጋር በትክክል አብሮ በመጻፍ መስራት ሲቻል ብቻ ነው::

አሁንም ቢሆን እነዚህ ነገሮች ለምን እንደተከሰቱ የማውቀው ነገር የለም::

በሕይወቴ የጨለማ ጊዜያቶች ሁሉ እግዚአብሔር አብሮኝ እንደሆነ አውቃለሁ::

ለምን? እያልኩ ከምጠይቃቸው ጥያቄዎች ባሻገር፤ ሌሎችም ጥያቄዎች አሉ:: እነዚህ ጥያቄዎች በጥልቀት አሰላስላቸው ዘንድ በጣም አስፈላጊ እንደሆኑ አስባለሁ::

እግዚአብሔር እውነተኛ የሆነ የስቃይ ስሜት ምን እንደሆነ እውቅ ዘንድ የፈለገው፤ የሌሎችን ስቃይ መገንዘብ እንድችል ፈልጎ ይሆን?

እግዚአብሔር መንግስተ ሰማይ እውን እንደሆነች እንዳውቅ ፈልጎስ ይሆን?

ከሞቴና ረዥም ጊዜ ከወሰደው የማገገም ሂደት፤ እግዚአብሔር እማር ዘንድ የፈለገው ነገር ምንድን ነው?

የእኔ የሕይወት ልምምድ ለሌሎች ከፍ ባለ ደረጃ ጥቅም ሊሰጥ የሚችለው እንዴት ነው?

ከእነዚህ ሁሉ ዓመታት በኋላ፤ ከእነዚህ ጥያቄዎችም ለብዙዎቹ መልስ የለኝም:: በጣም ጥቂት ነገሮችን ልማር ችያለሁ፤ እግዚአብሔር በምድር ላይ እንድቆይ የፈለገበት ምክንያት እንዳለው ልገነዘብ ችያለሁ፤ ምናልባትም የእርሱን ምክንያቶች ላላውቃቸው እችላለሁ፤ ደግሞም እኮ እግዚአብሔር ምክንያቶቹን ለእኔ የመግለጽ ግዴታ የለበትም::

ምንም እንኳን ለብዙዎቹ ጥያቄዎቼ መልስ ባይኖረኝም፤ ሰላም አለኝ:: እግዚአብሔር እንድቆይ በፈለገበት ሥፍራ ላይ እንዳለሁ አውቃለሁ:: እግዚአብሔር የሰጠኝን ሥራ በመሥራት ላይ እንደሆንኩም አውቃለሁ::

በዮሐንስ ወንጌል ላይ በሰፈረው ታሪክ ሁል ጊዜ እጽናናለሁ:: ዓይነ ሥውር ሆኖ የተወለደ ሰው ኢየሱስን አገኘውና ተፈወሰ:: ከዚያ



በኋላ፤ እግዚአብሔርን እያመሰገነ ዙሪያ ገባውን ሮጠ:: ይሁን እንጂ የዚህ ሰው ፈውስ ሰዎችን በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ለማነሳሳት ይፈልጉ የነበሩትን የጊዜውን የሃይማኖት መሪዎች አላስደሰታቸውም:: አስቀድሞ ዕውር የነበረውን አስጠርተው በመጠየቅ ኢየሱስ ክርስቶስ ኃጢአተኛ ሰው እንደሆነ እንዲያምን ሊያስገድዱት ሞከሩ:: በሃሰት እንዲመሰክርበት ማለት ነው::

ሰውዬው በማስተዋል፤ "ኃጢአተኛ መሆኑን አላውቅም፤ ዓይነስውር እንደነበርኩ፤ አሁን እንደማይ ይህንን አንድ ነገር አውቃለሁ" ሲል መለሰላቸው (ዮሐ 9፥25):: እንደዚሁም ሁሉ አንዳንዶች ምስክርነቴን ላያምኑት ይችላሉ፤ ምናልባትም ባጋጠመኝ ከባድ አደጋ ጊዜ ውስጥ የተፈጠረ የሆነ ዓይነት ምኞታዊ መሻት እንደሆነ አድርገው ያስባሉ፡፡ የሕይወት ልምምዴን አምነው እንዲቀበሉ አልከራከራቸውም::

በእኔ ላይ ስለሆነው ነገር አውቃለሁ:: መንግስተ ሰማይ እውን እንደሆነች እምነት ላለን ለእኛ፤ ምንም አይነት የማስረጃ ጋጋታ አያስፈልገንም:: በሕይወት የተለማመድኩት ምን እንደሆነ አውቃለሁ::

እግዚአብሔር በመንግስተ ሰማይ ዘላዓለማዊ ሕይወት ምን እንደሆነ ጥቂት ማስገንዘቢያ (ጥቆማ) እንደሰጠኝ አምናለሁ::

እንዲሁም ደግሞ ቀደም ሲል እንደጠቀስኩት አሁን በምድር በሕይወት ያለሁበት ከፊል ምክንያት ሰዎች ለእኔ በመጸለያቸው እንደሆነ አምናለሁ:: ዲክ ዋንሪከር ወደ ሕይወት ተመልሼ እንድመጣና ያለ አንጎል ጉዳት እንድኖር ጸልዮልኛል:: ዴቪድ ጀንቲሊስና ሌሎችም በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር ወደ መንግስተ ሰማይ መልሶ እንዳይወስደኝ ጸልየዋል::

እነሆ አሁን በዚህ አለሁ፤ በሕይወትም አለሁ፣ እናም ምክንያቱ ደግሞ እግዚአብሔር በሕይወቴ ሊያደርገው ያለው ዓላማው ገና ባለመፈጸሙ ነው። እግዚአብሔር ከእኔ ጋር ያለውን ጉዳይ ሲጨርስ መሆን ወደምናፍቅበት ሥፍራ እመለሳለሁ። በመንግስተ ሰማይ ስፍራ ተዘጋጅቶልኛል፤ እናም አንድ ቀን ለዘለቄታው ተመልሼ እሄዳለሁ።

ከእናንተም ጋር በዚያ እንድንተያይ እጸልያለሁ።